# መለያየት ሞት ነው

7ኛ ዕትም

ዓለማየሁ ገላጋይ



# መለያየት ሞት ነው

ዓለማየሁ ገላጋይ

2010 ዓ.ም.

መለያየት ሞት ነው


የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

© ዓለማገሁ ገላጋይ 2010 ዓ.ም.



አንደኛ እትም - ጥር 2010 ዓ.ም.

ሁለተኛ እትም - ጥር 2010 ዓ.ም.

ሦስተኛ እትም -የካቲት 2010 ዓ.ም.

አራተኛ እትም - የካቲት 2010 ዓ.ም.

አምስተኛ እትም - መጋቢት 2010 ዓ.ም.

ስድስተኛ እትም - መጋቢት 2010 ዓ.ም.

ሰባተኛ እትም - መጋቢት 2011 ዓ.ም.

# አበርክቶት

## ለተመስገን ደሳለኝ (ተሜ)

ማውጫ


## ፖለቲካ ........................................................................ 7

መለያየት ሞት ነው ........................................................................ 9

ስፖርት ለጦርነት ........................................................................ 21

በኑሮ መቃወም! ........................................................................ 25

"ኑ እንዋቀስ!" ........................................................................ 28

"ትሞታለህ!" ........................................................................ 32

ጠቅላይ ሚኒስትር "ከቁርበትም" ይምከሩ ........................................................................ 37

"በምን እንኖራለን?" እና "ስለምን እንኖራለን?" ........................................................................ 41

እናፍራለን እንጂ! ለምን እናፍር? ........................................................................ 45

እንጠረጥራለን እንጂ! ለምን እንጠረጥር? ........................................................................ 50

እንሰጋለን እንጂ! ለምን እንሰጋ? ........................................................................ 55

"የሞትንም እኛ ያለንም እኛ" ........................................................................ 58

"ከኢህአዴግ ጋር መጪው ጊዜ..." እንዴት? ........................................................................ 62

መክሸፍ እንደ ኢህአዴግ ምልጃ ........................................................................ 66

ይድረስ "ለባለቅኔ" በረከት ስምኦን ........................................................................ 70

የጠፋውን የኢህአዴግ "ህሊና" ፍለጋ ........................................................................ 76

እንዲያስፖራ "ነውራችሁን ፋቁት!" ........................................................................ 80

## ማህበራዊ ........................................................................ 85

"ጎንደር የህልሜ ከተማ ናት" ........................................................................ 87

የህይወት ጀንበር፤ በፀሐይ መጥለቂያዋ ሀገር ........................................................................ 94

ከሥነ ምግባር ባሻገር የት ደረስን? ........................................................................ 104

ወንዶች ሳያድጉ፣ አርጅተው የሚሞቱ ህፃን ናቸው? ........................................................................ 108

በሴት ዓለም ውስጥ አንድ ወንድ ........ 112
በወንዶች ዓለም ውስጥ አንዲት ሴት ........ 116
ሰውና ድክመቱ፤ ከወደ ሐዋሳ ........ 120
መርሳት፤ አንዱ ጥበብ፣ ሌላው ጀሃነብ! ........ 124
ሠለስቱ "ፋሲካዎች" ........ 129
በፋሲካ ይበሏል ወይስ ይምሏል? ........ 134
"የወረወርኩት አንካሴ መልሶ ለራሴ" ........ 138
ከሞት ጋር ጉባዔ ........ 141

## ጥበብ ........ 145

"ራሳቸውን ለመሳም የሚዳዳቸው ደራሲያን" ........ 147
የደራሲ ቤት፤ ገነት ቅብ ሲኦል ነው! ........ 157
ደራስያንን እንደሰው ያለመመልከት አባዜ ........ 160
አ! የደራሲ እውነት ከወዴት ነሽ? ........ 164
ደራስያን እንደ አባት ሲፈተሹ... ........ 168
ደራሲ ማደሪያ የለው ህዝብ ይዞ ይዞራል ........ 173
ዘመንና ገብረክርስቶሳዊ ዕጣ-ፈንታ ........ 178
በሥነ-ፅሑፍ መንገድ ላይ (ከዳኛቸው ወርቁ እና ከአዳም ረታ ጋር) ........ 183
"ሌቱም አይነጋልኝ" እና "ዞርባ ዘ ግሪክ" ጎን ለጎን ........ 188
"ልብ ብዬ ሳየው የሚያስቀኝ መፅሐፍ አለኝ" ........ 193
የሁለቱ ደራሲዎች የሁለት ሴት አባዜ ........ 198

# ፖለቲካ

# መለያየት ሞት ነው

ከተሰጠኝ ዕድሜ ግማሹን የኖርኩት አራት ኪሎ ነው። የተቀረውን ካዛንችስ። ነገር ግን የመላው ኢትዮጵያዊ ዕዳ እንዳለብኝ ሆኜ ተቀርጫለሁ። መቼም ተአምር፣ ትንግርት ሳይመስል አይቀርም። እንዴት ኢትዮጵያን ያህል ሰፊ አገር የተሰጠው ሰው እንዲህ ሕይወቱን በቁራጭ መሬት ላይ ከትሮ ያሳልፋል? እንዴትስ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በወገነ ብዙነት ተፈጠረ ወዳሻው አቅጣጫ አይፈስም? ትላንት ያደረበትን እንዴት ዛሬ ይደግማል? የዛሬው ቦታ ለነገው እንዴት አያሰለቸውም? ተቀባየ ብዙ ሆኖ ከተፈጠረ መስተንግዶውን እየቀያየረ እንዴት ለወገኖቹ ሁሉ እንግድነቱን አያዳርስም? እንዴት ቋንቋውን አይለዋውጥም? እንዴትስ በአንድ ቀጥዳ ውስጥ መኩራመት አይሳነውም? በምንስ ራሱን የአንድ አጥንት ሐረግ አድርጎ ማስቀጠል ይቻለዋል? በብዙ ምርጫ የመንፈግ ሕይወት እንዴት አይታክትም? ወደ ወገኖቹ የሚያደርሰኝ መጓጓዣ አንድ አቅጣጫ የያዘ ነጠላ መሆኑ እንደምን አይቆጠርም?

ኢትዮጵያዊነት ከቋንቋ በላይ፣ ከልምድ በላይ፣ ከቦታ በላይ፣ ከዘር ሐረግ በላይ፣ ጡት ከመጣባት በላይ፣ ከጐዲፈቻነት በላይ፣ ከቆዳ ቀለም በላይ፣ ከጋብቻ በላይ. . . መስጠት አይደለምን? ሁሉም ሲፈቀድልኝ እንዴት ቁራጭ ለማንሳት ዳዳሁ? ከሰፊው ጠባቡን ስለምን መረጥኩ? አቅጣጫ መጠቆሚያ የኔ መጠቀሚያ እንዴት ሊሆን ይችላል? "ካላመንክ የራስህ ጉዳይ!" አልልህም። የእኔን ሕይወት እንድታይ ግድ እልሃለሁ።

ኢትዮጵያ መጣችብኝ እንጂ አልሄድኩባትም። ፈለገችኝ እንጂ አልፈለኳትም፤ እኔን ሆነች እንጂ እሷን ለመሆን አልጣርኩም። ኢትዮጵያዊ ለመሆን ውዴታ የለም፤ ግዴታ እንጂ።

ከአራት ኪሎ አልወጣሁም፤ ከካዛንቺስ አላለፍኩም፤ ግን ኢትዮጵያዊነት ከቦታነት አልፎ እኔን ለመሆን ወደ አጥንትነት፣ ወደ ደምነት፣ ወደ አእምሮነት፣ ወደ እጅና እግርነት ተለወጠ። “እንዴት?” ካልከ “እንዲህ” እልሃለሁ።

አዲስ አበባ ደረቅ ደሴት ናት (ደረቅ ወደብ ይባል የለ?) ዙሪያዋን አልጌ የለበሰ የሜዳ ባህር አለ። ገልጣጣ ገጣጣ። የሱሉልታ ሜዳ፣ የለገዳዲ ሜዳ፣ የገፈርሳ ሜዳ፣ የጫጫ ሜዳ ... ከሜዳዎቹ ወዲህ የከተማዋ ድንበር ተራሮቿ ናቸው። የወጨጫ ተራራ፣ የየረር ተራራ፣ የእንጦጦ ተራራ፣ የየካ ተራራ፣ የአይነ ምሣ ተራራ፣ የጉስቋም ተራራ፣ አብዛኛው አዲስ አበቤ እነዚህ ተራሮች ከበስተጀርባቸው የያዙትን አዘውትሮ በአካል አይጎበኝም። የመላው አዲስ አበቤ ኑሮ ከመኖሪያ ቤት ወደ መሥሪያ ቤት የተዘረጋ የቀላል ባቡር ሐዲድ ነው። ውልፍት የለም። ያደለው አዲስ አበቤ በወርም በሁለት ወርም አንዴ የከተማዋን ጀርባ ወደሚያኩ መዝናኛዎች ይሄዳል። ሱሉልታ፣ ሜታ፣ ዱከም፣ ቡራዩ... ሥጋና ጠጅ ላይ በመዝመት የሆድ ግዳይ ይጥላል....

ተወልጄ ያደኩት አዲስ አበባ አይደል? እንደ አብዛኛው .... አዲስ አበቤ እግሬ እንጂ ህልሜ አልታሰረም። ምናቤ ነፃ ተጓዥ ነው። በራሪ ህልም አለኝ። በመንፈስ ስከንፍ የክልል ቀርቶ የሀገር ድንበር አያነቅፈኝም። ወገንተኝነት አይዘኝም፤ ብሄርተኝነት አይገድበኝም። የፍቅር እጄ በየአቅጣጫው እንደ ጨረር ይበተናል። ያገኘሁት ወገኑ ነው። “እኛ” ለማለት ቦታና ጊዜ አይገስፀኝ። እኔ አዲስ አበቤው ለማቅረብ ስል የማርቀው የለኝም።

ምን ላድርግ? የተወለድኩት ከአንድ እናትና አባት ይሁን እንጂ ያደኩት በብዙዎች ነው። የወላጅ እናት ለንዴቷ ስትጨክን፣ የምትመክር ሌላ እናት ከጎረቤት አለች፣ ያቺ የጉርብትና ወላጅ እናት ከትግራይ፣ ከኦሮሚያ፣ ከአማራ፣ ከሐረሪ ... መሆኗ ልብ አይባልም። ወላጅ እናት በእልህ የነፈገችው እህል ከጉርብትና እናት ይገኛል። ማን መርጦ ይወለዳል? እንዲያ ነው!

... አባት ሲያመር፣ ፀባዩ ሲገርር የሚመክር ሌላ የጉርብትና አባት ይነሳል። “እኔን ግደል!” ብሎ በጉርብትና ልጅ ገመድ ይገባል። ልጅ ከወላጅ የሚፈራውን፣ የተጎራባች አባትን ይጠይቃል፤

“እስከሪፕቶ ገንፍሎብኝ አባዬ ከሰማ ይገድለኛል” ይባላል።

እንዲህ ነው ያደኩት. . .

ተጎራባች አባት ከየት? ከሲዳማ? ከኩናማ?፣ ከድሬ?፣ ከቡሬ፣ ከኤርትራ?፣ ከጎርጎራ፣ ከጎንደር፣ ከሐረር?.... ምን ለውጥ ሊፈጥር?

...እኔ አዲስ አበቤው ያደኩት በደቦ ነው። የሴቶች ቀሚስ ተጋርዶ፣ ካንዱ ቤት ወደ ሌላ ቤት የተመላለሰው እንጀራ ህያው መረብ ሰርቶ፣ ህይወቴ ለዝንታለሙ አጥምዶታል። የበላሁት የብዙ ብሔሮችን ወዝ ነው። ከተማዬ እንጂ ህይወቴ በሚለያይ "ተራራ" አልተከበበም፤ ከተማዬ እንጂ ንሮዬ ደረቅ ደሴት አይደለም። አንድ ኪሎ በርበሬ በ "ቅመሱ" ሥም ስንት ደጃፍ ታንኳኳለች? ሽሮዋስ ለስንቱ ጎጆ ትሞሸራለች?

እትብቴ አንድ ጉድጓድ አጥቷል። በየቦታው ተዘርቷል። ኢትዮጵያዊ ባለበት ሁሉ እዚያ እትብቴ የተቀበረበት ይሆናል። ወገንተኛነቴ ተቀይጧል፤ አንዱን ጥሎ፣ ሌላውን አንጠልጥሎ መሆን አይሆንልኝም። የአባቴ ትውልድ አገር፣ የእናቴ ትውልድ አገር በተጎራባች ወላጆቼ ሲሳከር፤ ምን ይፈጠር?

እራሴን ልፈትሽ፣ ልቤን ልበርብር

.... እኛ መንደር የሚኖር ጅግሶ በዳሶ የሚባል ሰው ነበር። ኮፍያው ላይ "ጅግሶ በዳሶ ተዘዋዋሪ ኦርኬስትራ" የሚል አፅፏል። ሦስት ከበሮዎች፣ አቀራኝቶ በማማሰያ መሰል ዱላ ይደበድባል። የዕለት ጉርሱን ከዚያ የከበሮ ትርኢት ያገኛል። ሲሰክር ወላጆቻችን አምጡት ይሉናል። ከጠጅ ቤት ከነከበሮው ወርረን እናመጣዋለን። ጠዋት አረፋፍዶ ሲነሳ አዘውትሮ አንድ ጥያቄ ያቀርብልናል።

"ማነው ትንሽ ልጅ ቁርስ ያልበላ?"

"እኔ፣ እኔ፣ እኔ ..." ይላሉ ያልበሉ። በዕድሜ ከትንንሾቹ ጀምሮ ያለው እስኪያልቅ ሳንቲም ያድላል። መሀን ቢሆንም ባለልጅ አልሆነም?

...አንድ ሰሞን "ሸገር ካፌ" ፕሮግራም ላይ ስለ ጅግሶ በዳሶ አንዳንድ ነገር ሰማሁ። ጋዜጠኛ መአዛ ብሩ እና ሰዓሊ በቀለ መኮንን ሲወያዩ ጅግሶ በዳሶ እና ዋሽንት ተጫዋቹ አፈወርቅ ዮሐንስ ጓደኛሞች እንደነበሩ፣ አብረው እንደሰሩ፣ "ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ" አባል እንደነበሩ፣ ወደ በኋላ ጅግሶ ሁሉንም ትቶ በጉስቁልና መኖር እንደጀመረ። በእርግጥም ጎስቋላ ነበር። ወደ መጨረሻ ዘመኑ ላይ ለኛ ዳቦ የሚገዛበትን ሳንቲም እንዴት ይሰበስብ እንደነበር ለመመልከት ችያለሁ። ከበሮዎቹን በስልት ስለመታ ብቻ ሳንቲሙን አያገኝም ነበር። ጠጅ ጠጪዎቹ ሳንቲሙን ወለል ላይ ይወረውሩለታል። ጅግሶ በሁለት እጁ ተገልብጦ ዝቅ በማለት፣ ሳንቲሙን ወለል ላይ ይወረውሩለታል። ጠጪዎቹ ይደነቃሉ። ሌላ ሳንቲም፣ ሌላ በአስደናቂ ሁኔታ ሳንቲሙን በአፉ ያነሳል። ጠጪዎቹ ይደነቃሉ። ሌላ ሳንቲም፣ ሌላ መገልበጥ ... እንዲህ በስስትና በይሉኝታ ቢስነት በተጣለለት ሳንቲም ነበር በሊጋስነትና በወገንተኝነት ለኛ ዳቦ የሚገዛበት። የሥጋ አባት ከዚህ በላይ ምን ያደርጋል? በእኛና በእሱ መካከል ባዕድነት በየት በኩል ይገባል? የትውልድ አገሩ ዲላ፣ የአባታችን ትውልድ አገር ከመሆን ምን ያግደዋል? እንዴትስ ጌድኦነቱ ጌድኦነታችን አይሆንም? ወዙ አላለፈብንም?

ድካሙን አልተመገብንም? ልፋቱንና ውርደቱን አላሻመድንም? በየትኛው ቀዳዳ ጠላትነት ይነፍሳል? ባዕድነት ከሐዲነት አይደለምን? ... በመከባበር ብቻ ኖርን ማለት ሰብአዊነትን ማቅለል አይሆንም? ወገንተኝነትን ማራከስ? ሥጋን ማንኳሰስ?...

አዲስ አበቤዎች የፍቅር እጃችን አለነገር እንደጨረር በየአቅጣጫው አልተዘረጋም፤ ሰበብ አለው። ከየአቅጣጫው የተመገብነው ፍቅር ነው ሰበቡ፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ባዕድ ሳያደርጉ አሳድገውናል። አንዷ የመከራ ቀን በየትኛዋ የጉርብትና እናታችን ጥረትና በየትኛው ጉርብትና አባታችን ልፋት ተሟልታ እንዳለፈች በየልቦናዎቻችን ተመዝግባለች።

... እማማ አስካለ ዛዛ ደግሞ አሉ። ቀይ ፊታቸው ከአፍ በላይ ይናገራል። ላጠፋ ልጅ ግልምጫቸው ከቁንጥጫ በላይ ነው። መስመር ለያዘ ልጅ ፈገግታቸው እርጎ ነው። አረቄ ያወጣሉ። አሁንም ትዝ የሚሉኝ የሚግለበለበው እሳት፣ ከእንስራው ተርፎ ፊታቸውን የማለዳ ሰማይ አስመስሎት ሲያግመው ነው። የአረቄው ድፍድፍ፣ ከእንስራው እየተነነ በተዘረጋለት የቀርከሃ ቢርካ በኩል አልፎ በአንፃሩ የተገጠመችው ኩዳ ውስጥ አረቄ ሆኖ ይንጠባጠባል።

እማማ አስካለ ህይወት ውስጥ ኑሮ ያቺ ጠብታ ናት። ጠብ፣ ጠብ፣ ጠብ... እያለች ትጠራቀማለች። ኑሮ ነጠብጣብ ጠብታ ብትሆንም ለሰፈር ልጆች በልግስና መተላለፏ አይቀርም። እማማ አስካለ ልጆች ሲቀብጡ ብቻ ሳይሆን ሲራቡም ፊታቸውን አይተው ያውቃሉ። ወላጆቻቸው ሳያዩ ጠቀስ አድርገው ይለግሳሉ።

አድጌ ሥራ ይዤ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ወላይታ ለመስክ ሥራ ስሄድ፣ እማማ አስካለ ካፋቸው የማይለዩትን የዳሞታ ተራራ ያየሁት በፍቅርና በመስገብገብ ነበር። ከእኛ ጋር ያሳደጓት ያደራ ልጃቸው ብዙነሽ የት ትሆን? አፈላልጌ አጣኋት። ገና ከወላይታ እንደመጣች ሰሞን በናፍቆት ወንድሞቿን ታነሣሣ እንደነበር ትዝ ይለኛል። በዜማ ጮቤ እየረገጠች፡-

"ሙንጣዜ ላባ፣ ያሲኔ ላባ" ትላለች። ሙንጣዜና፣ ያሲኔ ና ማለት ነው አሉ። የቆየችውን ቆይታ፣ ከእኛ ጋር ለምዳ ወደ ወላይታ የተመለሰች ሰሞን፡-

"አለማየሁ ላባ ..." አላለች ይሆን?

ብዙነሽ የአስካለን የፍቅር ማህፀን የተጋራን እህቴ፣ አልነበረችም? ከአንድ ኢትዮጵያዊ ኣብራክ የተገኘን፤ ወደ እርሷ እንዳልሄድ የሚያቅበኝ የብሔር ቅጥብ የቱ ነው? ልጆቿ አትቴ እንዳይሉኝ ምን ይከለክለኛል? ጠብታ ኑሯን፣ ከኩዳ ባነሰች ቋት ተጠራቅማ፣ ከመጋራት በላይ ምን የአንድነት ምንጭ አለ? ...

... ወደ ሌላው ተጎራባች እናት ልተላለፍ።

አትዬ ግደይ ደግሞ አሉ። የሰፈር ልጆችን ወላጆቻቸው ባወጡላቸው ሥም አይጠሩም። የራሳቸው አላቸው። "ክብሮም፣ ሀለፎም፣ አባዲ፣ ኪሮስ - ና-አ" ይላሉ። እኔ ሀለፎም ነው ሥሜ። ቆይቶ ሀለፎም የሚባል የሥራ ባልደረባ አጋጠመኝ። ልቤ "ሞከሼ" ይለው ነበር። ሥምን ተንተርሶ የሚፈጠር ድንበር እኔ ዘንድ አልነበረም። ከዚህ በላይ ፀጋ ምን አለ? ይሄን ያህል ክብረት የት?

ኡፍፍፍፍ .... ! መስልቸት ሳይሆን ህመም አለበት። የአዲስ አበባ ድንበር ለአይን እንጂ ለምናብ ተራራ የለውም። በሁሉም አቅጣጫ እንዲያ ወዲያ ... ወዲያ ... ወዲያ፣ ወገን፣ ዘመድ፣ ሥጋ ... አለ። እትብቴ የተቀበረው የተወለድኩበት ቤት ጓሮ አይደለም። ሁሉም ቦታ ተሰራጭቷል። በአስተዳደጌ ውስጥ የሁሉም "እጅ አላፊ" አለብኝ - በማጉረስም በመቆንጠጥም።
ትግራይ ብቻ፣ አማራ ብቻ፣ ኦሮሞ ብቻ፣ ጉራጌ ብቻ፣ ሐረሪ ብቻ፣ ጋምቤላ ብቻ፣ ቤኒሻንጉል ብቻ፣ አፋር ብቻ፣ ሱማሌ ብቻ፣ ወላይታ ብቻ፣ ሲዳማ ብቻ፣ . . . መሆን ለኔ የተሰጠ አይደለም። ትግራይነትን ብቻ፣ አማራነትን ብቻ፣ ኦሮሞነትን ብቻ፣ አፋርነትን ብቻ፣ ወላይታነትን ብቻ. . . በሚያስቡ መገዛት ለእኔ ማነስ ነው። ማነስ ብቻ ሳይሆን ውርደት ነው። እንዴት ሁሉን ጥቂት ይበልጠዋል? እንዴት ባሕርን ወንዝ ይውጠዋል? በቀዬ ውስጥ አገር እንዴት ያድራል? ብዙ በጥቂት ይታሰራል?. . .

ሌጣውን የመጣ ብሔር ብሔረሰብ ተፈጥሮዬን ይቃረናል። አጥንቴን ያወድማል፣ ደሜን ይበክላል፣ የከፋፋዮች "ፀጋ" ቁርቁብኝ የብሔርተኛው እሳት ቢበላኝ እመርጣለሁ። . . . ይሄ ምርጫ የእኔ ብቻ አይደለም። የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ፍላጎት የጎሰኝነት ተቃራኒ ነው። ለዚህ ልከኛ ምሳሌው ሰሞኑን ሆኖ የተመለከትነው ሁነት ነው። መለያየትን ያጦዙ ባለስልጣኖች በህዝቡ ግብረ-መልስ ሲደናገጡ ከመካከላቸው ወደፊት ያስቀደሚቸው ስለ ብሔራዊ አንድነት የተሻለ መናገር የቻሉትን ነው። የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት አቶ ለማ መገርሳ ያደረጉት አንድነት ጠቀስ ንግግር አገር አቀፉን ውጥረት በመጠኑም ቢሆን ያረገበው ሕዝቡ ውስጥ የነበረው ብሔራዊ ስሜት ለመቀስቀስ በመቻሉ ነው። መለያየትን በወናፍ ሲያፋፍሙ ከነበሩ ባለስልጣኖች መካከል እንዲህ የሚል ሲገኝ መደናገር መፈጠሩም እውን ነው።

"የኦሮሞ ሕዝብ ብቻውን የትም ያህል ሊጓዝ አይችልም። ስለ ኦሮሞ አንድነት ስንል እዚህ ክልል ውስጥ ስላለው አንድነት ብቻ ማለታችን አይደለም። ይህ ሕዝብ አብሮት ከሚኖረው ከሌላውም ሕዝብ ጋር ያለውን አንድነትና በጥቅሉም ለአገር አንድነት ማለታችን ነው. . .። የኦሮሚያ ክልል የራሳችንን ክልል ብቻ ሳይሆን የዚህች አገር የአንድነት ችግር ለመፍታት ተግቶ እየሰራ ነው"።

ይሄ የአንድነት ንግግር ወደአስተውሎት የሚመልሰው ሕዝብ ብሔራዊ መሰረቱ ጠንካራ እንደሆነ ይጠቁማል። ኢትዮጵያ እንደ መንቶች እናት ተንጋላ መሞቷ ነው። በየትኛው ጎኗ? . . . ወደየትኛው አቅጣጫ? ለየትኛው ልጇ? . . . ባለንበት ተስፋ መቁረጥ ውስጥ መፍትሄው የአንድነት መልካም ንግግር መሆኑ ለገገርዎቻችን ያመላከታቸው አንዳች እውነት ያለ ይመስላል። ያዳቆናቸው ርኩሰት ካላቀሰስኳቸው ካለ ደግሞ መጨረሻቸውን ከወዲሁ መተንበይ አያዳግትም። መለያየት ሞት ነው እያልኩ ነው፤ ለተለያየው ብቻ ሳይሆን ለለያየውም የሚተርፍ ሞት!!

❖ ❖

በተለይ የብሔርና የዘር ሆሆታ ሲበዛ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ አዘቅዝቆና ጎድሎ ይታየናል። ዋስትና እናጣለን። "በሰላም ያዋልከን፣ በሠላም አሳድረን" ያልነው አምላክ ተዘናግቶ ለጉሠኞች ሴራ አገራችንን ይዳርጋት ይሆን? በልስኑ እምነታችን ንቃቃት ተፈጥሮ ቀጭን ጥርጣሬ ወደነፍሳችን ትነፍሳለች። እናስ? ይሄ ማብቂያው የት ነው? ትናንት ከርቀት የሚሰማው፤ ዛሬ ወደ ሁሉም እየተዳረሰ አይደለምን? በደኖ፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል፣ ጊኒር... እያልን ነበር፤ ዛሬ ይሄ ስጋት በሁሉም አቅጣጫ ተሰራጭቷል። . . . አዲግራት፣ መቐሌ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ደብረማርቆስ፣ ወልዲያ፣ ጂጂጂጋ፣ ጭሮ፣ አምቦ፣ ጅማ፣ በደሌ፣ በደኖ፣ ቤኒሻንጉል፣ ወሊሶ፣ መቱ፣ መቂ፣ ዝዋይ፣ አዳማ፣ ደሴ፣ . . . ከአባቶቻችን ምን ተሰጥቶን እኛ ምን ጨምረን በአጭር ጊዜ እዚህ ደረስን?- ሥጋት! መጠጊያ ማጣት! ዋስትና መጥፋት... ከእግዚአብሔር በታች ወዴት?...

...በዚህ ዘመን የተፈለገው እዚችጋ እንድንደርስ ነው። በሀገራችን፣ በከፍለ-ሀገራችን፣ በአካባቢያችን፣ በመንደራችን፣ በሠፈራችን፣ በቤተሰባችን፣ በራሣችን... እንዳንተማመን። ዋስትናችንን ከህበሻነታችንና ከጨዋ ህዝብነታችን ነጥቆ መውሰድ የሚሻ አካል አለ። ይሄ አካል ችግሩን ፈጥሮ መፍትሔው እሱ ጋ እንዳለ

የሚለፍፈው "መንግሥት" ነው። ማን አጣልቶ ማን ይገላግለናል? ማን አዋግቶ ማን ተኩስ አቁም ያውጅልናል?.... በዚህ መሀል የአገር ዕጣ-ፈንታ አጣብቂኝ ውስጥ ይሰነቀራል። ዘመኑና ዘመነኞቹ የፈለጉት እዚች ጋ እንድንደርስ ነው።

ሆሆታ፤ በተለይ የብሔርና የዘር ሆሆታ የዚች አገር ልጓም አድርጎ የሚመለከተው የዘመኑ መንግሥት ብቻ አይደለም። አያያዙ ይለያይ እንጂ ጥንትም ነበር። ከአፄ ምኒልክና ከኢትዮጵያ አንድነት ወዲህ እንኳ ይሄን የብሔር ሥጋት የአገሪቱ ልጓም ማድረግ አልቀረም። ልጅ ኢያሱ ያጠመዱት የብሔር ፈንጂ ጋብቻ ላይ የተመሰረተ ነበር ይባላል። ከተለያዩ ብሔሮችና ጐሣዎች ጋር የጋብቻ ዝምድና በመፍጠር፤ እሳቸው በሥልጣን እስካሉ ድረስ ረግታ የምትቆይ ኢትዮጵያን አዘጋጅተው ነበር። አቶ ኀበዜ ጣፈጠ "አባ ጤና ኢያሱ" በተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ ሥጋታቸውን ይገልፃሉ። ልጅ ኢያሱ በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ አገር ይረጋል። ከልጅ ኢያሱ በኋላ ግን እኔ እነግሥ፣ በእኔ እነግሥት ሁከት ይነሣል። ይሄን የልጅ እያሱ ድርጊት ከሥልጣን በላይ ለሀገርና ለህዝብ አለማሰብ ነው ይሉታል።

ከሥልጣን በላይ ለሀገርና ለህዝብ አለማሰብ የያኔ ብቻ ሳይሆን የአሁንም ችግራችን ነው። ልጅ ኢያሱ ከሁሉም ብሔር ወልደው የነጋሲ ዘርነትን በአገሪቱ ሁሉ ረጩት። እሳቸው በህይወት እስካሉ ድረስ ሁሉም በአልጋወራሽነት አቆብቁቦ ይጠብቃል። ከዚያስ? የእኛ እንጂ የእሳቸው ግድ አልነበረም። በዚህ ዘመንም ከመንግሥት አብራክ የተገኙ ካድሬዎች በልጅ ኢያሱ የነጋሲ ዘርነት መንፈስ ላይ ይገኛሉ። ሁሉም የየአካባቢው አልጋወራሽ ሆነው ኢህአዴግ እስካለ ድረስ አገር ይረጋል እያሉ ነው። ከዚያስ? የእኛ እንጂ የእነሱ ግድ አይደለም።

አፄ ኃይለሥላሴ የአገሪቱ ልጓም በእጃቸው እንዲሆን ያስቆጠራቸው ከብዙ ብሔር መወለዳቸውን እንደምክንያት በማቅረብ ነበር። ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አማራና ጉራጌ ዋና ዋና የአፄ ኃይለሥላሴ የዘር ግንዶቻቸው ናቸው። ስለዚህ "ኢትዮጵያ፣ ማለት እኔ ነኝ" እስከማለት ደርሰው ነበር። ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም አንድ ጊዜ ከአፄ ኃይለሥላሴ ጋር ሲነጋገሩ እንዲህ አሉኝ ይላሉ፡-

"አንተ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የምትለው፣ ኢትዮጵያ ያለእኔ ምንም አይደለችም፤ ዕድልዋ ከእኔ ጋር የተሣሠረ ነው። እኔ ነኝ የማደርሳት። ካለእኔ ትኖራለች ብለህ አታስብ" ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት "እንደዚህ በድፍረት ሲናገሩ በጣም ተገረምኩና ተበሣጨሁ።" ይላሉ። አፄውን ዝም አላሏቸውም የሚቀጥለውን ተናገሯቸው፡-

"እንዴት እንደዚህ ያስባሉ? ኢትዮጵያ እኮ ሕያው ነች! እኛ ሁላችንም ዐላፊዎች ነን። ኢትዮጵያ ግን አታልፍም። እስቲ ይመልከቱ! አፄ ምኒልክ ዛሬ የት ናቸው? አባትዎስ ራስ መኮንን የት አሉ? ሌሎቹስ ታላላቆችና ገናናዎች የነበሩት ሁሉ የት ናቸው? ኢትዮጵያ ግን አለች። ወደፊትም ትኖራለች።"

አፄ ኃይለሥላሴ የፊታውራሪን ሐሳብ ሊቀበሉ አልፈለጉም። "ኢትዮጵያ ያለ እኔ ትኖራለች ብለህ አታስብ!" የሚል አቋማቸውን ደግመው ደመደሙ። ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት በተስፋ መቁረጥ የራሳቸውን ተህዝቦ አስከትለው እንዲህ ይላሉ፡-

"ከዚያ ቀን ወዲህ በአፄ ኃይለሥላሴ ላይ የነበረኝ አስተያየትና ስሜት ሁሉ ተለወጠ። ከንቱ መንፈስ እንዳደረባቸው ተረዳሁት። እኔ ኢትዮጵያን ላንድነትዋ ለጅምላነትዋ ነው እንጂ ሌላው አያጓጓኝም። ንጉሦችና ባለጊዜዎች ከጥፋት የሚደርሱት በከንቱ ውዳሴና በከንቱ ትምክህት ነው። ፍጡሮች መሆናቸውን ይረሱትና ሁሉን ማድረግ የሚችሉ፣ ሁሉም ለእነርሱ ደስታና ክብር የተፈጠረ ይመስላቸዋል። በዙሪያቸው የሚከቡዋቸው ጥቅም ፈላጊዎች ሁሉ ይህንኑ እያስመሰሉ እንዲያምኑበት ያደርጓቸዋል። ታዲያ ከሕግ በላይ መሆን፣ ከፍጡር በላይ መሆን ያምራቸውና በዘፈቀደ እንስራ ይላሉ። የሚከራከሩዋቸውንና የማያደንቋቸውን እንደጠላት ያዩዋቸዋል፣ ያጠቋቸዋልም።"

ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት የተብከነከኑትና የተቹት እኛን ሆነው ነው። ትችቱም ሆነ መብከንከኑ የዚህም ዘመን ነው። በሽታውም የተዋረደ። ይሄ መንግሥት እዚህ መታበይ ላይ ደርሷል። ‹ኢትዮጵያ ያለእኔ ትኖራለች ብላችሁ አታስቡ።› የሚል አቋም ላይ ደርሷል። ይቺ አገር እብድ መሪ፣ ዕጣ-ፈንታዋ ይመስላል። ጨርቁን በጣለ የሥልጣን ፍላጐት አገር ገደል እስኪገባ መጋለብ የወደላይ ቤት በሽታ ሆኖ እስከ አሁን ዘልቋል። በወኪል ግልቢያ የሥልጣን እርካብ የረገጠ የመሰለው ኢሣያስ አፈወርቂ እንኳ፤ የብሔርና የዘር ሆሆታችንን እንደ ኑክሊየር እያብላላ መሆኑን ተናግሮ ነበር። ኑክሊየሩን አንዴ ከተኮሰው ለመቶ ዓመት "ራዲዮ አክቲቩ" ከአገራችን የማይጠፋ የቤት ሥራ እንደሚሆንብን አውጆ ነበር። እንኳን ከተዛተ ከተሰነዘረም ተጠብቀን ይሄው አለን።

በተለይ የብሔርተኞችና የዘረኞች መካካት ሲበዛ፣ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ አዘንብሎና ጐድሎ ቢታየን አያስገርምም። ዋስትና ብናጣም አያስደንቅም። በልስኑ እምነታችን ላይ ንቃቃት ተፈጥሮ ቀጭን ጥርጣሬ ወደነፍሳችን መንፈሱም እንደተአምር አይቆጠርም። ዋናው ጉዳይ በዚህ ዘመን እዚህ ሁኔታና ስሜት ላይ

እንድንደርስ በጥብቅ እንደተፈለገ ማወቁ ላይ ነው። ዋናው ጉዳይ በብሔራዊ ስሜታችን፣ በአንድነታችን፣ በታሪካችን፣ በፈጣሪያችን፣ በተጋድሏችን... እንዳንተማመን በጥብቅ እንደተፈለገ ማወቅ ላይ ነው። ከዛ ውጭ እብድ ገገር ቅዠምዠም ነው - ካጐነበሱ ያልፋል፤ ከመከቱት ይታጠፋል። ቀሪው ህዝብና ሀገር ብቻ ነው። "ኢትዮጵያ ያለ እኔ ትኖራለች ብላችሁ አታስቡ!" የሚል ጨርቁን የጣለ ገገር በፊትም ነበር፣ አሁንም አለ፣ በኋላም ይመጣል። በፊትም እንዳልነው፣ አሁንም እንደምንለው፣ በኋላም እንደምንደግመው (በፈታውራሪ ተክለሐዋርያት አንደበት) ይታወቅ።

"እንዴት እንደዚህ ታስባላችሁ? ኢትዮጵያ እኮ ሕያው ነች! እኛ ሁላችንም ዐላፊዎች ነን። ኢትዮጵያ ግን አታልፍም። እስቲ ተመልከቱ! ልጅ ኢያሱ የት ናቸው? አፄ ኃይለሥላሴ የት አሉ? የመንግሥቱስ ድምፅ መች ይሰማል? ሌላው ቀርቶ የቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ መች አሉ?.... ኢትዮጵያ ግን አለች። ወደፊትም ትኖራለች።"

❈ ❈

ይድረስ ወገን ከእኛው ለኛ
አበቅቴ ውሉን አልሳተም፣ ፅዋህን ተቀበለኛ
ይድረስ ለክቡር ወገኔ፣ ምነው ጥላችን ቀለለ?
እማማ ኢትዮጵያችን ለምን፣ እያደር እየዋለ
ማህፀኗ ከጐደሎ በቀር፣ ሙሉ ሰው አልወልድም አለ?
....
ዛሬ በቋንቋ ቦጠሊቅ፣ በምንተበትበው ቅስፈት
እንዴት እኛው ሰበብ እንሁን፤ ለዓለም ጥቁር ህዝቦች ውድመት?
መቼም የሰው ትንንሽ ዘር፤ እንደ ሂትለር አሳር መፍጠር
ህዝብ መሀል አጥር ማገጠር
የጐሳ ገደል መቆፈር።
ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን (ከ"ይድረስ ለኛ" የተቀነጨበ)

ፀጋዬ ያኔ (በ1989 ዓ.ም.) በመንታ ህመም ተይዞ ነበር። የአካልና የመንፈስ። የአካል ህመሙ ከኩላሊቱ ጋር የተያያዘ ነበር። የመንፈስ ጥዝጣዜው ደግሞ ከሀገሩና ከህዝቡ ዕጣ-ፈንታ ጋር የተቆራኘ። የአካል ደዌው በሞት ምላሽ አገኘ። የመንፈሱስ? ሞት የማይረታው መንፈሱ ዛሬም በአሊጋ-ቁራኛ እንደተያዘ ይሆን?

ከዚህ ውጭ ምን አማራጭ አለ? "ህዝብ መሀል አጥር ማጠር" ሆነ "የጐሳ ገደል መቆፈር" ዘንድሮም አልቆመ፤ ታዲያ? መንፈስ የማናሳርፍ ትውልድ ሆነን ልንቀር? እስከመቼ?...

ከሀገርና ከህዝብ ዕጣፈንታ አንፃር ተስፋ-አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ያለን ይመስላል። ጐሳን እንጠልጥሎ፣ ሌላውን ጥሎ በአውር ድንብር መጓዝ በዚህ ዘመን ውጤት እያመጣ መሆኑ ታይቷል። የጋራ አጥር ተነቃቅሎ፣ ደጃፉ ከደጃፉ ተገንጥሎ፣ ሁሉም የየበራፉ ፎካሪና አማራሪ ሆኗል ያሳዝናል። ፉከራው ለማን? ማማረሩ በማን?... ይሄንን ነው ፀጋዬ እንዲህ ያለው፤

"በዕውራን አመራር ከፋት፣
ዓለምን ያጥለቀለቃት፣
ከውሃና ከእሳት ጥፋት
የከፋው የቋንቋ መዓት።
...
ጠባብነት ብሎ ነገር፣ ይኸው በልሳን መሰሪ
አመሀኝቶ መአት ጠሪ
ሁሉ ቂም በቀል ዘሪ
ሁሉ አዕፅምት ቆፋሪ!...
መቻቻልን ካልተማርነው
በቋንቋ ሰበብ ተፋጅተን፣ ዓፅም መልቀም ምን ዋጋ አለው?"

እዚያም እዚህም የሚያስፎክረው፣ ሰበቡ ቋንቋ ነው። ዘሩማ አንድ የተቀላቀለ ነው። ልለይህ ቢሉት የሚያዳግት፣ ላጥራህ ቢሉት የሚጐሽ ነው። ሌላው ገጣሚ ሰሎሞን ዴሬሳ (ነፍሱን ይማረውና) የመሰከረው ይሄንኑ ነው። እንዲህ አለ፡-

"ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀምጦ እኔ የትግራይ ሰው ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ ብሎ አፍ ሞልቶ መናገሩም አለማወቅ ይመስለኛል። በሴት አያቶቻችን በራፍ ላይ ማን እንዳለፈ ስንቶቻችን ነን የምናውቀው? የእኔን ጥሩ ኦሮሞነት እግዚአብሔርና የሴት አያቶቼ ብቻ ናቸው የሚያቁት። የሁሉንም እንዲሁ። ጦር ባለፈ ቁጥር በመዋለድ፣ በንግድ በመገናኘት፣ ተቸግሮ ከአገር ወጥቶ ሌላ ቦታ በመኖር ይቀላቀላል።"

እንኳን እኛ ሶስት ሺህ ዘመናት አብረን ቆጥረናል የምንለው ኢትዮጵያውያን ቀርቶ፣ ሶስት መቶ አመት ያልሞላቸው አሜሪካውያን እንኳን ተቀላቅለን ጨርሰናል እያሉ ነው። እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም. የተካሄደ አንድ ጥናት እጄ ገባ። ጥናቱን ያካሄዱት በፍሎሪዳ አትላንቲስ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ፒተር ፋይን ናቸው። ፕሮፌሰር ፋይን ተማሪዎቻቸው አንድ ጥናት እንዲያደርጉ አዘዙ። የታዘዘው ጥናት

ተማሪዎቹ በራሳቸው ላይ የሚያካሂዱት ነበር። በቅድሚያ ከየትኛው ዘር እንደመጡ ግምታቸውን ይሰጣሉ። ቀጥለው በዘረመል ምርመራ (DNA) ያረጋግጣሉ።

አስራ ሁለት ተማሪዎች እራሳቸውን የአውሮፓ ስረ-መሰረት ያላቸው ነጮች እንደሆኑ ተናገሩ። አንዱ ጥቁር አፍሪካዊ ነኝ አለ። የዘረመል ምርመራ ውጤቱ ሲመጣ፣ ከአስራ ሁለቱ ተማሪዎች አንዱ ብቻ ሙሉ በሙሉ አውሮፓዊ ዝርያ እንዳለው ተረጋገጠ። አስራ አንዱ ግን የአውሮፓ፣ የአፍሪካ፣ የአሜሪካ ነባር ተወላጆች እና የምስራቅ እሲያ ጂን ቅልቅል ሆነው ተገኙ። ጥቁር አፍሪካዊ እንደሆነ የተናገረው ተማሪ ሃያ አንድ ከመቶ የአውሮፓ ቅልቅል ዝርያ እንዳለው ተነገረው። ፕሮፌሰር ፋይን እራሳቸው ነጭ አውሮፓዊ ነኝ ብለው ነበር። በምርመራው ሃያ አምስት ከመቶ የነባር አሜሪካውያን (ሬድኢንዲያን) ቅልቅል ዝርያ እንዳላቸው አረጋገጡ። ፕሬፌሰሩ ከጥናቱ መጠቃለል በኋላ ለ"uk Observer" ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ እንዲህ አሉ፡-

"አሜሪካኖች እራሳቸውን እንደተቀላቀለ ህዝብ ቢቀበሉ፣ ብዙ ነገሮች ሊቀየሩ ይችላሉ።"

እኛስ? እራሳችንን እንደተቀላቀለ ህዝብ ብንቀበል ብዙ ነገሮች ሊቀየሩ አይችሉ ይሆን? ደግሞስ እንደተቀላቀለ ህዝብ እራሳችንን ለመቀበል የሚያስችል ታሪካዊ መረጃ አይኖረን ይሆን? ለዚህ አፄ ኃይለስላሴን ማንሳት ብቻ በቂ ይሆናል። አፄው በአባታቸው የኦሮሞ፣ የአማራና የትግሬ ዝርያ እንዳለባቸው ሲነገር፣ በእናታቸው በኩል ደግሞ ጉራጌና ወሎዬ ናቸው። ከዚህ አልፎ በአባታቸው ሩሲያዊነትና አረብነት እንዳለ በሰፊው ይወራል። ይሄን በተመለከተ "የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ" ላይ እንዲህ የሚል ሰፍሯል።

"የአያታቸውን ውልደት ከየትኛው ጐሳ እንደነበር (አፄ ኃይለስላሴ) ባለመግለፃቸው አንዱ ኦሮሞ ናቸው፣ ሌላው ትግሬ ናቸው፣ ሲል የተቀረው ደግሞ አማራ ናቸው በማለት የተዘበራረቀ ገለፃ ቀርቦበታል። ጃንሆይም ይህንን ሁኔታ በስልጣን ዘመናቸው አንዴ ትግሬ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ኦሮሞ ነኝ እያሉ እንዳመቻቸው ተጠቅመውበታል።"

ሰሎሞን ዴሬሳ "በሴት አያቶቻችን በራፍ ላይ ማን እንዳለፈ ስንቶቻችን ነን የምናውቀው?" ሲል ህሊናችንን የሞገተው ይሄንን በመመልከት ይመስላል። ታላላቆቹ ገገርዎችና መኳንንቶች እድሉና አቅሙ ስለነበራቸው፣ ለአገዛዙም ግድ ስለሚላቸው ዘራቸውን የሚያትት ዜና መዋዕል አፃፉ። ይሄ እድልና አቅሙ የተነፈገን ብዙሃን በየትኛው የዘር ጥናት ተመስርተን በንፁህ ኦሮሞነት፣ ባልተነካካ አማራነትና በአንጡራ ትግሬነት... እንኩራራለን? ቋንቋ ከመውረስ ውጭ

ማረጋገጫችን ምን ይሆን? በግድም በውድም አንዱ ወደሌላው ሲዘልቅ አልኖረምን? እዚህ መዘላለቅ ውስጥ እንዴት ያለ የዘር እርግጠኝነት ይኖራል?....

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "የአባ ባህርይ ድርሰቶች" የተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ አጥብቀው የሚሞግቱት ይሄንኑ ነው። የማይገናኙና የማይጣጣሙ የሚመስሉ ብሔሮች ውስጥ ውስጡን በባህልም በዘርም መደበላለቃቸውን ይነግሩናል። ሲቀጥሉ፡-

"በደም የዘሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ከተራው ህዝብ ቤት እስከ ቤተ መንግስት የጎሳዎችና የነገዶች ግንኙነት ውጤት መሆናችንን የሚያሳየው ያያቶቻችን የጋብቻቸው ታሪክ ያልተፃፈው በኢትዮጵያውያን መካከል ጋብቻ ጉድ ወይም ብርቅ ስላይደለ ነው...

"...የየጎሳው ልጆች ያስመሰለን ታሪካዊ አጋጣሚና በቦታ መወሰን ምክንያት ግማሾቻችን ያንዱን ነገድ ቋንቋ፣ ግማሾቻችን ደግሞ የሌላውን ነገድ ቋንቋ ስለምንነጋገር ነው። ለምሳሌ ደምቢያን (ጎንደርን) እና ጎጃምን የወሰዱ የኦሮሞዎች ልጆች ቋንቋ አማርኛ ሆኗል፤ አማራ መስለዋል። የአርሲ ህዝብ ከግማሽ በላይ የሐድያ ትውልድ ሆኖ ሳለ ቋንቋው ኦሮምኛ ሆኗል፤ ኦሮሞ መስሏል። ይኸ መስሎ መገኘት ለጠላት መግቢያ ትልቅ ቀዳዳ ሆኖ እነሆ ሊያተራምሰን ይመላለስበታል።"

እነሆ ታሪክ ቆንጣሪና ቃላት ሰንጣሪ የገባበት የዘንድሮ የዘረኝነት ቱማታ "ኢትዮጵያዊነትን" የመዋዕለ-ህፃናት ጠባይ ሰጥቶት ተስተውሏል። ውጤቱ "አፅም መልቀም" ሆኖ ሳለ ከቆርኪ መልቀም እኩል መቅለሉ የዘረኝነት ተከታቢዎቹን ጮርቃነት የሚያሳብቅ ነው። ለነገሩ ፀጋዬ ገብረመድህን "በእርግማን፣ በጥላቻ ሴራ ከትበን" ሲል የገለፃቸው እነዚሁት የጐሰኝነት ባለሳምንቶች ሳይሆን ይቀራል?

"ይድረስ ለክቡር ወንድሜ መልአከ ሞትን አምልከን፣
እንደ ቅድመ ታሪክ አውሬ፣ በእልቂት ገደል ተናንቀን
በቋንቋዎች አመካኝተን፣ የሌለ ሰቆቃ ፈጥረን
ትውልዳችንን አምክነን
ልጆቻችንን በእርግማን፣ በጥላቻ ሴራ ከትበን
ከምናስጨርስ መርዘን፣
ከመስበር የታሪክ ድልድይ
ከመሆን የዘመን እኩይ
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ አዲስ ራዕይ አብረን እንይ።..."

# ስፓርት ለጦርነት

ልጅ ኢያሱ በቁመቷም፣ በደረቷም በተወሰነችው ድንክ የንግሥና ዘመናቸው ላይ ብዙ አይነት "ጠባይ" እንዳስቆጠሩ ይነገራል። ከዚህ ጠባያቸው አንዱ አጠገባቸው የተገኙ መኳንንቶችን በነገር እያነካኩና እያፎካከሩ አንዳንዴ በጅብዱ ያከራክራሉ፤ ሌላ ጊዜ በአካል ያታግላሉ። ስለዚህ ጉዳይ ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ‹ኦቶባዮግራፊ (የህይወቴ ታሪክ)" የተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

"...ታዲያ ልጅ ኢያሱ ቀኛዝማች ወልደአማኑኤልንና ቀኛዝማች ፋሪስን አታገሏቸው። ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል በንቀት አስተያየት እያየ ተጋጠመ። (ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል በራስ መኰንን ቤት በጉልበታምነቱ የታወቀ ነው) ቀኛዝማች ፋሪስ ጣለ፤ ልጅ ኢያሱ እያጨበጨቡ ደስታቸውን ገለጡ። እኛ ግን ዐፈርን (በልባችን ውስጥ የሚታገሉት ወልደአማኑኤልና ፋሪስ አይደሉም ሸዋና ወሎ፣ ክርስቲያንና እስላም ናቸው።) ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል ተገረመና እንደገና ታገሉ። ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል ጣለ።" (ገጽ 222)

ይሄ ታሪክ የመንደር ውሪ ጠባይ በመሰለ አስተዳደር ውስጥ አገራችን አልፋ ኖሯል? ያሰኛል። መኳንንቶቻችንን "ትችለዋለህ?" እያለ የሚያፏክር መሪ? "ይዋጣላችሁ" እያለ የሚያታግል ገገር?... ከሁሉም የከፋውና አደገኛው ደግሞ የፀሐፊው የፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ትርጉም ነው። ወልደአማኑኤልና ፋሪስ ለታገሉ አካባባዊነት ጋ ምን ወሰዳቸው? ሐይማኖት ጋ ምን አንጠለጠላቸው? ወልደአማኑኤል ሸዋን፣ ፋሪስ ወሎን ወክለናል አሉ? ያልተባለ በልብ አስቦ ማፈርን ምን አመጣው?... እንደዚህ ዘመን "በመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች" ስም "ወሎ"ና "ሸዋ" በግልፅ ግለሰብ ወክለው ሲታገሉ ቢያዩ ፊታውራሪ ምን ሊፅፉ ኖሯል? እንዴት ሊያፍሩስ ነበር?...

የዘመን ጠባይ ዞሮ መጥቷል። በዚህ ዘመንም በመንደር ውሪ ጠባይ በ"ትችለዋለህ" እና በ"ይዋጣላችሁ" አግባብ በብሔር ተቧድነን "ትግል" እየገጠምን ነው። ሁሉም ብሔር ሆነ ብሔረሰብ "እኔ" እና "እነሱ"ን የሚያጎለብትበት አመታዊ በዓሎች ታርቲመኛ እንዲሆን በልጅ ኢያሱ "መንፈስ" ተገድዷል። ፋክክሩ ስፖርትን አማካኝ ያደረገ መሆኑ እርግጥ ነው። ስፖርት ለጤንነት፣ ለወዳጅነትና ለሠላም የሚበጀው፣ ስፖርቱን ማዕከል አድርገው በተቧደኑ ክለቦች መካከል ሲካሄድ እንጂ ብሔርን መሠረት ሲያደርግ አይደለም። ብሔርን መሠረት ያደረገ ስፖርት ትርፉ የመለያየት ሠርጥን ማስፋትና እኔነትን ማጎልበት መሆኑን ይኸው እያየን ነው። እንደ ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ያልተባለን በልብ አስቦ ማፈር አይደለም። በገሃድ እታየ ነው። መቐለዎች የአዲግራቶችን ንብረት ያወደሙት፤ "አጋመ ይውጣ!" ያሉት በስፖርት ነው። ባህርዳሮች መቐሌ ላይ የተደበደቡት በስፖርት ሰበብ ነው፤ መቐለዎች ወልዲያ መጥተው በብጥብጥ ሳይጫወቱ የተመለሱት በስፖርት ነው፤ ፋሲል ከነማ ከመቐለ ከተማ ጋር ጎንደር ላይ እንዳይጫወት የተሰጋው በስፖርት ሰበብ ነው።

እናስ? መለያየት በስፖርት እውን አልሆነም? ስፖርት ለጦርነት አልዋለም? ብሄር ነክ ስፖርት ክብረነክ መሆኑን ለመረዳት ደግሞ የጨዋታው ዘገባ ምን እንደሚመስል ማየት ይበቃል።

ኦሮሚያ ማንን አሸነፈ? ትግራይ ማንን ረመረመ? ደቡብ ማን ላይ ሀትሪክ ሰራ? ቤኒሻንጉል ማንን በጨዋታ ሙሉ በሙሉ በልጦ ተገኘ? አፋር ማንን ጥሎ ገባ? ሶማሌ ማንን አታለለ? ሐረሪ ማን ላይ ሎጨዋ ከተተ?... ማን ላይ ምን ስሜት አደረ? ጊዮርጊስን፣ ቡናን፣ ደደቢትን... እንደምንደግፈው አይደለም። ለአርሰናል፣ ለቼልሲ፣ ለማድሪድ... እንደምንጮኸው አይሆንም። ይሄ የብሔር ጥያቄ ነው። ለዘር ትምክህት ቅርብ ነው። ግለሰብ እንኳን ሲታገል የሚተረጎም፤ ሸዋና ወሎ፣ ክርስቲያንና ሙስሊም የሚባል ነው።

በእግር ኳስ ረገድ ግብፅ አዘውትራ ኢትዮጵያን በሰፊ-የጎል ልዩነት ማሸነፏ ከስፖርታዊ ስሜት አልፎ በአገራዊ መቆርቆር የሚያንዘረዝራቸው ብዙዎች ነበሩ። አንድ ጊዜ ጋዜጠኛ ዓለምነህ ዋሴ በሬዲዮ ሲትከነከን ሰምተነዋል። ግብፅን ብቻ የሚያሸንፍ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቡድን እንዲኖር ሲመኝ ነበር። በእግር ኳስ በሰፊ ጎል ልዩነት መሸነፍ ግብፅን አተልቆ ለመመልከት የሥነ-ልቦና ድቀት እንዳይዳርገን ነበር ሥጋቱ፤ ግብፅ ላይ ያለን ታሪካዊ ቁርሾ ሠላማዊ ግጥሚያውን ጦርነታዊ

ፍልሚያ ቢያስመስለው አይደንቅም። አንድ ብሔር አጥቂ፣ ሌላው ተጠቂ፤ አንዱ ወራሪ፣ ሌላው ተወራሪ፤ አንዱ ትምክህተኛ፣ ሌላው ብሶተኛ... ተደርጎ በሚቀነቀንበት በዚህ ዘመን፤ ብሔር ተኮር ስፖርት "ለጤንነት"፣ ብሔር ተኮር ውድድር "ለወዳጅነት" ይሆናል ማለት ዘበት ነው።

በዚች አገር እንኳን ስፖርት ጦርነትም የወንድማማች የነበረበት ዘመን አልፏል። የከፋ የመጨረሻ ንጉስ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ፣ አምላክ በአሳቸው አድሮ የሚናገር መኘ የሚታመንላቸው ገዥ ነበሩ። ከአፄ ሚኒልክ ጦር ጋር ለመዋጋት በሚሰናዱበት ጊዜ የእንግሊዝ መልእክተኛ ወደ እርሳቸው መጣ።

"ምንድነው?" አሉት

"ዩጋንዳ ላይ የሰፈረው የእንግሊዝ ጦር ልኮኝ ነው።"

"ምን ብሎ?"

"ከምኒልክ ጋር መዋጋትዎ ስለማይቀር ጦር መሳሪያ እንላክልዎ ይላል።"

ንጉስ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ እንዲህ ሲሉ መለሱ:-

"አሁን የሚካሄደው ጦርነት የወንድማማቾች ጦርነት ነውና የእናንተ ዕርዳታ አያስፈልገኝም። እኔ ምኒልክን ካሸነፍኩ አገሩን በሙሉ አስተዳድራለሁ፤ እሱ ካሸነፈኝ አገሩን በሙሉ ይግዛ። እርዳታ የምጠይቃችሁ የውጭ ጠላት ሲመጣብኝ ብቻ ነው"

ይሄ በጦርነት ላይ የነበረው ኢትዮጵያዊ ወንድማማችነት ዛሬ በሰላሙም ጊዜ የለም ማለት ይቻላል። ሁሉም በየፊናው ተትከንካኝ እንዲሆን ስለተፈለገ ይሄው እየሆነ ነው። እንኳን ጦርነት፣ ስፖርትም በወንድማማቾች ፉክክር መታየቱ እጅግ፣ እጅግ... አጠራጣሪ ሆኗል። ቀድሞውንስ ሌላ ፍላጐት ከሌለ በስተቀር የእርስ በእርስ ጦርነት የመሰለ ስፖርት ፌስቲቫል በብሔር ብሔረሰብ ተቧድኖ ለምን? በማን መሸነፍ ማን ሊያዝን? በማን ማሸነፍስ ማን ሊጨፍር?...

የመላ ኢትዮጵያ ጨዋታዎች የስፖርት ውሎ ዘገባ ስናደምጥ ምን ይሰማናል? ከብሔር ወካይ ስያሜ ጋር ተያይዞ መሸናነፍ ሲለፈፍ ከሚሰማን ደስ የማይል ስሜት ባሻገር "የሰሜን፣ የምዕራብና የምስራቅ ደርቢ" በሚል የተወከሉ ተቀናቃኝ

ጥንድ ብሔሮች መደልደላችን የዕብደት አስመስሎብናል። የሰሜን ደርቢ ክልሎች አማራና ትግራይ መሆናቸው ነው። የምዕራብ ደርቢዎች ደግሞ ቤንሻንጉልና ጋምቤላ፤ ሐረሪና ኦሮሚያ የምሥራቅ ደርቢዎች ናቸው። ይሄ ምደባ የሚያስታውሰን አንድ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ሁለት ተቀናቃኝ የፖለቲካ ድርጅቶች መፋለምን አይደለም? ለምሳሌ ሕዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ እና ኢህአሠ በሰሜን ኢትዮጵያ አካሂደውት የነበረው የእርስ-በርስ ጦርነት። ወይም የመካከለኛ ኢትዮጵያ (አዲስ አበባ) ደርቢዎች ኢህአፓና መኢሶን የእርስ በእርስ መጫረስ ታሪክ… ደርቢ። ታዲያስ?

ብሔር ወካይ ጨዋታዎች በመንደር ውሪ ጠባይ፣ በይዋጣልን ግብግብ ከሚያስገኘው ውጤት በላይ የሚሰጠው የመለያየት ትርጓሜ አስፈሪ ነው። እንደ ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ያልተባለ ማዳመጥና ያልሆነ መመልከት አይደለም። ግለሰቦችን የብሔርና የእምነት ወካይ አድርጐ ትግላቸውን እንደ የእርስ በርስ ጦርነት ምፅአት መተርጐምም አይሆንም። ግልፅ ነው። የከፋፍለህ ግዛው ግብ ስላለው፣ በስፖርት ስም ማፏከር በየብሔሮቹ መካከል የሚፈጥረውን የቅሬታ ሰርጥ እንዲያሰፋው ታስቦ ብቻ ነው። ልፉ ቢላቸው እንጂ ሥር የሰደደ ወንድማማችነት ካለ፣ ወንድማማችነቱን እንኳን ስፖርት ጦርነትም እንደማያጠፋው በንጉስ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ታሪክ ተረጋግጧል። የእርሳቸውን መንፈስ ያውርድ! አሜን!!!

## በኑሮ መቃወም!

ለጠራረገን ሁሉ መግበስበስ የዚህ ዘመን ዓይነተኛ በሽታ ነው። የተገደድንበትን ነገር የምንተገብረው እስካልተገደድንበት ድረስ አፈግፍገን ነው። “እጃችሁን ስጡ” ስንባል እግራችንን ጨምረን እናስረክባለን። “አደባባይ አትውጡ” ከተባልን ካልጋችን ላለመውረድ እንወስናለን። የፍርሃት “ኔትወርክ” ዘርግተናል። ለጭነት ተመቻችተናል “ዱላ” የያዘ ሁሉ ይነዳናል። ያፈጠጠ ሁሉ አንገት ያስደፋናል...

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ለጠራረገን ሁሉ መጠራረጋችን ግድ ቢሆን እንኳን መግበስበሳችን ላይ እናስብበት። የተገደድንበትን ነገር ስንተገብር እስካልተገደድንበት ድረስ ማፈግፈጋችንን እንታዘብ። የተጠየቅነውን “እጃችንን” ስንሰጥ ሳንጠየቅ ያስረከብነው “እግራችን” ይቆጨን። አደባባይ አለመውጣትና ካልጋ አለመውረድ ምን አንድ እንዳደረጋቸው አስበን በራሳችን ላይ እንሳቅ። ጊዜ ለሰጠው “ዱላ ያዥ” ብቻ ስንነሳ፣ ለአስመሳይ ባለስልጣን አንገታችንን አንድፋ....

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...አደባባይ ባይሆንልን ቤታችንን ነፃ እናውጣ። “እኔና ቤቴ ግን በኢትዮጵያ አንድነት እናምናለን” ብለን እንፃፍ፣ ፅፈን ግድግዳችን ላይ እንለጥፍ። በአደባባይ ያጣነውን ነፃነት በቤታችን ውስጥ እንቀዳጅ፣ የተዋረደውን ባንዲራ በቤታችን ከፍ-ከፍ እናድርግ። የተሻረውን ካርታ ሳሎናችን ውስጥ እንሹም፣ ኤርትራና ኢትዮጵያን እንቀላቅል። የቤኒአሚሩ ጉብል ፓስተር አሁን የት ነው? እንፈልገው፣ ከሐረር ፓስተር አጠገብ የአስመራ ፓስተር አልነበረም? የት ጣልነው? ለምን? መግበስበስ ይሄ አይደለም? ከጥንቷ አገራችን ሲያባርሩን ስለምን አገራችንን ከልባችን

እናባርራለን? መከፋፈሉን ከጠላነው "ክልል" ማለትን አፋችን ውስጥ ማን ከተተው? ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉልን፣ አፋርን.... ክልል አድርጎ ቤታችን ምን አስገባቸው?...

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...እንኳን መንግሥት፣ ሴጣን... እንኳን ሴጣን ፈጣሪም ቢሆን በቤታችን፣ በልባችን፣ በመንፈሳችን፣ በነፍሳችን ለማዘዝ ፈቃዳችንን ይሻል። ደጃፋችንን ሲቆረቁር ካልከፈትን፣ ወደውስጥም እንዲዘልቅ ካልጋበዝን የመኖሪያ ልዕልና አይደፈርም። እዚያ ያልተገበርነው ነፃነት፣ እዚያ ያላስጠበቅነው መብት... የት? በጐዳና የማይታሰበውን ሠላማዊ-ሠልፍ ከሣሎን እስከመኝታ ቤት እናካሂድ፤ ለገዢዎች የፈራነውን ለልጆቻችንና ለትዳር አጋሮቻችን እንፈክር ቤታችንና ልጆቻችን የመጪው ዘመን እውነታ ማህደር ይሆናሉ - ቢያንስ።

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...እነሱ፣ ገዢዎቹ የሚጠላላ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሌት-ተቀን ይለፋሉ። እኛ የሚዋደደውን ማህበረሰብ ለማቆየት ቢያንስ በቤታችን ምን አደረግን? እራሳችንን እንጠይቅ! ሲለያዩን፣ ያለመለያየት ዕቁብ ጠጣን? ሲነጣጥሉን ያለመነጣጠል ዕድር መሰረትን? ጠላት ሲያደርጉን በጋብቻ ተዛመድን? ሲያቃቅሩን የአንድነት ፅዋ ማህበር አቋቋምን?... ወይስ ዓይን-አባት ከብሔራችን አጨን? የጡት አባታችንን ከቀያችን ሙጥኝ አልን? ጉዲፈቻ ከወንዛችን ፈለግን? ከጐሣችን አጨን? አማጫችንስ? ሽምጋያችንስ? ሽርካችንስ?... ከጐጣችን? "እጃችሁን ስጡ" ስንባል እግራችንን ጨምረን ማስረከብ ማለት ይሄ ነው።

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ፖለቲካዊ ከፉ ሥራን፣ በኢትዮጵያዊ ጨዋ ተግባር እንቃወም። ፋታ ያጣውን እናራውጥ፣ ኑሮ የከበደውን እንጫን፣ መግቢያ የሌለውን መድረሻ እናሳጣ፣ ጊዜ የጣለውን እንርገጥ፣ ከከሰረው እናትርፍ፣ የወደቀው ላይ "ምሣር" እንሁን... የዚህ ዘመን ፖለቲካ "እርስ - በእርሱ" ላይ የተመሰረተ ነው። መጣደፍን ሲፈጥሩልን እርስ በእርስ እንጋፋለን፣ ጠላትነትን ሲያቃርቡልን እርስ በእርስ እንባረራለን፣ እጥረት ሲያመጡልን እርስ በእርስ እንነጣጠቃለን፣ ጥርጣሬ ሲዘሩብን ጠላትነት እናበቅላለን፣ "ጃስ" ሲሉን እንነካከሳለን፣ ሲያጋጥሙን እንቧቀሳለን...

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ቤታችን፣ ልባችን፣ መንፈሳችንና ነፍሳችን ከዚህ ይፅዳ። ነጋዴ ነን? አላግባብ አናትርፍ፣ አከፋፋይ ነን? ተፈጥሯዊ ያልሆነ እጥረት አንፍጠር፣ መምህር ነን? ተማሪ ከተማሪ አናበላልጥ፣ እስፖርተኛ ነን? ብሔር አንወክል፣ አርቲስት ነን? ዘር ከዘር የሚከፋፈል ድግስ አናድምቅ፣ አሰሪ ነን? ሥራን ብቻ ማዕከል እናድርግ፣ ቤት አከራይ ነን? ለተከራይ እንዘን፣ ገበሬ ነን? ሰው በቆርቆሮ ቤት አንቀይር፣ ኮንትራክተር ነን? ጥራት አንቆነጣጥብ፣ ጋዜጠኛ ነን? ለሕዝብ ብቻ እንቁም፣ የሕግ ባለሙያ ነን? ፖለቲካ አንቀላቅል፣ የምክር ቤት አባል ነን? በእንቅልፍ ልብ እጃችንን አናውጣ...

...ዛሬ - ዛሬ...

...እውነታ ተገልብጧል። ሌባ ይንጐባለላል፣ ተዘራፊ ያፍራል። የቀማኛ ልጅ ደረጃ አግኝቷል፣ በላቡ የሚኖር አባት ያለው መግቢያ አጥቷል። አደባባይ የነውረኞች ሆኗል፣ ጨዋ መሸሸጊያ ጓዳ አጥቷል። አገሪቱ ከነውር የተገነባ ጎጆ ሆናለች። አድርባይ ጉልላት፣ አላዋቂ ክፍክፋት፣ ወሮበላ መርገፍ፣ አልጠግብ ባይ ደጃፍ... ሆነዋል። የዚህ ዘመን መሠረት ግን እኛ ነን። እንዴት?

እንዴትማ... የመኖር ዋስትናን ከማረጋገጥ በላይ የሚከማች ሀብት ሁሉ በማህበረሰብ ዘንድ የተሻሉ ሆኖ የመታየትና የመከበር ፍላጐት ነው። “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው” ሆነናልና የሀብት ጀርባ ማጥናት ትተናል። ለሌባ እንጎናበሳለን፣ ለቀማኛ ወንበር እንለቃለን፣ ለዘራፊ እንሽቆጠቆጣለን። ሌብነት እንደማሳለጫ የማቋረጫ መንገድ ብቻ ሆነ።

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ሌባን ማቆላመጥ ይቅር፣ አይናችን ይብላው፣ ሚስቱ ፊት ይሸማቀቅ፣ ልጁ ፊት ይሳቀቅ፣ አማት ደጅ አይድረስ፣ ከሰው ጋር አይቁረስ... ቤታችን፣ ልባችን፣ መንፈሳችን፣ ነፍሳችን... ብሎም አገራችን የሚፀዳው እንዲያ ነው። ያልተገባን ባደባባይ ባይቻል በኑሮ በመቃወም።

# “ኑ እንዋቀስ!”

እኛ ኢትዮጵያውያን ከወራሪዎቻችን አንፃር ብዙ ጀግንነትና ብዙ ኩራት አለን።
ከገዢዎቻችን አንፃር ደግሞ ብዙ ቅሬታና ብዙ ውርደት አከማችተናል። ለዛሬ
የጀግንነቱ መወድስ ይቆይና፣ የቅሬታና የውርደት መዝገባችን ይገለጥ።
ከገዢዎቻችን አንጻር ቅሬታ ሲያድርብን አንድም እንተርታለን፣ አለበለዚያም
እንዘፍናለን። የምንተርተውና የምንዘፍነው እምድጃ ዳር ሰው ሁሉ መተኛቱን
አረጋግጠን ነው። እንደ አፄ ቴዎድሮስ ዘመኗ ምንትዋብ አደባባይ ላይ የቅሬታ
ተረትና ዘፈን አንሞክርም። እንዲያማ ቢሆን ቅሬታን ውርደት አይከተለውም
ነበር። አንድ የቅሬታ ተረት እንጥቀስ፡-

“ሹም ለሹም ይጐራረሳል - ደሃ ለደሃ ይላቀሳል”

ይሄ ቅሬታ ዛሬም አለ። በአደባባይ መተረት ግን ሞታችን ነው። ተረቱ የከት
እንደሆነ ቀጥሏል። ይሄን ተረት ይዞ ገበያ የወጣ “ልበ-ድፍን” ለእርሱ ወዮለት።
የቅሬታና የውርደት ታሪካችን የሚያመለክተው ይሄንኑ ነው።

በጠላት ጊዜ ህዝባዊ የቅሬታ ተረት ይዘው አደባባይ የወጡ ሶስት ወንድማማቾች
ነበሩ አሉ። ጣሊያን ይሄን ሰምቶ ባንዳዎቹን በመላክ ያለምንም ችግርና እንቅፋት
ከህዝብ መካከል ወንድማማቾቹን መዝዞ ይዟቸው ሄደ። በዝግ ችሎት የፋሽስትን
አንቀፅ ጠቅሶ ሶስቱም ላይ ሞት ፈረደ። ሰቀላቸውም። ከዚህ በኋላ ሶስቱ
ወንድማማቾች ለህዝብ ቅሬታ ሳይሆን ለምድጃ ዳር ዘፈን ተመለመሉ።

ወይ አውቀው አያውቁ፣

ወይም አይጠይቁ፣

የነሲቡ ልጆች ሦስቱም አለቁ፤

ይቺ ህዝባዊ ዘፈን ህዝባዊ ውርደትን ወደ ሰማዕቶቹ የማዞር ጥበብ አለባት። ቅሌቱ የማነው? የህዝቡ? ወይስ የሶስቱ ወንድማማቾች? የህዝብን ቅሬታ ይዞ አደባባይ መውጣት አለማወቅ ነው? አደባባይ መውጣቱ የሚያስከትለው ዕዳ የአደባባይ ወጪው ብቻ ነው?...

ይሄ ህዝባዊ ውርደት በኛ ታሪክ ውስጥ ተደጋግሟል። ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት የሞቱት እንዲያ ነው። አፄ ኃይለሥላሴ ከማይጨው ጦርነት በኋላ ወደ አውሮፓ መሸሻቸው ደጃዝማቹን አስከፋቸው። በመሆኑም በዚህ አጋጣሚ ህዝቡ የሚጠቀምበትን "ህዝባዊ መንግስት" (ሪፐብሊክ መንግስት) የማቋቋም ፍላጐት አሳዩ። ፍላጐታቸው ከጠላት መሸነፍ በኋላም (አፄው ከተመለሱ በኋላ) አልከሰመም። በዚህ ሳቢያ ግጭት ተፈጥሮ እጅ እንዲሰጡ ሲጠየቁ ራሳቸውን አጠፉ። ህዝብ መህል ሆነው፤ ለህዝብ ጥቅም እየታገሉ፣ የመጨረሻ አማራጭ ራስን ማጥፋት መሆኑ አይደንቅም? ለየትኛው ህዝብ ነው ‹ህዝባዊ መንግስት› እንዲቋቋም የጠየቁት? ህዝቡ የለም? ወና አገር ነው? እንደ አጥማቂው ዮሐንስ የበረሃ አንበጣ እየበሉ፣ በረሃ ላይ ነው የጮሁት? ካልሆነ ታዲያ...???

ውርደት አይመስለንም እንጂ፤ የውርደት ታሪካችን ብዙ ነው። ሊጋባ በየነ ወንድማገኝ የተሰኙ መኳንንት ከአፄ ኃይለሥላሴ ጋር ፀብ ገጠሙ አሉ። መቼም ለራሳቸው አይደለም። ለራሳቸው ቢሆንማ ሊጋባነቱ በበቃቸው፤ ካልበቃቸውም ተለማምጠው በተጨመረላቸው ነበር። ያም ሆነ ይህ ሊጋባ በየነ "ሃይ-ባይ" ህዝብ በሌለበት አሰቃቂ ሞት ተፈረደባቸው። ውሃ ተከልክለው በውሃ ጥም አርረው ሞቱ። ይህ ሲሆን እኛ ምን አደረግን? ማድረጉ ይቅር ምን አልን? ምንም!! እንደውም የጭካኔውን ፍርድ የሚያበረታታ ዘፈን አወረድን፡-

ጠጅ አልጠጣም ብሎ እንደተጀነነ፣

ውሃ-ውሃ እያለ ሞተ አሉ በየነ፤

ዘፈንን ከክብር በላይ አስበልጠን እናይ ይሆን? ካልሆነ በላይ ዘለቀን ያህል አውራ አስቅሎ ለዘፈን ማድላት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? "በላይዬ ሸጋው በላይዬ፣ በላይዬ ጀግናው በላይዬ" ብሎ መዝፈን ከበላይ በላይ ይጠቅመን ይሆን?

"ተሰቀለ ቢሉ ኮፓርታው ነው ብዬ፣

የነሲቡ ልጆች ሦስቱም አለቁ፣

ይቺ ህዝባዊ ዘፈን ህዝባዊ ውርደትን ወደ ሰማዕቶቹ የማዞር ጥበብ አለባት። ቅሌቱ የማነው? የህዝቡ? ወይስ የሶስቱ ወንድማማቾች? የህዝብን ቅሬታ ይዞ አደባባይ መውጣት አለማወቅ ነው? አደባባይ መውጣቱ የሚያስከትለው ዕዳ የአደባባይ ወጪው ብቻ ነው?...

ይሄ ህዝባዊ ውርደት በኛ ታሪክ ውስጥ ተደጋግሟል። ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት የሞቱት እንዲያ ነው። አፄ ኃይለሥላሴ ከማይጨው ጦርነት በኋላ ወደ አውሮፓ መሸሻቸው ደጃዝማቹን አስከፋቸው። በመሆኑም በዚህ አጋጣሚ ህዝቡ የሚጠቀምበትን "ህዝባዊ መንግስት" (ሪፐብሊክ መንግስት) የማቋቋም ፍላጐት አሳዩ። ፍላጐታቸው ከጠላት መሸነፍ በኋላም (አፄው ከተመለሱ በኋላ) አልከሰመም። በዚህ ሳቢያ ግጭት ተፈጥሮ እጅ እንዲሰጡ ሲጠየቁ ራሳቸውን አጠፉ። ህዝብ መሀል ሆነው፣ ለህዝብ ጥቅም እየታገሉ፣ የመጨረሻ አማራጭ ራስን ማጥፋት መሆኑ አይደንቅም? ለየትኛው ህዝብ ነው ‹ህዝባዊ መንግስት› እንዲቋቋም የጠየቁት? ህዝቡ የለም? ወና አገር ነው? እንደ አጥማቂው ዮሐንስ የበረሃ አንበጣ እየበሉ፣ በረሃ ላይ ነው የጮሁት? ካልሆነ ታዲያ...???

ውርደት አይመስለንም እንጂ፣ የውርደት ታሪካችን ብዙ ነው። ሊጋባ በየነ ወንድማገኝ የተሰኙ መኳንንት ከአፄ ኃይለሥላሴ ጋር ፀብ ገጠሙ አሉ። መቼም ለራሳቸው አይደለም። ለራሳቸው ቢሆንማ ሊጋባነቱ በበቃቸው፣ ካልበቃቸውም ተለማምጠው በተጨመረላቸው ነበር። ያም ሆነ ይህ ሊጋባ በየነ "ሃይ-ባይ" ህዝብ በሌለበት አሰቃቂ ሞት ተፈረደባቸው። ውሃ ተከልክለው በውሃ ጥም አርረው ሞቱ። ይህ ሲሆን እኛ ምን አደረግን? ማድረጉ ይቅር ምን አልን? ምንም!! እንደውም የጭካኔውን ፍርድ የሚያበረታታ ዘፈን አወረድን፡-

ጠጅ አልጠጣም ብሎ እንደተጀነነ፣

ውሃ-ውሃ እያለ ሞተ አሉ በየነ፣

ዘፈንን ከክብር በላይ አስበልጠን እናይ ይሆን? ካልሆነ በላይ ዘለቀን ያህል አውራ አስቅሎ ለዘፈን ማድላት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? "በላይዬ ሸጋው በላይዬ፣ በላይዬ ጀግናው በላይዬ" ብሎ መዝፈን ከበላይ በላይ ይጠቅመን ይሆን?

"ተሰቀለ ቢሉ ኮፓርታው ነው ብዬ፣

ተሰቀለ ቢሉ ጠበንጃው ነው ብዬ፣

ለካስ በላይ ኖሯል ትልቁ ሰውዬ፣"

ከእነአቶ በዛብህ ቢያንስ በሞቱ አልተሾፈበትምና የበላይ ሁኔታ ከሌሎቹ ይሻላል። አቶ በዛብህ በጥይት ተደብድቦ ሲገደል ልብሱ በባሩዱ እሳት ለማለት ነው። ስለተያያዘ አካሉ ተቃጠለ አሉ። ያኔ እንዲህ ተብሎ ተዘፈነበት፡-

"አንተም ከፋ ነበርክ

ከፉ አዘዘብህ፣

እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ"

ግለሰብ ምን ከፉ ቢሆን የገገርዎችን ያህል ኃይል የለውምና ጉዳቱ ያን ያህል ነው። እንደውም መንግስትን በማስጋት የማለዘብ ጠቀሜታ ሳይኖረው ቀረ ብላችሁ ነው? እንኳን ህዝባዊ ቅሬታ ያለው ቀርቶ፣ ከግለሰብ ጋር ተጋጭቶ የሸፈተን ግለሰብ ገገርዎች "ምሬሃለሁና ግባ!" ማለታቸው ህዝብ ማኩረፊያ እንዳያደርጋቸው ሳይሆን ይቀራል?

በዚህ ዘመን ግለሰባዊ ተጋፋጭነትን በህዝባዊ መንፈስ አቅፎ-ደግፎ መከላከል የታየው ትንሽም በድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) የክስ ሂደት ላይ ነበር። ሁኔታው የክስ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ሲላክ አብሮ የተዳፈነ ይመስላል። እንደ በላይ ዘለቀ በአደባባይ ባይሰቀሉም፣ እንደ ፊታውራሪ ታከለ እራሳቸውን ባያጠፉም፣ እንደ ሊጋባ በየነ በውሃ ጥም ባይከነተሩም እዚህ ዘመን ላይ ህዝብን ያሉ ግለሰቦች ፍዳ እየተቀበሉ ነው። እኛ የዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን ከስላቅ፣ ከተረትና ከዘፈን ባሻገር የያኔዎቹ ኢትዮጵያውያን የረበበባቸው ምንቸገረኝነት እንደሰፈነብን ነው።

ግለሰብ ከህዝብ የበለጠበት ዘመን ቢኖር ይሄ ጊዜ ዋነኛው ነው ማለት ይቻላል። ግፉአኑ ግለሰቦች ህዝብ ከእነሱ የሚጠብቀውን ሩብ እንኳ እነሱ ከህዝብ የማይጠብቁ ሆደ ሰፊዎች ናቸው። ዝምታቸው ለተረዳው ይጫጫናል፣ የተወሰነባቸውን ያለቅሬታ መቀበላቸው ይወቀሳል፣ በእስርም ውስጥ እያሉ በአቋማቸው መፅናታቸው ‹እኛ ማነን?› እንድንል ግድ ይላል። ለመሆኑ እኛ ማነን?...

መንግስት ከሮጡለት ውሻ ነው። የገቡበት ይገባል። ግን በመሮጥና በመሸሽ ትጋት ደክመናል። ከኛ ተነጥለው "ለውሻው" ክራንቻ ጥርስ እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡትን መለስ ብሎ ለማየት እንኳ ፍርሃታችን አልፈቀደልንም። ከሚሸሽ ህዝብ ተነጥሎ፣ ለመዘንጠል ወስኖ የሚቆም ግለሰብ ማፍራት ለህዝብ ኩራቱ ነበር። አቋሙ ምንም ይሁን ምንም፣ የሚያሯሩጥ ገገርን አይን-ለአይን የሚገጥም ግለሰብ መፍጠር ለህዝብ መታፈሪያው ነበር። እኛ ግን አንዱን ለወንጭፍ ሌላውን ለወፍ ዳርገን ምንም ያልተፈጠረ ለማስመሰል እንጥራለን። እንዲህ ያለ ህዝብ መታፈሪያ ግርማው ምንድነው? ሲጭኑት አህያ፣ ሲጋልቡት ፈረስ መሆኑም አይደል? ከእንዲህ ያለ ትቢያ ውስጥ እንዴት ያለ ጨዋ ህዝብነት እንጥረን እናወጣ ይሆን?

አንስማውም እንጂ ከወደታች የሚነፍስ "ኑ እንዋቀስ" የሚል ፅጥተኛ ድምፅ አለ። ድምፁ የግለሰቦች ነው። የሚዋቀሰው ከአካላችን ሳይሆን ከህሊናችን ጋር ነው። የአገልግሎት ዋጋቸውን በልተን በዕዳችን ያስጠየቅናቸው ግለሰቦች አሉ። ጡሜና እርግጫ የጠገቡት እነርሱ እያሉ እኛ ግልምጫ የሚሸሽ ውርደታም ህዝብ ሆነናል። ልጆቻችንን ሰብስበን የእነሱን ልጆች በትነናል፣ ቤተሰቦቻችንን ሸክፈን የእነሱን ቤተሰብ አንከራተናል፣ ቤታችንን አሙቀን የእነሱን ጎጆ አቀዝቅዘናል...

"ኑ እንዋቀስ!" ይላል ንፋሱ

እንደኛ "ጨርቄን ቅሌን" ስላላሉ፣ "ጨርቅና ቅል" እንደሌላቸው መቁጠር የጨዋ ህዝብ ወግ አይደለም።

"ኑ እንዋቀስ!" ይላል ንፋሱ!!

# "ትሞታለህ!"

በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ-ልደት እና በዓለ-ጥምቀት መካከል እንገኛለን። ቀጥሎም ጥምቀቱን ስቅለት፣ ስቅለቱን ሞት፣ ሞቱን ትንሣኤ ይከተሏቸዋል። ዛሬ ይሄን ሰበብ አድርገን መለኮታዊውን ሳይሆን ምድራዊውን ሞት እናትታለን። በተለይም ትንሳኤና ስርየት የሌለበትን ፖለቲካ ሰራሹን "ዝንጋኤ-ሞት" እናወሳለን።

ሰውን ከክፋት፣ ከስስት፣ ከትዕቢት፣ ከዕብሪት... ጋር የሚያፋቅረው የመጀመሪያው ምክንያት ዝንጋኤ-ሞት እንደሆን በአመዛኙ ያስማማል። ከነተረቱ "ሞትን ማሰብ ከሁሉ መሰብሰብ" ይባላል። "ሞትን ያህል ዕዳ፣ መቃብርን ያህል እንግዳ" መዘንጋት ሰው በሁብቱና በጉልበቱ ፈፅሞ እንዲመካ ይገፋፋዋል፤ ማን-አህሎኝነት ይወርሰዋል። ይሄንን ከመሰረቱ የተረዱ ጥንታዊዎቹ ሮማውያን ለገዢዎቻቸውና ለጀግኖቻቸው አንድ አዛውንት ይመድቡ ነበር አሉ። ገዢው ማለዳ ተነስቶ ቁርስ ሲቆርስ ያ አዛውንት ድንገት ዘው ብሎ በመግባት አንዲት ቃል ብቻ ተናግሮ ይወጣል፡-

"ትሞታለህ!!"

ሮማዊው ጄኔራል ከድል መልስ በሰረገላ ሆኖ ወደ ከተማው ሲመለስ ህዝቡ ዘንባባ ይዞ በክብር ይቀበለዋል። ምርኮውና ግዳዩ እየተግተለተለ በፊቱ ሲያልፍ በዚህ ደስታ መካከል ያ አዛውንት ከጄኔራሉ ጀርባ መጥቶ ያንኑ ቃል አንዴ ተናግሮ ይመለሳል፡-

"ትሞታለህ!!"

ሞትን ማሰብ የመታበይ መድህን ነው። የመታበይ ብቻ ሳይሆን የማግበስበስ ፍቱን መድኃኒት ነው። "ሞትን በማሰብ ከሁሉ መሰብሰብ" የቻለ ገዢ በማጣት እዚህ

አገርና ሕዝብ ይቃትታሉ። “ሁሉን እንቋሻሽ፣ የተገኘውን እግበስባሽ” በሆኑ መሪዎች ፈቃድ ላይ ዕጣ-ፈንታችን ወድቋል። አንድ ሰው መብቱ እስከ መገንጠል ቢፀናለት ከኤርትራ የማያንስ ሀገር መሆን የሚያስችለውን መሬትና ሀብት በስርቆት እንደሰበሰበ መስማት የተለመደ ነገር ሆኗል።

አጤ ምኒልክ አገር-ረግቶ በተረጋጉበት ዘመን የግል መሬት እንዲይዙ ተመከሩ አሉ። እንዲህ ሲሉ ምላሽ ሰጡ፡- “መላው ኢትዮጵያ የማን ሆነና እኔ በግሌ መሬት እይዛለሁ?” ስለዚህም በስማቸው የተያዘ አንድም መሬት አልነበረም። እንደውም የእናታቸውን የዘር ርስት ወራሽ እንደሆኑ ቢታወቅም መሬቱን በባለቤትነት ተቆጣጥረው አያውቁም። ታዲያ አንድ ጊዜ መሬቱን የሚያርሰው ገበሬ ከምስለኔው ጋር በግብር ተጣልቶ ምኒልክ ፊት ሲቀርብ እንዲህ አሉ፡-

“ፈጣሪዬ የመላ ኢትዮጵያ አባት ስላደረገኝ እሱም (ገበሬው) ከልጆቼ አንዱ ነውና በስሙ ሊገብር ይችላል።”

አጤ ምኒልክን ለዚህ “በቃኝ ባይነት” ያበቃቸው አዘውትረው ሞትን ማሰባቸው ነበር። የአድዋ ድል 7ኛ ዓመት ሲከበር ለየመኳንንቱና ለየጭፍራው በፃፉት ድብዳቤ ላይ ይኸው ሞትን አለመዘንጋት በጉልህ ይታያል። “...በዚህ በየስራው ነገር በእንጨት በድንጋይ የማደክማችሁን አትመልከቱ። ይልቅ እኔን ስታጡ ብርቱ ሀዘን ያገኛችኋል።” ይላሉ። እንደ ሮማዎቹ ቄሳሮች “ትሞታለህ!” የሚል አስታዋሽ ሳይመደብባቸው “እሞታለሁ!” ያሉ ታላቅ መሪ ናቸው - አጤ ምኒልክ።

ከዚያ ጊዜ ወዲህ ነገር እየተበላሸ የመጣ ይመስላል። በሞት ፈንታ ዘላለማዊነት የነገሰበት የገዢ ልብ “የላይ ሰፈር” ሰዎቻችንን ተጠናወተ። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የነበሩ ተማሪዎች እንዲህ ሲሉ በቅኔ ንጉሱን አንጓጠው ነበር፡-

“ዛሬስ አቶ ኃይሌ አረጀ-ደቀቀ፣

ምድር ይይዝ ጀመር እየተንፏቀቀ፤”

ይኸው “የጠሉት ይወርሳል፣ የፈሩት ይደርሳል” ሆነና ከራሳቸው ከተማሪዎቹ መካከል የወጡት ጓዶቻቸው ዛሬ “ንጉስ” ሆነው “እየተንፏቀቁ ምድር በመያዝ” ከአፄ ኃይለሥላሴ ብሰው ተገኙ። ይሄን ጉድ ተማሪዎቹ ቢያዩ ምን ይሉ ነበር ይሆን?

ለመሆኑ “ለአንድ ሰው ስንት መሬት ይበቃዋል?” ይሄን የጠየኩት እኔ አይደለሁም። ሞት እንዳለ ገብቶት እርስቱን ለጭሰኞች በማከፋፈል ሙልጩን የቀረው ታላቁ ሩሲያዊ ደራሲ ልዮ ቶልስቶይ ነው። “አንድ ሰው ስንት መሬት ይበቃዋል?” ቶልስቶይ የፃፈው ተረት ርዕስ ነው።

ሰውየው ልክ-የለሽ የመሬት ጥማቱን ለማርካት ወደ አካባቢው አዛውንቶች ይሄዳል። በመሃከላቸውም አንድ ስምምነት ያደርጋሉ። ፀሃይ ወጥታ እስክትገባ በሩጫ መሸፈን የሚችለውን መሬት ሁሉ እንደሚወስድ፤ ይህ የሚሆነው ግን ጀንበር ከመጥለቋ በፊት ማለዳ የተነሳበት ቦታ ላይ መድረስ ሲችል ብቻ ይሆናል። ሰውየው “በደስታ” ብሎ ሩጫ ይጀምራል። ይሮጥና ይሮጥና “ይሄ ለስንዴዬ” ይላል። አሁንም ይሮጥ ይሮጥና “ይሄ ለገብሴ” ይላል። ሩጫውን በመቀጠል “ይሄ ለበቆሎዬ”...ቀና ሲል እየመሸ ነው። ወደተነሳበት ተመልሶ መሮጥ ይጀምራል። እቦታው ላይ ሲደርስ ግን ልቡ ፈንድቶ ይሞታል። ቶልስቶይም በአንዱ ገፀ-ባህርይ በኩል “ቅበሩት” ይላል። ለአንድ ሰው የሚበቃው መሬት የቁመቱን ያህል የሚቀበርበት ብቻ ነው።

የእኛዎቹ ባለስልጣናት ፀሎታቸው ሰምሮ የከተማ መሬት በመሰብሰብ ላይ ናቸው። የፎቅ ማሳ እያለሙ “ይሄ ለሚስቴ፣ ይሄ ለሚስቴ እህት፣ ይሄ ለእህቴ፣ ይሄ ለልጄ፣ ይሄ...” ሲሉ “በሩጫ” ልባቸው ፈንድቶ መሞታቸውን ዘንግተውታል። ሞትን በስልጣን እንቅልፍ ተላምደውት ከመሀከላቸው ጓዳቸው ሲነጠቅ እንኳ የማይበረግጉ ልበ-ደንዳናነታቸው ሆነዋል። ይሄ ልበ-ደንዳናነታቸው “ምን ያመጣብን ይሆን?” የሚያሰኝ ስጋት ይተክላል። እንደ አጤ ምኒልክ፣ ያለ-ቀስቃሽ መንቃቱ ይቅር፣ እንዴት በራሱ፣ በባለቤቱ (በሞት) የተወረወረ ፍላፃ እኩዮቻቸው ላይ ሲያርፍ መባተት ሳይኖር ቀረ? ለማንኛውም እንደ ጥንታዊዎቹ ሮማዎች እኛም ቁሳሮቻችንን “ትሞታለህ!!” በማለት እንትጋ፡-

“መሬት ሰበሰብክ? ትሞታለህ!!”

“ሀብት አጋበስክ? ትሞታለህ!!”

“ልብህን አደነደንክ? ትሞታለህ!!”

የብሉይ ኪዳኑ የአማሌቅ ንጉስ አጋግ በሌሎች ሞት ላይ ልበ-ደንዳና ነበር። ሰይፉ ሴቶችን ሁሉ ልጅ- አልባ ሲያደርግ ሞት ለእርሱ ተራ ነገር ነበር። ይሁንና ቀኑ

ደርሶ እርሱም በተራው ነብዩ ሳሙኤል እጅ ላይ ሲወድቅ ተንቀጠቀጠ። "ሰይፍህ ሴቶችን ልጆች አልባ እንዳደረጋቸው እንዲሁ እናትህ በሴቶች መካከል ልጅ አልባ ትሆናለች" አለ ነብዩ ሳሙኤል። ይሄን ጊዜ አጋግ "በእውኑ ሞት እንደዚህ መራር ነው?" ሲል እራሱን ጠየቀ። አጋግ ለገደላቸው፣ ሞት እንዲያ ከባድ እንደሚሆን እንዴት ሳይረዳ ቀረ? ልቡን ምን አደነደነው? መግደል በመገደል እንደሚጠናቀቅ ሳይገለፅለትስ እንዴት ቀረ?... አጋግን አልን እንጂ እኛስ ጋ እንዲሁ አይደል? ሞትን ከመሞት በፊት ማሰብ ለዚህች አገር ገዢዎች እንግዳ ነገር ነው። ከአጤ ምኒልክ በተጨማሪ ሞትን አሳቢ ንጉስ ሆነው ያገኘኋቸው አጤ ቴዎድሮስን ነው። ይቺን ታሪካቸውን እንመልከት፡-

አጤ ቴዎድሮስ የጐንደርን ሊቃውንት ሰብስበው እንዲህ ሲሉ ጠየቁ ይባላል፡-

"ጌታ ቀድሞ ዓለምን ፈጠረ፤ በኋላ ዓምላክነቱን ለማሳወቅ የበኸር ልጅ እያለ እያቀላመጠ ዘመነ አበውን፣ መሳፍንትን፣ ነገስታትን አሳለፈ። በኋላም ለእኛ ብሎ ከሰማየ-ሰማያት ወርዶ፣ ከድንግል ማሪያም ተወልዶ፣ ሰላሳ ሶስት አመት ኢየሩሳሌምን ዞሮ፤ አስተምሮ፣ ተገፎ፣ ተገርፎ፣ ሞቶ፣ ተነስቶ እኛን አዳነ። ይኸን ሁሉ ስራውን ከፈፀመ በኋላ ተመልሶ ወደ ሰማይ አረገ። ከዚህ ሁሉ ወዲህ እዚያ ምን ይሰራል?"

በአጤው ጥያቄ ሊቃውንቱ ሁሉ ተጨነቁ። "ምን ብንል ይሻላል?" እያሉ ሲያወጡ ሲያወርዱ አንድ አይነ-ስውር "እኔ ልመልስ ጃንሆይ?" አሉ።

"እስኪ መልስ ቆማጤ ቆመጥማጤ" አሉ ንጉሱ

"ንጉስ ሆይ፣ ቁና ይሰፋል" አላቸው።

"እውነቱን ነው ይሄ ምናምንቴ፤ አግኝቶታል። ወይኔ መይሳው! ይህን ጊዜ ባይሞላለት ነው እንጂ የእኔንም ቁና እየሰፋ ነው" ብለው መላሹን ሸልመው ሰደዱት።

ቁናው በሞት እጅ የሚላከልን የብድራት መስፈሪያ መሆኑ ነው። አጤ ቴዎድሮስ "የእኔንም ቁና" ያሉት የተቀጠበችውን የዕለተ-ሞት ቀንን ነው። ምነው ያሁኖቹ አጤዎች ከዚህ ቢማሩ? እስኪማሩ ግን እኛ ዝም አንልም "ትሞታለህ!!" እንላቸዋለን።

* በወታደር ተከበብክ? ትሞታለህ!!

* ጥይት በማይበሳው መኪና ሄድክ? ትሞታለህ!!

* አዘዝክ? ናዘዝክ? ትሞታለህ!!

* በውጭ አገር ገንዘብ አካበትክ? ትሞታለህ!!

* 40 ዓመት እንገዛለን አልክ? ትሞታለህ!!

* የሚች ሌጋሲ አስቀጥላለሁ አልክ? ትሞታለህ!!

* ትሞታለህ! ትሞታለህ! ትሞታለህ!...

# ጠቅላይ ሚኒስትር "ከቁርበትዎ" ይምከሩ

ይድረስ ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ፡-

ይሄ ጠቅላይ ሚኒስትርነት አመት ተመንፈቅ ሞላውም አይደል? "አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር" ማለታችንም እየተዘነጋ ሄደኮ። አመት ተመንፈቅ የሞላው ስልጣንዎ ልጅ ቢሆን ኖሮ ያለድጋፍ፣ በሁለት እግሩ የሚቆምበትና ያለመውተርተር የሚጓዝበት ዕድሜው ላይ ነበር። ስልጣንስ በእድሜ መጨመር በሁለት እግር መቆምና ያለመውተርተር መጓዝ ግዴታው ሳይሆን ይቀራል? ከሰው ራዕይ በተሰፋ አንቀልባ መታዘሉም ሳያበቃ ይቀራል?... ዛሬ ይሄን የአመት ተመንፈቅ የስልጣን እድሜ ታሳቢ በማድረግ "ከቁርበትዎ ይማከሩ" ለማለት ወደድኩ። "ከቁርበትዎ ይማከሩ" ስል...

...የሰሜን አርሶ አደር ከበድ ያለ የሕሊና ጥያቄ ሲቀርብለት ለመልስ አይቸኩልም። ጊዜ ይወስዳል። ጊዜ የሚወስደው ነፍስ-አባቱን ወይም ሚስቱን አለበለዚያም አምቻ ጋብቻውን ለማማከር አይደለም። ከበድ ያለ ጥያቄ ይዞ የመጣውን ሰው ጊዜ የሚጠይቀው "ከቁርበቴ ልማከር" በሚል ነው። እውነትም ደግሞ ከቁርበቱ ይማከራል። ከቁርበቱ የሚማከር ዕለት በጊዜ እራቱን ይበላል። መጠጥ በአፉ አይዞርም። የሚያደክም ቦታ አይውልም፣ ከወትሮው ሰዓት ቀድሞ ይተኛል። ከቤተሰቡ ሁሉ ማልዶ ወፍ ሳይንጫጫ ይነቃል። እንደምንቆ ውኃ ኩልል፣ ጥርት ባለው የማለዳ መንፈሱ የተኛበትን ቁርበት በጣቱ እያንቋቋ ከቁርበቷ ቅኝት ጋር ነገሩን ያወጣል፣ ያወርዳል። ያለማንም ተፅዕኖና ያለማንም ጣልቃ-ገብነት ውሳኔ ላይ ይደርሳል። ለአርሶ አደሩ፣ የቁርበቱ ቅኝት የሕሊናው ማደላደያ ናት። ቁርበቱን ሳያማክር ሐሳቡን አደባባይ ይዞ አይወጣም።

ጠቅላይ ሚኒስትር፤ "ከቁርበትዎ" የሚማከሩበት ወሳኝ ወቅት ደርሷል። የሌላ ሰው አምሳያ ስልጣንዎን በአጓለ-ምውታን ልጅነት ተቀብለው፣ በጉዲፈቻ አባትነት ማሳደግ ሊበቃ የሚገባው ቀን አሁን ነው። ስልጣንዎ የራስዎ አምሳያ እንዲሆን

ይጠበቃል። "መልኩ" ብቻ ሳይሆን ማጋጊያጫውም ምርጫዎን እንዲከተል ግድ ይልዎታል። በሰው "ማተብ"፣ በሰው "አልቦ" እና በሰው "ቃጭል" የተብጠለጠለ ሥልጣን ለአሻንጉሊት መንግስትነት መዳረጉን አሌ ማለት አይቻልም። ስለዚህ በሰሜን አርሶ-አደር ስልት በነገሩ ላይ ከቁርበትዎ ይማከሩ፡-

ከቁርበት በጣት እንደ ክራር መማከር ሕሊናን ማንቃት ነው። ጥርት፣ ኩልል ባለው የማለዳ መንፈስ ቁርበትን እየቃኙ አደላድሎ በነገሮች ላይ ማሰብን ከእርስዎ የምንጠብቀው ለደንታችንም ጭምር ነው። በዚህ ሃያ ሦስት አመት ብዙ የተወላከፈና የጐለደፈ አገራዊ ጉዳይ አለ። ያለፉት ጠቅላይ ሚኒስትር ባሻቸውና በታያቸው መንገድ ቅርፅና ይዘት ሰጥተው፤ "እፍ" በማለት ነፍስ የዘሩበት አስፈሪ ሁነት ውስጥ እንገኛለን። በዚህ አስፈሪ ሁነት ላይ ከቁርበትዎ ጋር እንዲመክሩ ግድ ይልዎታል።

ከኤርትራ ጋር በግፍ ተቆራርጠናል፤ መቆራረጣችን ሳያንስ ስር የሰደደ ጠላትነት አበጅተናል፤ ድንበራችንን በደም አስምረናል፤ ስጋነታችንን ቆራርጠናል፣ እነሱ ያለ እናት እኛ ያለልጅ ቀርተናል። እነሱ ጉሮሯችን ላይ፣ እኛ ልባቸው ላይ ቆመናል... ጠቅላይ ሚኒስትር ይሄን እውነት ከቁርበትዎ ጋር ይምከሩት።

በሀገር ውስጥም አልደላን። እኛ ብዙሃን የነፃነት ሽርፍራፊ፣ የሙብት እንጥፍጣፊ፣ የሀብት ትርፍራፊ እንኳ አጥተናል። ተስፋችን ከድንበር ወዲያ፣ በስደት ሰብዕና ላይ ታንጿል። ነፃነት፣ ሙብትና ሀብት ቀድመው ተሰደው ያማልሉናል። እነሱን ለማግኘት ሞት የማንፈራ፣ ውርደት የማንጠላ ሆነናል። ሞትና ውርደታችን የዓለም ማጣፈጫ ጨው ሆኗል። መታደናችንንና መጨፍጨፋችንን የተቀበልን እንስሳ ሆነናል... ይህ ሁሉ የፖለቲካ ስልጣን ማደላደያ ዋጋ መሆኑ ይቆጫል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ይሄንን እውነታ ከቁርበትዎ እንጂ ከአማካሪዎችዎ ጋር አይምከሩ። አሁን አሁን አማካሪነት ረከሶ ቦታው የማይፈለጉ ፖለቲከኞችና የተጠረጠሩ አባሎች መወርወሪያ ወና ክፍል ሆኗል። ያም ባይሆን ለአንጡራው ሀበሻ ከቁርበት የተሻለ አማካሪ ከየት ሊመጣ? አንዳንዴ ስለቁርበት መማከርትነት እንዲህ አስባለሁ...

...አፄ ዳዊት የመነኑት ከቁርበታቸው የተማከሩ ዕለት ይመስለኛል። አፄ ቴዎድሮስ አልማረክም ብለው ራሳቸውን ያጠፉት ከቁርበታቸው የተማከሩ ዕለት መሆን አለበት፤ አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ የጀመሩት ቁርበታቸውን ያማከሩ

ዕለት… አፄ ኃይለሥላሴ መአት የወረደባቸው ከቁርበታቸው ባለመምከራቸው፤ መንግሥቱ ኃይለማርያም የሸሹት የሚያማክሩት ቁርበት በማጣት፤ መለስ ዜናዊ አገር የጐነዳደሹት ለቁርበታቸው ጊዜ በማጣት መሆን አለበት።

እርስዎ ግን ቁርበትዎን ያማክሩ፤ አዋጆችንና ህጐችን ይመርምሩ። አንዳንድ ጊዜ ከሀገር ስጋት ሳይሆን ከግለሰብ ፍርሃት የሚመነጩ ህጐች እንዳሉ ልብ ይበሉ። "የፈሪ ጦሩ፣ እቅፍ ሙሉ" ተብሎ እንደተተረተው ያለ ማለት ነው። እቅፍ ሙሉ ጦር ለአንድ ጦረኛ የነጠላ ጦርን ያህል ሙያ እንደማይሰራ ይታወቃል። እንደውም አንዱን ጦር ሳይቃጡ ከእነ እቅፍ ሙሉ ጦር ጠላት እጅ ላይ መውደቅ ይከተላል። የዚህ ዘመን ህጐችና አዋጆች ሙብዛታቸው ለአይን እየከበዱ ኑሮን ለስጋት ዳርገውታል። ሙያ ሲሰሩ ግን አይታይም። ከውጭ ጥቃት መከላከያነት ይልቅ የአገር ውስጥ ሙብት ላይ መፏለያ እቅፍ ሙሉ ጦር ሆነዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ይሄን ይመርምሩ፣ ቁርበትዎን ያማክሩ።

በሽብርተኛ ህግ ስም ስንት ግፍ ተሰራ? መከራከሪያቸው ሳይሆን ፍርዳቸው ጆሮ እየሳበ፣ በይቅርታ በሉኝ ኩፈሳ ከመንጐማለሉ ምን ተተረፈ? አንሶ ከማሳነስ ውጭ ምን ጠብ አለ? ካፈጠጠ ጋር ሁሉ ማፍጠጥ ከመንግስትነት አውርዶ የተራ-አስከባሪ ባህርይ አያላብስምን? በውረድ እንውረድ የጐረምሳ ጠባይ መፍትሄ የሚፈለግለት ነገር አልበዛም?…

ጠቅላይ ሚኒስትር፤ እንዳላሰለችዎ ፈራሁ እንጂ ጣጣችን ብዙ ነው። "ለውጭ አልጋ፣ ለውስጥ ቀጋ" የሆነ መንግስትዎ የተራ አስከባሪ ባህሪውን ደማችንን ደመ-ከልብ የሚያደርጉ መንግስታት ላይ ቢተገብር እንዴት በኮራን ነበር። ነገር ግን "የምታሸንፈውን ምታ" እንደተባለው ፈሪ ባል "ሽመሉን" ተግባር ላይ የሚያውለው "እቤት" ገብቶ እኛ ላይ ብቻ ነው። እሱ ያላከበረን እሞሌ ነንና ባለዕዳ ባይቀበለን አይገርመንም። ይሄ ሁሉ ሰሞኑን የሚመረምሩት፣ ቁርበትዎን የሚያማክሩት ነው።

ክቡር ሆይ! አንዳንድ ጊዜ መንግስትዎ ፍቺ የሌለው የጅል ስራ ሲሰራ ይታያል። ለምሳሌ መሬት ወይንጠጅ ይመስል አከርሞ ለማብሰል መሞከሩን እንዴት ያዩታል? አፈናቅሎ፣ አፍርሶ፣ አጥሮ ሳይጠቀምበት ደግሞ ሌላ ማፈናቀልና ማፍረስ ይጀምራል። እንደወራሪ ጦር ስራው ማፍረስ ብቻ ይሆን እንዴ? ያሰኛል… ደግሞስ በዓለም ምግብ እጥረት የተሳበበው የኑሮ ውድነታችን አለም ሁሉ ወደነበረበት ሲመለስ ምነው እኛ ብቻ እዛው ቀረንሳ? ይሄም ከቁርበትዎ ጋር የሚመከሩበት

አብይ ጉዳይ ነው። ሆድን አሸንፎ ማደር የዕለት ተዕለት ጀብዱ ሆኖ ከተሞቻችን "በጀብደኞች" ተጥለቀለቀች'ኮ ጃል!!

የቋንቋው፣ የብሔሩ፣ የባንዲራው፣ የሕገ-መንግስቱ፣ የፕሬሱ፣ የአንድ ለአምስቱ፣ የሊዙ፣ የሙስናው፣ የቫቱ... ጉዳይ ሁሉ ቁርበትዎን ጠባቂ ነው። የእነዚህ ነገሮች ባሉበት መቀጠል ስልጣንዎን "የዛር ፈረስ" ጠባይ ይሰጥብዎታልና ከቁርበትዎ ጋር ይምከሩ። ይሄን የምልዎ አዳጋችነቱ ጠፍቶኝ አይደለም። ግን ደግሞ "የሰይጣንን አመጣጥ የማያውቅ አይመነኩስም" እንደሚሉት ያለ ነው። የፖለቲካ ምንኩስናዎ የአካባቢ ሰይጣንዎን አመጣጥ ሳይረዳ አልተከናወነም የሚል ተስፋ አለኝ። ለማንኛውም በዚህም ጉዳይ ላይ ከቁርበትዎ ይምከሩ።

# "በምን እንኖራለን?" እና "ስለምን እንኖራለን?"

ከቤቴ ስወጣ ቅኝቱ ሀዘን የሆነ የአየር ሁኔታ ተቀበለኝ...

"በምን እንኖራለን?" ከሚለው ይልቅ "ስለምን እንኖራለን?" የሚለው ኑባሬያዊ ጥያቄ ራስ-ምታት የሆነበት ዘመን ላይ ደርሰናል። መንግስት ባይሳካለትም "በምን እንኖራለን?" የሚለውን ጥያቄ ኢላማ አድርጎ፣ ከቅዠት በተዳበለ እውነታ፣ የህልም ጦር እየወረወረ ይገኛል። ስንኑታ ባናገኘውም፣ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገራትን የመቀላቀል "ፖለቲካዊ ዕላት" ከአረፋ መሰል ህልም ተቀርፆ ታድሎናል። "ፖለቲካዊ ዕላቱ"ን "አምልኩ" በሚሉ "ፖለቲካዊ ቀሳውስት" ዘወትር ደጃፋችን እንደተቆረቆረ ነው። "የአሸባሪዎች ምዕአት ደርሳለችና ልማታዊ ንስሃ ግቡ!" ከመባልም ታክተናል። መጪው ጊዜ የበለጠ ጭልምልም የሚልብን ደግሞ "በምን እንኖራለን?" ሳይሆን "ስለምን እንኖራለን?" ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ ነው። እውነት ስለምን እንኖራለን?

ከቤቴ ስወጣ የተቀበለኝ ቅኝቱ ሀዘን የሆነ የአየር ሁኔታ እቅፉ ውስጥ ጣለኝ፣ የሚሽግጉ ቀዝቃዛ ጠብታዎች ያሉት ከባቢ አየር። ፊቴን ወደ ብሔራዊ ቴአትር መለስኩ። እዚያ ከአንድ ገጣሚ ጋር ቀጠሮ አለኝ። አእምሮዬ ጉዝጉዞ ሐዘን ተቀምጧል።

እርግጥ ነው በዚህ ዘመን "በምን እንኖራለን?" የሚለውን ጥያቄም መመለስ ቀላል አይደለም። ጉዟችን ከዕለት ዕለት ወደ ድቅድቁና ወደ ጥልቁ ሆኗል። ከትናንት ዛሬ ጨልሟል፣ ጠልቋል። ከዛሬ ነገ ይጨልማል፣ ይጠልቃል። በትውልድ ፍርቅርቅ ውስጥ እንኳ፣ እንዳንነሳ ሆነን ወድቀናል። መማሰናችን እኛን አያኖርም፣ ለልጆቻችን አይተርፍም። ከልጆቻችን ነጥቀን እንድንበላ እየተገደድን ነው፣ ሞተን እንኳ ከሸክም አንወጣም፣ ልጆቻችን የሚፍገመገሙት እኛን ተሸክመው ይሆናል።

የልጆቻችን ታዛዮች ብቻ ሳይሆን የልጆቻችን ጡት ጠቢዎች እንድንሆን፣ ጊዜና ባለጊዜዎች ግድ ብለውናል። "በምን እንኖራለን?" ቀላል ጥያቄ አይደለም። ይሁንና "ስለምን እንኖራለን"ን አያክልም።

ሩሲያዊው ደራሲ ፊዮዶር ዶስተዮቭስኪ በህይወት ውስጥ "በምን?" ከማለት ይልቅ "ስለምን?" እንደምትከብድ "Brother Karamazov" የተሰኘ መጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ይላል...

"...የሰው ልጅ ኑባሬያዊ ምስጢር መኖር ብቻ አይደለም። የሚኖርለት ነገር ማግኘትንም ያካትታል። የተደላደለ የህይወት ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ የሰው ልጅ ለመኖር ስምምነት አያሳይም። በምድር ላይ ከመቆየት ይልቅ እራሱን ማውደም ይመርጣል።" [...The secret of man's being is not only to live, but to have something to live for, without a stable conception of the object of life, man would not consent to go on living, and would rather destroy himself than remain on earth....]

"በምን እንኖራለን?" አካላዊ ህልውና ላይ ሲመሰረት "ለምን እንኖራለን" ግን የነፍስ ጥያቄ ነው። አካላዊ የህልውና ጥያቄ መልሱ ምን ቢከብድም እንደነፍስ ፈትሮ አይዝም። ተሸንጋይ ነው። ተታላይና ታጋሽ ነው። በቀን ሶስቴ መብላት ባንችል ወደ ሁለት፣ ከዚያ በቀን አንዴ ወደመመገብ ወርደናል። በቀን አንዴ ከመብላት አሽቆልቁለን "በቀን ግማሼ" እና "በቀን-ሩቤ" ውስጥ ብንወድቅም አካል በፍግምግሞሽ እንደምትቀጥል ከኛ የቀረበ ምስክር አይኖርም።

ከተማችን ውስጥ በቀን አንዴ መደበኛ ምሳ መመገብ የተሳናቸው ግድርድሮች ተበራክተዋል። አትክልት ቤት ገብተው ሙዝ በዳቦ፣ ጭማቂ በአምባሻ ወይም አትክልት ብቻ በልተው የሚውሉና የሚያድሩ ዘመናዊ መሳይ ረሃብተኞች አሉ። ወይም ካፌ ገብተው፣ ሻይ ከኬክ ጋር አዘው፤ ከእርሱም ላይ ሩቡን በህፍረት ሳይበሉ ትተው የሚወጡ። እነዚህ በመብላትና ባለመብላት መካከል የሚወዛወዙ "ዘመናዊዎች" ማታ ጥርሳቸውን የሚያፋጩቱና አምሮታቸውን የሚወጡ መስለው ቆሎ ከመንገድ ዳር ገዝተው ይቆረጣጥማሉ። ይቺን "ግማሼ" እና "ሩቤ" የረሃብ ሽንገላ ይዘን እየኖርን ነው። ያውም ይሄም ከብዶ...

...የአንድ ብር ሽንብራ ዱቤ ቆሎ አስራ ስምንት ፍሬ ነው፣ የአንድ ብር ኦቾሎኒ አስራ ሁለት ፍሬ ነው፣ የአንድ ኬክ አማካኝ ዋጋ አስር ብር ነው፣ ሙዝ ኪሎ አስራ

ሁለት ብር፣ አምባሻ አምስት ብር፣ ጭማቂ አስራ አምስት ብር፣ አትክልት በዳቦ ሃያ አምስት ብር፣ ሻይ ሶስት ብር፣ ማኪያቶ ከሰባት እስከ አስራ አንድ ብር... እዚህ መንግስትና ሀገር ውስጥ ነፍስን ማቆየት ትልቅ ኢንቨስትመንት አይደል? ይህም ሆኖ የ"በምን እኖራለሁ?" ጥያቄ "ስለምን እኖራለሁ?"ን አያከልም።

"ስለምን እኖራለሁ?" የነፍስ ጥያቄ ነው። የውጥንጥናሽ መንገድ። ስሌቱ ኪስ ውስጥ ባለነገር ላይ ሳይሆን ረቂቅ ሀብት ላይ ይመሰረታል። ለህይወት ትርጉም የሚሰጡት እነዚህ ረቂቅ ሀብቶች ደግሞ መሰረታቸውን የሚጥሉት በተረጋጋ ማህበሰረሰብ ላይ ነው። ማህበረሰብ ሲናጋ በእድር፣ በዕቁብ፣ በማህበር፣ በቤተዘመድ ጉባኤ፣ በጋብቻ፣ በአምቻ፣ በቡና ታርቲመኛ፣ በጓደኛ... የሚመሰረተው ግለሰባዊ ሰብዕና ትርጉም ያጣል። "ስለምን እኖራለሁ?" ምላሽ የሌለው ጥያቄ ይሆናል። ህይወት ነዳጅ እንዳለቀበት መኪና የደረሰችበት ቦታ ላይ በተስፋ መቁረጥ ትቆማለች። ዶስቶየቭስኪ "የሰው ልጅ ኑባሬያዊ ምስጢር መኖር ብቻ አይደለም" ያለው ለዚህ ነው። ከመኖር ባሻገር "በተደላደለ የህይወት ግንዛቤ ውስጥ የሚኖሩለት ነገር ማግኘትንም ያካትታል"

የኑሮ ውድነት እንደፈጠረው ዘመናዊ-ረሃብ ሁሉ ለዚህም ከራሳችን የተገኘ ምሳሌ አናጣለትም፡-

አራት ኪሎ ከፀሐይ መታሰቢያ ቡና ቤት በታች ነው። ቤቱ በመንገድ ዳር፣ በመንደር መግቢያ ጫፍ ላይ ይገኛል። የቤቱን ባለቤት እኩዮቻቸው በስማቸው ሌጣውን "ዓይናለም" ይሏቸዋል። ታናሾቻቸው ደግሞ "እትዬ አይናለም" ሲሉ ይጠሯቸዋል። ልጆቹ "እማማ ዓይናለም"። ወደ መንደሩ የሚገባው ሆነ የሚወጣው ነዋሪ ለእሳቸው ሰላምታ ሳያቀርብ አያልፍም።

"ዓይናለም ደህና ዋልሽ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን! ደህና ዋላችሁ? አትገቡም.."

ለሚቀርብላቸው ሰላምታ አንድ ቀን ብቅ ብለው መልሰው አያውቁም። ቤታቸው ውስጥ የሚሰሩትን እየፈጣጠሙ "እግዚአብሔር ይመስገን!..." ይላሉ።

"እትዬ ዓይናለም ደህና አደሩ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን! ደህና አደራችሁ? አትገቡም?"

ለብዙ አመታት፣ ከስላሳ አመት ለማያንስ ይሄ ተደጋግሟል። በመጨረሻ አራት ኪሎ ለልማታዊ-ጥፋት ታጨች። እማማ ዓይናለም አቅማቸው ኮንዶሚንየም ስላልፈቀደ የቀበሌ ቤት መረጡ። ወደ ፒያሳ አትክልት ተራ አካባቢ ተገኝቶላቸው እዚያ ገቡ። ሰፈሩ እንደ አራት ኪሎ የተደበላለቀ ባለመሆኑ ሁሉም የየራሱን ደጃፍ ዘግቶ የሚቆዝምበት ሆነና ከቤት የሚወጣ የሚገባውም አፉን እንደለጉመ ስከም-ስከም ይላል።

እማማ ዓይናለም ጥቂት ጊዜ አልጉመጉሙ አሉ። "እንዴት ያለ ሰፈር ነው፣ የእግዜር ሰላምታ የሌለበት" እየቆየ ሲሄድ ይጨንቃቸው ጀመር። ቢቸግራቸው በየቤቱ እየዞሩ፡-

"ኧረ የእግዜር ምሳና እራት! ኧረተው እንደምን አደራችሁ እንባባል" ይሉ ጀመር። ነገሮች አልተለወጡም። "ምናችሁ ይጐዳል እንደምንቀላችሁ ብትሉ?"

ምንም!

ዘበት ሲቆይ ስብዕና መሆኑ እየተረጋገጠ ሄደ። ልምድ ይመስል የነበረው ሰላምታ መለዋወጥ ሲታጣ የጤና መቃወስና የህይወት መጥፋት ምክንያት ሆነ። ነባር ሰፈር የነባር ነዋሪዎች ማንነት ነው ማለት ይቻላል። በየትኛው ዘበት፣ የትኛውን ስብዕና እንደተከለ ልብ ሳይባል ይቆይና ሲፈርስ ማንነትም አብሮ ይነኩታል። መንግስት እንደ ዶሮ ጭሮ መበተኑን እንጂ ማን ምን ላይ እንደሚወድቅ መለስ ብሎ አያይም። ቢያይም፣ በነባር መንደሮች ያለውን የነባር ነዋሪዎች ድምፅ አስተባብሮ አያሰላም። በመሆኑም "በምን እንኖራለን" ከሚለው የማመፅ ስጋት እንጂ ሌላ ጥያቄ ይልቅ "ስለምን እንኖራለን?" ከፍተኛ ስጋት ሆኗል።

ከቤት ስወጣ ቅኝቱ ሀዘን የሆነ አየር ሁኔታ የተቀበለኝ በውስጤ የእማማ ዓይናለምን ዕጣ-ፈንታ እያመናተልኩ ነበር። ስሜቱም በዚያ ሳቢያ ነው።

# እናፍራለን እንጂ! ለምን አናፍር?

ራስ ብሩ ወልደገብርኤል አንድ የቅብጠት ስራ እንዳከናወኑ ታሪክ ይዘከራል። ራስ ብሩ ቤታቸውን (አሁን ኤግዚቢሽን ማዕከል የሆነውን) ለባንክ አስይዘው በመበደር የሰፉ-የተንሰራፉ ድግስ ደገሱ። ድግሱ ላይ የአዲስ አበባ ህዝብ በነቂስ እንዲገኝ አዝዘው አበሉት፣ አጠጡት። ድግሱ ቅጥ-ያጣ ነበርና ጠጁ በገንዳ ተለቀቀ። የአዲስ-አበባ ነዋሪ እንደኩበት አፉን ገንዳው ላይ ለግቶ ጠጁን መጠጠ። ቅጥ አልባው ድግስ ቅጥ አልባ ስካር የለቀቀበት ብዙ የአዲስ አበባ ቅጥ ያጣ ነዋሪ በየሜዳው ተፈንችሮ ቅጥ ባጣ መንገድ የጅብ ሲሳይ ሆነ አሉ።

የያኔው መከላከያ ሚኒስትር ራስ ብሩ ማን፣ ምን ሹክ ብሏቸው ይሄን እንዳደረጉ ግልፅ አይደለም። ምናልባት በማብላትና በመብላት ላይ ከተመሰረተው የጌታና የሎሌ ግንኙነት አንዳች ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት አስበው ይሆናል። "የጮማዬ ጌታ!" የሚል ሞቱን ከሞታቸው ለማስቀደም መሽቀዳደሙ እሙን ነው።

የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ቅጡ ያልተያዘላቸው የውጭ ምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች፣ አፍሪካውያን መሪዎችን በአጠቃላይ የተንሰራፉ ድግስ የመደገስ ፍላጎት የተጠናወታቸው ናቸው ይላሉ። ያለ-የሌለውን አጋፍሬው ብቻ ሳይሆን እንደራስ ብሩ በአራጣ ተበድረው በየሰበቡ ያበላሉ፤ ያጠጣሉ። ይሄ ሀብትን ወደምግብነት የመለወጥ ፍላጎታቸው አህጉሪቱ ከምግብ እጥረት እንዳትወጣና በረሃብ እንድትቀጣ ለማድረግ ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ እነዚያው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ያስረዳሉ። በዚህ ትንታኔ የሚስማሙት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ገብርኤል ዳንኤል "ረሃብ ድርቅና መንስኤዎቻቸው" በተሰኘው ጥናታቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

"ዋና ከተማዎችን ማጋጌጥ፣ የተንዛዙ በዓሎችን ማክበር፣ ዓይን የሚስቡ ሃውልቶችን ለስም ማስጠሪያ ማቆም የብዙ አፍሪቃ መንግሥታት ተቀዳሚ ተግባራት የሆኑ ይመስላሉ።" የጥናቱ ንዑስ-ድምዳሜ ይሄ ባህሪያቸው አህጉሪቱ የምግብ ዋስትናን እንዳታረጋግጥ ምክንያት ሆኗል ነው።

ከተቀሩት አፍሪካውያን ጋር ቀላቅሎ

እኛ ኢትዮጵያውያን ፈርጾብን ሀገራችንን ከተቀሩት አፍሪካውያን ጋር ቀላቅሎ ለመመልከት ዘገምተኞች ነን። እንዲህ ያሉ አህጉራዊ ትችቶች ሲሰነዘሩ እስከናገናዝብ ድረስ ኢትዮጵያን ከአህጉራዊ ችግሩ ገንጥለን በእንከን-አልባነት እንሞሽራለን። ግን ብዙ አንቆይም፤ ስናገናዝብ ችግሩ ውስጥ እንደተዘፈቅን እናረጋግጣለን።

እነራስ ብሩን ለእነ ራስ ብሩ ዘመን ትተን ወደዚህ እንምጣ። ዋና ከተሞችን በማጋጌጥ አልተጠመድንም? ዓይን የሚስቡ "ሀውልቶችን"ስ ለስም መጠሪያ አላቆምንም? ከምንም በላይ የተንዛዙ በዓሎችን በማክበር አልዳከርንም?... በልመና የተገኘውን ሀብት በጌትነት አልበተንም? ዛሬን ስንደግሥ ነገን አልረሳንም? አዲስ አበባን ስናድስ "ሮም በአንድ ቀን አልተገነባችም" የሚለውን ብሂል አልዘነጋንም? ከተዋጋው እስካልተዋጋው ዋና ከተማችን በአንድ ቀን ካልዘመነች አላልንም? ከተዋጋው እስካልተዋጋው "ሰማዕት" ድረስ ሐውልት አላቆምንም?...

ስለተንዛዙ ... ጉዳይ ትተን ስለተንዛዙ

...የከተሞች ማጋጌጥ እና የሃውልት ማቆማችንን ጉዳይ ትተን ስለተንዛዙ በዓሎች ... መንግስታዊ በዓሎቻችን እናውሳ። አሁን በዚህ ሰዓት በብዙ በዓሎች ስርጥ ውስጥ መንግስታዊ በዓሎቻችን እናውሳ። አሁን በዚህ ሰዓት በብዙ በዓሎች ስርጥ ውስጥ

"ጨፍሩልኝ"፣ ዳኛ ሲይሞ "ሽንጥ እና ዳሌ አሳዩልኝ"... ይላል። በዚህ በዚህ እራሱ የሚጠላቸውን ፊውዳሎች ("ነፍጠኞች") ሆኖ ቁጭ! እንዲህ የተባለላቸውን፡-

"ግብሩ ሰፊ ነው ጠጁ ባህር

የዳኘው ጌታ ያበሻ አድባር።"

በእነዚህ ፌስቲቫሎች ላይ ላይታፈስ የሚፈሰው ሀብት ብዙ ነው። ለምሳሌ ስምንተኛው የብሔር-ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ጅጅጋ ላይ ሲካሄድ፣ ከሀገሪቱ የተለያየ አቅጣጫ የፈለሱት እንግዶች ቁጥራቸው በውል አይታወቅም። እስከ አራት እና አምስት ቀናት የተጓዙም ነበሩባቸው፤ ከእነዚህ በተጨማሪ የውጭ ሀገር መሪዎች፣ አፈ-ጉባኤዎች፣ ዲፕሎማቶችም ተገኝተዋል። የሩዋንዳ፣ የጅቡቲ፣ የሱማሌ ላንድ፣ የኬንያ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎችም መጥተዋል። በመሪዎች ደረጃ ጁባላንድ፣ ፑንትላንድና ጅቡቲ ተሳታፊ ነበሩ። 13 አምባሳደሮች አገሮቻቸውን ወክለው ተገኝተዋል። የውጭ ባለሃብቶችና የአለም-አቀፍ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎችም ነበሩ። ወጪው ነገሮችን በማስላት እንጂ ብሮችን በመቁጠር የሚደረስበት አይመስልም። የበዓሉ ዝግጅት የተጀመረው ከሶስትና ከአራት ወራት አስቀድሞ ነበር። በተለይ የፀጥታውን ጉዳይ አስተማማኝ ለማድረግ ከተማው ላይ ውጥረት ያነገሰ ቁጥጥር ሲደረግ ነበር። እነዚህ ሁሉ ወጪዎች አሉባቸው። የሚገርመው ግን ወጪው ሳይሰላ ወጪውን ለማጀብ የተከናወኑ ጥቂት ተግባሮች እንዲጐሉ መፈለጉ ነው። ለምሳሌ ጅጅጋ በአሉን ለማክበር ዘጠኝ ነጥብ 7 ኪሎ ሜትር አስፋልት መንገድ መገንባቱ ይዘገባል። ግለሰብ እንኳን የሰርጉን ወጪ ለቤት ማሟያ በጀት በሚቀይርበት በዚህ ዘመን፣ ልማታዊ መንግሥታችን ምን ነካው? የድግሱን ብር ለጅጅጋ መንገዶች ቢያውል 90 ኪሎ ሜትር መንገድ መገንባት አይቻልም ነበር? ያውም ባይበልጥ?

የብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል ወጪው "የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም" ተብሎ ለማስተማሪያነት የሚመደብ የስህተት ክስተት አይደለም። በየዓመቱ እየዞረ የሚመጣ አዙሪት ነው። ቀጣዩ የበዓል አክባሪ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሶማሌ ክልል ተሞክሮ ቀስሞ፤ በዓሉን በድምቀት ለማክበር ዝግጅቱን ከወዲሁ እንደጀመረ በኩራት ገልጿል። "እግዚኦ!" እንጂ ሌላ ምን ይባላል? ከድህነት አዙሪት ተላቅቀው ወደፈጣንና ተከታታይ እድገት መሸጋገር ተያያዙ እየተባለ በመንግስታችን የሚነገርልን ህዝቦች፤ ወደ ሀብት ፍጆታ አዙሪት እንግባ? ማብቂያው መቼ ነው? ብሔር-ብሔረሰቦች ዘንድሮ ጅጅጋ ላይ የተለዋወጡት የባህልና የቋንቋ እሴት

ሳይዘነጋ ሶስትና አራት አመታት ባለመቆየቱ ይሆን በየአመቱ እየተገናኙ እንዲለዋወጡ መደረጉ?...

መንግስት እንደጠጪ አባወራ እጁ ላይ ያለውን በግዴለሽነት አጨብጭቦ ለመጨረስ መቸኮል የለበትም። ፌስቲቫሎች የመንግሥት "ዳንስ ቤቶች" መሆናቸው እሙን ነው። በአሜፍሩኝ ሀገር አይገነባም። በተለይ ለደሃ ሀገር መንግሥት የተንዛዛ በዓል መጠቋቆሚያ ሐፍረቱ ነው። ነውር ተይዞ አደባባይ አይዋልም።

አንዳንድ ጊዜ ምን እንደሚሰራ የሚታወቅ አይመስልም። ለምሳሌ ሰባተኛው የመንግሥት ከፍተኛ ተቋማት የስፖርት ፌስቲቫል ሲከበር ስድስት ሺህ ተማሪዎችን በ12 ዓይነት ስፖርቶች እንዳሳተፈ ይነገራል። እንደጅጅጋ ሁሉ ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ በዓሉን ለማክበር በከፍ ዝቅ ብዙ ወጪ አድርጓል። ከአዲስ አበባ ስታዲየም እያንስም የተባለለት የሀሮማያ ዩኒቨርስቲ የስፖርት አካዳሚ ብቻ በሙቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር ተመድቦለታል። ይህ በእንዲህ እንዳለ እዚያው ሰሞን ላይ የሚዘገቡ የዩኒቨርስቲ ነክ ችግሮች ያስደነግጣሉ። ለምሳሌ ሙቱ ዩኒቨርስቲ የቤተ-መጽሐፍት አለመሟላት፣ የቤተ-ሙከራዎች ሙሉ በሙሉ ስራ አለመጀመር፣ የተማሪዎች ዶርም አካባቢ ውሃ አለመኖር፣ ግቢው አጥር-አልባ ከመሆኑም በተጨማሪ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ባለመሰራታቸው ተማሪዎች በአቧራና በጭቃ መማረራቸው፣ የሙብራት መቆራረጥና የኢንተርኔት ያለመኖር ችግሮች መደራረብ ተጠቁሞ፤ በዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት በዶ/ር መኮንን ዲንኮ የእምነት ቃል ተደግፈዋል።

ይህ ምን ማለት ነው? እንደራስ ብሩ መኖሪያችንን አስይዘን ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን ጤንነት፣ ደህንነት፣ ህይወት... ለአደጋ አጋልጠን "መደገስ" ተገቢነት አለው? ከተንዛዙት በዓሎቻችን የምናተርፈው ምንድነው?....

የፌስቲቫሎቹ መዘዝ በህብት ብክነት ብቻ የሚደመደም ቢሆን ደግ፤ ከፍተኛ የስራ ጊዜ ጥፋትም አለው። የፌስቲቫሎቹ ዝግጅትና መጓጓዣ ቀናት ሳይደመር በዓሉ ብቻ ከሶስት እስከ አስራ ስድስት ቀናት የሚወስዱ ነበሩ። የ12 ፌስቲቫሎች ድግስ በአማካኝ በአንድ ሳምንት እንኳ ቢሰላ፤ ከአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሶስት ወሩ የመራገጫና የሙብለጥለጫያ ነው ማለት ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ የመሰለፍ ራዕይ ላላት አገር፣ ከተፈጥሮ አደጋ በላይ ውድመት የሚያስከትል መንግስት-ሰራሽ ጥፋት አይሆንም? ስኮትላንዳዊው ተጓዥ

ጀምስ ብሩስ እንዲህ ሲል የተቸው ይህን መሰሉን መንግሥታዊ ለውድቀት መደገሶችን ሳይሆን ይቀራል?

“ትላልቅ ጉንዳኖች፣ የአይጥ መንጋ... ብዙ እህል ፈጀ። ከዚህ ሁሉ መቅሰፍት የባሰው ግን መጥፎ መንግሥትና አስተዳደር ነው። መጥፎ መንግስት ህዝቡ ከተፈጥሮ፣ ከተመክሮ ያገኘውን ንብረቱን፣ ማንነቱን ከመቅጽበት ያወድምበታል” (Travels to discover the source of Nile)

ከዚያ ሁሉ ጊዜ በኋላ የብሩስ ትችት ላይ መገኘት ቢያንስ ቢያንስ አያሳፍርም? ያሳፍራል እንጂ ለምን አናፍር?

# እንጠረጥራለን እንጂ! ለምን እንጠረጥር?

ከጥንት ጀምሮ አገራችንን ያጠርነው በጥርጣሬ ነው። የመጀመሪያው ረድፍ ድንበራችን ጥርጣሬ ነው። ይሄን ያሳበረ ጠላት ቀጥሎ ማገርገር ይጠብቀዋል። ይሄን ላለፈ ወታደር አለለት። በህገረ-ህበሻ ስለህበሻ ምድር በር እንጂ ልብ ወለል ብሎ አይከፈትም። ከመልካም ንግግር፣ ከጥሩ ገፀ-በረከት ሆነ ከወዳጅነት ጥያቄ ጀርባ፤ ምን እንዳለ በጥርጣሬ እንመረምራለን። ጥርጣሬያችንን የትኛውም መልካም ነገር አያደናግዘውም።

ከሦስት ሺህ ዓመት አስቀድሞ ይሄን ኢትዮጵያዊ ጠባይ ያልተረዳው የፋርስ ንጉስ ካምቢሴስ በጥርጣሬ የታጠረ ድንበራችንን ለማሳበር ሞከረ። መልዕክተኞቹን ውድ ገፀ-በረከት አስይዞ፡- "ወዳጃችሁና እንግዳችሁ ለመሆን እፈልጋለሁ" አለ።

"የኢትዮጵያውም ንጉስ አልተታለለም ነበር" ይላል ታሪክ ፀሐፊው ሔሮዶቱስ። መልዕክተኞቹን እንዲህ አላቸው፡- "የፋርስ ንጉስ እነዚህን ገፀ-በረከቶች አሲይዞ የላካችሁ በወዳጅነቴ ላይ ከፍ ያለ ዋጋ ስላስቀመጠ አይደለም። የመጣችሁት በግዛቴ ላይ ስለላ ለማግኘት ነው። ስለዚህ እናንተ አባዮች ናችሁ። ያም ንጉሳችሁ መጥፎ ሰው ነው።"

ምን ጀግንነት ቢሞላ፤ ተላላነት ከታከለበት ከንቱ ነው። እጅና እግርን አጣጥፈው እንደተቀመጡ፣ ሙያ የመስራት ዕድል ሳይገጥም ጠላት እጅ መውደቅ ይከተላል። ስለዚህ እንጠረጥራለን፤ የጠረጠርነው እውን ሲሆን እናገረግራለን፤ ማገርገራችን ያልመለሰው ካለ እንፋለማለን። ኢትዮጵያ እንደ ከበሮ በሰው እጅ ሲያይዋት የምታምር፣ ሲይዟት የምታደናግር ሀገር ናትና፤ እስኪይዟት አምሮታቸውን ለመወጣት መጣራቸው አልቀረም። ይሄን ጥረታቸውን በጥርጣሬ ማጠር ደግሞ የእኛ ሥራ ሆኖ ቆይቷል።

ከሺህ አቆጣጠር ወደ መቶዎቹ መጥተን ይሄን ታሪክ አብራሄ እናድርግ:-

በ1487 ዓ.ም. ነው። የፖርቹጋሉ ንጉስ ዳግማዊ ዮሐንስ፤ በወቅቱ በኢትዮጵያ ላይ የሚነገረውን አድምጦ ስለሀብቷ ጐመጀ። አጣርተው ይነግሩትም ዘንድ ሁለት ሠላዮች መለመለ። ሠላዮቹ ፔድሮዲ ኮቬልሀምን እና አልፎንሴ ዲ ፔይቫን ይባላሉ። ፔይቫን መንገድ ላይ ወባ በሽታ ገደለው ይባላል። ኮቬልሀም ግን በዘይላ ወደብ አድርጐ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ገባ። ኢትዮጵያውያን የኮቬልሀምን መቃበዝ አይተው ጠረጠሩት። እናም አንድ ጥያቄ አቀረቡለት:-

"አንተ ከነትዝብትህና ምርመራህ ወደ ሀገርህ ከተመለስክ እኛ ጦርነት ውስጥ መግባታችን ነው። ስለዚህ ስለሰላይነትህ በጀግና መልክ እንግደልህ? ወይስ በምርኮ እኛን መስለህ ከሀገር ሳትወጣ ትኖራለህ?"

ኮቬልሃም ኢትዮጵያውያንን መስዬ እዚሁ ልኑር ስላለ መሬትና ሚስት ተሰጠው። ኢትዮጵያዊ ወግና ሥርዓት አጠና። አንዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች ሥልጣንም አገኘ ይሉታል። ብቻ ኮቬልሃም ጥርጣሬ ባስከተለው ምርኮ ኢትዮጵያዊ ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ኖሮ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከእነስለላ ምስጢሩ ሞተ። ምርኮ ካጐናፀፈው ኢትዮጵያዊ ክብር ጋር፣ ፍታቱ በግዕዝ ተከናውኖ ግባ መሬት ተባለ።

ያኔ ባንጠረጥር እንመነጠር ነበር። ያኔ ብንመነጠር ደግሞ፤ አሁን ያለን ብዙ ኢትዮጵያውያን የዘር ግንዳችን ከሥሩ ስለሚቆረጥ፣ ምናልባትም በህይወት የመገኘቱ ዕድል አይገጥመንም ነበር። መጠርጠር ደጉ!! ጥሩ ነገር ሲቀርብልን ጥርጣሬያችን እንዳይታጠፍ በተረት እንደግፈዋለን። "ጠርጥር ከገንፎም አለ ስንጥር" እያልን።

ጠላት የገንፎ ገፀ-በረከት ሲያቀርብ፣ በስንጥር መኖር እንጠረጥረዋለን። ገንፎውን እንደ ዓሣ በብልሃት ብንበላም፤ ጥርጣሬያችን አይከስምም። የገንፎውን "ኳሮ" እንሰልላለን። ኳሮ ምንም ቢታጣ እንኳን ጊዜ የሚያመጣውን እንጠብቃለን። ጥርጣሬ! ጥርጣሬ! ጥርጣሬ!...

ጥርጣሬ ጋሻችን ነው። አትጠርጥሩኝ ማለት ለእኛ ጋሻችሁን ጣሉና ልውጋችሁ እንደማለት ነው። አለመጠርጠር የሚሻውን ሰው አብዝተን እንጠረጥራለን። እስከዛሬ "አምናችኋለሁ! አምናችኋለሁ!" እያለ እኛም በእርሱ ላይ እምነት እንድናሳድር በመወትወቱ አቻ ያልተገኘለት ሰው፤ የፋሽስት ኢጣሊያ ጄኔራል ሱዋ

ኤቸሌንሣ ናዚ ነው። ልቡ ግን ጠርጣራነታችንን ሳይገነዘበው አላለፈም። በመስከረም 1932 ዓ.ም. "የቄሣር መንግሥት መልክተኛ" ጋዜጣ ላይ፣ ጀኔራሉ የተናገረው እንዲህ ተዘግቧል፡-

"ታማኝነታችሁንና ቅን አገልጋይነታችሁን አቋርጣችሁብኝ አታውቁም። አሁንም እስካሁን ድረስ በቅንነትና በመታመን መንግሥትን እንዳገለገላችሁና ደስ እንዳሰኛችሁ፣ ወደፊትም እንደዚሁ በመልካም ፈቃድና በልብ ቅንነት፣ በታማኝነት ሥራችሁን እየሠራችሁ መንግሥትን ስታገለግሉ፤ ከመንግሥት ቸርነትና ከናንተ ቅን አገልግሎት መካከል የሚገኘው የሥራ ፍሬ ዘወትር እየተሻሻለና እየበለጠ ይሄዳል።"

ጀኔራሉ በዚች ቁራጭ ንግግር ስንት ጊዜ ታማኝነትንና ቅንነትን ጠቀሰ? ማን እንዲያምነው? የሚገርመው ነገር የጄኔራሉን መልዕክት ይዞ በወጣው በዚህ ጋዜጣ አናት ላይ አንድ ነባር የቁም-ፅሁፍ በብዕር ስፍሮ አገኘሁ። "የቀጣፊ ንግግር" ይላል። ጀኔራሉ ከራሱ ቀጥተኛ ንግግር ባሻገር፤ በዘመኑ የነበሩትን ባንዳ መኳንንት፣ ሹማምንትና ጳጳሳት ሳይቀር ስለታማኝነት እንዲናገሩለት ግድ ይላቸው ነበር። ባንዳው ልዑል ራስ ኃይሉ ስለኢትዮጵያ ህዝብ ወክለው ጄኔራሉን የሚያስደስት ዲስኩር ሲያደርጉ፣ እንዲህ እንዳሉ ተዘግቦ ነበር፡-

"ከዚህ ያለው (የኢትዮጵያ ህዝብ) ዛሬ በድል አድራጊነትዎ ደስ ብሎት ትዕዛዝዎን ለመቀበል የተሠለፈ፤ ወደፊትም በደሙ ውለታዎን ለመመለስ የተዘጋጀ ታማኝዎ ነው።"

ጄኔራሉ የኢትዮጵያን ህዝብ ጠርጣራነት ያውቀዋልና የልዑሉን ቃል አምኖ ለአንድ ቀንም እንቅልፍ እንደማይወስደው የተረጋገጠ ነው። ኧረ ልዑል ራስ ኃይሉም ቢሆኑ በዚህ ጠርጣሪ ህዝብ እታመናለሁ ብለው አያምኑም። ይሄ ገራገሪ ህዝብ እሳቸውን ቀርቶ፤ የያኔው የኢትዮጵያ ሊቀ-ጳጳሳት ርዕስ ብፁዓን አቡነ ዮሐንስንም ብዙ ሲናገሩ አላመነም። ፋሽስት ተሸንፎ ሊወጣ ሦስት ወር ብቻ ሲቀረው የአስተርዮ ማርያም በዓል ላይ አቡኑ እንዲህ አሉ፡-

"...(ቀዳሚሃ ለጥበብ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር) የጥበብ ሁሉ መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው። እግዚአብሔርን የሚፈራ ህግን ይፈራል፣ ሰውን ያከብራል። በዚህ ምክንያት እሱም የተፈራና የተከበረ ይሆናል። ሁለተኛም የዚህ ተከታይ መንግሥትን (የፋሽስት) ማክበርና መፍራት ነው። መንግሥትን የሚፈራና

በመንግሥት ፈቃድ የሚተዳደር ህዝብ ከክፉ ነገር ተጠብቆ ይኖራል። ...በኃጢአትነቱም በሥጋ በመሬታዊ አደባባይ፣ በነፍስም በሰማያዊ አደባባይ የነፍስ ፍርድ አስፈርዶ ወደስቃይ ቦታ ያወርዳል..."

እንደውም ከግዝቱ በኋላ መጠርጠሩም ሆነ ማገንገኑ ባሰ ማለት ይቻላል። ብሶ ተባብሶ ወደራሳችን ሰዎችም ዞረ። የኃይለሥላሴ መንግሥት እንግሊዝን ሸሽቶ አሜሪካ ውስጥ ስለተወሸቀ ጠረጠርነው፤ ገነገንበትም -- የደርግ መንግሥት ምዕራቡን ፈርቶ የምሥራቁን ታዛ ስለተጠለለ ጠረጠርነው፤ ገነገንበትም.... ይሄ መንግሥት ከሥሯ ወጥቶ፣ ሥሩ ለወተፋት ኤርትራ ጠበቃ ስለቆመ ጠረጠርነው፤ ገነገንበትም...።

ከጠረጠርን ምን ውድ ገፀ-በረከት ቢቀርብልን ከልባችን አይዘልቅም። ፋሽስት ኢጣሊያ ከጅማ እስከ አስመራ መንገድ ገንብቷል፣ ድልድይ አቁሟል፣ የሁለት ወሩን መንገድ ወደ ስምንት ቀን አውርዷል... ታዲያ ምን ይሆናል? ባንዲራ ጥሏል፣ ህዝብ ፈጅቷል፣ ሉአላዊነት ደፍሯል። ይሄን አልፎ ውለታው አይዘልቀንም።

አፄ ኃይለሥላሴም ትምህርት አስፋፍተዋል፣ መንገድ ጨምረዋል፣ ኤሌክትሪክ ዘርግተዋል... ታዲያ ምን ይሆናል? "የውጭ አልጋ የቤት ቀጋ" ሆነዋል። ጊዜአችንን በከንቱ ኩራት አባክነዋል፣ በረሃብ ፈጅተዋል። ይሄን አልፎ ውለታቸው አይዘልቀንም።

የደርግ መንግሥትም ከእኛ በላይ አገሩን ወድዶ ተንቀጥቅጧል፣ በዕውቀት ማነስ እኛ አገሬዎቹን በአገራችን ላይ ጠርጥሯል... ታዲያ ምን ይሆናል? አገሬውን በአገሬው ላይ አስነስቷል፣ አገሬውን በአገሬው ፈጅቷል፣ ይሄን አልፎ ውለታው አይዘልቀንም።

በዚህም መንግሥት ብዙ ተሰርቷል፣ የሚሰራውም ከተሰራው ይበልጣል... ታዲያ ምን ይሆናል? ኢትዮጵያዊ መንፈስን ጥሏል፣ ከኛ ይልቅ ለባዕዳን አድልቷል፣ በታሪካችን ተሣልቋል፣ የተዋረደ ሪፈረንደም አካሂዷል፣ እራሱ ለቀረፀው የሪፈረንደም ጣኦት ቅድሚያ ሰጥቶ ሰግዷል፣ አገር በድሏል፣ ወደብ አልባ ዝግ አገር አድርጎናል። ይሄን አልፎ ውለታው አይዘልቀንም።

ፋሽስት "ቦኖሴራ" ብሎ ሄዷል፣ የኃይለሥላሴ መንግሥት "ፋታ ፋታ!" እንዳለ ጠፍቷል፣ ደርግ ስለአንድ ጥይትና አንድሰው ተሰድዷል። ይህ እስኪሆን ድረስ

በጥርጣሬ ታጥረን ነበር። አሁንም የሚሆነው እስከሚሆን ጥርጣሬ ውስጥ ነን። ይሁንና ኢትዮጵያዊ ጥርጣሬ ኢትዮጵያዊ ክፍተት አይደለም። የውጭ ጠላት ሲመጣ፣ ጥርጣሬ ከቤት ንብረት ጋር ወደኋላ የሚቀር ነው። ጥርጣሬ ከድል በኋላ የምንመለስበት ቤት ንብረታችን ነው። ደርቡሽን ከመደምሰስ በኋላ፣ ሱማሌን ከመቅጣት በኋላ፣ ኤርትራን ከማሸማቀቅ በኋላ... ምናልባትም ዳግማዊ መሐዲን ከማስተንፈስ በኋላ... ጥርጣሬን እንደሀገራዊ ክፍተት ቆጥሮ፣ የቅሬታችን ምንጭ የሆነውን ጥፋት ማዳፈን፤ የዚህ መንግሥት ዘመን-አመጣሽ ዘዬ የሆን ይመስላል። ከዚህ ሁሉ "ይቅርታ" ማለት ምን ገዶ? ኤርትራ በእኔ ምክንያት ሄደች፣ ኢትዮጵያ በኔ ምክንያት ወደብ አልባ ሆነች፣ ባንዲራ በእኔ ምክንያት ዝቅ አለች፣ ሥነ-ምግባር ጠፋች፣ ድህነት ተንሰራፋች፣ አድባር-ቀዬ ደነገጠች... ወዘተረፈ። ይቅርታ! ይቅርታ! ይቅርታ! ማንን ገደለ?

## እንሰጋለን እንጂ! ለምን አንሰጋ?

እንዴት አንሰጋ? እንሰጋለን እንጂ! በዚህ ሁኔታ አለመስጋት ተፈጥሯዊ ነውን? አይደለም። በደንብ መስጋት ነው ተፈጥሯዊው። ሰው ሁሉ በዘር እየተቧደነ ነው፤ በዘር መቧደኑ ባልከፋ፤ ሌላው ዘር ላይ የቅሬታ አስተያየት እየሰጠ ነው፤ አስተያየቱ ብቻውን ባልከፋ፤ የቂም በቀል ዳርዳርታ እያሳየ ነው… እና በዚህ መካከል እንዴት አንሰጋ?

የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት ነው። አማኝ ከመሆን፣ ስልጡን ከመሆን፣ ሰብዓዊ ከመሆን፣ አመዛዛኝ ከመሆን… ያወጣል። ወደ ደመነፍስነት ያዘዋውራል። የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት ነው… ባሪያ ፍንገላ የዘረኝነት ውጤት ነው። ዘር ማጥፋት የዘረኝነት ውጤት ነው። የዘር ፍሬ መስለብ የዘረኝነት ውጤት ነው። ሴት መጥለፍ የዘረኝነት ውጤት ነው።… እነዚህ ሁሉ የሚደረጉት የራስን ዘር አስፋፍቶ፣ ተጎራባች ዘርን ከመራባት ለማቆርቆዝ ነው።

…የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት ነው። ሰውን እንደሰው አለመቁጠር የሚመጣው በዘረኝነት ነው። ሰብዓዊ ፍጡርን እንደአይጥ፣ እንደውሻ፣ እንደአህያ… መቁጠር፤ ቆጥሮም በእነዚህ እንስሳት ላይ የሚደረገውን ሁሉ ለማድረግ መድፈር የሚመጣው በዘረኝነት ነው። ሌላም የከፋ ነገር አለ። ሰውን ሰው የሚበላው ከዘረኝነት ተነስቶ ነው። ተክለፃድቅ መኩሪያ አንድ የቆየ መፅሃፍ አላቸው፤ "ከጣዖት አምልኮ ወደክርስትና" የሚል። አንዳንድ ጎሳዎች ሌሎች ጎሳዎችን እንደሰው ባለመቁጠር እያደኑ እንደሚበሏቸው ይነግሩናል። ዘመናዊነት የሚሰማቸው አንዳንድ ዘረኞች ደግሞ፣ የሰው በረት አዘጋጅተው እየቀለቡ በማደለብ ለበዓልና ልዩ ለሆነ ድግስ ያርዷቸዋል ይሉናል።

የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት ነው…

...ኤቭሊን ሪድ የተባለች የማህበራዊ ጥናት ተመራማሪ ደግሞ “WOMEN'S EVOLUTION” የተሰኘ መፅሀፏ ላይ ሌላ የዘረኝነት ጉድ ትነግረናለች። አንዳንድ ጎሳዎች ከእነሱ ዘር ውጪ የሆነ ሰው ይዘው በማረድ ደሙን ይጠጡታል። ሪድ፣ “ደሙ ለጤና እንደሚበጅ ያምኑ ነበር” ትለናለች። ይሄ ነባር እምነት በዚህ ዘመንም ደሙ በወይን ጠጅ ተቀይሮ “ለጤናችን” በማለት ብርጭቆ የምናጋጨው ለዚያ እንደሆነ ትጠቁመናለች።

የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት ነው...

...በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አዶልፍ ሒትለር ያደረገው ከጥንቶቹ ጐሣዎች የተናነሰ አይደለም። አይሁዶችንና ጂፕሲዎችን ሰብስቦ በማጐር፣ በጋዝ አፍኖ ከገደለ በኋላ ከሰውነታቸው በሚወጣ ሞራ፣ ሳሙና ይሰራ ነበር። ፀጉራቸው ለማዳበሪያነት ይውል ነበር። ለትራስ ይሆናል። ከተቃጠሉ በኋላ አመዱ ለማዳበሪያነት ይውል ነበር። ሳይንስ፣ ዘመናዊነት፣ ኃይማኖተኝነት፣ ሥነ-ምግባር፣ አልተበሉም ማለት ይቻላል? ሳይንስ፣ ዘመናዊነት፣ ኃይማኖተኝነት፣ ሥነ-ምግባር፣ አልተበሉም ማለት ይቻላል? ስለዚህ እንዴት አንሰጋ? እንሰጋለን እንጂ! ሥልጣኔ... ዘረኝነትን አይገራውም። ስለዚህ እንዴት አንሰጋ? እንሰጋለን እንጂ! ሥልጣኔ... ዘረኝነትን አይገራውም። ተፈጥሯዊ ነው? አይደለም!! በዚህ ሁኔታ እያለን አለመስጋት ተፈጥሯዊ ነው? አይደለም!!

የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት እንደሆነ እናውቃለን...

...ከዘረኝነት ጋር ከተነካካ ሳይንሱ ብላሽ፣ ቴክኖሎጂው ብላሽ፣ እምነቱ ብላሽ፣ ጥበቡ ብላሽ፣ ሥልጣኔው ብላሽ፣ ጨረቃ ላይ መውጣቱ ብላሽ... ነው። እነዚህ ሁሉ የሚጠቅሙት የዘረኝነት ደመነፍሳዊነትን ምክንያታዊ ለማስመሰል ብቻ ነው። በዘረኝነት ተነስቶ ባሪያ ለመፈንገል፣ በዘረኝነት ተነስቶ ዘር ለማጥፋት፣ በዘረኝነት ተነስቶ ሰው ለመብላት... ሳይንስ በምክንያትነት ሲቀርብ ታይቷል። ቻርለስ ዳርዊን ለዚህ ምሣሌ ነው። “Existing human races are located at different rungs of the ‘evolutionary ladder’ that the European races were the most ‘advanced of all and that many other races still bear simian features.” (አሁን ያሉት የሰው ዘሮች ‘በዝግመተ-ለውጡ መሠላል’ በተለያየ የመወጣጫ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። የአውሮፓውያን ዝርያዎች ከሁሉም ዘሮች በላይ የላቁቱ ናቸው። ልክ ሌሎቹን የሰው-ዘሮች ሁሉ እንደ ዝንጀሮ መሰል ፍጡር በሚያስቆጥራቸው ንፅፅሮሽ እንደማለት ነው።) በዚህ “ሳይንስ” ምክንያትነት የቅኝ ተወላጆን ቢፈጁ፣ ምድሩንም ቢወርሱ እንደጥፋት ይቆጥሩታል?

የብዙ መጥፎ ነገር ምንጩ ዘረኝነት ነው...

....ስብሐት ገብረእግዚአብሔር "ሰባተኛው መልአክ" ውስጥ የሚነግረን አስከፊ ታሪክ አለው። ቅኝ ገገርዋ አውሮፓዊት አገር ቤልጂግ፣ ከቅኝ ተገዢዋ አፍሪካዊት ኮንጎ ሰባ-ሰባት ጊዜ ታንሣለች። ይሁንና ኮንጎ የቤልጅጉ ንጉስ የዳግማዊ ሌዎፖልድ የግል ርስቱ ነበረች። ቤልጅጎቹ ልብ ሲሉ ወንዶቹ ኮንጎዎች በዝተዋል። የሚያሰጋ ብዛት። ስለዚህ ቤልጂጎች ወታደሮቻቸውን በጥቅል ሳይሆን በተናጠል እየተዘዋወሩ ኮንጎዎቹን ወንዶች እያደኑ እንዲገድሉ ትዕዛዝ ሰጡ፤ ትዕዛዙ ግን አልተፈፀመም። ወታደሮቹ ጫካ ገብተው በጥይቱ አውሬ ሲያድኑ ይውላሉ። ይሄ ስለታወቀ የወታደሮቹ አለቆች ሌላ ትዕዛዝ አስተላለፉ። "የገደላችሁትን ጥቁር እጅ እየቆረጣችሁ አምጡ" አሉ። አሁንም ወታደሮቹ አውሬ ሲያድኑ ሲያድኑ ይውሉና አመሻሽ ላይ ወደ ጥቁሮች መንደር ጉራ ይላሉ። ጥቁሩን ወንድ አሰልፈው እጅ እጁን በመጉመድ በጆንያ ሞልተው ለአለቆቻቸው ያስረከባሉ። ይሄም ታወቀ፤ ወታደሮቹ የሚውሉበት ጫካ አካባቢ ያሉ ኮንጎአውያን አንድ አንድ እጃቸው የተጎመደ ሆኑ።

...የቤልጂጎቹ የቅኝ ሀገር ተወላጆችን የመፍጀት ውሳኔ በጣሊያን በኩል አድርጎ እኛም ጋ መጥቶ እንደነበር የሚነግሩን አቶ ተስፋሚካኤል ትኩእ ናቸው። "ሀገሬ የህይወቴ ጥሪ" የተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ ምፅዋ ስለነበር አንድ ሶልዳቶ ሀኪም ይነግሩናል። ዶክተር ሮኮ ይባላል። እሱ የሚሰራበት ሀኪም ቤት የሚገባ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በመርዝ ይገደል እንደነበርም ይተርኩልናል። "ከ60 የማያንሱ የእኛ ሰዎች ከእኔ ጋር (ሆስፒታል) ገቡ። በየቀኑ 3 እና 4 እየሞቱ አለቁ።" ይሉናል። ስለዚህ ጥርጣሬ ገባቸው። "እንድጠራጠራቸው እውነት ነበረኝ። ስለምን፣ ጣሊያን የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጥር ለመቀነስ፣ ወጣቶችዋ ሲፈፀሙ ስተት ብሎ ገብቶ ለመያዝዋ ባለብዙ ምኞት መሆኗን በብዙ መንገድ አረጋገጥሁና በጥንቃቄ ላይ ጥንቃቄ ጨመርሁ።"

የብዙ መጥፎ ነገሮች ምንጬ ዘረኝነት ነው...

..."አትግደል" የሚለው ከትዕዛዛት አንዱ በምዕመናን የሚጣሰው ዘረኝነት ሲኖር ነው፤ እርምን ያለመብላት ተፈጥሯዊ ህግ የሚታለፈው ዘረኝነት ሲሰፍን ነው፤ "አትዝረፍ" የሚለው የህሊናን ደንብ የሚደመስሰው ጎሰኝነት ሲናኝ ነው፤ አብሮ መኖር ዋጋ የሚያጣው፣ በአንድ ቤተ-መቅደስ መፀለይ የሚቀረው፣ ገጀራ የሚነቀነቀው... በዘረኝነት መታበይ ሲመጣ ነው። የዚህ ሁሉ ፍንጬ እኛ ዘንድ እየታየ ነው። እንዴት አንሰጋ? እንሰጋለን እንጂ!...

የእብድ ገላጋይ ቆንጨራ እያቀበለን፤ አለመስጋት ተፈጥሯዊ አይደለም። እንሰጋለን!! የዘር ዛር ሲያንዘረዝር፣ እንዴት አንሰጋ? እንሰጋለን እንጂ!!

# "የሞትኳም እኛ ያለኳም እኛ"

ነባር የሁለት ፅንፍ ፖለቲካዊ ክርክሮች ናቸው። "መንግስት የሕዝቡ ቅጂ ነው" እና "ሕዝብ የመንግሥት ሥሪት ነው" የሚሉት። የፈረንሳይ አብዮትን ተከትሎ በወቅቱ የተነሱ የፖለቲካ ፈላስፎች እርስ-በእርስ የሚያናቁራቸው ሁለት ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ክርክሩን አጧጧፈው። አንዳንዶቹ "የሕዝቦች አስተሳሰብ በአመዛኙ የመንግስታቸውን ባህርይ ይወስናል" ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ በተቃራኒው "የህዝቦችን አስተሳሰብ የሚወስነው የመንግስታቸው ባህርይ ነው" ይላሉ።

ከተናቋሪ ፈላስፎቹ መካከል አንዱ ሲስሞንዲ (J.C.L. Sismondi) እንደሚለው "የፖለቲካ ለውጥ የብሔራዊ ጠባይ ለውጥን ይቀድማል። ስለዚህ የመንግስት ባህርይ የሕዝቦች ባህርይ ጥገኛ አይደለም።" ሲስሞንዲ ይሄን አቋሙን ሲያስተነትን እንዲህ ይላል፡-

"Nature was the same for Italians of all ages: only governments changed and these changes always preceded or accompanied changes in the national character." (ሁልጊዜም ለሮማውያን /ለኢጣሊያውያን/ ተፈጥሮ አንድ ዓይነት ነበረች። ልዩነት የነበራቸው መንግስታቱ ብቻ ናቸው። ሁልጊዜም የመንግስታቱ መለዋወጥ ከብሔራዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ቀድሞ አልያም በአንድ ላይ ይተገበር ነበር እንደማለት ነው።)

ኢትዮጵያም ውስጥ ተፈጥሮ ለዝንት አለም አንድ ነበረች። ተለዋዋጩ መንግሥት ነው። ዋናው ጥያቄ "መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ አስተሳሰብ በምን አይነት ሁኔታ ይቆያል?" የሚለው ነው። ብሔራዊ አስተሳሰባችን መንግሥታችንን ይቀርፃል? ወይስ መንግሥት እንዳሻው ቅርፅ የሚሰጠን የእጁ ውስጥ እርጥብ ጭቃዎች ነን? ስለዚህ ጉዳይ ታሪካችን ምን ይላል?...

ታሪካችን ሲታሰስ ውሎ ሲታሰስ ቢታደር ስለህዝብ ባህርይና ፍላጐት የታነፀ መንግሥት አይገኝም። እንደውም ትንቅንቁ ሁሉ "እኔን መስለህ እደር" ባይ ንጉስ ህዝቡን ከመንግሥት አፎት ጋር ለማስማማት በግፍ ለመቀጥቀጥ በመነሳቱ ነው። መንግሥት አስተዳደራዊ፣ ኃይማኖታዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ባህሪው እንደፈቀደለት ድንገት ተነስቶ ሕዝቡን "እንዲህ ሁን" ለማለት ጥቂት ሲያቅማማ አይስተዋልም። ጭራሽ ሕዝቡ የራሱ ፍላጐት እንዳለው እንኳን ጥቂት ግንዛቤ ያላቸው ገዢዎች የሉም ማለት ይቻላል። በእርግጥም ደግሞ ህዝቡ የሚቆስለው፣ የሚደማውና የሚሞተው ለቤተክርስቲያን ወይም ለገዢዎች አለበለዚያም ለአማፂዎች ጥቅም እንጂ ለራሱ ፍላጐት አልነበረም። ህዝቡ ከተሸናፊ ወደ አሸናፊ ያለ ውል የሚተሳሰፍ "ብሔራዊ-ዕቃ" ነበር ማለት ይቻላል።

በሸዋ መርአድ አዝማች ኃይሌ በሣህለ ሥላሴ አልጋ በተቀመጡበት ዘመን ነው ከአቶ ሰይፉ ጋር ቂሙ የማይበርድ የቅድስት ኃይማኖት ጦርነት ጀመሩ። ይቺን የሚነግሩን አለቃ አጥሜ ናቸው። "በዚያን ዘመን በዚያች ወራት የነበረ ሰው እንዴት ያሳዝናል!? ታላቅ ሽብር ሆነ ልጅ ሲወለድ ስሙ ሽብሩ ወይም አሣርአየሁ ይባል ነበረ" ይሉናል። ሸዋ አፄ ቴዎድሮስን በወደደና በጠላ ተከፋፍሎ ይዋጋ ጀመር። የኃይል ሚዛኑ ወዴት እንዳጋደለ ባልለየበት በዚያ ዘመን ሕዝቡ በማን ሥም እንደሚደኖኝ ግራ ተጋብቶ ቆየ። ዳኛ ጠፋ። "በቴዎድሮስ አምላክ" ወይም "በሠይፉ አምላክ" ወይም "በኃይሌ አምላክ".... ቢሉ የሚሰማ ታጣ። በዚህ መካከል አንድ ባላገር ወንበዴዎች ሲደበድቡት "በድብልቅልቁ አምላክ!" አለ ይባላል።

ሕዝቡ ይሄው ነው፤ ድብልቅልቁ አልፎ አዝማች ኃይሌ መጡ፣ አቶ ሠይፉ አሸነፉ የእሱ ጉዳይ አይደለም። አሸናፊውን ተቀብሎ በሥሙ መደኖኘት በቂው ነው። ሥልጣን ከህዝብ ፍላጐት እንደማይመነጭ ደምድሞ ተቀምጧላ!

እንደውቅያኖስ የተንሰራፋው ጥልቅና ምጥቅ ታሪካችን ውስጥ አንዳንድ ለየት ያሉ አንፀባራቂ ዕንቁ መሣይ ገጠመኞች ብርሃን ሲያፈልቁ ይታያሉ። በ1919 ዓ.ም. ነው፤ በአፄ ሱሱኒዮስ ዘመን። አንድ ሰው ለየት ያለ አላማ ይዞ ተነሣ። አላማው የህዝብ ፍላጐትን መሠረት ያደረገ ነበር። ሸዋ የመንግሥት ማዕከል መሆኑዋ ከቀረ ወዲህ በነዋሪዎችዋ መካከል የተፈጠሩትን ችግሮች ለማቃለል ያለመ ነበር። አማፂው ወልደቅብርያል የሚባል ሰው ነበር። እራሱን "ቴዎድሮስ ፀሐይ" እያለ ይጠራል። "ይሄ ሰው በተለይ ከግራኝ ወረራ ጀምሮ በሸዋና በወሎ ውስጥ ሃይማኖታቸው የተለያዩ አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ አርጐብኛና አፋርኛ ተናጋሪዎች ተጨናንቀውና ተጣበው ይኖሩ ነበርና በመካከላቸው የተፈጠሩ የኢኮኖሚና የባህል ቅራኔዎችን

ለመቀነስ፣ ከተቻለም ለማስታረቅ ምክሯል" የሚሉን መርዕድ ወልደ አረጋይ "የቴዎድሮስ አላማዎች ከየት እንደመነጩ" በሚል ጥናታቸው ላይ ነው።

ከወልደቅብርያል በፊትም ሆነ በኋላ በታሪካችን የህዝብ ፍላጐት መንግሥትን ሲያስጨንቅ የታየ አይመስልም። እንደውም አንዳንዴ አንዳንድ ነገሥታት የሕዝብን ጥያቄና ፍላጐት አንስተው ለመተርጐም ሲጣጣሩ በተላላው ሕዝብ እንደ ጠላት ተቆጥረው ሲጠፉ ይታያል። ለዚህ ምሣሌ ቀዳማዊ ቴዎድሮስ ናቸው።

ቀዳማዊ ቴዎድሮስ የነገሱት በ1412 ይሁን እንጂ የንግሥና ዘመናቸው ከአንድ ዓመት አልዘለለም። ምክንያቱም የገባሩ ህይወት ሰቆቃ የሞላው እንደሆነ አይተው ይሄን ለማሻሻል በመሞከራቸው ከባላባቱና ከቤተክርስቲያን ተቃውሞ ገጥሟቸው በሕዝቡ ተባባሪነት እድሜያቸውና መንግሥታቸው አጥሯል። ሕዝቡን ለመምሰል ሞክሮ በሕዝቡ የጠፋ ሌላው መንግሥት የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ አስተዳደር ነው። አፄው መቅደላ ላይ በእንግሊዞች ተከብበው የፃፉት ደብዳቤ እንዲህ የሚል አንቀፅ አለው፡-

"ያገሬ ሰው ግብር ሥራት ግባ ብየብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ (እንግሊዞች) ግን በሥራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ። ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውየ ነው። ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል እስልሞአል እያሉ አስሩን ምክንያት ይሰጡኝ ነበረ። እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይሰጠው የወደደው ይሁን።"

ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት የህዝቡ ቅጂ ሆኖ አያውቅም። መንግሥት የህዝብ ፍላጐትን በመቃረን የሚያስጓራ መንፈስ የተጠናወተው ነው። ህዝቡ ከተሸናፊ ወደ አሸናፊ ያለውል የሚተላለፍ ብሔራዊ-ዕቃ ነበር። ሽግግሩ በንጉሱ ሰላማዊ ሞት ቢከናወን እንኳ ተተኪው የሚያስነግረው አዋጅ ሕዝብ ፍላጐት እንዳለው ከግምት የሚከት አይደለም።

"የሞትንም እኛ ያለንም እኛ። ነጋዴ ነግድ፣ ገበሬ እረስ፣ ሽፍታ ከዱር፣ ሌባ ከመንደር ውጣ። እንቢ ያልክ ለገላህ እዘንለት" በቃ! እኛም ሟቹን ትተን አዲስ በነገሰው ሥም እስከንምል ጥቂት ጊዜ መደናገር ያገኘን እንደሆን እንጂ ሌላ ችግርም፣ ፍላጐትም የለንም።

ለእኛ የህዝብ አምሳያ መንግሥት የፈረንጆች ቅንጦት የወለደው ህልም ነው። እንኳን ያኔ በታሪክ አሁንም ቢሆን ፍላጐትን ከመንግሥት ፍላጐት ውስጥ መፈለግ እንጂ የተጣራ የሕዝብ ፍላጐት የሚባል ነገር የለም። የህዝቡን ፍላጐት ከመንግሥት "አፎት" ጋር ለማስማማት ቅጥቀጣው አሁንም አልቆመም። ሕዝቡን እንደ ብሔራዊ-ዕቃ ቆጥሮ መረካከብ እንደቀጠለ ነው። አዋጁንም በምክር ቤት

ምድረ ላይ እደምጠዋል። "የምትገም ነው፤ ያለገም ነው..." አይነት በዚህ ዘመን በሕዝብ ላይ ያደር የሆነ፤ አሁን ያለሆነ እንደም እንኳ የለም።

ጉዳያችንን በአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የግዕዝ ቅኔ እንዝጋ፦

"ኅሊናተ ለአልባም ለእግዚአብሔር

ወሰ.ያየ እናም ነሙ ያለማዐ

ለዘና ወላከዩ ለሀገራችን ኢትዮጵያ"

ትርጉሙ፡

እግዚአብሔርን አንድ ነገር ጠይቄዋለሁ፤

እሱም አፈልጋለሁ፤

የሀገራችንን የኢትዮጵያን

ለዘሮች ሰላምን እንዲሰጥ።

# "ከኢህአዴግ ጋር መጨረው ጊዜ..." እንዴት?

የዘመኑ ገገርዎች መታበያ ታግሎም ሆነ ተፎካክሮ የሚጥል ጠንካራ ተቃዋሚ አለመኖሩ ነው። ስለዚህ "ነገሮች ባሉበት ሁኔታ ለአርባ እና ለሃምሣ ዓመታት ይቀጥላሉ" ሲሉ በአደባባይ ይናገራሉ። የመታበይ ትምበያቸው መሰረቱን የጣለው የተቀናቃኞች ወቅታዊ አቋም ላይ ነው። እንደሚሉት እንበልና ኢህአዴግን ታግሎም ሆነ ተፎካክሮ የሚጥል ተቃዋሚ ተቋም የለም፤ አይኖርም። ግን ነገሮች ባሉበት ሁኔታ ያን ያህል አመታት ይቀጥላሉ? እንዴት ቢቋጠር? እንደምን ቢጠፈር? ምን ያህል ቢወጠር?... ለአርባ እና ለሃምሣ ዓመታት ሳይላላ ይቆያል?

ጉዳዩን ከሚቋጠረው፣ ከሚጠፈረው፣ ከሚወጠረው... ተጨቋኝ አንፃር ብቻ ማየት ሰዋዊ ባህርይን አለመረዳት ይመስላል። ሰው እኮ ማጣቱ ብቻ ሳይሆን ማግኘቱም በሌሎች ማጣት ሲከበብ ደስታ ይነሳዋል። ነፃነት ማግኘቱ በሌሎች ጭቆና ላይ ከተመሰረተ ይጠላዋል። የሙብት ማስከበር ፍላጐቱ የሌሎችን ሙብት እስከመግፈፍ ከተንሰራፋ በህይወት እርካታ ማጣት ይከተለዋል... ይሄንን በእኛ የፖለቲካ ታሪክ በግላጭ ተመልክተነዋል። አገራችን ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው ፊውዳላዊ ጭቆና የተገረሰሰው ብሶት ከወለደው ጭቁን በፊት የጨቋኝ ወገኖቹ እርካታ ማጣት በመገንፈሉ ነበር።

የተማሪዎች የተቃውሞ ንቅናቄ መሪ የነበረው ጥላሁን ግዛው የደጃዝማች ግዛው ልጅና የልዕልት ሣራ ወንድም ነበር። የመኢሶኑ ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ የመከላከያ ሚኒስትሩ የጄኔራል መርዕድ መንገሻ ልጅ ነው። ዶ/ር ንግሥት አዳነ፣ ቢኒያም አዳነና ዮሴፍ አዳነ የእርሻ ሚኒስትሩ የአበበ ረታ የእህት ልጆች ናቸው። የኢህአፓው መሪ ብርሃነመስቀል ረዳ የዳኛ ልጅ ነው፣ ፀጋዬ ደብተራው የወረዳ አስተዳዳሪ አባት ነበሩት፣ የዳዊት ስዩም አባት የኢጋመ አውራጃ አስተዳዳሪ ነበሩ፣ ጌታቸው ማሩ የኮሎኔል ልጅ ነው። ዘሩ ክሽን ቅድመ አያቶቹ የአፄ ቴዎድሮስና

የአፄ ዮሐንስ የታወቁ የተደነቁ ተዋጊዎች (በአሁኑ አባባል ነፍጠኞች) ነበሩ። ጠቅቅስን የማንዘልቀውን...

ጭቁኑ ጭቆናውን ከመረዳቱ አስቀድሞ የጨቋኙ ወገን ትክክል አለመሆኑ ገብቶት ነበር ማለት ይቻላል። ጭሰኛው፣ ባላባቶች መኖሪያ ድረስ እያመጣ የሚገብረው እራሱን ከመብላትና ከመጠጣት ቆጥቦ መሆኑ ለጨቋኙ ወገን እንቅልፍ የሚነሳ እውነት ሆኗል። ለተጨቋኙ ግን በእግዚአብሔር ትዕዛዝትና ፈደል ባለመቁጠር ተጠቃልሎ በተለምዶነት ተወስዷል። የያኔዎቹ የተማሩት ወጣቶች የህሊናን ጥያቄ ከጥቅም ጥያቄ በላይ አድርገው እንዲያዩ ግድ ብሏቸዋል። ስለዚህ የገዛ እርስታቸውን "ለአራሹ!" ብለው ጮኹ። በገዛ ወላጆቻቸው የተቋጠረውን ፈቱ፣ የተጠፈረውን አላሉ፣ የተወጠረውን አረገቡ... ለዚህም የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት ከፈሉ...

ለዚህ ዘመን ቋጠሮ፣ ለዚህ ዘመን ጥፈራና ለዚህ ዘመን ውጠራ፣ የሚቆረቆር ህሊና፣ የሚያደላድል ህልውና... የለ ይሆን?... ብዙ ጥያቄዎች እየተረገጡና እየተረመረሙ አርባና ሃምሣ አመት መዝለቅ የሚያስችል ሀኔታ አለ? ከወዲያ ይቅር፣ ከመሃል የሚያፈነግጥ አይኖርም? መርገጥ የሰለቸው? መረምረም የታከተው?...

በአፄ ኃይለሥላሴ ፀጥታ ሰራተኞች የተገደለው የተማሪዎች ንቅናቄ አውራ ጥላሁን ግዛው የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በኩርፊያ የጠየመ ነበር አሉ። ጥላሁን የቃጣው ባይመታቸውም ከእርሱ እጅ የወጣው መምቿያ ሌሎች እጅ እንዲገባ ሆኗልና ወገኖቹ አስከሬኑን ተቀይመውት ነበር። ያስኮረፋቸው ተረት ግልፅ ነው። "የራሱን ትቶ የሰው አክባሪ፣ የበላበትን ወጪት ሰባሪ"

የጥላሁን ሞት ያገኦደለው ከወገኖቹ ውጪ ላሉት ነበር። "ጥላሁን-ለምን፣ ለምን ሞተ?"፣ የጥላሁንና የመሰሎቹ ፖለቲካዊ ሁነት ትክክለኛ ስያሜ ሳይሰጠው ለረጅም ጊዜ ቆይቷል። የኋላ-ኋላ ግን ኢህአፓዎች እንዲህ ያለውን የስርዓት ወገንተኝነት ትቶ ከሥርዓቱ ተቀናቃኞች ጋር የሚሰለፍን ሰው "መደቡን የሸጠ" በሚል ስያሜ ይጠሩት ጀመር። ስያሜው ማንኳሰስ ቢመስልም በእነሱ ዘንድ ያለው ግንዛቤ ግን ማሞካሸት ነው። "የሸጠ" የሚለው ቃል አንድን ነገር ስለግል ጥቅም አሳልፎ መስጠት በመሆኑ ጥቅመኝነትን የሚገልፅ ነው። ኢህአፓዎች ስለምን ይሄን ቃል "ክቡር" ላሉት ድርጊት መግለጫ እንዳደረጉት ግልፅ አይደለም። "አገሩን የሸጠ"፣ "ወገኑን የሸጠ"፣ "እናቱን የሸጠ"... ሲባል የሚሰማን ኢህአፓዎች

“መደቡን የሸጠ” ሲሉ አይሰማቸውም። በአንፃሩ ለግለሰቡ አክብሮትና አድናቆት
አላቸው። ያም ሆነ ይህ ድርጊቱ እንጂ ቃሉ ግድ አይለንም።
“መደቡን የሚሸጥ” በዚህ ዘመን አይከሰት ይሆን? መቼም የዚህ ዘመን ትግል
በብሔር ተጀምሮ በመደብ መጠናቀቁ ግልፅ እየሆነ መጥቷልና “መደቡን የሚሸጥ”
ብንጠብቅ አይፈረድብንም።

ኢ-ፍትሕዊት፣ ጭቆና፣ አፈና፣ ብዝበዛ... እስካለ ድረስ “መደባቸውን የሚሸጡ”
ታጋዮች በየትኛውም ሥርዓት መኖራቸው የግድ ነው። የግድ ብቻ ሳይሆን ሰዋዊ
ጠባይም አለበት። “Humanism” (ሰብአዊነት) የተሰኘው የፍልስፍና ዘርፍ ለዚህ
ድጋፍ ይሰጣል። የሰው ልጅ ህሊናዊ እና ምክንያታዊ (Rational) መሆኑ በራሱ
የተዛባና የተንጋደደ ነገር እያየ እረፍት እንዳያገኝ ያደርገዋል። ስለዚህ ከተዛባውና
ከተንጋደደው ነገር ተጠቃሚ ቢሆን እንኳን ጥቅሙን ትቶ የተዛባውን
ለማስተካከል፣ የተንጋደደውን ለማቃናት ይሞክራል። ስለዚህ ፍልስፍናው በሰው
ልጅ ጠባያት ላይ እምነት ከማሳደር፤ ለሰው ልጅ ሁሉ ነፃነትንና መብትን
ከማጎናፀፍ መርህ ይነሳል። በአጠቃላይ ግን “መደብ መሸጥ” ሰብዓዊ ባህርይ
እንደሆነ በገደምዳሜ ይለፍፋል።

የተማሪዎቹ “መደብ መሸጥ” ከማቆጥቆጡ አስቀድሞ አንዳንድ ፍንጮች ታይተው
እንደነበር ታሪክ ያስረዳል። የግርማሜና የመንግስቱ ነዋይ “መደብ መሸጥ”
ለኋለኛው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጥንስስ ነበር ማለት ይቻላል። ግርማሜ ነዋይ
አሜሪካ ድረስ ሄደው ከኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪያቸውን የተቀበሉ
የሥርዓቱ ተስፈኛ ነበሩ። ይሁንና ከተደላደለ ኑሯቸው ይልቅ የሌሎችን የኢትዮጵያ
ህዝቦች ያጋደለ ህይወት እያዩ መትከንከን አበዙ። አዝማማሚያቸው በመንግሥት
ስላልተወደደ ከመሀል አገር እንዲርቁ ተደረገ። ይሁንና እንዲያስተዳድሩ
በተላኩበት በወላይታና በጂጂጋ አካባቢ የመሬት ስሪቱን ከማሻሻል እስከ መሬት
ማከፋፈል የሚደርስ እርምጃ ወሰዱ። ይሄንን እርምጃ መንግሥት ጣልቃ እየገባ
በማደናቀፉ የለውጥ ሙከራው የአስተዳደሩ ማዕከል ላይ ማነጣጠር እንዳለበት
ወስነው የ1953ቱን የመፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ አካሄዱ። ሙከራው ከሸፎ
ግርማሜ ዝቋላ አካባቢ ተታኩሰው ሞቱ። ወንድማቸው ጄኔራል መንግሥቱ
ቆስለው ከተያዙ በኋላ በስቅላት ተቀጡ፣ የፀጥታው ኃላፊ ሌተናል ኮሎኔል
ወርቅነህ ገበየሁ እራሳቸውን ገደሉ። የዚያ ዘመን “መደባቸውን ሻጮች” ሙከራ
በአካል የተቋጭ ቢመስልም መንፈሱ ግን ሳይገታ ወደተማሪዎቹ ተላለፈ።

በዚህ ዘመንስ "መደቡን የሚሸጥ" አይከሰት ይሆን?

አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ፣ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት፣ ክቡር ሀዲስ ዓለማየሁ... "መደባቸውን ለሸጡ" አባቶች ነበሩ።

በዚህ ዘመንስ? ታግሎም ሆነ ተፎካክሮ የሚጥል ጠንካራ ተቃዋሚ ባለመኖሩ ነገሮች ባሉበት ሁኔታ ለአርባና ለሃምሣ ዓመታት ይቀጥሉ ይሆን? ከዚህ የመታበይ ትምበያ ጀርባ "መደቡን ለመሸጥ" የሚገደድ ባለህሊና ይጠፋል? ጥያቄዎች ሲረመረሙና ድምፆች ሲታፈኑ ከመካከላቸው የሚከነክነው ይጠፋል?...

ጭቆና ካለ፣ ጨቋኝ እንደጨቆነ አይቀጥልም፤ በዝባዥ እንደበዘበዘ አይኖርም፣ አፋኝም እንዳፈነ አይዘልቅም.... ለውጡ የሚጠበቀው ከተጨቆኑት፣ ከተበዘበዙትና ከታፈኑት ብቻ አይደለም። ከጨቋኙ፣ ከበዝባዡና ከአፋኙም ወገን ነው። የሰው ልጅ ተፈጥሮ ግርንቢጥነት እዚህ ላይ ነው። ፍትሕ እስከሌለ ድረስ ኃይል መጨበጥም ሆነ ጥቅም ማስጠበቅ ለሕሊና እረፍት አይሰጥም። የሰው ልጅ ማህበራዊ አቋም ይሄንን አይፈቅድም። ከኃይሉም ሆነ ከጥቅሙ የሚጋሩት ልቀው እስካልተገኙ ድረስ ሥርዓቱ እራሱን በራሱ በሚያጠፋበት "ቁስል" መመታቱ አይቀርም።

# መክሸፍ እንደ ኢህአዴግ ምልጃ

ሰውየው ተስፋ አስቆራጭ ነገር ገጥሞት ለሴጣን ተሣለ አሉ። ስዕለቱ የደረሰ እንደሆን እጥፍ ኩታ አገባለሁ አለ። የማይሆን የመሰለው ነገር ሆኖ ስዕለቱ ሰመረ። እጥፍ ኩታው ቢዘጋጅም ስዕለቱን ተቀባዩ ሴጣን አልተገኘም። ይልከሰከስበታል ተብሎ የሚታሰበውን ቦታ ሁሉ አሰሰ። የለም፤ ሰውየው ግራ ቢገባው የአካባቢውን አዛውንት ያማክራቸዋል።

“ችግርህ ይሄ ነው? በል ኩታውን ይዘህ ተከተለኝ” አሉ። አዛውንቱ ይዘውት የሄዱት ምልጃ የሚካሄድበት፣ ዕርቅ የሚከናወንበት አደባባይ ነበር። የደረሱት ከተማላጁ አንዱ ዕርቅ አልፈልግም ብሎ ሽምጋዮቹን ሲያንገላታ ነበር። እምቢ-ባዩ ሰው ሽማግሌዎቹን ረጋግጦ ሲሄድ አዛውንቱ፤ ሴጣን ተሳዩን ጠጋ ብለው “ሴጣን ማለት ሽምግልና የናቀ ሰው ነውና ኩታውን ለእሱ ስጠው” አሉት።

ምሳሌው ሕዝባችን ለምልጃና ለሽምግልና ያለውን ቦታ የሚያሳይ ነው። ተበዳይ ምን በደሉ ቢከፋ በ”ይቅር ለእግዚአብሔር” ይካሳል- ልቡን ያነፃል። የበቀል ሥራ ይከስማል፣ የሥጋት ኑሮ ይመከናል። ሽምጋዮችን እረግጦ መሄድ ከሰው የማያስቆጥር ሴጣንነት የሆነው ሰላምን፣ ፍቅርን፣ የልብ ንፅህናን ... የመናቅ ተግባር በመሆኑ ነው። ጠላትነት አስፍኖ፣ አድብቶ በመኖር እየመከቱ መሰንዘር እውነትም የሴጣን ምርጫ ነው።

ከዚህ “እርቅ አክባሪ” ሕዝብ የወጣ የማይመስል፣ ሽምጋዮችን ረግጦ ሂያጅ አስተዳደር ከሰፈነብን ቆየ። ከ97 ምርጫ ጋር በተያያዘ የተካሄደው “የሽምጋይ-ተሽምጋይ ድራማ” ከአንጡራው የምልጃ ባህል አንፃር ሲታይ ድርድር እንጂ ሌላ አልነበረም። መንግሥት “አይድረሱብኝ፣ ይፈርሙልኝ፣ ይቅርታ ይጠይቁኝ፣ ይጎናበሱልኝ...” በሚልበት ድርድር ውስጥ “ይቅር ለእግዚአብሔር” ነበር ማለት

አይቻልም። መንግሥት ከመጀመሪያውም እነዚህን የማስፈረምና የማጐናበስ ጥቅሞቹን ባያይ ኖሮ፤ "የሸምጋይ-ተሸምጋይ ድራማው" ለመድረክ ሳይበቃ በግልምጫ ያመከነው ነበር።

መንግሥት አፍ ለመለጐም ካላስፈረመና ለክብሩ ካላጐናበሰ በስተቀር፤ ከስምምነት ይልቅ መናቆርን፤ ካብሮነት ይልቅ መለያየትን የሚመርጥ "ሽምጋይ ረጋጭ" ሆኖ ቆይቷል። አደጋውም ለሀገርና ለሕዝብ በሚተርፍበት አኳኋን ተንጠርብቦ እያተረመረመ ዓመታትን አስቆጥሯል። አንድ ቀን ላለመዝነቡ ምንም መተማመኛ የለም። በእርቅ ሊያልቅ የሚችል ቅሬታ ይዞ መንገድ በመጥፋቱ ብቻ የሚንጠራወዘው ኢትዮጵያዊ ብዙ ነው። ሀገር እንደ ፉክክር ቤት ሳትዘጋ የማደር ዕጣ አይገጥማት ይሆን? እዚህ ላይ የሜኔኒያስ አግሪፓን ተረት (Fable of menenius Agrippa) መጥቀስ ተገቢነት ይኖረዋል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ494 ዓ.ዓ. ሮማ ውስጥ ነው። ተጨቆንን ያሉ የፐሌቢያን ህዝቦች በገገርዎቻቸው በፓትሪሺያን ላይ አምፀው ግጭት አስነሱ። ግጭቱን በዕርቅ ለመጨረስ ሲሞከር ፓትሪሺያን እንደኛዎቹ ገገርዎች "ሽምጋይ ረጋጭ" ሆነው አስቸገሩ። ይሄን ጊዜ አግሪፓ ይሄን ተረት ተናገረ። ተረቱ እጅ እና አፍን ምሳሌ ያደረገ ነው።

"በአንድ ወቅት እጅ በአፍ ላይ ቅሬታ ያድርበታል። በመሆኑም አምፆ አፍን አላጐርስም አለ። በእጅና በአፍ አለመታረቅ ሳቢያ መላ ሰውነት በረሃብ ይቀጣ ጀመር። የረሃቡ መዘዝ የሰውነት ክፍል ለሆነው ለእጅም አልቀረለትም። መነመነ። ስለዚህ የፐሌቢያን እና የፓትሪሺያን ህዝቦች ኩርፊያና ምልጃ አለመቀበል፤ ለመለዋ ሮም ውድቀት ምክንያት ሊሆን ይችላል።"

እኛስ? በመንግሥት ምልጃ ጠል መሆን አንመነምን ይሆን? አንጠፋ ይሆን? በሸምጋይ ረጋጭነት የሚፈጠረው "ሽንቁር" ለመሰረታዊ ጠላቶቻችን መሹለኪያነት አያገለግል ይሆን? የእርቅ ጥያቄ በቀረበ ቁጥር መኰፈስና የክብር ማስጠበቅ ግርግር ማስነሳት ጥቅሙ ለማነው? ...ግልፅ አይደለም። አኩራፊ፤ ጀርባውን ለሰጠው ሀገርና ሕዝብ ፊቱን መመለስ ሲፈልግ ህገ-መንግሥቱን የማፍለም ፖለቲካዊ ቅስና የዚህ መንግሥት አይነተኛ ባህርይ ሆኗል።

የእርቅ ጥያቄ ሲቀርብልን ከእርቁ ለማትረፍ ማሰብ ያለብን እርቁ የሚያስገኘውን ሠላም ብቻ መሆን ይኖርበታል። ኢህአዴግ ግን የእርቅ ጥያቄ ሲቀርብለት ሕገ-መንግሥትን ተገን በማድረግ ተሸፋፍኖ መተኛትን መላ አድርጐ ይዞታል። "ሕገ-መንግሥቱን ሳይሸራርፉ ከተቀበሉ..." ይላል። እዚህ ላይ ያለው ዋነኛው ፍላጐት ሕገ-መንግሥቱን የናቁት ሁሉ እግሩ ሚሜ ሥር ሲወድቁ በማሣየት የተቃዋሚነት መንፈስን መስበር ነው። በሌሎች የትግል ጐራዎች ካገኛቸው ድሎች በላይ ከእርቅ መፈለጉ ሲያስተዛዝብ የኖረ ጉዳይ ነው።

ኢህአዴግ በፈጠረው መንፈስ "ሕገ-መንግሥት አይከለስ፣ ሕገ-መንግሥት አይከሰስ" ብለን ከተቀመጥን ሃያ አመታት አልፎን ወደ ሰላሳዎቹ ተጠግተናል። ሕገ-መንግሥቱ "ከአፍ የወጣ አፋፍ" ሆኖብን፣ እንዳፈተለከ ቃል መሰረዝና መደለዝ አልታሰብ ብሎናል። ሕገ-መንግሥቱ እኛው ያረቀቅነው መተዳደሪያ ሳይሆን ከሰማይ የወረደ ፅላት ያህል እየተቆጠረ መጥቷል። በእርግጥም ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ የቆምንበትን መሬት ገሃነምም፣ ገነትም የማድረግ ኃይል እንዳለው በመንግሥት እርምጃ እያየን ነው። "ሕገ-መንግሥቱን በሀይል ለመናድ የሞከሩ" የተሰኘ አንቀፅ የተጠቀሰባቸው ሰዎች በኢህአዴግ ፖለቲካዊ ውግዘት ምድራዊቷን ገሃነም በአይነ-ሥጋ ለመገናኘት እንዲችሉ ተደርገዋል። ሕገ-መንግሥት የፅድቅና የኩነኔ ምንጭ የሆነባት ብቸኛዋ ሀገር የእኛዋ ኢትዮጵያ ትመስላለች። ሌላው ሀገር፤ ሕገ-መንግሥት ሕዝቦች እየቆረቆራቸው ‹ተኙበት› የሚባሉበት የፒስታ ፍራሽ አይደለም። የእርቅ ቅድመ-ሁኔታም አይሆንም። የአሜሪካ ሕገ-መንግሥት በሕዝቦች ጥያቄ ከሃያ ሰባት ጊዜ በላይ ተሻሽሏል። ሕገ-መንግሥት ሌላ ተአምር ሳይሆን እድርተኞች ተስማምተው እንዳረቀቁት የእድር መተዳደሪያ ደንብ ነው። እድርተኞቹ ለመተዳደር አላሞች ባላቸው ሰዓት ላይ መተዳደሪያ ደንቡ ይከለሳል። የትኛውም እድር "መተዳደሪያ ደንቡን ለመናድ" የሚል የክስ-አንቀፅ የለውም። ሕገ-መንግሥትም እንደዚያ ብቻ ነው። ሕገ-መንግሥት ይከለስ፣ ይወቀስ ስለተባለ ማማተቡና "እግዚኦ!" ማለት አይጠበቅብንም።

አቶ ታደሰ መላኩ "Introduction to Constitutional Law" የተሰኘ መጽሐፍ አላቸው። ገጽ 159 ላይ ሕገ-መንግሥት እንደተቀሩት ፍጡራን ሁሉ ልደትና ሞት እንዳለው ይመሰክራሉ። ("Like all other creatures, Constitutions have a

beginning and an end.") ይሁንና የሕገ-መንግሥት ፍፃሜ ለየቅል እንደሆነ ይናገራሉ። አብዛኛዎቹ ፍጡራን ፍፃሜያቸው በሞት ይዘጋል። ሕገ-መንግሥትን ግን በማሻሻል ከሞት መታደግ ይቻላል። ("while most creatures end up in death, Constitutions can be rescued through amendment") የኢህአዴግ ሕገ-መንግሥት ግን "የዘላለም ህይወት አለው" ተብሏል። ለክብሩም እርቅ የሚያመጣው ሰላም መስዋዕት እየተደረገለት ነው። ለአጠቃላይ ዕርቅ መሰረት ከሆነ ሕገ-መንግሥቱ ድምፅ ቢሰጥበት፣ ካስፈለገም ቢከለስ ምን ይለናል? ስለምን ለራሳችን አድራጊ ፈጣሪ "ጣኦት" እንቀርፃለን? ለምን ሕገ-መንግሥት ላይ ጥያቄ መነሳቱን እንደመደፈር እንቆጥረዋለን? "ባንዲራ ጨርቅ ነው" ተብሎ የለ? ሕገ-መንግሥት ወረቀት ነው ቢባል ምን ‹እግዚኦ በሉ› ያሰኝናል? ሕገ-መንግሥት ፈርቶ-አደር መሆናችን አይገርምም? ፈጠረን ወይስ ፈጠርነው? መተዳደሪያችን ነው ወይስ መተዳደሪያው ነን? ...ኢህአዴግ ምልጃ ገብቶት ይሄን የሕገ-መንግሥት ከፉ ጥላ ከላያችን ቢገፍልን ደግ ነበር። ግን የምልጃ ሾተላይ ነውና እንደሌሎቹ ምልጃዎች ሁሉ ይሄም ምልጃ መከሸፉ የማይቀር ነው።

# ይድረስ "ለባለቅኔ" በረከት ስምኦን

ለባለቅኔ በረከት ስምኦን...

..."ባለቅኔ" ስልዎ ጥቂት ግር እንደሚሰኙ እገምታለሁ። እንደእኔ፣ እንደእኔ ባለቅኔነት የየቀልብና የየስሜታችን ግለሰባዊ ብያኔ እንጂ የአገልግሎት ብዛት የሚያስገኘው የስምምነት ማዕረግ አይደለም። እርስዎ ለእኔ በአንዲት ግጥምዎ ባለቅኔዬ ሆነዋል ብል መመዘኛነቱ የእኔ እንጂ የሌላ ሰው ሊሆን አይችልም። ባለቅኔነትዎ ለእኔ ነዋ!

የእርስዎን ግጥም ከማቅረቤ በፊት አንዲት ግጥም ያላትን ዋጋ በህንዳዊው ባለቅኔ በካቢር አስደግፌ ላሳይ። ካቢር ህይወቱን ሙሉ ተቆጥሮ የማይዘለቅ የተፈጥሮ-መወድስ ግጥሞችን ፅፏል። ይሁንና መላ-ዕድሜውን ጠቅልላ የያዘችው አንዲት ባለሁለት ስንኝ ግጥም ናት። የግጥሟን የመጀመሪያ ስንኝ የፃፉት ወጣት ሳለ ነበር። እንዲህ ትላለች፡-

"ትንሽ ጠብታ

ጠፋች ከባህር ገብታ"

ካቢር ይቺ ግጥም በአንጥልጥል እንደቀረች ይሰማው ስለነበር ህይወቱን ሙሉ ሲያንቀራብጣት ኖረ ይባላል። በመጨረሻ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ ለመሞት ደቂቃዎች ሲቀሩት ትልቁን ልጁን አስጠራው።

"አቤት?"

"ያቺን ግጥሜን አስተካክልልኝ ከስር እንዲህ የሚል ስንኝ አክልበት፡-

"ያቺው ጡብታ ነች

ባህሩን ውጣ ያስቀረች" በልልኝ። ይሄን ተናግሮ ወዲያው ህይወቱ አለፈች። ቅኔዋ የካቢር ከፈን ነበረች። ተጠቅልሎባት ኖረ፣ ተጠቅልሎባት ሞተ። ካቢር ይቺን ግጥም ብቻ የፃፈ ቢሆን ኖሮ ባለቅኔ ሳንለው ልንቀር ኖሯልን? አይመስለኝም። እንደውም ካቢር ለእኔ ባለቅኔ የሆነው በዚ ነጠላ ስራው ብቻ ነው። እንደእርስዎ!

የእርስዎም ግጥም የዋዛ አይደለችምና "ባለቅኔ ነዎት" ማለቴ አይደበዝዝብኝም የሚል ተስፋ አለኝ። እንደ ካቢር ቅኔ ባለሁለት ስንኝ የሆነችው ግጥምዎን ያገኘኋት "ሶረኔ" የተሰኘ መጽሐፍ ላይ በሰማኒያዎቹ መገባደጃ ላይ ነው። ግጥሟ እንደተዋጣለት ሰላይ ድብዛዋን አጥፍታ፣ ምንጯን አድበስብሳ ነበር "ሶረኔ" ላይ የወጣችው። ማለቴ የእርስዎ መሆኗ ሳይገለፅ፣ ስምዎን ሳታገለድም መለመላዋን ለተደራሲ እይታ ተጋለጠች። "የማነች?" የወቅቱ ጥያቄያአችን ነበር። ከሁለት ይሁን ከሶስት አመታት በኋላ ሁነኛ ሰው አግኝተን ግጥሟ የእርስዎ መሆኗን አረጋገጥን። ያኔ ስለእርስዎ የነበረን ግምት እንደማሽላ እንጀራ እምሽክሽክ ብሎ ከእጃችን ጠፋ። ፊትዎና ንግግርዎ ውስጥ ደም የማይረጭ፣ህያውነት የተነፈገ ልብ ይታየን ስለነበር፣ እርስዎ ልብ ላይ ፍቅርና ናፍቆት በቀሉ? አሁንም ጥያቄአችን ቢሆን አይፈረድብንም። እንደምን አይፈረድብንም። ለማንኛውም ግጥሟ ይቺ ናት፤

እንደተፋቀርን ላንተያይ - ሳንተያይም ልንፋቀር፣

እንደመናን ካለም ነገር - ከስሙተራ ስንባረር፣

በታጋይ ህግ ተገድበን - በአጉል ሥርዓት ስንጠፈር፣

መቸስ ምን እንላለን - በተስፋ ከመሞት በቀር፤

ግጥሟ የነባራዊ ሁነት ቋሚ ላይ ተጠምጥማ የምትለመልም የሐረግ ህልውና ያላት ቅኔ ናት። ብቻዋን መሬት ለመሬት ትሳብ እንደሆን እንጂ ቆሞ የመስተዋል ዕድል አይኖራትም። ነባራዊ ሁነቱ የትጥቅ ትግል ዘመን ነው። ታጋዮች እርስ-በእርሳቸው ፆታዊ ፍቅር ሆነ ጉድኝት እንዳይኖራቸው በጥብቅ የተከለከሉበት ወቅት ባለቅኔ በረከት ልቡና ላይ እርፎ ያቆጠቆጠው ተሃዝቦ ለግጥሟ ህልውናዋ ሆኗል። የግጥሟ መልእክት ከቁጭትና ከሙብከንከን ድሪያ ቢወለድም እንደፉከራ ከርሮ ሳይሆን በጠባዩ ለዝቦና ለስልሶ የወላጆቹ ልጅ መሆኑን ያስተናል። የሚገርመው

ደግሞ ልዝብነቱና ልስላሴው ከፍርሃት ሳይሆን ከድፍረት መገኘቱ ነው። ባለቅኔው (ተራኪው) የቆመለትን ዓላማ የሚያስፈፅመውን ህግ "አጉል ጠፉሪ ስርዓት" አድርጎ ለመፈረጅ ፍርሃት አልሸበበውም። እንደውም ከተገቢው በላይ ደፍሯል ማለት ይቻላል። ግጥሟ ላይ ታጋዮቹ የአለማዊ ህይወት "አዳምና ሄዋን" ሆነው ከሥጋዊው የፍቅር ፅድቅ፣ በምድራዊው መልአክ (የትግል ህግና ስርዓት) ሲባረሩ ምስል ትከስትልናለች...

ይሄንና ሌላውንም ምክንያቴን ዋቢ አድርጌ፣ የበረከት ስምኦንን ባለቅኔነት ብቀበል የሚያስፈርድብኝ ጥፋት ሆኖ አይታየኝም። እንደውም ትግሉና ስልጣኑ ገዳፋ (እንቅፋት) ባይሆንብዎ ባለቅኔነትዎ ካሉንና ከነበሩን ገጣሚዎች ጋር የሚያወዳድርዎ በሆነ ነበር እላለሁ። ግን ምን ይሆናል? እንደ ካርል ማርክስና እንደማኦ ሴቱንግ ሁሉ የእርስዎም ባለቅኔነት ትግልና ስልጣን ጥልቅ ውስጥ ተጣለ።

ባለቅኔ በረከት ስምኦን...

...ከትግልና ከስልጣን ጥልቅ አምልጠው የወጡ ሌሎች ጥቂት ቅኔዎች እንዳልዎት ስጠረጥር ኖሬአለሁ። ይሁንና እንደባሪያ ድንግል ተድበስብሰው ከቀሩ ቅኔዎችዎ ቀድሞ ሌላ የህይወት ቅኔዎ ደረሰኝ። የዚህ ደብዳቤ መነሻም ይሄ የህይወት ቅኔዎ ነው። የህይወት ቅኔዎን ፍንጭ ያገኙሁት "የሁለት ምርጫዎች ወግ" የተሰኘው መጽሐፍዎ ሲታተም ነው። በመጀመሪያ በ2003 ዓ.ም. ብቻ ሳይሆን አሁን በቅርቡ ሁለተኛ ህትመት ያዘዙት ከኢትዮጵያ ሸሽተው ኬንያ ነው አሉ። ኢትዮጵያ እኮ ህልምዎ ናት፣ ኢትዮጵያ እኮ የገዛ ፍላጎትዎ የፈጠራት ቅዠት ናት። ታዲያ ከገዛ ህልም ይሸሻል? የገዛ ፍላጎት ካስገኘው ቅዠት ይመለጣል?...

እርግጥ አይካድም፤ ኢትዮጵያ የህትመት ብቻ ሳይሆን የኑሮም ረመጥ ናት። ታዲያ ማን ቢጋግት ማን ይጠበስባት ብለው ሸሿት? ይሄ የህይወት ቅኔዎ አንድ በውል ያላወኩትን የትግል አጋርዎን ግጥም አስታወሰኝ። ግጥሙ ለኢህአፓ የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ተደርጎ ይቆጠራል። ርዕሱ "ሞናሊዛ" ነው።

"...አንተ ሊዎናርዶ የሮማ ልጅ

የሰራሃትን ልታሻሽል

ልታፈርሳት ልትገነባት

ደግመህ ደጋግመህ ልትሰራት

ሰልስህ ልትሰራ ስትችል

ጣዖት አደረግካት በሞትህ አጉል አጉል

ለራስህ ፍጡር እግዚአ ልትል

...የሮማ የዋህ ሰው ሊዎናርዶ

በፍቅር ትንታግ ተማግዶ

የቀረፀውን አጉል ወድዶ

ራሱን በራሱ ንዶ---ርዶ--- የሚል። የእርስዎ የህይወት ቅኔ የዚህ ተቃራኒው ነው። እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ እንደተባለ እርስዎም በኢትዮጵያ ሳይፀፀቱ እንዳልቀሩ ነው የህይወት ቅኔዎ የሚመሰክረው። ይሄንኑ የ"ሞናሊዛ"ን ላህይ ተከትለን የእርስዎን የህይወት ቅኔ እንግለጠው ብንል፦

...ሰልስህ ልትሰራ ስትችል

እርግፍ አደረግካት በሽሽትህ አጉል-አጉል

በራስህ ፍጡር እግዚአ ልትል

...የሮማ የዋህ ሰው ሊዎናርዶ

በህልም ትንታግ ተሞልቶ

የፈጠረውን አጉል ጠልቶ

እራሱን በራሱ ሸሽቶ...

እርግጥ አይካድም፣ ኬንያ የህትመት ብቻ ሳይሆን የኑሮ ርካሽነቷ ከኢትዮጵያ በእጥፍ እጥፍ ዝቅ ይላል። ለዚህ የህትመትም ሆነ የኑሮ ርካሽነት አንድ ኢትዮጵያዊ ቢማልል አይፈረድበትም። ይሁንና ኢትዮጵያን በዚህ መልኩ ለሰራትና ለገነባት ብቻ ሳይሆን ሊያሻሽላትና ሊያፈርሳት በሚችል እንደርስዎ ባለግለሰብ

ሸሸቱ ሲከናወን የሥነ-ምግባር ጥያቄ ያስነሳል። ኮልኩለው፣ ኮልኩለው ባሳበዱት መኪና (ኢትዮጵያ) ላይ የተሳፈርነውን፣ ዕጣ-ፈንታችን መሆኑን አምነን ሳይሆን ተገደን የተቀበልነውን እኛን ባለንበት ሁኔታ ሹፍርናዎን ጥለው እንደመውረድ ያለ ድርጊት ነው የሰሩት። እኛስ? ይሄን በእርስዎ ሹፍርና ያበደ መኪና (አገር) ጥለን የት እንሂድ?

እንዳልኩት ኢትዮጵያ ላይ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ኬንያን ለሚመለከት ያቺ ጎረቤት አገር ታማልላለች። የዶሮ አርስቶ 16 ሽልንግ ዋጋ አለው አሉ። በእኛ ወደ ሁለት ብር ከስድሳ ሳንቲም ማለት ነው። ይሄ የኬንያውያን አኗኗር በኛ በኢትዮጵያውያን አኗኗር ሲተረጎም ወደ ኋላ አሽቀንጥሮ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ላይ ያደርሰናል። አፕልና ወይን ጨምሮ ሌሎች ፍራፍሬዎች የደሃ ኬንያውያን መተከዣዎች ናቸው አሉ። እኛ አገር ቅቅል በቆሎና ቆሎ እንኳን ደሃ-አይደርስብሽ ምግብ ከሆኑ ሰነባብተዋል። እኛ ዘንድ አንድ ኮስማና በቆሎ መንገድ ዳር ተጠብሶ ስንት እንደሚሸጥ ያውቃሉ? ከሦስት ብር ከሃምሳ እስከ አራት ብር። ኬንያ ሄደን አንድ ብር ከ20 ሳንቲም ብንጨምር፣ የእኛዋ ጐስቋል ጐዳና ተዳዳሪ በቆሎ የሁለት ዶሮ አርስቶ ጌታ ትሆናለች። እርስዎና ጓዶችዎ በዚ አገር ላይ አስማት ነው የሰራችሁት ማለት ይቻላል። እንዴት አስባችሁ፣ እንዲህ ተሳካላችሁ? እውነትን ወደ ቅዠትነት የመለወጥ ተአምር ነው የሰራችሁት።

እና ይኸውልዎ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ እርስዎ ባለቤቱ ያቀለሉትን አሞሌ እኛ ባለዕዳዎች እንቀበል ዘንድ ግድ ሆኖብናል። የግፍ ዘመን ነውና ምን እናደርጋለን? እርስዎ ወላጅዋ የሸሸዋትን ኢትዮጵያ እኛ ባለዕዳዎቹ እናዝላለን፣ እሹሩሩ እንላለን፣ እናጠባለን...

ባለቅኔ በረከት ስምኦን...

...ከጥበባዊ ቅኔዎ፣ ህይወታዊ ሰምናወርቅዎ ገዘፈ መሰል? መጽሐፍዎን ኬንያ ማሳተምዎ ሌጣውን ይሄን ያህል አያናግር ይሆናል። ነገር ግን ከዚህ ድርጊትዎ ጀርባ እንደ ውቅያኖስ ውስጥ የበረዶ ተራራ ጫፍ ኢምንት የሆነው ችግር ውስጥ-ውስጡን የመንሰራፋቱ ምክንያት ስለሆነብኝ ነው። እርስዎ ለሃምሳና ስድሳ ሺህ ብር ትርፍ በመጽሐፍዎ የሸሿትን ኢትዮጵያ እኛ በኑሮና በሕይወት እየተቤዠናት አለን። ረሃብና እርዛታችንን እንደቦረንትቻ እየቀለብን አብረናት እንኖራለን። ደግነቱ ኑሯችን ወደ "ተስፋይቱ ምድር" የሚደረግ ጉዞ እንደሆነ እየተነገረን ነው። ቢሆን

እንኳ “ጉበስ የሚደርሰው ለፍልሰታ፣ እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ” እንዳለው ገበሬ ያለ ዕጣ-ፈንታ ውስጥ ነን።

በአናንተ ዘንድ እኛ ሲያጥቡን የምያናለቅስ ጨቅላ አይነት ነን። እርግጥ ነው፤ በዘመን አመጣሽ ዋግምትዎ እየታከምን ሊሆን ይችላል። ስንታገም ደም እየፈሰሰን እንደምንታከምም እናውቃለን። የእርስዎና ጓዶችዎ ማገም ግን ከደም በላይ ቅስምና ጅስም የሚያፈስ ሆነ። ከቅዠት የሚቆጠረው እውነታችን እናንተን አስፈሪ ተዋናይ እያደረገ ማቅረብ ከጀመረ ሰነባበተ። እርግጠኛ ነኝ እርስዎም ህልም ውስጥ እኛ አስፈሪ ገፀባህርይ ሆነናል። የህይወት ቅኔዎ የሚመነጨው ከዚህ ይሆን? በሰበብ ባስባቡ ውጭውን የመማተር ድብቅ ሽሽትዎስ ?ይሆን ይሆናል!!

# የጠፋውን የኢህአዴግ "ህሊና" ፍለጋ

የሸዋው ንጉስ ምኒልክ እና የጎጃሙ ንጉስ ተክለሃይማኖት በወዳጅነት ዘመናቸው ላይ ናቸው። አንድ ጥላ ሥር ቁጭ ብለው ሲጨዋወቱ እንዲህ የሚል ቃል ተገባቡ አሉ፡-

"እኔ ቀድሜ የሞትኩ እንደሁ ልጆቼን አደራ"

"ድንቅ፤ እኔም ብቀድምህ እንደዚያው የልጆቼን ነገር አደራ። እንደራስህ ልጆች ለወግ ለማዕረግ አብቃልኝ።"

"ምንገዶኝ፣ ወንድሜ ሙት ቃሌን ስጥቻለሁ።"

"እኔም ወንድሜ ሙት ብያለሁ።"

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ የጐጃሙ ንጉስ ቀድመው ከዚህ አለም በሞት ይለያሉ። ንጉስ ምኒልክ በወቅቱ አጤ ተብለው የንጉሰ-ነገሥቱን መንበር ተቆናጠዋል። ለንጉስ ተክለሃይማኖት የገቡትን ቃል ባለመዘንጋት ልጃቸውን "ራስ" ብለው የጐጃም ገዢ ያደርጓቸዋል።

ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ሥልጣናቸውን በአግባቡ ከመያዝ ይልቅ በልጅነት ይቦርቁ ጀመር። ሮሮ በዛ። የሚቀርብባቸው አቤቱታ እየከፋ ሲመጣ ንጉስ ምኒልክ ወደ አዲስ አበባ አስጠርተው እንጦጦ ላይ አራት ወር እንዲታሰሩ አዘዙ። ይሁንና ራስ ኃይሉ በእስር ላይ እያሉ ስለተረሱ አራት አመት ቆዩ። በመጨረሻ ራስ ኃይሉ ለአጤ ምኒልክ እንዲህ የሚል ግጥም ፅፈው ላኩላቸው፡-

> "አደራ ይላል ሟች- እሺ ይላል ቀሪ፣
>
> መቼም የለም ብሎ- ቆሞ ተናጋሪ፤"

አጤ ምኒልክ እጅግ ደነገጡ አሉ። "ፍቱልኝ፣ ፍቱልኝ" ብለው ሾመው ሸልመው ወደ ጐጃም ላኳቸው።

የዛሬ ፅሁፌ ይቺን ተረት መሰል እውነት በዘመናዊ ተረክ መድገም ነው። የእኛ አገር ነገር ግልፅ ነው። ከጥንት ጀምሮ በፅሁፍ ከቀረበ ህግ ይልቅ ቃል ለገቡለት ህሊና ያደላል። ከህገ-መንግሥቱ፣ ከወንጀል መቅጫውና ከፍትሐ-ብሔሩ በላይ ለህገ-ልቡና የምናደላው ለዚህ ነው። ይሄን ይዘን ከነገሥታቶቻችን ወደ ታጋዮቻችን እንውረድ...

...በዚህ ዘመን እንደ አጤ ምኒልክ ቃል ከብዶ፣ ከህገ-መንግሥቱ በላይ ጥቂት መተማመን ይፈጥርብን የነበረ አንድ የታጋዮች ልምድ ነበር። እሱም በተሰዉ ጓዶቻቸው ሥም የሚያቀርቡት የተፈፀመ መሐላ ነበር። “ሥጋ ብያት!” [የሰማዕታትን ሥጋ] የሚል፤ ዘንድሮ ዘንድሮ ይሄ መሀላ እየከሰመ እና እየከሰረ መጥቶ ከመደመጥ ተሰናብቷል ማለት ይቻላል። በእርግጥም ደግሞ ነገሮች ሁሉ ተለዋውጠውና “የቀኝ ኋላ ዙር”ን ያህል በተቃራኒ በተቆመበት ሁኔታ በየትኛው ህሊና ይኼ መሃላ ይደፈራል? “ሥጋ ብያት” በመጥፋት የተደመደመ ብርቅዬ “ምናምን” እንበለው? ያም ሆነ ይህ የእኛ ሥጋት መሃላውን እንደ ቅርስ በመቁጠር በመብከንከን የሚጠቃለል አይደለም። ከዚያ ይልቅ ግዳችን ከ”ሥጋ ብያት” መጥፋት በስተጀርባ ያለው እውነታ ነው። መሃላው ለምን ጠፋ? በምን ጠፋ? እንዴት ጠፋ?...

እያንዳንዱ ታጋይ (ተሳሳተም አልተሳሳተም) ተጠሪነቱና ተጠያቂነቱ በትግሉ ለተሰዉት ጓዶቹ አላማ ነበር ማለት ይቻላል። እንግዲህ የድርጅቱ የኢህአዴግ “ህሊና” የሚመነጨው ከዚህ ከታጋዮቹ የሰማዕት ታማኝነት ነበር። የመሃላው መጥፋት የህሊናው ባለበት ያለመገኘት ምልክት ነው፤

በ”ሥጋ ብያት” መጥፋት ብቻ ለእያንዳንዱ አንጡራ ታጋይ የምናቀርብለት ብዙ ጥያቄ አለን። ከተሰዋው ጓድህ ጋር አንገት ለአንገት ተቃቅፋችሁ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ምን አይነት በደል አያችሁ? እንዴት ያለ ብሶት ተቀሰቀሰባችሁ? ምን ወሰናችሁ? እንዴት ትግሉን ተቀላቀላችሁ? ለምን ዓላማ እንሰዋለን አላችሁ? የትኛውን ውጣ ውረድ ጐን-ለጐን አለፋችሁ? የትኛውን መዝሙር አቀነቀናችሁ? ምን ተገማገማችሁ? የትኛውን ተስፋ ተቋደሳችሁ? የት፣ እንዴት ለዘላለም ተለያያችሁ? አንተ እሱጋ፣ እሱ አንተጋ ምን አስቀራችሁ? በመጨረሻ አሁን የምትኖረው የተሰዋው ጓድህን ፍላጐት ያማከለ ነው? እንዲያ ከሆነ ታዲያ መሃላህን ከአፍህ ላይ ምን ጠለበው?...

የዘንድሮ ነገር፣ የጥንቱ ሁኔታ እንደሰፈሬድ ላይ ሩጫ ዞሮ መምጣት ቢመስለን አይደንቅም። የተሰዋው ታጋይና በህይወት ያለው ታጋይ በትግል ዘመናቸው ላይ ናቸው ብለን የአጤ ምኒልክንና የንጉስ ተክለሃይማኖትን ገጠመኝ ወደዚህ ዘመን ብናመጣው አያስኬድ ይሆን? እስኪ እንሞክረው፡-

...አንድ ጥላ ስር ቁጭ ብለው ሲጨዋወቱ እንዲህ የሚል ቃል ተገባቡ፡-

"እኔ ቀድሜ የሞትኩ እንደሁ አላማዬን አደራ"

"ድንቅ እኔም ብቀድምህ እንደዚያው የአላማዬን ነገር አደራ። ሳታዛባ ለወግ ለማዕረግ አብቃልኝ።"

"ምን ገዶኝ፣ ጓዴ ሙት ቃሌን ሰጥቻለሁ"

"እኔም ጓዴ ሙት ብያለሁ።"

ይሄ ዘመን መጣ፤ የተሰዋው ተሰዋ፤ ያልተሰዋው ከበረሃ ከተማ ገባ። አላማ በግል ጥቅም ታስሮ ተረሳ።

አደራ ይላል ሚች- እሺ ይላል ቀሪ፣

መቼም የለም ብሎ ቆሞ ተናጋሪ፤

አብዛኛው ታጋይ /ሁሉም ላለማለትና ትሁት ለመሆን/ "ሥጋ ብፆት"ን በመሸሽ ላይ ይገኛል። በትግሉ ለተሰዋ ጓዱ ያለበትን ተጠሪነትና ተጠያቂነት ሸሽቷል። ተጠሪነቱና ተጠያቂነቱ ለራሱ፣ ለሚስቱና ለልጁ ሆኗል። የሚሸሸው ተጠያቂነቱን ብቻ ሳይሆን ከዚያ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችንም ጭምር ነው። ለመሆኑ የዚያ የተሰዋ ታጋይ አደራ ደሃው ህዝብ አልነበረምን? ታዲያ በየት በኩል እራስህን ከአደራህ ከህዝብ አስቀደምክ? ሀብት አካበትክ? ዘመዶችህን ጠቀምክ? ህግን ከለላ አድርገህ በደልክ? ኮንትሮባንድ ነገድክ? ከታክስ ሸሸህ? ህንፃ ሰራህ? ማናለብኝነት ተፀናወተህ? ምን አድርባይ አደረገህ? ትዳርህ፣ ሚስትህ፣ ልጆችህ በየትኛው አቋራጭ ከተሰዋው ጓድህ ቀደሙ? የእሱን መሰዋት እንዴት በድሎትህ ለወጥክ?... ህሊናህን ሸሸህ? "ሥጋ ብፆት"ን ገደፍክ?....

መሐሪ ተክሌ (ሙሴ)... ልዑል... አጋዚ... ዑስማን... ክበበው... አስረዳ... ዋልታ... መስፍን... የእነዚህና የሌሎቹ የተሰዉ ታጋዮች መታሰቢያ አላማቸው አልነበረምን? "ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል" እና "መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ" እያሉ በየተቋማት ላይ ሥም መለጠፍ ህሊናን ያሳርፋል? ከዚያ ይልቅ "ሥጋ ብፆት" አይበልጥም? ህሊና አይገዝፍም?... ዛሬ አንጡራው ታጋይ የሚሸሻቸው ብዙ አንጡራ ጥያቄዎች አሉ።

"አደራ ይላል ሚች እሺ ይላል ቀሪ፣

መቼ የለም ብሎ ቆሞ ተናጋሪ" የዘመኑ እንጉርጉሮ!!

በዚህ አገር ተጨባጭ ሁኔታ የህግ ነገር እምብዛም አያስተማምንም። የህግ አናቅፅ ካጣመሟቸው የሚጣመሙ ብረት መሰል ለጋ ነገሮች ናቸው። የአናቅፁ ወጋግራ እንኳን የብርሃን ጠባይ ያለው ዘረኛ ሰበባ-ሰበብ ቀርቶ እንደ ተራራ ግዘፍ የነሣውን ብሔርተኝነት ያሾልካል። ስለዚህ በዚህ አገር ነባራዊ ሁኔታ ህሊናና ቃል ይቀድማል። ለቃልና ለህሊናችን ያብቃን!!

# እነዲያስፓራ "ነውሯችሁን ፋቁት!"

ከኢትዮጵያዊው አንፃር ስንመለከተው ስደት በዚች ሀገር ሦስት አይነት መስተንግዶ ቀርቦለታል ማለት ይቻላል። ከጠላት በፊት፣ በጠላት ጊዜ እና አሁን።

ስደት ከጠላት በፊት

ከጠላት በፊት (ከ1928 አስቀድሞ) ስደት ለአንጡራው ኢትዮጵያዊ፤ የነውር ድርጊት ብቻ ሳይሆን ለየትኛውም መከራ በአማራጭነት የሚቀርብ ጉዳይ አልነበረም። ለዚያ ዘመን ኢትዮጵያዊ፤ ስደት ከስር መነቀል ነው። መጠውለግ፣ መድረቅና መርገፍ የሚያስከትል ከሥር መነቀል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን አንድ ቤተሰብ አለ። አባት፣ እናትና አንድ ልጅን ያካተተ ቤተሰብ። የዚህን ቤተሰብ ታሪክ መመርመር ስደት ለዚያ ዘመን ኢትዮጵያዊ ያለውን ገፅታ ያሳያል። የዚያ ቤተሰብ አባት አፄ ቴዎድሮስ ናቸው፤ እናት እቴጌ ጥሩ ወርቅ፤ ልጅ ደግሞ ልዑል ዓለማየሁ ካሣ።

አፄ ቴዎድሮስ የፋሲካ ማግስት ሰኞ፣ ሚያዝያ 5፣ 1960 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰዓት ከ10 ደቂቃ እራሳቸውን ያጠፉት፤ ምርኮ የሚያስከትለውን ውርደት በመጥላት ነበር። ምርኮው መታሰርና ወደእንግሊዝ መጋዝም አለበት። አፄ ቴዎድሮስ ይሄንን ጉዳይ ቀደም ሲል ከእንግሊዛዊው ጀኔራል ናፒየር ከተፃፈላቸው ደብዳቤ ተረድተውታል። "በክብር መልካም አያያዝ እንደሚደረግልዎ ቃል እገባለሁ" ይላል። "እኔ ቴዎድሮስ! እኔ ነኝ እስረኛ የምሆነው?" አሉና እራሳቸውን አጠፉ።

የዚያ ቤተሰብ እናት እቴጌ ጥሩወርቅ ደግሞ ከሀገር የመሰደድ ዕጣ በልጃቸው በኩል መጣባቸው። ልጃቸው ልዑል አለማየሁን እንግሊዞች ሊወስዱት ስለቆረጡ እናቱ ሆዳቸው ባባ። ከሰባት አመት ልጃቸው ጋር ለመሰደድ ወሰኑ። ስደት ያስከተለው ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ተደራርቦ፤ እናት በጉዞ ላይ እንዳሉ እንጣሎ አጠገብ ሐይቅ ሐጥላ ከሚባል ሥፍራ ላይ ሞቱ።

ስደትን በጥቂቱ የቀመሰው ልዑል ዓለማየሁ ኑሮው ባይጓደልም፣ ደስታ ግን አልነበረውም። ንግሥት ቪክቶሪያ ማስታወሻቸው ላይ “ምስኪኑ ልጅ አሁንም ፍርሃቱ አለቀቀውም” ብለው አስፍረዋል። እንደ አባቱና እናቱ ሁሉ ልዑሉም ታሞ በሕዳር 15 ቀን 1872 ዓ.ም. እንግሊዝ፣ ሊድስ ውስጥ አርፏል። ለዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን ስደት በአማራጭነት የማይቀበሉት (እንደ ቴዎድሮስ)፣ ቢቀበሉትም የማይፈፅሙት (እንደ እቴጌ ጥሩወርቅ)፣ ቢጀምሩትም የማይቀዩበት (እንደልዑል ዓለማየሁ) ነበር ማለት ይቻላል።

ስደት በጠላት ጊዜ

“ድንግል ሀገሬ ሆይ ጥንተ ተደንግሎ

ህፃናቱ ታርደው ያንቺም ልብ ቆስሎ

ልጅሽ ተሰደደ አንቺን ተከትሎ

የህፃናቱን ደም አዘከሪ ኩሎ”

ይሄ የዮፍታሔ ንጉሴ ግጥም የተፃፈው በጠላት ጊዜ ነበር። የዚያ ዘመን ስደት ለአንጡራው ኢትዮጵያዊ በሶስተኛ አማራጭነት ቀርቧል። ከአርበኝነት እና ከባንዳነት ቀጥሎ። አርበኝነት እንደማያዋጣ የተሰማቸው ባንዳነትን ስለተፀየፉ፣ መሰደድን መርጠዋል። የዚያ ክፉ ዘመን ኢትዮጵያዊ ስደት፣ ኢትዮጵያ ስትሰደድ እሷን ተከትሎ የሚከናወን እንደሆነ ዮፍታሔ በግጥሙ ጠቅሷል። “ልጅሽ ተሰደደ አንቺን ተከትሎ” የሀገሩን ዱካ ተከትሎ መሰደድን ዮፍታሄ ቀምሶታልና ጠንቅቆ ያውቀዋል። ስለዚህ ጉዳይ ዮሐንስ አድማሱ ምስክርነቱን ሲሰጥ፡-

“(ዮፍታሔ) መንፈሳዊ ትግሉ እመቤቱ ስለሆነችው፣ በእመቤታችን ስለመሰላት ስለድንግል ሀገሩ ሚጠት (ምፅአት) ነበረ” ይላል (ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ አጭር የህይወቱና የፅሁፉ ታሪክ ገፅ 122)

የጠላት ጊዜ ኢትዮጵያዊ ሲሰደድ የእናት ሀገሩን መቀነት ትልም አድርጎ ጥላዋን ተጎናፅፎ ነውና ምንጊዜም ከልቡ አትጠፋም ነበር። ፋሽስት፣ ኢትዮጵያዊውን ከሀገሩ ማስወጣት ቢችልም፣ አገሩን ከኢትዮጵያዊው ልብ አውጥቶ መጣል እንደተሳነው ፍፃሜ መንግሥቱ ላይ ደርሷል። ለፋሽስት ውድቀት ይሄ የኢትዮጵያውያን አገርን ከልብ የመውደድ ጠባይ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

እራሱ ዮፍታሔ ንጉሴ በስደት ከተቀመጠበት ሱዳን ተነስቶ በተደጋጋሚ ሀገሩ በመግባት መረጃ የማቀበልና የመሰለል ስራ ይሰራ ነበር።

ስደት በዚህ ዘመን

የዚህ ዘመን ስደት ጭራውን የቋጠረው ከአብዮቱ ጅማሬ ጋር ነው። የርዕዮተ-ዓለም ሽንፈት የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመንተኞችን እንዲሰደዱ አስገደደ። የአብዮት ዘመን ንትርክ በጥይት ምላሽ ማግኘት ሲጀምር እልቂት ያሰጋቸው ስደትን ምርጫ እንዲያደርጉ ግድ አላቸው፤ የፖለቲካ መቻቻል ውኃ ሲበላው እና አንድ አይነት "ዩኒፎርም" መልበስ በደርግ ያለ አማራጭ ሲቀርብ፤ ሁኔታውን መለወጥ የተሳናቸው ስደት ግዴታቸው ሆነ... ዮፍታሔ እንዳለው ከእነዚህ ጋር ሁሉ ሀገር አብራ ተሰደደች። እንደፋሽስት ኢጣሊያ ሁሉ ደርግም ኢትዮጵያውያንን ከኢትዮጵያ እንጂ፣ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ማስወጣት ተስኖት ቆየ።

ከዚያ ዘመን ስደት ጋር ጭራውን የቆለፈው የዚህ ዘመን ስደት ምክንያቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነው። ኢኮኖሚያዊው ስደት በአንድ ነባር ተረት ይጠቃለላል "የተመረረ ደሃ ይገባል ከውኃ"።

የዚህ ዘመን ስደት በአመዛኙ ከውርደት ጋር ተፈጣጥሟል ማለት ይቻላል። ከመቶ አመታት በፊት ሐጂ ለማድረግ ከሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ጭብጦ ይለምኑ የነበሩት ሳውዲዎች ዛሬ ሳይሰሩ ከሰማይ በወረደላቸው የሀብት መና ጠግበው ያደረጉትን አይተናል። ገንዘብ ከጭንቅላት ስልጣኔ ቀድሞባቸው አውሬነትን ለመተግበር አስችሏቸዋል። የዚህ ዘመን ስደት ለእኛ መሸፈኛ እራፊ ጨርቅ ያጣንለት ገመናችን መሆኑ እሙን ነው።

በዚህ መንግሥት ጡጫ፣ እርግጫና ግልምጫ የተሰደደው የፖለቲካ ጥገኝነት ፈላጊ ኢትዮጵያዊ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዳዲስ ጠባይ እያመጣ እንደሆነ ይነገራል። እዚህ ተፀየፍኩት ያለውን ዘረኝነት፤ እዚያ ካልተገበርኩት በሚል ግብግብ ላይ ይገኛል አሉ። የስደት ሀገር የጐጠኝነት ኮሎኒም እያቋቋሙ ነው አሉ። ያሳዝናል! አንዳንድ የአሜሪካ ስቴቶችማ ከየስቴቱ ባንዲራ ጋር በውስጠ-ታዋቂ የሚውለበለብ የጐጠኝነት ሰንደቅ አዘጋጅተዋል። ለምሳሌ ሲያትልና ሳንሆዜ የጐንደሮች ስርወ-ንግስ አለ፤ ሚኒሶታ ደግሞ ሰማኒያ በመቶ በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቁጥጥር ስር ውሏል አሉ። ኮሎምቦስ -ኦሀዩ ከሄድን የትግርኛ ተናጋሪዎች ፌዴሬሽን አለ።

("ፌዴሬሽን" ያልነው በልማት ማህበር ስም በአውራጃ ተከፋፍለው ስለተቀመጡ ነው። የሽሬ ልማት ማህበር፣ የአጋመ ልማት ማህበር፣ የተንቤን ልማት ማህበር... ወዘተ)

የዚህ ዘመን ስደት ገመና ይሄ ነው። ፋሽስት ኢጣሊያም ሆነች ደርግ ያልቻለውን ኢህአዴግ ችሏል። ኢትዮጵያዊውን በጡጫ ሆነ በእርግጫ ከኢትዮጵያ ከማስወጣት ባሻገር ኢትዮጵያዊነቱንም ከልቡ ፈንቅሎ ለመጣል ችሏል። "ከለማበት የተጋባበት" እንዲሉ መንግስት ጐረድ-ጐረድ አድርጐ የሰጠንን ኢትዮጵያዊነት ዲያስፖራዎቻችን እየሰለቁና እያደቀቁ በማጥፋት ላይ ይገኛሉ። ቀደም ሲል ሲያትል ውስጥ ሬዲዮና ማዕከል ያለው ጠንካራ የጐንደር ተወላጆች ኮሚኒቲ ነበር። ያኔ የጐንደር ኮሚኒቲ በመቋቋሙ ትልቅ ጭቅጭቅ ተነስቶ ነበር። "ለምን የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አልሆነም?" የሚል ቅሬታ ገንፍሎ የጐንደር ኮሙኒቲን ነቅንቆት ነበር። የያኔ መልሳቸው "አልቻልንም!" የሚል ነበር። "የኢትዮጵያ ኮሚኒቲን ለማቋቋም ሞክረን ቅሬታ ያላቸው መካከላችን እየገቡ ያፈርሱብናል። ስለዚህ በጐንደር ስም አቋቁመን ኢትዮጵያዊ መንፈስ እንዲኖረውና ሌላውም ኢትዮጵያዊ እንዲካተት ወሰንን" አሉ።

ዛሬ የጐንደር ኮሚኒቲ ለኢትዮጵያ በዝቶባት ተከፋፍለዋል አሉ። የሰሜን ጐንደር እና የደቡብ ጐንደር ጐጠኞች፤ በአንድ ቤተ-ክርስቲያን የማያስቀድሱ ጠላታሞች እስከመሆን ደርሰዋል። ስለዚህ የሜሪላንዱ ገብርኤል፤ ከብዙሀን ወደጐንደር፣ ከጐንደር ወደደቡብ ጐንደር ንብረትነት ተሸጋግሯል። ይሄም ሆኖ ቅሬታው አልቆመም። የቤተ-ክርስቲያኒቱን የቦርድ አባልነት ከዘጠና ከመቶ በላይ ደብረ-ታቦሮች መያዛቸው ቅሬታ እያሳደረ ጉምጉምታ ተነስቷል። የዲሲው (ሜሪላንድ) ሚካኤልም በሰሜን ጐንደሮች ቁጥጥር ስር ቢውልም አዚያም ቅሬታ አለ። ‹ጭልጋዎች› በዙ እየተባለ ነው። ሲያትል ሳንሆዜ ደግሞ የአርማጭሆዎች የበላይነት እየተቀነቀነ ይገኛል። የኮሎምቦሱ አህዩ ስላሴን ደግሞ ወልቃይቶች ነግሰውበታል ይባላል...

ወዴት እየወረድን ነው? ዘመንና ዘመነኞች የሰጡን የሀገር ጐረድ-ጐረድ አልበቃ ብሎ ጐጠኝነትን እንደ ዱቄት እየሰፈርን መከፋፈል ዕጣ-ፈንታችን ሊሆን? አንድነት ከተነወረበት ሀገር እርቀን፤ በስደት አንድነትን የምናነውር ከሆነ መጨረሻችን ምንድነው? አንድነትን በምትሰብክ ቤተ-ክርስቲያን ስር መለያየትን ካፀደቅን ተስፋችን የት ናት? ኢህአዴግ እንኳን አዚህ ያላደረገውን "የወረዳ

ፌዴሬሽን"፣ እዚያ ከተገበርን በኋላ ለየትኛዋ ሀገር ነው ኢትዮጵያ ኤምባሲ በር ላይ የምንጮኸው?...

ሚስጢሩ ግልፅ ነው። የዚህ ሁሉ መተራመስ ምንጩ ከሃገር ህልውና ይልቅ ሆድን የማስቀደም የስደተኞች ፖሊሲ ተግባር ላይ መዋሉ ነው። በእግዚአብሔር ስም፣ በቤተ-ክርስቲያን ጥላ ስር፤ ሰው ሁሉ አዛውንት ዘመዱን ባልሰራበት ተጠዋሪ ማድረግ ምኞት አለው። በቅስና ስም ከሀገር ቤት የሚመጣ አዛውንት፤ ያለምንም ችግር የአሜሪካ ቪዛ እና ግሪን ካርድ ያገኛል። ይሄን ካገኘና ዕድሜው ከ65 ዓመት በላይ ከሆነ የማህበራዊ ዋስትና ተደጓሚ (Social security incentive) ይሆናል። በወር 550 ዶላር በጥሬ ገንዘብ፣ የ200 ዶላር የምግብ ድጐማ (በኩፖን)፤ እንዲሁም የነፃ ህክምና ፈቃድ (Medicare) ይኖረዋል። ስለዚህ አብዛኛው ስደተኛ የቤተ-ክርስቲያን ቦርድ አባል በመሆን አዛውንት ዘመዱን የመጥቀም ህልም አለው። እንግዲህ እዚህ መሀል የሀገር ህልውና በወረዳ-ገንጣዮችና አስገንጣዮች እጅ ላይ ይወድቃል። "በወረዳ ፌዴሬሽን" ምክር ቤት ቀርቶ በቤተ-እግዚአብሔር እንኳን በአንድ የማይሰበሰብ ማህበረሰብ እውን ይሆናል። ስደተኛዋ ኢትዮጵያ በወረዳም ተከፋፍላ በቃሽ ካላት ጥሩ ነው። ምናልባትም ነገ በወረዳ ገንጣዮች ላይ ቅሬታ የሚያሳድር የቀበሌ ተቆርቋሪ ያምፅና ቀበሌውን ገንጥሎ ከጭቆና ያላቅቅ ይሆናል። ምናልባትም በቀበሌ ቤተ-ክርስቲያን ቦርድ አባሎች ኢ-ፍትሃዊ አሰራር የሚያምፅ ብሶት የወለደው ስደተኛ፤ የመንደሩን ቤተ-ክርስቲያን ለመንደርተኛው ጥቅም ይቆጣጠረው ይሆናል... ምናልባትም ይሄ የስደተኞች መንፈስ ወደ ሀገር ቤት ገብቶ፤ ኢትዮጵያን ከጐረድ-ጐረድነት ወደ ክትፎ ስጋነት ያወርዳት ይሆናል።

የዚህ ዘመን ስደት እውነተኛ ገፅታ ይሄ ነው። እዚህ ባለው ህዝብና መንግስት ከመበሳጨት ወይም ከመቆጨት በፊት እዚያ ያለውን ነውር መፋቅ ግድ የሚል ይመስለናል። መተዛዘባችንን በየፍታሄ ንጉሴ ግጥም ብንደመድምስ?

> "ሳትከፋፈሉ ባንድነት ሆናችሁ፣
>
> ነውራችሁን ፋቁት ሳይጠፉ ስማችሁ።"

[illegible]

# ጣህሀሬዋ

[illegible]

# "ጎንደር የህልሜ ከተማ ናት"

"ዓይን ማየት ነው የሚያቅ

የብርሃን ዕድሜ አዚሙ እስኪያልቅ ...

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ ዳግም አዘቦን አየኋት

ዙሪያ ቅፅሯን አስተዋልኳት

አጠናኋት አዳመጥኳት ...."

ባለቅኔው ፀጋዬ ገብረመድኅን፤ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ "አዘቦን" ዳግም ሲያያት ተፀፀተባት። "ሰው እንደ አይጥ በየጥሻው ሲጥ ሲል" ያየባት። "መሬቷ እንደ ሞረድ ስለት፤ ጥርሷ ሲፋጭ እንደ ደወል ሰቆቃ እንጂ እኮ ድምፅ አደል!" ያለባት። አዘቦ የአመታት አቀበት ጅስሟን፣ ቅስሟን አስገብሯት፣ ያወጣት ጉልላት ላይ ሆና ፀጋዬ አገኛት። "እሰይ አልኳት" ይላል። እኔስ?

... እኔም ከአስራ አራት ዓመት በኋላ ጎንደርን ሳያት ታጨሁባት። ከእንባዬ ወይም ከፈገግታዬ ላጣቅስባት፤ ከስሜቴ አምስት አውታር አንድም ዘለሰኛ እንደ ላስቲክ ልጎትትባት፤ ወይም ከስሜት ስምንት አውታር እንደ ትዊስት ባለ ቅብጠት ላናጥርባት ታጨሁባት።

ጎንደርን ካየኋት አሥራ አራት አመት ሞላት፤ ቢሆንም ውስጤ፣ ደማቅ ቀለም አላት። አመት እንደ ዓለት ቢነባበርባት የማይቀብራት ከተማ ናት። ሁልጊዜም ከታች ሆኜ ወደ ላይ የማያት ድብርነት አላት። እንደ ብዙ ከተሞች ከፍት አፍ "አሁን" የማይጮህባት፣ ጥንታዊ አስተዋይነት የረበበባት ናት። ሁልጊዜም ... ጎንደር ስሄድ ላለፈው ማንነቴ የአሁን እኔነቴ ይሰግዳል፤ ይገብራል፣ ይጎናበሳል ...

እንዴትስ እንዲህ ላያደርግ ይችላል? የአሁን ማንነቴ ምን ይዟል? ብቻውን የት ደርሷል?

... ጎንደር ሄዶ፣ የፋሲል ግንብን አይቶ፣ በቅድመ አያቶቼ የማይኮራ ማነው? ፋሲለደስ ጎንደርን እስከቆረቆረበት 1623 ዓ.ም ድረስ ያለው ዘመን፤ "ምንም" እንደሆነው ሁሉ ከዚያ ወዲህም ከአፄ ቴዎድሮስ በኋላ እንዲሁ ታላቅነት በኪነ-ህንፃ የመግዘፉ ነገር "ምንም" ይሆናል። ዛሬን የሚወቅሰው ጥንታዊ ግንባታ፣ በፋሲል ቤተ መንግስት ቅርፅ አይወሰንም፤ ወደ ይዘቶቹም ይማትራል። የመታጠቢያ ገንዳው፣ የፋሲለደስ ልጅ (የቀዳማዊ ዮሐንስ) ቤተ - መፃህፍት እና ለቆንስላዎች የተዘጋጁት ቢሮዎች - መኖሪያ ቤት፣ ምሽት ማሳለፊያ መጠለያ ብቻ ለሆነብን ለእኛ መተዛዘቢያዎቻችን ናቸው። አሁን ከአራት መቶ አመት በኋላ እንኳን ቤቶቻችንን ከመዋኛ ገንዳ ጋር ማዳበል ቀርቶ ከመጠለያ ሰቀቀን ያለመገላገላችን ምልክቶች ናቸው። የመኖሪያ ቤት፣ ቢሮና ቤተ - መፃህፍትማ "ከቀበጡ አይዘሉ"ን የሚያስተርት የመሰበር ምልክ ተደርጎ ይታያል።

... ትርፍ ማከል ሲያቅተን "ጥሪያችንን" በላን። መኖራችን ዕዳ፣ በህይወት መገኘታችን ወቀሳ ሆነብን። ያለፈውን ያላስቀመጥን፣ የዘር እህል ያልቆጠብን፣ የ"ባዶ" መተላለፊያ ድልድይ ሆንን። ጎንደር ወቀሳዬ ናት። እዚያ ሄጄ ስመለስ ቀና ማለት ያቅተኛል፤ መንፈሴ ይጎብጣል፤ ነፍሴ በመፃጉነት ትቃትታለች ...

... ዛሬስ?

"ግጥም በመሰንቆ"ዎች ሲጋብዙኝ "ላስብበት" አልኩ። እንደ አቡነ ጴጥሮስ ፅዋ ግብዣው መራር ሆኖ ታየኝ። "አዎ፣ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ" እንዳሉ አቡኑ፤

"እሸሽግበት ጥግ አጣሁ፣

እምፀናበት ልብ አጣሁ" ማለት አሰኘኝ። ግን ደግሞ መሸሸግ መፍትሔ አይደለምና "ይቺ ጽዋ ከእኔ ትለፍ" ለማለት አልደፈርኩም።

"መቼ ነው?"

"የካቲት አራት፣ አርብ ዕለት" አሉኝ።

"ጥሩ፤ አርብ ጠዋት እመጣለሁ፣ ቅዳሜ ጠዋት እመለሳለሁ።"

"ትችላለህ"

ይቺ ናት ስልታዊ ማፈግፈግ። "መጣሁም" "ቀረሁም" ለማለት የሚያመች ውሳኔ:-

በተባለው ቀን የጎንደርን ግጥም በጎንደር መሰንቆ አፈጣጥሜ አደምጣለሁ። ግሩም እንደሚሆን እተማመናለሁ። ኪነ - ህንፃ ባይሆንልንም ኪነ - ጥበብን አስቀጥለን፣ እዚህ መድረስ አላዳገተንም።

በጥንቲቱ ጎንደር፣ በቀዳማዊ ኢያሱ ዘመን "ግጥም በመሰንቆ"ን የመሰለ ልማድ በቤተ መንግስት አካባቢ እንደነበር አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ይገልፃሉ። በዘመኑ ያልተለመደ ስለነበርም ነቀፌታና ውግዘት ይደርስበት የነበረው በአለማዊ አይን ተዳኝቶ ሳይሆን ከቀኖና አንፃር ተገምቶ እንደነበር መጠርጠር አያዳግትንም።

ጎንደር በቀዳማዊ ኢያሱ ዘመን (ከ1675-1699 ዓ.ም) በጥበብ ምሽትነት የማይቀነበብ ምናልባትም "የጥበብ ፌስቲቫል" ሊባል የሚችል ድግስ የማዘጋጀት ልማድ ነበራት። ካህናቱ ከመንፈሳዊው ባሻገር ዓለማዊ ቅኔ የሚያቀርቡበት መድረክ "የፌስቲቫሉ" አንዱ አካል ነበር። መኳንንቱ የእርስ በእርስ የበገና ጨዋታ ፉክክር ያካሂዱ ነበር። የሰንጠረዥና የገበጣ ውድድር በወንድ መኮንንኖችና በሴት ወይዘሮዎች መካከል ይደረግ ነበር።

ይሄንን "የጥበብ ፌስቲቫል" ከአለማዊና ከመንፈሳዊ አንፃር አይቶ መዳኘት ሁለት ፅንፍ ድምዳሜ ላይ እንደሚያደርስ ግልፅ ነው። እንደ እኔ ያለው ዓለማዊ ዘጋቢ፣ ጥበብ በምን ያህል ሁኔታ ማበብ እንደጀመረች አስረግጦ ወጉን ሊያፍታታ ይሞክር ይሆናል። መንፈሳዊው በይበልጥ አክራሪው መንፈሳዊ ግን እንደ አለም ፍፃሜ መዳረሻ እርከን ሊመለከተው ይችላል። ለምሳሌ ከመንፈሳዊ ወገን የሆኑት አለቃ አፅመጊዮርጊስ እንዲህ በማለት ከግሳጼ ጋር ይገልፁታል።

"(በአፄ ኢያሱ) በዚያ ዘመን በዚያ ወራት የቀልድ የቧልት የጨዋታ ዘመን ነበረ ካህናቱ በቅኔ እርስ በርሳቸው ይሳደቡ ነበር፣ መኳንንቱ በበገና ይጫወቱ ነበር፣ ወታደሩ በክራር አዝማሪውም በመሰንቆ ሲያዘምር የሚናገረውን በማድነቅ የወንድ መኮንን፣የሴት ወይዘሮ በሰንጠረዥና በገበጣ፣ ሲጫወቱ ሲያቧልቱ በፍቅር በጋብቻ ተቀላቀሏቸው። በዘመኑ ዝሙት፣ በስካርና ዘፈን እጅግ በዛ። ጎንደር ያለልክ ሰማች፣ ገረረች።"

በዚህ ዘመን አንድ መንፈሳዊ ሰው፤ "ግጥም በመሰንቆ"ን ቢጋበዝ ሊሰጥ የሚችለውን አስተያየት ተንተርሶ ከአራት መቶ ዓመት በፊት የነበረውን መገመት ይበቃል። አለቃ አፅሜ የጎንደር በጥበብ መላቅ ለእሳቸው አልታያቸውም። ቅኔን ወደ አለማዊ ጉዳይ አውርዶ የእለት ተዕለት ህይወት ማስተንተኛ ማድረጉ ጎፍንኗቸዋል።

ምናልባትም ይሄ "የጥበብ ፌስቲቫል" በጎንደር እንዳይቀጥልና እንዲዳፈን የመደረጉ ውሳኔ ላይ የእንዲህ ያሉ ሰዎች አስተያየት ትልቁን ድርሻ ሳይወስድ አይቀርም። ያኔ "የጥበብ ፌስቲቫሉ" ቀጥሎ ተስፋፍቶና ተንሰራፍቶ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በሙዚቃ፣ በስፖርት፣ በግጥም፣ በልቦለድ፣ በሥነ ስዕል ... የት እንስፈነጠር ነበር? ...

አንዳንድ ጊዜ ታዲያ በዚያ የጥበብ ድግስ ላይ የነበርኩ፣ የነበርኩ ይሰማኛል። ነገሩ እንደማይታመን ይገባኛል፤ ግን ምክንያቴን ልግለፅ።

"አንዳንድ በህይወታችን የሚያጋጥመን አስገራሚ ነገር አለ። ለሰው ብንነግረው አያምነንም። ልቦለድ አስመስለን ብንናገረው ደግሞ "ኢ-ተአማኒ ነው አይታመንም" ይላል። ፈጣሪ ግን አያልቅበትምና ኢ-ተአማኒ የምንለውን እሱ በህይወታችን እንዲደርስ አድርጎ ያሳየናል።"

ይሄን ያለው ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ነው። "መይሳው ካሳን ፍለጋ" በተሰኘ መጣጥፉ መግቢያ ላይ። እውነትነት አለው፤ የህይወት ምስጢርነት ከሰው ልጅ አምክኑያዊ መረዳት በላይ የሚሆንበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። በሌላ ሰው ቀርቶ በራሳችን ላይ የደረሰን ትንግርታዊ ሁነት ፍቺ ስለምናጣለት ለታዛቢ መንገር ይቅርና እራሳችን አምነን ለመቀበል ሲያዳግተን ያታያል። ስብሐት እንዳለው "ፈጣሪ ግን አያልቅበትምና ኢ-ተአማኒ የምንለውን እሱ በህይወታችን እንዲደርስ አድርጎ ያሳየናል"

በእኔ ህይወት የደረሰውን (ባታምኑትም) ልንገራችሁ ... ከአስራ ሁለት ወይም ከአሥራ ሦስት ዓመቴ ጀምሮ አንድ አስጨናቂ ህልም በተደጋጋሚ አይ ነበር። ህልሙ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ይጎበኘኛል። ከህልሙ ላይ የሚቀነስ ወይም የሚጨመር አንዳች ነገር አልነበረም። ህልሙን እንዳደኩበት መንደር አጥርቼ አውቀዋለሁ። ሂደቱ ስለማይዛነፍ ቀጥሎ የሚሆነውን አውቀዋለሁ። ህልሙ በውሃ ድምፅ የታጀበ ነው። ውሃው ሰው ሰራሽ ፏፏቴ ሆኖ የፏፏቴውን ግራና ቀኝ ይዘው የተገነቡ መንትያ ደረጃዎች አሉ። ደረጃዎቹ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ያለውን

ስባ ደረጃ ይመስላሉ። እኔ የሚያሳድደኝን ሳላውቅ በፍርሃት የድንጋይ መወጣጫዎቹን እንደ እባብ በደረቴ እየተሳብኩ ለመውጣት እጣጣራለሁ። አይሆንልኝም። ደረጃዎቹ አልጌ እንደጠገቡ ሁሉ እያሚለጩ ይከዱኛል። እፍጨረጨራለሁ የፏፏቴው ውኃ እየተፈነጣጠረ በድምፁና በጤዛው ያጅቡኛል። ... ይሄንን ህልም ቢያንስ ለሃያ ዓመታት አይቼዋለሁ። በሣምንት አንዴ እንዳየሁት ቢሰላ እንኳን ከአንድ ሺህ ሰማኒያ ጊዜ በላይ ተመላልሼበታለሁ። ፈጣሪ ካላጣው ህልም ስለምን በህልም ድግግሞሽ ያሰከረኛል? ስል ጠይቄአሁ። ፍቺ ለማግኘትም ደከሜያለሁ። ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ያሉትን የድንጋይ ደረጃዎች መርምሬአለሁ። አንዳቸውም ከህልሜ መወጣጫዎች ጋር አልገጠሙልኝም። ምንድነው? ለምንድነው? ፍቺ አለው? ... ምንም!

ጋዜጠኛ ሆኜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወለድኩበትን አዲስ አበባ አልፌ የተለያዩ አካባቢዎች መሄድ ጀመርኩ። ድሬደዋ፣ ጋምቤላ፣ ሰመራ፣ አዋሳ፣ ዲላ፣ ደሴ፣ ባህርዳር፣ ጎንደር። ህልሜን ጎንደር አገኘሁት። አገር ለማየት ስዘዋወር ፒያሣ አካባቢ ከሃያ ዓመታት በላይ እየደጋገምኩ የዳሁበትን መንታ የድንጋይ መወጣጫና ፏፏቴ እዚያ አገኘሁት። ድንጋጤ ምንድነው? ከተወለድኩ አንስቶ ከአዲስ አበባ ወጥቼ አላውቅም። የድንጋይ ላይ ጌጡን፣ የፏፏቴ ቁመናውን ሁሉ አጥርቼ የማየው ይሄ ህልሜ እንዴት ውስጤ ገባ? አሁንም ምስጢር ነው። የሚገርመው ደግሞ ያንን የጎንደር መንትያ ደረጃ ካየሁ በኋላ ህልሜ፣ ለአንዴ እንኳን ብቅ ሳይል መጥፋቱ ነው። ህልሜ ተልዕኮውን ፈፀመ? ወይስ ምን? ...

... ባለፈው ሰሞን ወደ ጎንደር ሄጄ እዚያ የህልሜ ስገነት ፊት ቆምኩ። ከበስተኋላዩ አዲሱ የአፄ ቴዎድሮስ ሀውልትና ቋራ ሆቴል አሉ። ፊት ለፊቴ ሁለቱ መወጣጫ የድንጋይ ደረጃዎች መካከላቸው ላይ መናፈሻ ተገንብቷል። ጋሽ አበራ ሞላ ነው አሉ እንዲህ ያደረገው። መናፈሻው “ሰማዕታት” ተብሏል። የህልሜ አንዱ አካል ፏፏቴው ተነስቷል።

ጎንደር የህልሜ ከተማ ናት፤ ምናልባትም ከልደት በፊት-በፊት የማውቃት፤ ለአንዱ ጀግና አድሬ የተዘዋወርኩባት፣ ወይም በክፋት ያስጨነኩባት ... ከመረገዜ በፊት የሞትኩባት፤ ከመወለዴ አስቀድሞ አፈር የቀመስኩባት። የእኔ የልጅ ልጆች እዚያ አሉ፣ አሁን ጓደኞቼ የሚሆኑ፣ የያኔውን ፎቶዬን ሙጥኝ፣ ያሉ። ቀብሬን የሚጎበኙ ... ነፍሴ የገባት አንዳች ነገር አለ፤ ለሰው ቢያወሩት እንግዳ የሆነ። ሥጋዬ የተኛ ነው፤ ነፍሴ ቢጓጉጠው - ቢጓጉጠው ሩሁን ያላገኘው። አሁን ይሄ ለሰው የሚነገር

ነው? ያውም ቁስ ለናጠጠበት ለዚህ ዘመን ሰው? ... እንደ ስብሐት "አንዳንድ በህይወታችን የሚያጋጥመን አስገራሚ ነገር አለ" ብለን እንቀጥል ...

ከክርስቶስ ልደት 570 ዓመታት በፊት የኖረው ፒታጎራስ (Pythagoras) ነፍስን በጊዜአዊ አካል ውስጥ የምትኖር ሕያውት አድርጎ የሚመለከትበት እምነት ነበረው። ነፍስ አንዱን የዘር ሐረግ ለቅቃ ሌላውን እየተንጠላጠለች ... አንዱ ጊዜአዊ ቤት (አካል) ሲፈርስ፣ ሌላ አዲስ ቤት ውስጥ እየገባች ዘላለማዊነቷን ትቀጥላለች ይላል። "የሥጋ ቤት" መልቀቁና መከራየቱ በሰውና በእንስሳት መካከል ለመከናወን የሚያግደው ነገር እንደሌለ ይሄው የጥንት ፈላስፋ ያስተምራል። በቀለ ተገኝ መኮንን "የምዕራባውያን ፍልስፍናና ሥልጣኔ ታሪክ (፩)" በተሰኘ መፅሐፋቸው ስለ ፒታጎራስ እምነት እንዲህ ይላሉ፡-

"... ፒታጎራስ ለማስጨበጥ የሞከረው እምነት ይህን መሳይ ነበረ፡- ከሁሉ አስቀድሞ ነፍስ ለዘለዓለም ኢመዋቲት (ሕያውት) ነገር መሆንዋንና ከአንድ አይነት ፍጥረት ወደ ሌላ እንደምትጋባ፣ ከዚሁም ተያይዞ ማንኛውም ሕያው ፍጥረት መተካኪያ ጊዜውን እየጠበቀ እንደገና በመውለድ ከህልውና ህልውና ሲሸጋገር ይኖራል እንጂ ፈፅሞ ሌላ አዲስ ነገር እንደማይመጣ፤ ማንኛውም ህያው ፍጥረት ሁሉ ከሌላው ጋር እንደ ቤተ ዘመድ - ወይም እንደ አንድ አምሳልና አካል መተያየት እንደአለበት ማወቅ ያስፈልጋል። በዚህ አይነቱ የተነሣ ፒታጎራስ ቅዱስ ፍራንሲስ ዘአሲስ ያደርግ እንደነበረው ዐይነት በእንስሳቱ መሀል በየጊዜው እየተገኘ መንፈሣዊ ቃሉን ያሰማቸው ነበር ይላል።"

ይሄን የነፍስ ከሥጋ ወደ ሥጋ መንጦልጦል ሕንዶች "ሳም ሳራ" (Samsara) ሲሉት ምዕራባውያን ደግሞ ሜተምሳይኮስስ (metempsychosis) ወይም ዳግም ልደት (reincarnation) በሚል ሰይመውታል። በዚህ አዙሪት የተጠመደችው ነፍስ፣ አልፎ አልፎ በትውስታ ካለፈ ህይወቷ የምትጎትታቸው ሁነቶች እንዳሉ እነ ፒታጎራስ ይናገራሉ።

እናስ?

... የፒያሣው መንትያ የድንጋይ መወጣጫ፣ ያለፈው ሕይወቴ ቃርሚያ ትዝታ ይሆን? ከሆነስ ያንን ደረጃ ብቻ ምን ሙጥኝ አሰኘኝ? ... የልሜን አጋዥ የትውስታ ፍርፋሪ ባገኝ ብዬ ከተማዋን ለማሰስ ተነሳሁ።

አጠገቤ የ"ትንሳኤ ናፋቂዎች" ደራሲ ተስፋ በላይነህ አለ። የጎንደር ልጅ ነው። ከአርበኞች አደባባይ ጀርባ "ከቡልኮ" ተነስተን በቀድሞ ልዕልት ተናኘወርቅ፣ በአሁኑ ህብረት ትምህርት ቤት በኩል ቁልቁል ወረድን። ከፎገራ ሆቴል በስተግራ የአንገረብ ወንዝን ታከከን ወደ ደብረ ብርሃን ሥላሴ አቀናን። የነፍሴን ትውስታ የሚያግዝ አንዳች ነገር አላገኘሁም። ደብሩ ጥንታዊ አሰራሩ ያስደምማል። ቅፅሩ በምስጢራዊ የዋርዲያ ማማ የተከበበ ነው። መወጣጫው የድንጋይ ሆኖ ከሩቅ ለመቃኘት እንዲያስችል ከፍ ተደርጎ ተገንብቷል። ያንን ነፍሴ አላወቀችውም። ከቅፅሩ ወደ ቤተክርስቲያኑ ማተርኩ። በጥንታዊ ስዕላት አሸብርቋል። ቅድስት ድንግል ማሪያም የአንገት ላይ የንቅሳት ውቅሯ እንዳማረ ሆኖ፣ ፊት ለፊት ትታያለች።

ነፍሴን ፈተሽኩ፣ ሽራፊ ትውስታ አጣሁ። የተመለስነው በባጃጅ ነው። ጎንደር በባጃጅ "ዝንብ" ተወርራለች። ጥዝዝዝዝ ... የሚሉት የመሬት ለመሬት ዝንቦች የጎንደርን ግርማ ይፃረራሉ።

እንደተግለብላቢ መጤ ከተማ ሞተር በተገጠመለት ዝንብ መወረሯ ያስቆጫል። ጎንደር ጭራ ያሻታል። ጥዝዝዝ - ጧ! በምትኩ ቁመናው ባማረ ፈረስ የሚጎተት ሰረገላ ይበዛላታል። ጎንደር የጥሞና ከተማ ናት። ተንጦዝጧዥ ነገር ሁሉ ይፃረራታል።

ነፍሱን ይማርና ፋሲል ሆቴል የነበረበት ጋ ስንደርስ ከባጃጅ ወረድን። "ላቭ ስትሪት" መጤ ድርጊያና ቃሉን ከጥንታዊው "ቁብ አስጥል" ጋር በጉራማይሌ አዋህዶ አየነው። የራስ ሚካኤል ስሁልን ህንፃ ቃኝተን በ"ሰማዕታት" መናፈሻ አናት ብቅ አልን።

በህልሜ ሃያ ዓመት የዳህኩበትን የድንጋይ ደረጃ በእግሬ ቁልቁል ወረድኩበት። ምን አዛመደን? ምን አገናኘን? ምን አቀራራኘን? ... "ፈጣሪ ግን አያልቅበትም"ና ኢ-ተአማኒ የምንለውን እሱ በህይወታችን እንዲደርስ አድርጎ ያሳየናል" ከማለት ውጭ ምን መተማመኛ አለን?

# የህይወት ጀንበር ፤ በፀሐይ መጥለቂያዋ ሀገር

በውልብታ መሰል ዕይታ እንተዋወቃለን። የእሷን እንጃ እንጂ የእኔ የውልብታ ወለምታ ለአመታት አብሮኝ አለ። ለነገሩ ከተማ - ከተማ ናት። እንኳን ለተሸጋጋሪው፣ ለዕድሜ ገባሪውም መመዝገቢያ ልቡና የላት። ሐውልት ብታቆምላት፣ መታሰቢያ ብታኖርላት፣ ትውስታ ብትሰፍርላት... ከልቡናዋ መኖሩን እንጃላት...

...በውልብታ መሰል ዕይታ የሞሸርኳት ጋምቤላ ናት። አይኔ ሀይቅ ሆኖ ያስመጣት፣ ልቡናዬ ጥሪት አድርጐ የቋጠራት... የአሥራ አምስት አመት ቀለቤ ናት። በፊት፣ ገና በፊት ልጅ ሳለሁ ሰሜኖች ከደቡብ ሱዳን እስኪወጡ ኙዌሮች መንደሬ ድረስ መጡ። እነ ሚስተር ሄኖክ፣ አንቶኒ፣ አኬሎ፣ ኡጁሉ...የሚባሉ። አንድ ሰሞን ይጠፋሉ፤ ደግሞ ለደቡብ ሱዳን ተዋግተው ነው ተብሎ ይመጣሉ። ሲያሻቸው ሱዳን፣ ካልሆነም ኢትዮጵያዊ ይሆናሉ እየተባሉ ይታማሉ። ለእነሱ አዲስ አበባ አንድ መላ ሳይኖራት አልቀረም እያልኩ አስባለሁ። ብዙ መከራ ማቅጠኘያ ጥቂት ደስታ የሚሸምቱባት ቦታ ናት። መጠጥ፣ ጭፈራ፣ ሴት... መጠጥ፣ ጭፈራ፣ ሴት... ከዚያ ጦርነት።

ሕይወት ለእነዚያ ታጋዮች በእነዚህ ምሕዋር ላይ የምትሽከረከር ናት።

ወደ ጋምቤላ ስሄድ በኙዌርኛ ሠላምታ ሲያቀርቡልኝ ድንግርም አላለኝ።

"ማለ"

"ማለ"

"ማለ ሙጋ"

"ማለ ቾምቾም"

ያኔ፤ አገራችን ከሻዕቢያ ጋር ጦርነት ላይ ስለነበረች ጋምቤላ አውሮፕላን ማረፊያ ለመድረስ አስር ደቂቃ ሲቀረን መስኮቶቻችንን እንድንዘጋ ተጠይቀን ነበር። እንኳን ለገና ገና የአየር ላይ ጉዞ፤ መሬት የተቆናጠጠ ቤት መስኮት ሲዘጋ እንዴት እንደሚጨንቅ አስቡት። ማረፊያችንን በመንገሚገጭ አውቀን ወረድን። አውሮፕላን ማረፊያው ከጋምቤላ ከተማ አስራ ስድስት ኪሎ ሜትር ይርቃል። የሚገርመው ምንም አይነት የትራንስፖርት አቅርቦት አለመኖሩ ነበር። ጥቂት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ሰው ለመውሰድ ሲመጡ ሌሎቹንም መንገደኞች አጭቀው ይመለሳሉ።

የያኔዋ ጋምቤላ ከተማዋም፣ ትራንስፖርት የላትም። ታክሲ፣ ባጃጅ፣ አውቶቡስ፣ ሎንቺና...ምንም አልነበራት። አንዳንድ የመንግሥት መኪኖች የኋላ እግራቸው እንደተሰነከለ ውሻ ዝልል፣ ዝልል እያሉ ያልፋሉ። መንገዱ እንደ ገበጣ መጫወቻ በጉድጓድ የተሞላ ነበረአ! በዚያ በተቅለጠለጠ ሙቀት፣ መሣፈሪያ ማጣት፣ ለደጋ ሰውነት እንዴት?... ግራ ተጋብቼ ነበር። ብቸኛው የኪራይ ተሽከርካሪ ብስክሌት ነበር።

አልጋ "ፓርክ ሆቴል" ያዝኩ። ቀጫጭን የበረሃ ዛፎች በርብራብ ላይ ተሰድረው ዳስ የሆኑበት ሰፊ ክፍት ቦታ አለው። ዳሱ ከፀሐይ ቀጥተኛ ጥቃት እንጂ ከወበቁ አይከላከልም። የውኃ ጥያቄ ለአፍታም አይገታም። እየጠጡ ይጠማሉ፣ ሆድ በውኃ ተቆዝሮ እርካታ ይሰንፋል - ምን ይባላል?

"ሻይ ወይም ቢራ ጠጣ" አለኝ የታዘበኝ።

እውነትም ተሻለኝ።

ጋምቤላ ላይ ሌላ የገረመኝ የጠለስ ዝናብ ጉዳይ ነበር። ከወደ ሰማይ ወረቀት ተቃጥሎ ሲያልቅ የሚቀረውን የመሰለ ጠለስ ይወርዳል። ሸሚዝ ላይ ሲያርፍ ከላብ እርጥበት ጋር ተዋህዶ ጥላሸት ይሆናል። ለሁለት ቀን ሚስጥሩ አልገባኝም ነበር። አንድ አመሻሽ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ሆቴል እየሄድኩ ሳለ፣ አሥር እርምጃ ያህል እግራችን አንድ ላይ የተራመደብንን ልጅ ጠየኩ።

"ይሄ ምንድነው?"

ልጅቷ ፈገግ ብላ አየችኝና "የደጋ ሰው ነህ?" አለችኝ።

"አዎ" አልኳት

"ይኸውልህ፤ ከከተማው ውጭ ረጃጅም የበረሃ ሣሮች አሉ። በሰደድ እሳት ሲቃጠሉ ወደ ሰማይ ይወጡና ከተማው ላይ ይወርዳሉ።"

ልጅቷን ልብ ብዬ አየኋት። ፀጉሯ ዞማ ነው፤ መልኳ ለጥቁረት የሚያደላ ጠይምነት አለው። አይኖቿና ጥርሶቿ ሣጫ - በረዶ የመሰሉ ናቸው። "አንቺ የጋምቤላ ልጅ ነሽ?" ስል ጠየኳት። በጭንቅላቷ "አዎ" አለችኝ። አፍንጫዋንና አይኖቿን የጨቆነ ወፍራም ጉንጭ አላት።

"አንተስ?"

"አዲስ አበባ"

"እዚያ አከስት አለኝ፤ በአመት፣ በአመት እመጣለሁ"

ምን ይባላል? ዝም! ጥቂት ተራመድን። ድልድዩን አልፈን ወደ ኢትዮጵያ ሆቴል አንድ ላይ ታጠፈን።

"ተማሪ ነሽ?" (ቢገባኝም)

"አዎ"

"ሰፈርሽ እዚህ ነው?" (ቢገባኝም)

"አዎ"

ይቺ ናት ጨዋታ መጥፋት።

"እኔ አለማየሁ እባላለሁ፤ ጋዜጠኛ ነኝ።"

"ኙዋል እባላለሁ"፤ ኙዋል ሳይመን"

"የምን ሥም ነው?ማለቴ..."

"የኑዌር ነው። አባቴ ኑዌር ነው። እናቴ የትግራይ ሴት ናት"

"ኑዌርኛ ትችያለሽ?"

"አዎ"

"ትግርኛም?"

"አዎ"

"አማርኛ በደንብ! ታድለሽ?"

ሽኩርምሚታም ሣቅ አስተናገደች። ኢትዮጵያ ሆቴል ስለደረስን ለመሰናበት ቆም አለች። ሰውነቷም እንደ ጉንጮቿ ሞላ ያለ ነው።

"እንኳን ተዋወቅን" አልኳት።

"እሺ" አለችኝ።

"እሺ አይባልም፤"

"ታዲያ?"

"እንኳን ለመተዋወቅ በቃን ነዋ"

"እሺ እንደሱ፣ በቃ ልሂድ..."

"ሁልጊዜ እዛች ዛፍ ሥር እቀመጣለሁ፤ ስታልፊ ሰላም በይኝ" አልኳት።

"እሺ ቻው"

"ቻው"

እራሴን ከኢትዮጵያ ሆቴል ጋር ማቆራኘቴ የታወቀኝ ቆይቶ ነው። ቁርስ እዚያ እበላለሁ፤ ለምሳ እሄዳለሁ፤ ከአራት ሰዓት ቀደም ብዬ ቦታው ላይ እገኛለሁ። ኘዋል ሦስት ቀን ዝር አላለችም። ሆን ብላ የምገኝበትን ሥፍራ ሸሸታዋለች። የቀኑን ጥበታ የማበቃው በአብሪ ነፍሳት ሲታጀብ ነው። በጨለማው ውስጥ እንደገና አምፑል ብልጭ ድርግም እያሉ ሲጓዙ አቅጣጫቸውን ለመለየት በአይኔ እከተላቸዋለሁ። በቅፅኝ ወደ ፓርከ ሆቴል ሳመራም በእነዚሁ ነፍሳት ታጅቤ ነው። አይን ያጫውታሉ። ብልጭ ብላ የያዘችውን አቅጣጫ ጠፍታ ትቀይረዋለች። ቀኝ፣ ግራ እያሰቡ እስከትበራ መጠበቅ፣ አነሁላይ ጨዋታ ነው።

በሦስተኛው ቀን ለዘገባ የማመራው ወደ ጋምቤላ ትምህርት ቢሮ ነበር። የጋምቤላ መምህራን አንድ ያቋቋሙት ማህበር አለ። ከሌላ አካባቢ የሚመጡ ዘመድ አልባ ተማሪዎችን ማህበሩ ከአባላት በሚዋጣ ገንዘብ እየረዳ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል። የአባላቱን ቃለ መጠይቅ እንደጨረስኩ ወደ ከተማው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሄድኩ። ተረጂ ተማሪዎችን ፍለጋ ነበር። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ለአረፍት ተደውሎ አንድ ሁለት ተማሪዎች እንዳነጋገርኩ

ከሩቅ ኘዋልን አየኋት። አሷም አይታኛለች። አፍራ ትደበቃለች ስል ያለማንገራገር ወደ እኔ መጣች።

"እንኳን ለመተዋወቅ በቃን" አለችኝ

"እንደሱ አይባልም" አልኳት

"እህስ?" አለች

"እንኳን ዳግም ለመገናኘት በቃን"

"እሺ እንደሱ"

"ለምን ጠፋሽ? ስጠብቅሽ..."

"ለምን ጠበከኝ?"

"እንድናወራ"

"ኢትዮጵያ ሆቴል አይሆንም። እዚያ ቤቴ አለ" አለች።

"ታዲያ የት?"

"ፓርክ ሆቴል ግቢ ውስጥ ይሻላል"

"ጥሩ፣ አልጋ የያዝኩት እዚያ ነው" ካልኩ በኋላ ቆጨኝ። ሌላ ነገር ይመስላት ይሆን?

"አልጋ ውስጥ አይደለም፤ ውጭ ነው"

"እሺ" አባባሏ አሳቀኝ።

እውነትም አመሻሽ ላይ መጣች። የበረንዳው ደፍ ላይ ተቀምጠን ያዘዝችውን ለስላሳ መካከላችን አኑረን አወራን። አስተዋይ ናት። ለእንግዳ ሰው የሚሆን ገለፃ አላት። የጋምቤላን ጠለስ ተከትላ ስለ ሣር ቃጠሎው አወራችኝ።

"ሣሩ በሰደድ እሣት ሲቃጠል እዚያ የተሸሸጉት ነፍሳት ሁሉ ወደ ጥርጊያው መንገድ ይወጣሉ። አባብ፣ እንሽላሊት፣ አይጥ... ብዙ። አሞራዎች ደግሞ ከጥርጊያው ላይ እየጠለፉ ይዘዋቸው ይከንፋሉ። አየር ላይ ለመነጣጠቅ እርስ በእርስ ይጣላሉ። አንዱ የለቀቀውን ሌላው ይቀልበዋል። ሁኔታው የሚያስፈራ

ቢሆንም ግን ደስ ይላል። አባቴን እዚያ ይዞኝ እንዲሄድ እለምነውና ሲወስደኝ ወዲያው እንመለስ እለዋለሁ።"

"ለምን?"

"ያስፈራል፤ ግን ህይወት ነው አይደል?..."

ብቀጥል ውስጤ የማይበርድ ሐዘን ለመቀስቀስ የምትሰንፍ ልጅ አይደለችምና ፈርቼ ተውኩት። ግን አልቀረም። በራሷ ህይወት በኩል መጣች።

"እናትህና አባትህ በፍቅር አንድ መሆናቸውን የበለጠ የሚያረጋግጡት አንተን ሲወልዱ ነው። ግን..."

"ግን ምን?"

"ለእናትህና ለአባትህ ዘመዶች ግማሽ ዘመድ ነህ፤ ሁለቱም ዘመዶች ልጆቻቸው የራሳቸውን እንዲያገቡላቸው ስለሚፈልጉ ከሌላ ጋር በመሆናቸው ይናደዳሉ። ሲወልዱ ደግሞ በቃ በአንተ ምክንያት ተቆራርጠው እንደቀሩ ያስባሉና አይወዱህም፤ አይጠሉህም። ዘመድ ነህ፤ አይደለህም ለማለት ይቸገራሉ። እንዴት ያምማል መሰለህ"፤

ለሰሚው ለእኔም ያምማል...

...የጋምቤላ ጀንበር አለላ በመሰለ ቀለም ታጅባ ወደ ማደሪያዋ አዘቅዝቃለች። ጋምቤላ የኢትዮጵያ ጀንበር መሰዊያ የአምልኮ ምኩራብ ነች። እንግዲህ ሲጨላልም ምዕራባዊት ኮከብ ትወጣለች። ለጊዜው አካባቢው እሣት ከብቦ የመጨፈር ስሜት ፈጥሯል። ኝዋል ውስጧ ያለውን ሀዘን እያመናታለች ነው። እኔ ሀዘን በመፍራት እየሸሸሁ እንደሆን ታውቆኛል። የሰው ልጅ ይሄው ነው። ለደስታ የሚተጋውን ያህል ለሀዘን መካፈል ዳተኝነት አለበት፤ ፀፀት---

"ግማሽ ዘመድ ስትይ አልገባኝም" አልኩ ከፀፀት ሽሽት ወደ ሀዘኗ ዘልዬ ለመግባት።

"የአባቴ ወላጆች ከኙዌር ወገን የሆነች ሴት እንዲያገባላቸው ይፈልጉ ነበር፤አባቴ ግን እናቴን ከትግራይ ወደደ። በዚህ ቅሬታ አደረባቸው። ወጣትነቱ ገፋፍቶት ነው ብለው ጊዜ ሲጠብቁ እኔ ተረገዝኩ። ልጃቸውን እንደነጠኳቸው ቆጠሩት፤ የእናቴም ወላጆች ጋ እንደዚያው አይነት ስሜት አለ። እኔ በመሀል ቤት በእናቴም በአባቴም ወገኖች የማልፈለግ ሆንኩ።"

ያልቀመሰችው ሚሪንዳ ከአካባቢው በወረሰው ብርሃን ወደ ቀላት አዘንብሏል። እያወራን ያለነው ስለአለመፈለግ ነው። በገዛ ዘመዶች፣ በገዛ ሥጋዎች ስለአለመፈለግ። አቀረቀርኩ። ነጠላ ጫማ የሚያዘወትሩ እግሮቿ፣ የሸፍን ጫማ ቅጣት እንዳልደረሰባቸው ያስታውቃሉ። ከፍትፍት ያሉ ጣቶች፣ ወዛምና ለስላሳ ቆዳ ተለብጠው ደርበብ ባለ ቀለም የአፍላነት መስካሪዎች ሆነው ቀርበዋል።

“ልጅ ሆኜ አንድ ነገር እመኝ ነበር”

“ምን?”

“ለነገሩ አሁንም እመኘዋለሁ። የሆነ የተረት ሰው፤ ምንጣፍ በአየር ላይ እያበረረ የሚሄድ፤ ወይም መጥረጊያ ተሳፍሮ የሚከንፍ፣ ከእናቴም ከአባቴም ወገኖች ያልሆነ፤ ትውልዴን የማያውቅ፣ ማን እንደሆንኩ የማይጠይቅ፤ እንዲሁ አይቶ የራራልኝ፤ እንዲሁ የወደደኝ፤ የወላጆቼ ትውልድ ወዳልሆኑ ሰዎች ይዞኝ እንዲሄድ፤ ብርርር በቃ። አዲስ ቋንቋ፣ አዲስ ባህል፣ አዲስ ቦታ፣ አዲስ...”

ቀና ብዬ አየኋት፤ ማንነቷን የመሸሽ ፍላጐቷ ይሄን ተረት እንዳስመኛት ገብቶኛል። ዘመዶቿ የገፈታተሩት ማንነቷን ወዴት ትሸሽዋለች? ምዕራባዊት ኮከብ ዕጣ ፈንታዋ፣ ከምዕራብ ሰማይ ፈቀቅ ይላል? ይሄን እያሰብኩ ድንገት ቡልቅ ያለች የሳቅ ሽራፊ ከወደ ኘዋል መጣች።

“ምነው?” አልኳት

“ጅል ነኝ? በደንብ ሳንተዋወቅ እውነቴንም፣ ህልሜንም ዘከዘኩ። ከማንም ጋር እንደዚህ አውርቼ አላውቅም።”

“ምኑ ነው ስህተቱ?”

“ላንተ እንጂ ለእኔማ ጥሩ ነው። እዚህ አትኖር፣ እንደ ንፋስ ዝም ብዬ ነገርኩህ፤ ዝም ብለህ የነገርኩህን ይዘህ ትሄዳለህ አይደል?”

ያኔ ኘዋል ዝም ብላ የነገረችኝ መስሎኝ ነበር። ግን ቆይቼ ሳስበው ዝም ብላ አልነገረችኝም። ያ የተረት ጀግናዋ፣ ያ በሚበር ምንጣፍ ሆነ መጥረጊያ ይዟት የሚጠፋው ምናባዊ ገፀባህሪዋ የተገኘ ሳይመስላት አልቀረም። ያኔ ግን ልቧን ሳይሆን ቃሏን ሰማሁ። የነፋስ አምሳያ ንሰሃ አባት ተደርጌ መቆጠሬን አጐላሁ። ለእሷ እኔ “እኔ” አይደለሁም ማለት ነው? ነፋስ? ተባራሪ ሃሳብ አቆሰለኝ።

“ልሂድ” አለችኝ

“ጥሩ” አልኳት።

አንድ ነገር እንድል ሳትጠብቅ አልቀረችም። በጋምቤላ ጀንበር ታከኬ ፊቷን አየሁት። ለወትሮው የበአልነት ስሜት ያሳድር የነበረው ቅላት፣አሁን ንዴት የቋጠረ ፍም እባጭ መሰለ። ምን አናደዳት? በፍጥነት ተነስታ ሄደች፣ እኔና ያልተነካው ለስላሳዋ ቀረን።

ካወራችልኝ ይልቅ የሆነችልኝ አንዳች መልዕክት ያለው መሰለኝ። በቀጣዩ ቀን አዚያው ፓርክ ሆቴል በረንዳ ላይ ሆኜ ነፍሴን በቢራ እያለዘብኩ ጠበኳት። ምዕራባዊት ኮከብ የለችም። ነገ ማለዳ ወደ አቦቦ እሄዳለሁ፤ ለሦስት ቀንም አቆያለሁ። መሄዴን ነግሬአት የሚያድርባትን ስሜት መረዳት አሻኝ። ግን ሳትመጣ ቀረች። ነፋሷ ወሬዋን ይዞ እንደሄደ ቆጠረችው። ነፋስ፣ እራሱ፣ ያወራንለት ነፋስ መቼ፣ እንዴት ተመልሶ ይመጣል?

ወደ አቦቦ የምሄደው ከጋምቤላ ምክር ቤት መኪና ተመድቦልኝ ነው። እሩቅ ስለመሰለኝ በሌሊት መነሳት ዕቅዴ ነበር። ግን ሾፌሩ ከሦስት ሰዓት በኋላ መጣ። ለካ አቦቦ ከጋምቤላ ከተማ የምትርቀው አርባ ኪሎ ሜትር ብቻ ነው። ከተማዋን እንደለቀቅን ኙዋልን የሚያስታውስ ትዕይንት ፊቴ ላይ ተደቀነ። ከሦስት ሜትር በላይ ቁመት ያለው የበረሃ ሣር ተቀጣጥሎ ይግለበለባል። ብዙ አሞሮች ጥርጊያው መንገድ ላይ ዝቅ ብለው ያንዣብባሉ። እሣት የፈሩ ነፍሳት፣ እራሳቸውን ለአሞራ አሳልፈው ይሰጣሉ። አንዳንድ ጊዜ ህይወት እንዲሁ ናት። ከሁለት ሞት አንዱን በአማራጭነት ታቀርባለች። ተቃጥሎ ወይም ተበልቶ ማለፍ።

አንጡራው የጋምቤላ ልጅ በሚያጥበረብረው ፀሐይ ስር ቆዳው እያብረቀረቀ ሲሄድ አየዋለሁ። ደግሞ ጐጀው ውልብ ይላል። መሬት ውስጥ በተቀበረው ሙቀጫ በቆሎ ሲወቀጥ፣ በግልድም የታዘለ የኙዌር ልጅ ----- እዚህ እንግሊዞች ፈጥነው ያልጣሉት ኢትዮጵያዊነት እንዳለ አውቃለሁ። ተስፋሚካኤል ተኩአ የፃፉት ግለታሪካቸው ላይ ያገኘሁትን አንድ ታሪክ አጫውታችሁ ልለፍ።

እንግሊዝ ሱዳንን ስታስተዳድር ነው። ጋምቤላን በዜጐቿ ታስለላለች። ለዚሁ ተልዕኮ ወደ ጋምቤላ የዘለቀ አንድ እንግሊዛዊ ወደ አካባቢው ባላባት ሄደ አሉ።

"ምንድነው?" ሲለው

"አንበሳ ለማደን ነው የመጣሁት። ከኢትዮጵያ መንግሥት የማደን ፍቃድ አግኝቻለሁ?" የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊርማና ማህተም ያለበት ፈቃድ አቀረበ።

"ታዲያ" አለው አኝዋኩ

"ታዲያማ ደመወዝ የምሰጣቸው ሰዎች እንዲያጋድሉኝ ስጠኝ"

እንግሊዛዊው የተደነቀበትን ጉዳይ ሲገልፅ እንዲህ ይላል፡- "ልብስ የሌለው፣ ፊደል የማያውቅ የኑዌር ባላባት ለእኔ ለእንግሊዝ ካፒቴን እንዲህ ሲል መልስ ሰጠኝ፤ አንተ አደን አድነህ የሀገሬን አንበሳ እንድትገድል ከኢትዮጵያ መንግስት ተፈቅዶልሀልና ግደል፤ እኔ ግን የሀገሬን አንበሳ እንዲያጋድሉህ ብዬ የምሰጥህ ሰዎች የለኝም" ብሎ በቁጣ ቃል መለሰልኝ። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው በዱር እንደሚያስገድለኝ ተረዳሁት፤ እና ተመልሼ በመጣሁበት መንገድ አደን የሚሉት ሳላድን ካርቱም ተመልሼ ገባሁ። እንዲህ ያለ በሀገር ፍቅር የተነደፈ ብርቱ ኢትዮጵያዊ ኑዌር ገጠመኝ። የሀገሩ አንበሳ እንዳይሞትበት በማሰቡ ከፍ ያለው ምስጋና ይገባዋል"

የጋምቤላን አንበሳ እንደ ወገን የሚቆጥረው አንጡራው ኑዌር እንደምን ኘዋል ሳይመንን ሳይቀበል ቀረ? ወደ ተረት ዓለም አበረረ? ... የማየው፣ የምሰማው፣ የማስበው ሁሉ ወደ ኘዋል ሳይመን ያመራሉ ...

... የአልዌር ግድብን አልፈን፣ የአኮቦ የስደተኞች ካምፕን ጎብኝተን፣ በጕኝዶ አድርገን አቦቦ ገባን። ጋምቤላን በውልብታ ሠላምታ ለአመታት እንዳስባት ያደረገኝ ሌላው ገጠመኝ እዚህ አቦቦ አገኘኝ። አቦቦ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ጎራ ብዬ ጠቅላላውን የቁጥር መረጃ ሰበሰብኩ። ታሪክ የሚያውቅ አዛውንት አገኝ እንደሆን ስጠይቅ አንድ ሽማግሌ አገናኙኝ። በራፋቸው ላይ ተቀምጠዋል። ቤታቸው ለመፈራረስ ያዘመመ፣ ግቢውም ጭር ያለ ነው። የሌሎቹ ኑዌሮች ግቢ በሁለትና በሶስት ሚስቶች የደመቀና በብዙ ልጆች ያሸበረቀ ነው። ለምን?

አዛውንቱ ባህልና ታሪክ እየደባለቁ በተኮላተፈ አማርኛ አጫወቱኝ። መጨረሻ ላይ ገና ስንገናኝ አንስቶ ቅር ስላለኝ ጉዳይ አነሳሁባቸው።

"ሚስትም ልጆችም የሉኝም" አሉኝ ተከዘው። "ዕድሜ ልኬን ጨርሶ አላገባሁም።"

"ለምን?"

"ያኔ ሚስት ለማግባት የሚከፈለውን የከብት ጥሎሽ አልቻልኩትም ነበር። ወይም "ድኝ" የተሰኘ የባህር ዕንቁ ባገኝ ኖሮ ሚስት ማግባት እችል ነበር። ጎግ ድረስ በእግሬ እየተመላለስኩ፣ ታታ ሐይቅ ውስጥ እየጠለቅሁ ፈለኩ፤ አጣሁ። ድሙኝ እንዲሁ በቀላል እንደማይገኝ ሳውቅ ትቼው ተቀመጥኩ። ይኸው አረጀሁ።"

ሌላ የባህል ቁስለኛ። ማነው የበደላቸው? እየፈለጉ ሳያገቡ፣ እየተመኙ ሳይወልዱ ብቸኛ ህይወትን ማባከን በእንዴት ያለ መመዘኛ ይለካል? ... ልቤን እንደጨፈገገው በሦስተኛው ቀን ወደ ጋምቤላ ከተማ ተመለስኩ። አሏጋ አከራዬን ሰው ፈልጎኝ እንደሁ ጠየኳት። የለም! ምዕራባዊት ኮከብ በእኔ ተስፋ ቆርጣ ጠፍታለች። ሌላ የተረት ጀግና ሐሰሳ ላይ ትሆናለች።

በቀጣዩ ቀን ኢትዮጵያ ሆቴል አካባቢ ተዟዟርኩ። የጐዌሮች ገበያ እዚያ ነው። መኖሪያቸው የማይንቀሳቀስ ባለ ረጅም ፍርጎ ባቡር ይመስላል። በሁለት ሀዲድ ላይ ድርቅ ብሎ የቀረ መንታ ባቡር። ግንባር ለግንባር የገጠሙ ብዙ ቤቶች እንደ ጥርጊያ መንገድ ድንጋይ የተኮለኮለበትን ሽንጣም ጣሪያ ይጋራሉ። አንድ ትንሽ ልጅ ጠየኩ። የኘዋልን ቤት በተቃራኒው ጠቆመኝ። የተንሰራፋ የግንብ አጥር ያለው፣ ዝምታ የሰፈነበት የብረት በር፣ የማይደፈር ሆኖብኝ ባዶ ልቤን ተመለስኩ።

... የጋምቤላ ልምዴ መጥፎ ነው። አመታት ያላገሙት፣ የጊዜ ንብርብሮሽ ይቅር ያላሉት ... የውልብታ ወለምታዬ ናት። ያለ ተፈጥሮዋ ለመወርወር የተዘጋጀችው ምዕራባዊት ኮከብ፣ የት አርፋ፣ እምን ውስጥ ተወትፋ ይሆን?

# ከሥነ ምግባር ባሻገር የት ደረስን?

ሁለት የአእምሮ ህመማንን አውቃለሁ፤ ከነበሩበት ሥርዓት ያተረፉትን ሥነ-ምግባራዊ ሀብት ይዘው ከጤና መቃወስ ጋር የሚኖሩ፤

አራት ኪሎ፤ ግብአተ-መሬታቸው የተፈጣጠመው ሥጋ ቤቶች አካባቢ ከላይ ታች- ይላል። በወሬ፤ ቀደም ሲል፣ አፍላው አብዮት ሳይበርድ ገና፣ የጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሾፌር ነበር ይሉታል። ከተፈጥሮ በተጨማሪ ውርጭና ሀሩር ተጋግዘው አጥቁረውታል። ግዙፍ ነው። ላይ ላዩን ለሚያየው ከቀድሞ ህይወቱ ያልረሳው ስሙን ብቻ ይመስላል።

"ግርማ!" ሲሉት ዘወር ብሎ ያያል።

ትዝ ይለኛል አንድ ጊዜ ብሎን መሰል የነሐስ ቀለበት አግኝቶ ጣቱ ላይ ይሰካዋል። ቀለበቱ አጥብቆ ስለያዘው እየቆየ ሲሄድ ጣቱ እያበጠ በመምጣቱ አንድ ዘግናኝ እርምጃ በራሱ ላይ ወሰደ። በድንጋይ ጣቱን ቀጥቅጦ ቆረጠው። የቀለበት ጣቱ ተጐርዳ ያየው ሁሉ ግርማ ፈፅሞ እራሱን እንደሳተ ደመደመ። ግን አልነበረም፤ እንደ ጣቱ ቆርጦ የማይጥላት፣ ከአካሉ በላይ እራሱን የሆነች አንድ ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ ነበረው። ታማኝነት። የአካባቢው ነዋሪዎች ግርማን ለመሰለል ብር ሰጥተው "ዘርዝረህና" ይሉታል። የላከውንና የተላከውን ፈፅሞ አይረሳም። አንዳንዴ ለጨዋታ የላኩት ይደበቁበታል። አደራ ሳይበላ ይጠብቃል እንጂ ውልፍት አይልም። እርሱን ባሰብኩ ቁጥር አንድ ጥያቄ ለራሴ አቀርባለሁ። ከአእምሮ ህመም በላይ፣ እራሱን ከመርሳት በላይ፣ አካልን ቆርጦ ከመጣል በላይ፣ ከከፍተኛ የመጠጥ ሱስ በላይ... መታመንን እንዴት አጥብቆ ያዘ? እንዴት?... እንዴት?... እንዴት?...

ሁለተኛውን የአእምሮ ህሙም የፅሁፌ መደምደሚያ ባደርገው ይሻላል፡-

ለሰው ልጅ ማህበር ሆነ፣ ሥልጣኔ ዋነኛ ጠላቱ የሥነ-ምግባር መታጣት እንደሆነ የዓለም ተደጋጋሚ ታሪክ ያሳየናል። ከሰዶምና ገሞራ ሆነ ከባቢሎን ወዲህ ግሪክን ያህል የሥልጣኔ ማማ የተገረሠሠው ዜጎቿ ሁሉ ሀብትና ድሎት ላይ አትኩረው ሌላውን ሥነ-ምግባራዊ ግዴታ ቸል በማለታቸው ነበር። በእነሱ እግር የተተኩት ሮማውያንም የእድገት ደረጃቸውን ያጣጣሉት በዚሁ ህዝቡ ውስጥ በተስፋፋው ኢ-ሥነ ምግባራዊነት የተነሣ ነበር። ህዝቡ ጭፈራ፣ ቧልት፣ ሀብት፣ ድሎት.... ወዳድ ሆነ።

ሁሉንም ነገር ለዝሙት፣ ለቀልድ፣ ለስካር... ሲል ገበያ ላይ አቀረበ። ሲውቶኒየስ (Suetonius) የተሰኘ የታሪክ ሰው "Biography of caesar" የተሰኘ መጽሐፍ ላይ ስለወቅቱ ሁኔታ እንዲህ ይላል፡-

"...They were financiers who thought only of accumulating interest upon interest, aristocrats who staggered from one enjoyment to another enjoyment, who scorned all regular labor, all exertion, even the exertion of governing and waging war and finally, the lumpen proletariat, who lived by selling their political power to the highest bidder."

(በትርፍ ላይ ትርፍ ስለማካበት ብቻ የሚጨነቁ ባለኃብቶች፣ ከአንዱ ደስታ ወደሌላ ደስታ በመዝለል የተጠመዱና በላቡ የሚኖረውን የሚያናንቁ መሣፍንቶች፤ ጥቅም ማጋበስ ብቻ፣ ሌላው ቀርቶ ጦርነትን እንኳ በባለቤትነት መያዝና ማትረፍ መለያቸው የሆነ በመጨረሻም የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራቾች በመሸጥ የሚተዳደሩ ለምፐን ፕሮሊታሪየት ተፈጠሩ)

ወደኛ አገር እንምጣ...

...ምንም እንኳን ሀብትና ሥልጣኔ አይኑር እንጂ ህዝቡ ከአቅሙ በላይ ወደ ገንዘብ አትኩሮቱ እየተገፋ ይገኛል። በተለያየ ዘዴ መንግሥት ህዝቡን እያለ ያለው "ከሌለህ አትኖርም" ነው። የ"የትም ፍጪው፤ ዱቄቱን አምጪው" ማስገደድና ያለመጠራጠር እየመራን ያለው ደግሞ ወደ ኢ-ሥነ ምግባራዊ አኗኗር ነው። የጥንቱ ሳይሆን ከቅርብ ጊዜ በፊት የነበረው የመተሳሰብ፣ የመተዛዘንና የይሉኝታ አኗኗር ይትባህላችን ዛሬ ጠፍቷል ማለት ይቻላል። ኑሮአችን በአጠራጣሪ ነገሮች ተከብባለችና ለገበያ የማናቀርበው ነገር የለንም። ኢትዮጵያዊ ጨዋነት፣ ኩራትና ክብር በይዞ መገኘት ሊለወጡ በየደጁ ተኮልኩለዋል። ሌብነት እንደማሪያም መንገድ ታይቷል፣ እምነት ማጉደል ማሳፈሩ ቀርቷል፣ ኢድርባይነት አነስተኛ ሥራ ፈጠራ ሆኗል...

ከጥቂት አመት በፊት ነው፤ አንድ "Ethiopian Economy" የተሰኘ ኮርስ ይሰጥ የነበረ መምህር ደጋግሞ ይናገር የነበረው የሥነ-ምግባር ጉድለት ዛሬም ትዝ ይለኛል፣

"እናንተ የምትገረሙት ሥልጣን ይዞ በሚቦጠቡጠው ነው እንዴ? አጠቃላይ ህዝቡ እሱን እያወገዘ መቼ ቦታውን ለቆ እኔ ተቀምጬ በቦጠቦጥኩ የሚል ሆኗል" ይል ነበር።

የዚህ መምህር አባባል ቢጋነንም ፈፅሞ ስህተት ግን አይደለም። መንግሥት በፈጠረው ግፊት የአብዛኞቻችን ተስፋ የተንጠላጠለው በአግባቡ ሰርቶ የማደግ ተፈጥሯዊ ጠባይ ላይ አይደለም። ከዚያ ይልቅ የአጋጣሚና የአቋራጭ መከበር ልባችንን አማልሎታል። በአርግጥም ደግሞ አይፈረድም። መንግሥት ለመኖር፣ ለመብላት፣ ለመጠለል...

እየጠየቀን ያለው በነባራዊ ሁኔታ ሰርተን ልናገኝ ከምንችለው በላይ እጅግ የተመነጠቀ ነው። እናስ? ከየት? እንዴት? እንብላ? እንኑር? እንጠለል?...

በአንድ ወቅት ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ወቅታዊ የአኗኗር ስልት መመሪያዎችንን ተቀብለን እንደነበር አስታውሳለሁ። "እስካልተያዙ ድረስ ሌብነትም ሥራ ነው" ብለውን ነበር። ለካንስ ሌባን ሌባ የሚያሰኘው ድርጊቱ ሳይሆን መያዙ ኖሯል? የሀሊና ነገር ውኃ አልበላውም ትላላችሁ?

የካድሬዎቹን ቋንቋ ልጠቀምና እንደሀገርና እንደ ሕዝብ መጠን የመቀጠል አደጋ ሆኖ ከፊታችን የተጋረጠው ድህነት ወይም አሸባሪነት አይደለም። የሥነ-ምግባር ችግር እንጂ። አገራዊው የሥነ ምግባር ችግራችን ምንጩ ደግሞ እንደ ጥንታውያኑ ሮማውያን ለጭፈራ፣ ለቧልት፣ ለቀልድ፣ ለዝሙት፣ ለሀብት፣ ለድሎት... ስንል ሁሉንም ነገር ገበያ ላይ በማቅረባችን አይደለም። መንግሥት ሁሉንም ነገር ነጥቆና ጠቅልሎ የኃይል ማካበቻ፣ የማይነጥፍ ምንጩ አድርጎ ፈጥርቆ ስለያዘን ነው። ሌላው ቀርቶ እጃችን ላይ ባለው እንኳን ዋስትና እንዳይሰማን ሆነናልና። የመኖር ዋስትናችንን በሌብነት ለማረጋገጥ ቀዳዳ እንፈልጋለን። እውነቱን ለመናገር የእኛዎቹ ሳቂታ ‹Lumpenproletariat› በማጨብጨብ ተወስነው የፖለቲካ ሥልጣናቸውን በመሸጥ ቢተዳደሩ እንኳን እኛ ያለንበትን እንዳይኖሩበት በመሥጋት በመሆኑ የዕጣ-ፈንታችን ተጋሪዎች እንደሆኑ እንረዳለን። ተረድተንም ሳናመር ይቅር እንላለን።

ሥነ-ምግባራዊ ጉድለቶቻችን ከአገር-አቀፍ ውጤቱ ባሻገር በግለሰብ ደረጃ እየተበተበ የዕለት-ተዕለት ኑሯችንን እያስተጓጎለብን ይገኛል። የበፊት አከራይና ተከራይ በመተሳሰብ፣ በመተዛዘንና በይሉኝታ የተመሰረተ ግንኙነታቸው ከሥጋ-ዝምድና የሚያስንቅ ቅርርብ ይፈጥር ነበር። ዛሬ ያ የለም። አከራይ እንደማጅራት መቺ የቀትን መጨለም አይቶ የሚያደባ ሆኗል። ተከራይም "የተከራይ አከራይ" ፈሸካ ከመንግሥት እስኪነሩ በመቀላወጥ የሚልመጠመጥ ሆኗል። ንግዳችንና ሸመታችን የመዘራረፍ ፍላጎት ያለበት ነው። እናት ልጇን፣ ጉብል እጮኛውን፣ ወንድም እህቱን፣ አጎት የእህት ልጁን... የገቢ ምንጩ ለማድረግ ሲገፋፉ ከፊት ለፊት "ገደል" መኖሩን እንኳን ልብ አይልም፤ ልብ ቢልም ግድ የለውም። ...ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ከድሎትና ከሀብት ማካበት ፍላጎት እንዳልሆነ እንረዳለን። የመኖር ዋስትናን ከማረጋገጥ እንጂ።

ከአራት መቶ አመት በፊት በአፄ ኢያሱ ዘመነ-መንግሥት የጥጋብ ሥነ ምግባር ጉድለት ተከስቶ እንደነበር አለቃ አፅመጊዮርጊስ ይነግሩናል። "...በዚያ ዘመን፣ በዚያ ወራት የቀልድ፣ የቧልት የጨዋታ ዘመን ነበረ። ካህናቱ በቅኔ እርስ በእርሳቸው ይሳደቡ ነበር፣ መኳንንቱ በበገና ይጫወቱ ነበረ፣ ወታደሩ በክራር አዝማሪውም በመሰንቆ ሲያዘምር የሚናገረውን በማድነቅ የወንድ መኮንን፣ የሴት ወይዘሮ በሰንጠረዥና በገበጣ፣ ሲጫወቱ ሲያቧልቱ (ይውሉ ነበር)" ይሉናል። ያኔም ቢሆን ቀልዱ፣ ቧልቱ፣ ጨዋታውና በቅኔ መሳደቡ የህዝቡ ሳይሆን የገዢዎቹ እንደነበር ከገለፃው እንረዳለን። ችግር እንጂ ጥጋብ አላሸነፈንም። ቢሆንስ፣ በችግርም ቢሆን ተሸንፎ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን፣ መተሳሰብንና መተዛዘንን ለገበያ ማቅረብ ታላቅነት ነው? እራስን ማስቀደም

አይሆንም?... ለሞት እንጂ ለሙበላት ስንሽቀዳደም አንታወቅም ነበርኮ.... በማለፍ እንጂ አሳልፎ በመስጠት አንፈረጅም ነበርኮ... እንኳን በጤንነት በአእምሮ ህሙምነትም የማንዘነጋት ታማኝነት ዛሬ የት ጠፋች?

የፅሁፌ መዝጊያ አደርጋታለሁ ወዳልኩት የሌላኛው የአእምሮ ህሙም ታሪክ ልሸጋገር፤

ካሣንቺስ አካባቢ አንድ የታወቀ ተንከራታች አለ። የዱላውን ጫፍናጫፍ በጨርቅ አስሮ እንደጠበንጃ የማንገት ልምድ አለው። አካባቢውን በወታደራዊ ንቃትና ኩራት እየቃኘ በዘብ ስልት ከወዲያ ወዲህ ማለቱ ቀደምሲል መለዮ ለባሽ እንደነበር ይመሰክራል።

ቁጭ ሲል ወታደራዊ ንቃቱን አይዘነጋም። በላስቲክና በጨርቅ የተተበተበ ጫማውን እየነቀነቀ በአቤቱታ ስሚነት ጭንቅላቱን በአፆንታ ይወዘውዛል።

ሰሞኑን ስለዚህ ሰው የሰማሁት ነገር እጅግ አድርጎ አስደነቀኝ። ይሄን ጉዳይ ያጫወተኝ በግርምት እራሱን እየነቀነቀ የባህር ኃይል አባል እንደነበረ ነገረኝ።

"እ...ሺ" አልኩት

"የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ እሱና ጓደኞቹ ከምፅዋ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ። ጓደኞቹ እድል ስለገጠማቸው ከኢትዮጵያ ወጥተው በሙያቸው ሲሰሩ ቆይተው ይመለሳሉ። እሱን ሲያዩት አላመኑም። አዘኑ። ገንዘብም አዋጥተው በፖስታ ሰጡት። እሱ ግን ነገሩን በጥርጣሬ ነበር ያየው። ልክ ጥበቃውን ለማስተጓጐልና ኃላፊነቱን ለመፈታተን አንዳች ነገር አድርግልን በሚል ጉቦ እንደሰጡት ቆጠረው። ስለዚህ ገንዘቡን በሌላ ፖስታ አሽጐ መለሰላቸው አሉ።"

የአእምሮ ህመም ያላዘናጋው ታማኝነታችንን ምን ነጠቀን? እራስን ከመርሳት፣ እውነታን ከመሳት፣ ማንነትን ከመዘንጋት በላይ የሆነ መታመናችንን እንዴት አጣን? እንዴት?.... እንዴት.... እንዴት?....

# ወንዶች ሳያድጉ ፣ አርጅተው የሚሞቱ ህፃን ናቸው?

“ወንዶች ስትባሉ የህፃንነት ጠባይ ያጠቃችኋል። ሳታድጉ ነው አርጅታችሁ የምትሞቱት” ይሄን የምትለው የበዓሉ ግርማ ገፀ ባህርይ ናት፤ “ደራሲው” ውስጥ የተሳለች፤ ስብለወርቅ ታፈሰ ብሩ የተባለች፤ የደብተራ ልጅ፤ በመጽሐፍ ቀበኛ፤ በባል ቁራኛ የተያዘች። ቀበኛው ደራሲው ሲራክ ነው፤ ቁራኛው ደግሞ ዘመን ዓለሙ የተሰኘ የአብዮት ተጋጁ። እዚህ ቅርቃር ውስጥ ስብለወርቅ ተፈጥርቃ ትኖራለች። ዳኘነቷ የብዙ ወንዶች ህመም እንደሚሆን ግልጽ ነው። ወንዶችን ሁሉ እፍኝ የገቡ ቁጠማ አድርጋ በክርክር ስል ማጭድ ቋጭዳለች።

እውነት ወንዶች እንደዚህ ነን? የህፃንነት ጠባይ አለን? ሳናድግ አርጅተን እንሞታለን? ተነግገሪያችን ህፃን ምን ያደርጋል? እኛስ?

ስብለወርቅ ይሄን የምትለው ውብ ብትሆንም ባሏ እጅ ከገባች በኋላ “ዋጋዋ” እየቀነሰ በመምጣቱ ነው። በንግግር ያራክሳታል፤ ከሕሊናዋ አልፎ አካሏን ያንሣቁልባታል። ዘመን ስብለወርቅን እስኪያገኝ አልቅሷል - እንደ ህፃን፤ ሲያገኛት ስቋል - እንደ ህፃን፤ ውሎ ሲያደር የት እንደተወሸቀች ረስቷል እንደህፃን፤ “አስታውሰኝ” ስትለው “አልፈልግም!” ብሷል - እንደ ህፃን።

ግን ሁላችንም እንዲህ እንደ ዘመን ነን? ጥያቄው ከበዓሉ ግርማ አንፃር ከተነሣ መልሱ “ነን!” ነው። “ህፃን ነን! ያውም ሳናድግ አርጅተን እንድንሞት የተፈረደብን ህፃን!!”

እንዴት?

እንደዚህ፤ እዚያው “ደራሲው” ውስጥ ዋናው ገፀባህርይ ሲራክ አጥምዶ የያዛትን ሚስቱን ችላ ብሎ ስብለወርቅን ለመያዝ የሚንጠራራ ሆኖ ተፈጥሯል። ቃል በቃልም እንዲህ ይላል፡-

“የፍቅር ቅመሙ ታዲያ ከምኑ ላይ መሰለሽ? መለየት መኖሩን ከማወቅ ላይ ነው። እንደ ህይወት ማለት ነው። ሞት ባይኖር የህይወት ጣዕም እንዴት አድርጐ እንደሚገባን አላውቅም። ይገባን እንደሆን ማለቴ ነው” (ገፅ 66)

የሲራክ (የወንድነት) ቅመሙ ከእነዚህ ቃላት የተውጣጣ ነው። (ቢያንስ በበዓሉ ግርማ ድምዳሜ) መለያየት መኖሩን እስካወቅን ድረስ ፍቅር አለ። መለያየት የሞተበት ትዳር ውስጥ ግን ፍቅርም በድን ነው። ሞት የማይታወቅበት ህይወት በዘልዛላነት እንደሚቸከን ሁሉ መለያየት በባህልና በእምነት ግብአተ መሬቱ የተፈፀበት ትዳር ፍቅርን ያፍናል። የሲራክ ህይወት በገቢር ይሄው ነው። መኖሪያ ቤቱ ሲገባ የሚሞተው ልቡ፣ መስሪያ ቤቱ ሄዶ ስብለወርቅን ሲያገኝ ከሙታን ይነሳል። ህፃንም ይሄው ነው። ዛሬ አልቅሶ ያስገዛውን መጫወቻ ከጥቂት ጊዜ በኋላ (የራሱ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ) ላይፈልገው ይችላል። ሌላ ሰው ወደያዘው ሌላ ዕቃ ሊያተኩርም ይችላል። የሰብወርቅ (የበዓሉ ግርማ) ተሐዝቦ ባያስደመድምም ለማግደርደር አይሳነውም።

ከዚህ ጋር ኩታ ገጠምነት ያለው አንድ ተረት ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር አጫውቶኝ ነበር። የጥንት ፈረንሳዮች በትዳር ላይ ያላቸው ወግ ከአሁኖቹ ለየቅል ነበር አሉ። አንድ መኳንንት ወደ ቤቱ የሚገባው ፍቅረኛው ጋ አምሽቶ፣ አኳሽሞና የፍቅር ወግ ጠርቆ መሆን ይገባዋል ተብሎ ተደምድሟል። እና የዚያ ዘመን ተሳታፊ አንድ ፈረንሳዊ ከሚስቱ በላይ በፍቅረኛው ቁራኛ ተይዞ ሲሰቃይ አንድ ወዳጁ እንዲህ ሲል ጠየቀው አሉ፦

"ፍቅር እንዲህ ከፀናብህ ለምን ሚስትህን ፈትተህ እሷን አታገባትም?"

"እሷን አግብቼ የት አባቴ ላመሽ?" አለ አሉ አፍቃሪ።

የወንድ ሁሉ ህይወት ይሄው ነው? የተያዘችውን ወደ ኋላ፣ ያልተያዘችውን ወደፊት አድርጐ፣ በሴት እንደታጠሩ መጓዝ? በመፈለግና ባለመፈለግ መካከል መወዛወዝ? በህፃንነት ምህዋር ላይ ሲሽከረከሩ ኖሮ ነፍስ ሳያውቁ አርጅቶ መሞት? ነው? በማግኘት ታክቶ፣ በማጣት ተብከንክኖ መቅረት?...

...ሴቶችስ? ይሄን ጥያቄ ሲራክም አንስቶታል። ስብለወርቅ በወንዶች "ህፃንነት" ስትብከነከን "በሴቶች አይብስም?" ብሏታል። ምን መለሰች?

"ፍፁም! እዚህ ላይ በጣም ተሳስተሃል። እኛ ሴቶች አንዴ ከወደድን እንወዳለን። ሌላ ወንድ ያለ አይመስለንም። የምታራክሱንም ለዚሁ ነው"

ሲራክ በመከራከሪያው አልቀጠለም፣ በሰብለወርቅ ምላሽ የያዘውን ለቅቋል። ዖታውን አስረትቶ ያለዖታው "አጉራሽ ጠናኝ" ብሏል። እዚህ ውስጥ ደራሲው በዓሉም ያለ ይመስላል።

እንዴት?

እንደዚህ፣ በዓሉ ግርማ የፃፋቸው ልቦለዶች ሁሉ ዋና ገፀባህሪው የሚገኘው በሁለት ሴቶች ሰርጥ ውስጥ፤ ነፍሱ የሳንሳ ተይዛ ነው። በ "ደራሲው" ውስጥ ፅጌ ሃይለማሪያምና ሰብለወርቅ ታፈሰ የሲራክ ህይወት የጀርባና የፊት ችካሎች እንደሆኑት ሁሉ፤ የ "አሮማይ"፣ የ "ህዲስ"፣ የ "የቀይ ኮከብ ጥሪ" እና የ "ከአድማስ ባሻገር" ዋና ገፀባህሪዎችም ዕጣ ፈንታ በመቂናጣዊ መወዛወዝ ተለጉሟል። መነሻና መድረሻቸው፣ ትልምና ግባቸው፣ ሳቅና እንባቸው በሁለት ሴቶች ሰርጥ ውስጥ ታቁሯል። አንዴ ይሁን፣ ሁለቱም ግዴለም፣ እንዴት ተደጋገመ? ያሰኛል።

የ"አሮማይ"ው ዋና ገፀ ባህርይ ሮማን ህለተወርቅ እና ፊያሜታ ለተባሉ አንስታይ ሉአላዊነቶች ተባዕታዊ መስዋዕትነት የሚከፍል ባተሴ ነው። እንዲሁ ህዲስ በስሙ የተሰየመው ልቦለድ ውስጥ በኃላፊና በመጪው ጊዜው በወከላቸው ሽታዬና አይናለም በተባሉ ሴቶች ዘብጥያ ወርዷል። "የቀይ ኮከብ ጥሪ" ውስጥ ያለው ደርቤ ደግሞ እንደ ቀንና ሌሊት እየተፈራረቁ የሚያስተኙትና የሚያነቁት ሁለት ሴቶች በበዓሉ ግርማ ተመድቦበታል። ሒሩት እንደ ስሟ ሌሊትና ፍትወት ወከላለች፤ ፍኖት ደግሞ የህይወት መዳረሻ መንገድነቷን ትጠቁማለች። እዚያ ሰርጥ ውስጥ ደርቤ መጨበጥና መልቀቅ ተስኖት ይባትላል። "ከአድማስ ባሻገር" ውስጥም በራሷ የምኞት ዓለም አበራ ወርቁን የምትቃብዘው ሰናይት እና ለመግራት የምንትገላታው ሉሊት አሉ።

... አንድ ነገር ሲደጋገም "ለምን?" ማሰኘቱ የወግ ነው። እንደውም አለመጠየቁ ተፈጥሯዊነት ያጣል ማለት ይቻላል። ከበዓሉ የጥበብ ዓለም እስከ ህይወት ህማም ድረስ የተዘረጋ ፍትሻ የሚያስፈልገው ድግግሞሽ ነው። የወንድን ዓለም መንታ አንስታይ "ፀሐይ" የሚፏልልበት እንግዳ ተፈጥሮ ማላበስ የአንድ ደራሲ የጥበብ ነጠላ ግብ ከሆነ አጠያያቂነቱ እሙን ነው። በዓሉ ህይወት ውስጥ ምን ገጠመኝ አለ? በተደራሲያኑ ምን ግንዛቤ እንዲወሰድ ይሻል? በእርግጥ ድግግሞሹ ከድምዳሚው የፈለቀ ነው? ወይስ ልብ ሳይለው ይተገብረዋል? ...

በእኛ የአማርኛ ሒስ አግባብ እንዲህ ያለ ጥያቄ ተነስቶ ትንታኔ የተሰጠበት ሥራ አላጋጠመኝም። በውጭው ዓለም ግን አለ። ለምሳሌ እንደ በዓሉ ግርማ ሁሉም ስራዎቹ አይሁን እንጂ ሩሲያዊው ደራሲ ፊዮዶር ደስተየቭስኪ መንታ ሴቶች የሚያዋክቡት ዋና ገፀ ባህርይ ደጋግሞ ስሏል። "The Brothers Karamazov" ውስጥ ካተሪና ኢቫኖቭና ግሩሼንካ የተባሉ ሴቶች በእኩል ጉልበት የተሳሉ መንትያ ሴት ገፀ ባህርያት ናቸው። "The Idiot" የተሰኘ ልቦለዱ ውስጥ አግላያ እና ናፃስያ ፍሊፓቭና አሉ። በተመሳሳይ ቫርያ እና ሶኒያ ደግሞ "Crime and Punishment" ውስጥ ተገዳዳሪ ገፅታ ተላብሰው በዋና ገፀ ባህሪው በራስ ኮሊንኮቭ ህይወት ይፈራረቃሉ። እንዲሁ በ "The Insulted and Injured" ልቦለድ ውስጥ ታዳጊያዊ ኔሊ እና ኮረዳዋ ኒዛኖቫ ዕድሜያቸውን ያላማከለ ፉክክር ገጥመው ቀርበዋል።

ይሄ የዶስተየቭስኪ አዝማሚያ እንደኛው በዓሉ ችላ አልተባለም። ሁኔታውን ግልፅ ለማድረግና ድምዳሜ ለመስጠት የሚሞክሩ ብዙ ጥናቶች ተሰርተዋል። እኔን ሊያሳምኑኝ ከዳዱኝ ጥናቶች ውስጥ አንዱ ወደ ዶስተየቭስኪ ኃላፊ ጊዜ ተጉዞ ሊያገናኘው የሚጥር ነው። Konstantin Muchulsky የደራሲውን ህይወትና ሥራ በሚዳስስበት መፅሐፉ ላይ እንደጠቆመው፤ የጥንድ ሴቶች መገዳደር ምንጩ ፎንቪዚና የተባለች ሴት ነች።

እንዴት? ...

... እንደዚህ ነው። ፎንቪዚናን ዶስተየቭስኪ የሚያውቃት የሩሲያን ንጉስ በመግደል ሴራ ተከስሶ ሞት በተፈረደበት ማግስት ነው። በዚያን ጊዜ የሞት ፍርዱ ተሽሮ በአራት አመት የጉልበት ቅጣት ተቀይሮለት ወደ ሳይቤሪያ እየተጓዘ ነበር። አብረውት ሴረኞች የተባሉ (Desemberist) አሉ። ከእስረኞቹ የአንዱ ሚስት ከባሏ ላለመነጠል ወደ ላይቤሪያ አብራ እየተጋዘች ነበር። ያቺ ሴት ናታሊያ ፎንቪዚናን ስትሆን ዶስተየቭስኪ በእስር ያሳለፋቸውን አመቶች እያነበበ የተፅናናበትን መፅሐፍ ቅዱስና አሥር ሩብል እንደሰጠችው ማስታወሻው ላይ አስፍሮት ተገኝቷል።

በተጨማሪም የጓደኛው ሚስት ብትሆንም ዕድሜ ልኩን ሲያፈቅራት እንደኖረ፤ ባለቤቷ ከሞተ በኋላ ሳምንትም ሳይቆይ የጋብቻ ጥያቄ እንዳቀረበና እንዳልተቀበለችውም አልሸሸገም። ፎንቪዚና ለፍቅር የተገዛችለት ባሏ ከሞተ በኋላ የጥንቱን መሆን ተስኗት በብዙ ድካመት ተከባ ቀሪ ህይወቷን ገፍታለች። እንደ ሙቹሉስኪ ድምዳሜ፤ ዶስተየቭስኪ በልቦለዱ ውስጥ የሚቀርፃቸው መንታ ሴቶች፤ በጥንካሬና በድክመት የዚችን ሴት መንታ ህይወት የሚያንፀባርቁ ናቸው። ዶስተየቭስኪ እንደ በዓሉ ግርማ ሁሉ ከህይወት ወደ ልቦለድ በመቅዳት የሚታወቅ ደራሲ ነውና የሙቹሉስኪ ድምዳሜ እውነትነት አያጣም።

... ለመሆኑ ስለ በዓሉ ግርማ እና ስለ መንቶ ሴት ገፀ ባህርይ አሳሳሎቹ ምን ማለት ይቻላል? የሕፃንነት ጠባይ ስለሚያጠቃቸውና ሳያድጉ አርጅተው ስለሚሞቱ ወንዶች ያለው ድምዳሜስ? እንዴት? ለምን እዚህ ድምዳሜ ላይ ደረሰ? ከኑሮውና ከህይወቱ ጋር እንዴት ይተራጎማል? በምን ይገናኛል? ... ብዙ ጥያቄ፤ ምናልባትም ምላሻቸው ከእኛ ብዙ የራቀ ...።

# በሴት ዓለም ውስጥ አንድ ወንድ

ሰማይና ምድር መንትዮቹ የእግዚአብሔር የበሕር ልጆች ናቸው። እነዚህ መንትዮች ድስትና እፊያው እንደመሰሉ እግዚአብሔር ሁሉን በውስጣቸው አከማች። እግዚአብሔር ይህን በሰማይና በምድር መካከል የተከማቸ ሀብት ለማማጠጫ ልጁ፣ ከፍጥረታት ሁሉ ታናሽ ለሆነው ለስድስተኛ ቀን ልጁ ሰጠ... እግዚአብሔር ሰውን በስድስተኛ ቀን .. እንደተገላገለ.. የባህር አሶችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትን፣ ምድርን፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ..ግዛ!.. አለው።

ግና እግዚአብሔር ምንኛ ቃሉን አጠፈ? ማማጠጫ የመሰለውን ሰው ጥሳ፣ የሥራ ቀኖችን ተላልፋ ሔዋን (በ8ኛ ቀን) ትፈጠር ዘንድ ግድ ሆነ። ሴት በአቋራጭ የመጣች የእግዚአብሔር የማማጠጫ ልጅ ናት። እናም... ወላጅ ወረተኛው... የፈጣሪ ልብ ወደዚች ጨቅላ አደላ። አዳምን ጨምሮ ለርሷ የተፈጠረ ሆነ። በመሆኑም ለወንድ ከተሰጠው የገሃድ ቃል በስተጀርባ ሴት እርሱን ጨምራ ትገዛ ዘንድ ከስውር ፍቅር የተበጀ ስውር እጅ ተሰጣት.... ወንድ ከዚያች ዕለት አንስቶ ምስኪንነቱን የማያውቅ ምስኪን ሆነ።

ወንድ ገና ዘር እያለ የሴት ማህፀን ካላገኘ ፅንስ አይሆንም፣ ፅንስ ቢሆንኳ ሴት ካላስፈለጋት ወደ ልጅነት አይተላለፍም፣ ልጅ ሆነ እንበል - ሴት ጡት ካላጠባችው የት ሊደርስ? ጡት ቢጥልም - እህል ውሃ ቢልም - የዖታ ሱስ ያከለፈልፈው ዘንድ ግድ ነው። ሴት ወንድ ላይ ያገባችው ልጓም ቢረዝም እንጂ አይበጠስም። ወንድ ኖሮ፣ ኖሮ ሲጎፈይ እንኳ ምርኩዙ እንጨት ሳይሆን ሴት ነው። በደከመ ጊዜ ታዛው ነች። ሌላው ቀርቶ ወንድ ሲያጣጥር አልጋው ከሴት የተሠራ ጠፍር ነው። ቢሞት እንኳ ሸኙቱ ያለሴት ቀዝቃዛ፣ ቀዝቃዛ፣ ቀዝቃዛ ነው።

ወንድ በስውር ከተሻረበት የገሃድ ቃል በመነሳት ዓለምን ለመጠቅለል ቃትቷል። የሞንጐሉ መሪ ጀንጂስ ከሐን የዓለምን አንድ ሦስተኛ ምድር ጠቅልሏል። ግዛቴም ብሏታል። የሮማው ታላቁ አሌክሳንደርም እንዲሁ አድርጓል። ይህ ሁሉ ግን ለበላይዋ ሴት ቀለብ የተደረገ የዝና ክምችት ነው። እያንዳንዱ ጦረኛ በልቡ

የሚታጠቀው ተጨማሪ የጦር ዕቃ አለው። ያ የጦር ዕቃ ..ሴት.. ይሰኛል. . . (ይሄንን በሐበሻው ጠረኛ ላጉላው)



አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ቴዎድሮስነታቸው ከጉጂቻው ውጭ ነው። ለልጃቸው አባት፣ ለሚስታቸው ባል ናቸው። አንድ ጊዜ ገብርዬ (የጦር ሚኒስትራቸው) ወደ አፄው ቤት ሲገባ ጌታው በሚስታቸው (በተዋቡች) ጥፊ ሲነዱ ይደርሳል። ገብርዬ ግልፍ ይለውና... እንዴ! ጌታዬን?!.. ብሎ ጐራዴውን ሲመዝ አፄው መካከል ይገቡና እንዲህ አሉት...

"..ገብርዬ፣ ልብ በል። አንተ የምታውቀኝ ታጥቄ፣ እርሷ የምታስወልቀኝ አውልቄ" ናት።..

..ሱሪ ከማስወለቅ.. በላይ ጀግንነት፤ ..ሱሪ ከማውለቅ.. ያነሰ ተሸናፊነት የት መጥቶ? እናም ሴቶች ምስኪንነቱን በማያውቀው ምስኪን ወንድ ላይ ባለ ስውር እጅ ስውር ጌቶች ናቸው። ወንድ በማያገባው ለሴቷ ግን ትርጉም ባለው ጉዳይ ጉዳዩ እያለ ደሙን አፍስሷል፣ አጥንቱን ከስክሷል፣ ህይወቱን አሳልፏል. . . ከዚህ ሁሉ በከፋ ከፈጣሪው ተጋጭቷል።

. . .ንጉስ ሰለሞን ስለ እቁባቶች ፍቅር አጓጉልኛ ተራምዶ አምልኮ-አማልክት ቀዬ ገብቷል። የሰገደው ግን ለግዑዛኑ ጣኦታት አልነበረም፤ በስውር እጃቸው ለዳሰሱት ጌቶቹ ሴቶች እንጂ። አባቱ ንጉሥ ዳዊትስ ቢሆን? በዓመቱ መለወጫ ነገሥታት ወደ ሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ እርሱ ብቻ በምንጣፉ ላይ የቀረው ንጉሥ ዳዊት ከምንጣፉ ሲወርድ የመልካም ጦረኛውን የኦርዮንን ሚስት አየ። እርሷ ሴት. . . እርሱ ወንድ። ከርሷ አስቀድሞ ንጉሥ ዳዊት ስለ ስውር ሥልጣኗ ተንበረከከ። አለያማ እርሱ ንጉሥ እርሷ የአሽከሩ ሚስት አልነበረችምን? ግና ስውር እጅ አለና እርሱ ወደቀ። እናም አረገዘች። ዳዊትም ምስጢሩን ለመሸፈን ተጣጣረ፣ ሁሉንም ሞከረ። ባለመሆኑ ከመጋለጡ አስቀድሞ ኦርዮንን አስገደለ። ዳዊት ልታይ፣ ልታይ ከሚለው ዓለማዊ ሥልጣኑ የከፋ ስውር እጅ እንዳረፈበት ፈጣሪው አይረዳ ይሆንን? የማይቋቋመው የሴት ኃይል እንደገዛው ባይረዳም።

ግድ የማይሰጣቸው አሉ። ማክስዌል ሪስ የተባለ እንግሊዛዊ ደራሲ ..ሚስቴ እዚያ ከሌለች ገነት ለእኔ ምኔ ነው?.. ብሏል። ደፋር ይመስላል። ግና እንዳያያዙ ተይዞ ነው። ዓለምን ያለሴት አይቷት ወና ሆናበታለችና ገነትን ቢጠራጠር አይፈረድበትም።

ደግሞምኮ ከሴት የተነጠለች ገነት እንዴት እንደምታጓጓ ግራ የተጋቡ ሰዱቃውያን ይሄንኑ ጥርጣሬያቸውን ለኢየሱስ አንስተውለታል። "... ሰባት ወንድማማች በእኛ ዘንድ ነበሩ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ፤ ዘርም ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት፤ እንዲህም ደግሞ ሁለተኛው፣ ሦስተኛው፣ እስከ ሰባተኛው

ደረሰ። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች። ሁሉ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች..”

ጥያቄው ትንሣኤ ሙታንን ተስፋ ያደረገ ወንድ ሁሉ ጥያቄ ነው። እዚህ ውሃ ቀርቦ ጥማት እንዳለ ሁሉ፣ እህል ቀርቦ ረሃብ፣ ጠኔ እንዳለ ሁሉ ሴት ቀርቦ ስም ያልሰጠነው ግዴታ አለ። እናስ ለጥማቱ የወተት ወንዘ፣ ለረሃብ መና እንዳለ ሁሉ... ማለቱ ነው ያ-ወንድ። ደግሞምኮ ዘፍጥረት ላይ እነዚያ የገነት እንግዶች መሬትን ሲጐበኙ የተመለከቷቸውን የሰው ልጆች ስለቆነጁባቸው ወርደው ተገናኝተዋቸቸዋል። እናም ለዓለም ኃይል የማይመጥኑ ኃያላንን ኔፍሊምን ወለዱ። እግዚሃር እስኪያጠፋቸው ቀን ድረስ።

ወንድ የተሠራው ከሴቶች ጡብ ነው። ሰብዕናውን ብንከፋፍለው እናት፣ እህት፣ አክስት፣ የከንፈር ወዳጅ፣ እጮኛ፣ ሚስት. . . የሚባሉ ፍርስራሽ ጡቦችን ነው የምናገኘው።

የሳይኮ አናሊስስ (Psychoanalises) አጋፋሪ ሲግመድ ፍሮይድ ይሄንኑ ይነግረናል። ለወንድ እናት የሚስት መክተቻ የዕድሜ ማለዳ ስልቻ ናት። ሚስት ደግሞ እንደተራገፈ ጆንያ ምንም ያልያዘች እናት። እናም ወንዱ የሴት እጅ እንደተቀባበለው መጨረሻ የመቃብር አፍ ተከፍቶ ያጠናቅቀዋል። የሴት እጅ ቅብብሎሹ በግማሽ መንገድ ቢቋረጥስ? ማለቴ አንድን ወንድ ከእናቱ እጅ ላይ የምትቀበለው ሌላ ሴት (እጮኛ፣ ፍቅረኛ፣ ሚስት...) ቢያጣ? ወንድ ህይወቱ የጐፈነነ ይሆናል። ሰዓሊው ቪንሰንት ቫን-ጐህ የሴቶች እጅ መታጣት ሰለባ እንደነበር ታሪኩ ያስረዳል። የቫንጐህ እናት የከንፈር ወዳጅ ወይም ሚስት ሆና የምትቀበልላት ሌላ ሴት በማጣቷ በተፈጥሮ ግፊት ..ሜዳ.. ላይ አኖረችው። ቫንጎህ የአክስቱን ልጅ አፈቀረ። እሷን ነዋ ምርጫ አልባ ዳሰሳው ያገኘው። አልሆነም። እንዲህ እንዲያ ሲል መሸበትና አንድ ጊዜ አንድ አካሉን ነጥላ የምትወድ ሴት ተፈጠረች። ..ጆሮህ ሲያምር.. አለችው። ያ የወደደችለትን ጆሮውን ቆርጦ በፖስታ ሰጣት። ምን ያስገርማል? ሁላችን እንዲሁ አይደል የምናደርግ። በሴቶች ተወደደልን ያልነውን ዓይናችንን፣ አፍንጫችንን፣ ድምጻችንን... ባንቆርጠውም አሸሞንሙነን እሱኑ ብቻ ሆነን እንቀርባለን። ቫን ጎህ ወንድ፣ ወንድ ቫንጐህ።

ፍሬደሪከ ኒችም ያው ነበር አሉ። ስውር ኃይላቸውን ሳይረዳ ሴቶችን ..እርም.. ያለ። ሌላው ቀርቶ ዛራቱስትራ የተባለውን ገፀ ባህሪውን ..ከህይቅ ድንፋታ ተወለደ.. ይለዋል። ከሴት ተጽዕኖ ለማላቀቅ። ግና ምን ይሆናል ከ..ሴት.. የተገኘው ደራሲ ኒች ከህይቅ ድንፋታ የተገኘውን ገፀ-ባህርይ ብዙ ምሬት ያናግረዋል። ..ወደ ሴት ጋ ስትሄድ አኮርባጅህን አትዘንጋ.. ይላል። ከኑሮ ወጪት የተጨለፈ የሚመስለውን ልምድ እንዲህ ሲል በዚሁ ገፀ ባህርይ አንደበት ያወጣል. . “....በጦረኞች ዘንድ እጅግ ጣፋጭ ፍሬዎች ተመራጭ አይደሉም። ስለዚህም

እነዚህ ጦረኞች ሴቶችን አጥብቀው ይወዳሉ። ምክንያቱም እጅግ ጣፋጭ ከተባለችው ሴት እንኳ የሚገኘው ውጤት መሪር ነውና።"

ኒች አንዳንድ ጊዜ ከሚሰማው ገጠመኙ አንፃር ከታየ ሰውየው በሴቶች ላይ እንዲህ ቢያመር አይፈረድበትም ያስብላል። ኒች አሚሚቱ በቂጥኝ አባላዘር በሽታ አብዶ ነው ስለሚባል።

ወንድ ዘር ነው። ..ሴት.. ከሚባል ምድር የተገኘ ተክል። እዚያው በቅሎ፣ እዚያው አሽቶ፣ እዚያው ወድቆ ዳግም የሚበቅል የዘር አዙሪት። ለዚህ ሁሉ ግን ሴት ፈቃዷን ልትሰጠው ግድ ይላላ። ለማኘነቱን አውቆም ሆነ ሳያውቅ በሴት እርጥባን የሚኖር ሰንካላ ነው ወንድ። ጌታም ቢሆን። በተገፈፈ ክብሩ፣ በተነጠቀ ቃል ኪዳኑ እየተኩራራ አልቦ ስልጣን የጨበጠ።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን ላይ ላዩን ሲያዩዋቸው ባሪያ አሳዳሪ ነበሩ። ነገር ግን በሴት በባሪያ ተዳዳሪ አሁን አሁን ሳይንስ እየተንኳተተ የዋሽንግተንን ዘራቸውን ባሮች የዘር ግንድ ውስጥ አገኘው። ያቺ.. ባሪያ.. ብሎ የጠራት ሴት እናት ምድሩ ነችና ላይወድቅባት፣ ላይበቅልባት አልቻለም። ይሄ እኛም ሀገር ነበር። ባሪያ አሳዳሪው ከባሮቹ መርጦ የሚሰግድላትን ባሪያ.. ሴት.. ያበጃል። እዚያም ወንድ፣ እዚህም ወንድ።

ሁሉ የገባው ሊባኖሳዊው ደራሲ ካህሊል ጅብራን ይመስላል። "..ሴቶች የዓይኖቼ መስኮቶች፣ የነፍሴን በሮች ከፈቱልኝ.." የወንዶች ጥንካሬ ከዚህ እንደሚነሳ ጅብራን ንስሀውን ሰጥቷል። "..ደራሲያን ሆኑ ባለቅኔዎች ስለሴቶች እውነቱን ለመረዳት ይጥራሉ.." ይላል ጅብራን። "..የሚደንቀው ግን አሁንም ስለሴቶች ልብ የሚያውቁት የለም። ምክንያቱም መፈተሻ ዓይኖቻቸው የተወለዱት ከመጐምጀት ነውና ላይ ላዩን ከመንሳፈፍና ድክመቷን ከማንጠር ውጭ ጠብ የሚልላቸው የለም።.." ይኸው ነው! የጂብራንን ልቡና ይስጠን!!

# በወንዶች ዓለም ውስጥ አንዲት ሴት

የአዲስ አበባ ወንድ የመልበሻ ቤት መስተዋት ሆኗል። ሴቶቹ በሱ ፊት ላይ አለባበሳቸውን ያያሉ፤ የአዲስ አበባ መንገዶች፣ ካፌዎች፣ ባሮች፣ ቢሮዎች፣ ሆቴሎች፣ የፀሎት ቤቶች... አለባበስ ማሳያ መድረኮች ሆነዋል።

ወንዱ የጥሞና ጊዜ ተነፍጓል። ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲሰራ፣ ሲፀልይ፣ ታክሲ ሲጠብቅ... በሞዴሎች ተከቦ ነው። ህይወቱ የናይት ክለብ ውስጥ እስረኛ ሆናለች። ሲወለድ ሳውና ባዝ የገባ ሲሞት ይወጣል። ኑሮው በላብ መጠመቂያ ሥፍራው ሆናለች። አይኑ ሸሽቶ የትም አይደርስም። እድሜ ልኩን መስከ መካከል እንደቆመ ሁሉ በአበባ ተሰላችቷል። ..ትቢያ.. ናፍቆታል።

ሴቶች፣ የወንዶች አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ሆነዋል። አይኑን ያገለግላሉ፣ ልቡን ያገለግላሉ፣ ስሜቱን ያገለግላሉ... የሴቶች የመጨረሻ አማራጭ ..የወንዶች ገበያ.. እንደሚፈልገው ሆኖ መገኘት ነው። ህይወታቸው በወንዶች ህልም የተፈበረከ ነው። ከሰው የሚጠበቀው ከዘንድሮ ሴቶች አይገኝም። ወንድ የሚፈልገውን ግን አያጣም። አይኑ፣ ጆሮው፣ አፍንጫው፣ ምላሱ... በሴቶች ትጋት ሥር ተጠምዶ ተደናቅፏል። አንዲት ሴት ከአንዲት አበባ ጋር በንፅፅር ቆማለች። የወንድ ቀልብ እንደ ንብ ሲጠመድላት ከማየት ውጭ ሌላ ህልም የላትም።

እንግሊዛዊው ደራሲ ዲ.ኤች ላውረንስ ይሄንን ታዝቦ አንዲት የመረረች መጣጥፍ አቅርቦ ነበር። “Give her a pattern” ይላል ርእሱ “The real trouble about women is that they must always go on trying to adapt themselves to men’s theories of women, as they always have done.” ብሏል። (የሴቶች ዋነኛ ችግር ወንዶች ስለሴቶች የሚኖራቸውን ፅንሰ ሃሳብ አሚልተው ለመገኘት ሁልጊዜም መጣራቸው ነው)

የዘንድሮ ሴቶች ሴት የመሆን መብት የላቸውም፤ ወንድ የሚፈልገው አይነት ሴት አንጂ። ሴቶች የወንዶችን ህልም ለመተርጐም ህይወታቸውን የሚሰዉ ጭዳዎች ናቸው። በመሰልጠን ሥም እራሳቸውን ለዖታ ባርነት አጋልጠዋል። ኧረ እንዳውም ከባርነት ወርደው ለአሻንጉሊትነት ተዳርገዋል። ሁኔታውን "living Doll" ይለዋል Cliff Richard የተባለ አቀንቃኝ።.. ህያው አሻንጉሊት.. እንደማለት ነው። "I got myself a sleeping, walking, crying, talking Doll" (እራሴን የምትተኛ፣ የምትሄድ፣ የምታለቅስ፣ የምታወራ አሻንጉሊት ሆኜ አገኘሁት) የዘንድሮ ሴቶች ሰው መሆናቸው የሚረጋገጠው ስለሚተኙ፣ ስለሚሄዱ፣ ስለሚያለቅሱና ስለሚያወሩ ብቻ ነው። እንደ አበባ ..ንብ.. መጥራት የህይወት ትርጉማቸው ሆኗል።

ከላውረንስ መጣጥፍ እንጥቀስ፤

"When a woman is throughly herself, she is being what her type of man wants her to be, when a women is hysterical its because she doesn't quite know what to be, which pattern to follow, which man's picture of woman to live up to." (አንዲት ሴት በትክክል እራሷን እንደሆነች የሚቆጠረው በእሷ አንፃር ያሉ ወንዶች እንድትሆን የሚፈልጉትን ሆና ስትገኝ ነው። በከፍተኛ ሁኔታ የምትጨነቀው ደግሞ በወንዶቹ ፍላጐት መሆን የሚገባት ሳይከሰትላት ሲቀር፤ የትኛውን ሴት የመሆን ሞዴል መከተል እንዳለባት ሲጠፋትና በእንዴት ያለው ወንዶች በሚወዱት የሴቶች ምስል መሰረት መኖር እንዳለባት አልገባት ሲል ነው።)

የሴቶች ፍላጐት የት ነው? ግብ? ምርጫ? ህልም? ህይወት? ኑሮ? ...ከወንዶች አንፃር የሚቆመው እኩልነታቸው የታል? ሰውነታቸውስ? ክብራቸውስ? ነፃነታቸውስ? ...የራሳቸው የሆነው ፍርሃታቸው የትኛው ነው?

ሼላ ሮውቦታም የተባለች የሴቶች መብት አቀንቃኝ ..ሌላው ቀርቶ ፍርሃታችን እንኳን የእነሱ (የወንዶች) ነው.. ትላለች። ከፍርሃት አቅም የተውሶ የሆነበት ህይወት እንዴት ያለው ነው? የዘንድሮ ሴቶች ግባችሁን መርምሩ፣ ምርጫችሁን መርምሩ፣ ህይወታችሁን መርምሩ፣ ኑሮአችሁን መርምሩ፣ ከወንዶች አንፃር የሚቆመው እኩልነታችሁን መርምሩ፣ ሰውነታችሁን መርምሩ፣ ክብራችሁን መርምሩ፣ ነፃነታችሁን መርምሩ... ፍርሃታችሁን እንኳ የእናንተ መሆኑን መርምሩ...

የኖርዌይ ተወላጁ ፀሐፌ ተውኔት ሔነሪክ ኢ.ብሰን ለሴቶች ተቆርቋሪነቱ ይታወቃል። ከስምንት አመት ትዳር በኋላ ህይወትና ኑሮዋን የምትመረምር አንዲት ገፀ ባህርይ አለችው። ኖራ ሔልመር ትሰኛለች። ከልጅነቷ አንስቶ የነበረው ህይወቷ የአሻንጉሊት እንደነበር ትደርስበታለች። የተውኔቱ ርእስም “Dolls house” ነው (..የአሻንጉሊቷ ቤት..) የምትተኛ፣ የምትሄድ፣ የምታለቅስ፣ የምታወራ... እንዲሁም የምትወልድና የወለደችውን የምታሳድግ ህያው አሻንጉሊት። ዓለምና ሥርዓቷ ለሴቶች ገሃነምና የገሃነም ድንጋጌ እንደሆኑ ትደርስበታለች። ግጭት ውስጥ ትገባለች። በስተመጨረሻ ወላጆቿን፣ ባሏን፣ ልጇን፣ ቤቷን፣ አካባቢዋን... ለቃ ትሰደዳለች። “..ማነው ትክክል? እኔ? ወይንስ የተቀረው አለም?..” የመጨረሻ ቃሏ ነው።

የእኛ ሴቶች ጋ የሚጐድለው ይሄ ነው። ወደ ፋሽን ኢንዱስትሪነት በተቀየረው የወንዶች ፍላጐት ውስጥ መዳከራቸውን አይጠይቁም። የወንዶች አቅርቦት መሆናቸውን አይመረምሩም። ዳሌአቸው እንዲኮራ፣ ጡታቸው እንዲቀለበስ፣ አንጀታቸው እንዲሞት፣ አካሄዳቸው እንዲቀየር (ካትዎክ)... ሲጠየቁ ያለ ተጨማሪ ማብራሪያ ያደርጉታል። ያልተመረመረ ኑሮ ውስጥ የነፃነት ህይወት እንዳሌለ አይረዱም።

ሲወገዝ የነበረው አሮጌው ዓለም በአዲሱ ዓለም ውስጥ አድፍጦ ቀጥሏል። አሮጌው አለም ከወንዶች አንፃር ሴቶች ምን መምሰል እንዳለባቸው ናሙና ሲፈጥርና ሲያስፈፅም ቆይቷል። ጥንታዊዎቹ ሮማውያን ከሐብት ማካበት ፍላጐታቸው አንፃር ተነስተው ሴት ለሚስትነት ምራቋን ዋጥ ያደረገች ብትሆን የተሻለ እንደሚሆን ያስቡ ነበር። ከተቻለ ፊት ብትገኝ የካበተው ሃብት አይባክንም ይላሉ። በመሆኑም የዚያ ዘመን ወጣት ሴቶች በባህርይ ብቻ ሳይሆን በአቋምና በአለባበስም ፊት ለመምሰል ክፉኛ ይጥሩ እንደነበር ላውረንስ ይነግረናል። ቄሳሩ ኔሮ ለሴቶች የሚያወጣውን መስፈርት ቶሎ ቶሎ እየቀያየረ፣ የአገሪቱን ሴቶች በማደናገሩ ይታወቃል። ያም ሆኖ የዘመኑ ሴቶች በተለዋዋጩ የቄሳር መስፈርት ልክ ..የተንጦለጦለ.. ለውጥ በማድረግ እራሳቸውን በተፈላጊነት ሲያወዳድሩ ነበር።

በዳግም ልደት ዘመን (Renaissances) ደግሞ የተማረች ሴት ተፈላጊነት እንዳላት መታሰብ ተጀመረ። ለዚህ እንደ ዳንቴ ያሉ ደራሲያን ከፍተኛ አስተዋጾ እንዳላቸው ይወራል። ያም ሆነ ይህ የሴቶች ህይወት ከመፃህፍት ጋር የተጣመረ፣ ከግጥሞች ጋር የተዳበለ፣ የሙትንትን ኑሮ ሆነ። ቻርልስ ዲከንስ የተባለው እንግሊዛዊ ደራሲ

ቢ..ዬቪድ ኮፐርፊልድ.. ልቦለዱ ውስጥ ነፍስ ያላወቀች ሚስት ይዞ ብቅ አለ። ዶራ ትባላለች። ምዕራባዊው ወንድ ይቺን ሴት ናሙና አድርጎ ወሰደ። እንደ ውሃ ላይ ኩበት የሚዋልለው የሴቶች ህይወት፤ ሕፃን ልጅ መስሎ ወደ መታየት አዘነበለ። ቢራቢሮ ማባረር፣ ለአበባ ቀልብን ማጣት፣ በጨዋታ እራስን መሳት... የሴቶቹ የማስመሰል ውሎ ሆነ።

በኤልሳቤጣዊው ዘመን (16ኛው ክ/ዘመን) ደግሞ አንዳች አስፈሪ መስፈርት ለሴቶች ቀረበ። ዘመኑ ወንዶች ሐብት ለማሰስ እረጅም ጉዞ የሚሔዱበት ስለነበር፣ ባሎች የሚስቶቻቸው ነገር አሳሳቢ ሆነባቸው። በመሆኑም የወሲብ ፍላጎታቸውን ለመገደብ የሴት ልጅ ግርዛት መፍትሄ ሆኖ ቀረበ። በመሆኑም ሴቶቹ ያለ አንድ ተቃውሞ የሴቶች ግርዘት አስፈፃሚ ሆነው ተገኙ።

ዘመናችን ይሄንን የሴቶች ግርዘት አውግዞታል። ውግዘቱ ዘመን ስለፈቀደለት እየተተገበረ ይገኛል። ለመሆኑ ወደፊት የሴት ልጅ ግርዘት አስፈላጊ የሚሆንበት ዘመን ቢመጣና የተፈላጊ ሴት መስፈርት ቢደረግ ሴቶቻችን ይቃወሙ ይሆን? አሁን ባለው ሁኔታቸው አይመስለኝም!! እራቁት አደባባይ እስከመውጣት የቀበጠውን የወንዶች መስፈርት አስተግብረው የለም? ለሚሸፋፈነው ለግርዘት ገመና መልሳቸው እንቢ ይሆናል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው።

# ሰውና ድክመቱ ፲ ከወዴ ሐዋሳ

የዛሬ አሥራ አራት ... ወይም አሥራ አምስት ዓመታት ገደማ ...

.... ሀዋሳን ለመጀመሪያ ጊዜ አየኋት። ነገር ፈላጊ ዝናብ ተንኩሷት የሚፏለለው አቧራዋ አድፍጧል። ሁሉን መርማሪ ልሁን ባይ ነበርኩና አጎንብሼ መሬቱን ዳሰስኩት።

ዱቄት የተነሰነሰበት አምባሻ የዳሰስኩ እስኪመስለኝ ለስልሷል። ሙቀቷ ግን ለዝናቧ አልተጎናበሰም። እንደውም "ምን ሲደረግ?" ያለ ይመስል በወበቅ ልብስ ለማስወለቅ ይተናነቃል ...

... ሀዋሳን ሳላውቃት በጋዜጣ ለማስተዋወቅ መምጣቴ ለእኔው አስገርሞኝ ፈገግ አልኩ። የማያውቅ ያስተዋውቃል? ስል እራሴን ጠየኩ። ወለፈንዲ ይሏል ይሄ ነው። የሥነ ማህበረሰብ (Anthropology) ዘመናዊ ድምዳሜ እንደ እኔ ያለ እንግዳ ሰው፣ ለእንግዳ ማህበረሰብ ጥናት ልከኛ እንደሆነ ይጠቁማል። እንደውም በሁሉም ነገር መደነቁ ሳይረግብ ጥናቱን ቢያከናውን ይመረጣል ይላል። አለበለዚያ ይላመድና ችላ የሚለው ይበዛል።

ሀዋሳ ኮረዳ ከተማ ናት። ነባርና ባህላዊ መሽኮርመሟን ዘመናዊ ግዴለሽነት ሊረታው የሚተናነቃት። ጉራማይሌነት የጎላባት። የራሷ የሆነና ያልሆነ ፍልሚያ የገጠመበት መልክ አላት። ለእኔ ሁሉም ነገር አዲስና እንግዳ ነገር ነበር። ሌላው ቀርቶ በጋሪ ላይ የተጫኑት ሙዞች ግራ አጋብተውኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። እንደ መጥረቢያ ብረት የተጠፈጠፈ ሙዝ ስመለከት የመጀመሪያዬ ነበር። የሙዝ ዝንጥፍ ከእነ ቅርንጫፉ የተቆጣ ጃርት መስሎ መቅረቡ ለእኔ እንግዳ ነገር ነበር።

ያኔ ሀዋሳን ለማስተዋወቅ ከጣርኩበት ውጣ ውረድ በላይ ሀዋሳ እኔን ከተፈጥሮዬ ጋር ያስተዋወቀችበት ገጠመኝ የዕድሜ ልክ ስንቄ ሆኖ ቀርቷል። ያኔ ሰው ሌላውን

ከሚያስተዋውቅ እራሱን ቢጠይቅ ምን ያህል በበጀው ስል የደመደምኩበት ገጠመኝ ነበር። እንዲህ...

... ወደ ሀዋሳ ጤና ቢሮ ጎራ ብዬ አንዳንድ መረጃዎችን ቃረምኩ። መረጃዎቹ ኤችአይቪን ከመከላከል አኳያ ተስፋ የሚጣልበት ድርጅት እንደተቋቋመ ጠቆሙኝ። ሊቀመንበሯ ወ/ሮ ብርሃኔ ነበረች። አገናኙኝ። ድንቡሽቡሽ ክብ ፊት። የቀነበረ መልክ አላት። በፈገግታ ተቀበለችኝ። (ባልሳሳት) የማህበሯ ሥም "ንጋት የሀዋሳ ሴቶች የፀረ ኤድስ ማህበር" ነበር። ወ/ሮ ብርሃኔ ቀደም ሲል "የተስፋ ጎህ ኢትዮጵያ" የሀዋሳ ቅርንጫፍ ኃላፊ ነበረች። እሱን ትታ ነው ፆታ ነክ ማህበር ያቋቋመችው።

ለምን?

ወ/ሮ ብርሃኔ ፊቷ ላይ የወጣችው ፀሐይ የጠለቀች መሰለች። ለአፍታ ዝም ብላ ቆየችና በረጅሙ ተነፈሰች። ጠበኳት፤ "እንዴት እንደምነግርህ አላውቅም ..." አለችኝ።

"ግዴለም እንዴትም አድርገሽ ንገሪኝ" አልኳት።

የተደላደለ ሰውነቷ በጥልቅ መሰረት ላይ እንደተገነባ ሁሉ መነቃነቅ ጭንቁ ይመስላል። ግን ያላትን ያህል ቅልጣፌ አላጣችም። በመነሳት የቃለ ምልልስ ቅርፅ የያዘ አቀማመጣችንን አፍርሳ አጠገቤ ተቀመጠች።

"አየህ፤ ተራ የፆታ መቆርቆር ኖሮኝ በአክራሪ ሴትነት ይሄን ማህበር አላቋቋምኩትም። በተጨባጭ ሳየው የቆየሁት ነገር ህመም እየሆነ ስላስቸገረኝ ነው" አሁንም በረጅሙ ተንፍሳ፤ "ስንቴ እንበደል?" ስትል ጠየቀችኝ።

የምለው ግራ ገብቶኝ ዝም አልኩ።

"በሐዋሳ የተስፋ ጎህ ቅርንጫፍ ሀላፊ እያለሁ የሚያሙ ብዙ ነገሮች አጋጥመውኛል። አብዛኛዋ ሴት ለህመሙ የተጋለጠችው በራሷ ምክንያት አይደለም። በተለይ ባለትዳር ሴት ... እሱን እንተወውና እዚያ አዲስ አበባ ያሉት የማህበሩ አንዳንድ አመራሮች ፌውዳልነት እየተሰማቸው ከመጡ ቆዩ። አዲስ ሴት አባል መጥታ እዚህ ስትመዘገብ መልከ መልካም ከሆነች ፎቶዋን እያዩ ወደ አዲስ አበባ እንድትላከላቸው ይጠይቃሉ። ያማል! ያቺ ሴት ወደዚያ ከሄደች በመደለል

ወይም በማስፈራራት ሌላ ነገር .... ስንቴ እንበደል? እነዚህን ሴቶች ነፃ ለማውጣት ያቋቋምኩት ማህበር ነው።"

ዝም! የተደላደለ እውነትን የሚያዛባ መልስ ነበር። ያኔ በግለሰቦችና በጥቂት ሰዎች ላይ እንዳኮርፍ የሚገፋፋ ስሜት አድሮብኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ሰዎቹ በግል ድክመታቸው ተጠልፈው እንደተወለካከፉ ቆጥሬው እነሱን ባላገኝም ከምስላቸው ጋር ተሟግቼ ለመርታት ዳድቶኝ ነበር። የሰው ልጅን እና ዓለምን ፍፁም አንፅቶ መመልከት የሚያስከትለው ድምዳሜ ድክመቴ እንደሆነ እስካውቅ ድረስ ቁጣው ከእኔ ጋር ቆየ። ሰውንና ዓለሙን በምልአት ማወቅ አይከጀል ይሆናል፤ ያም ሆኖ "ሰውን ሰው ያደረገው ድክመቱ ነው" ለማለት የሚያስችሉ ምሳሌዎችን ለማግኘት የሚገድ አይሆንም። ያኔ ለሰው ልጅ አፈጣጠር ማዘን ይከተላል። "የሰው ልጅ በእንዴት ያለ ድክመቱ ላይ እንዴት ያለ መስቀል ተሸከሞ፣ ምን ያለ ተራራ እንዲወጣ ተፈረደበት?" ያስብላል። "በእኛ ይብቃ፣ ትውልድ ይዳን" የሚል መሪ ቃል ሥር እንኳን ሆን ተብሎ በስህተትም የሚዛነፍ ነገር የሚኖር አልመሰለኝም ነበር። ሁሉም አእምሮውንና ልቡን በገዛ ጓጉንቸር እንዳይከፈት አድርጎ በዘጋበት በዚያ ወቅት የተስፋ ጎሕ አባል መሆን ለመጠቋቆሚያነት እራስን አሳልፎ ከመስጠት ወዲያ ምን አለ? ለአንድ ግለሰብ ጊዜ የፈቀደው ነብይነት አልነበረም? የሰው አይን እንደ አንበሳ የሚሰብረው ፍላጋ የፈቀደው ሐሜትን ፈለግ አድርጎ በሚንጎማለልበት በዚያ ወቅት "ኑ እዚህ አለሁ" ማለት ከሰውነት ውጭ ከመለኮታዊ ተግባር ፈፃሚነት አያስመድብም? ... ግን እዚያም ሰውና ድክመቱ አሉ። ወ/ሮ ብርሃኔ እንደ አውሎ ነፋስ የገለበችው "ክንብንቤ" መራቆት እንዲሰማኝ አደረገኝ። የተነገረኝ እውነት ሆነ አልሆነ እዚያ ሰውና ድክመቱ አሉ። ሥጋ በመንፈስ ላይ ቢያደፍጥ እንጂ ጨርሶ አይረታም። የመብላትና የፍትወት ፍላጎት ከመናኒያን ደጅ እንኳን ጨርሶ ፈቅ የማይሉ የሰው ልጅ ሁሉ ንቁ ጠላቶች ናቸው። በይበልጥ እንደ ልቡ መብል ያገኝ ያለ ፍትወት ጥያቄ ማደር የማይወጣው አቀበቱ ነው። መንፈሳዊዎቹን እንኳን "ህልመ ሌሊት" እና "ሶፊያ" በሚል የሚጠሩት የፍትወት እንቅፋት መንገዳቸውን ሞልቶታል። ምክንያቱም እዚያም ሰውና ድክመቱ አሉና።

በተፈጥሮ ህግ መብላት ህይወትን ማቆየት ነው። ህይወት የሚቆየው ደግሞ ዘር ለመተካት ነው። ዘር መተካት ዞሮ ህይወት ማቆየት ይሆናል። የሰው ልጅ የዚህ አዙሪት ተሽከርካሪ ባለዕጣ ነው። ህይወት ለሰው ልጅ ፍርጃ ከመሆን እራሷን የምትሸሽገው በመብላትና በፍትወት ውስጥ ደስታን በማኖሯ ብቻ ነው። ደስታን

በመቻት በህይወት ተኮድኩደን በኑሮ እንገፈግፋለን። ዘር መተካት እስከመጨረሻዋ እስትንፋስ ድረስ የምንከፍለው ዕዳችን ነው። ስለ ዘር መተካት አካል ቢደክም እንኳን ፍላጎት አይረግብም። ዓለም እራሷ የመብላትና የፍትወት ውጤት ናት። "የከንቱ ከንቱ፣ ከንቱ ነው" እስክንለው ድረስ የምናከማቸው መብላትና ፍትወትን ነው። ወርቅ ውስጥ የመብላትና የፍትወት ልኬቶች አሉ። ሐብት መከመር፣ ህንፃ መገተር፣ አየር ማሽከርከር ... ከበስተጀርባው መብል የመራብና ፍትወት የመጠማት ፍርሃት አለ። ከመጥገብና ከወሲብ በኋላ ዕዳን የመከፈል ፍፁም ሰላምና ድካም የሚሰፍነው ለዚህ ነው።

ማርቀቅና ማጥለቁን ትተን ወደ "መሬት" እንውረድ። ብርሃኑ ዘሪሁን እንደ ቡና ሥርዓት በሦስት የሚያከትም ታሪክ ቀመስ ልቦለድ አለው። "ማዕበል - የአብዮት ዋዜማ፣ የአብዮት መባቻ እና የአብዮት ማግሥት" የሚል። ለአብዮቱ መፈንዳት በማቀጣጠያነት ወሎን በአካል ጐብኝቶ ልቦለዱን እንደፃፈው "የካቲት" መፅሔት በ1972 ዓ.ም ባደረገለት ቃለ ምልልስ ላይ ገልጿል። እዚያ ረሃብ በለሸለሸውና ባሟሸሸው ህዝብ መካከል ሰውና ድክመቱ አልቀሩም።

እንዲህ ይገልፀዋል፡- "ሕይወት እስካለ ድረስ የተፈጥሮ ፍላጐቶች፣ የተፈጥሮ ስሜቶችና ባህርዮች አሉ። በዚያ በተጨናነቀ ሰፈር (መጠለያ) መካከል ወንድና ሴት በጋቢ ውስጥ ተሸፍነው በደከመ ሰውነት የፍቅር ስሜታቸውን ይወጣሉ። ሌሎች አይተው እንዳላዩ ያልፏቸዋል። ለደስታና ለምኞት ኑሮ ተስፋ ቆርጠው የመጨረሻ ኃይላቸውን ለወሲብ ስሜታቸው ብቻ በማዋል እንደተቃቀፉ ምናልባትም ከጭንቀት የተነሣ እንደተጣበቁ ሞተው የሚገኙ ባልና ሚስት አሉ። ሞት በሚወስደው ህይወት መጠን በዚያ መጠለያ ውስጥ ብዙ ህይወት ይዘራ ነበር" (ገፅ 81)

ተፈጥሮ ጨካኝ አራጣ በሊታ ናት። ከሰጠችን ይልቅ የምታስገፈግፈን የትየለሌ ነው። ታመን አንተኛም፣ ደክመን አናርፍም። ተርበን እንኳን ዕዳ ከመገፍገፍ አንታገስም።

ኡፍፍፍፍ!!

# መርሳት ፲ አንዱ ጥበብ ፣ ሌላው ጀሃነብ!

ስለመርሳት ሳስብ ሁለት ሰዎች አስታውሳለሁ፤ አንዱ... በመርሳት የታወቀ፣ ወይም የመርሳት ተሰጥኦ ያለው አለበለዚያም የመርሳት ችግር ያለበት አንድ ልጅ አለ። ለመርሳት ፣ የሚያሳየው ፍጥነት ከዕለት ወደ ዕለት ጨምሮ ወደ መጨረሻ ገደማ እያወራም መዘንጋት ጀመሮ ነበር። ለምሳሌ፡-

አንድ የጎረቤት ሰው መጥቶ "ቹቹ፤ እናትህ አለች?" ሲለው

"የለችም" ብሎ ይመልሳል

"የት ሄደች?" የሚል ጥያቄ ሲደገምለት እረስቶ

"ማን?" ብሎ መልሶ ይጠይቃል

"እናትህ?" ሲሉት

"እራስህ እናትን" ሲል ለፀብ ይጋበዛል።

...ሌላኛውን የተዋወቅሁት ነፍሱን ይማርና በአያሻረው (አስማማው ኃይሉ) ወግ ነው። አሜሪካ ውስጥ ለሠላሳ አምስት አመታት የኖረ የኢህአሠ (የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ሠራዊት) ታጋይ ነው። በመጨረሻ ዕድሜው ላይ ሁሉን በመርሳት የአእምሮ ህመም (Alzheimer) ተያዘ። ዘመድ፣ አዝማድ ብቻ ሳይሆን ቋንቋ ሁሉ ጠፋው የአፍ መፍቺያ ቋንቋ ተራ ቱማታ በሆነበት ወቅት አንድ ቃል ብቻ አልጠፋውም ነበር፤ ያም ቃል የትግል ሥሙ የነበረ ነው። "በትግል ስሙ ሲጠሩት ይዞራል" ብሎ አያሻረው አለቀሰ፡-

በእርግጥም ያስለቅሳል። ያ የትግል ሥም ምን ትኩረት ቢሰጠው፣ እየትኛው የአንጎሉ ጥግ ቢወሸቀው ትውስታን ሁሉ ከሚያጠፋው የአእምሮ ወረርሽኝ ተረፈ?

ከበሽታው በላይ የትግል ሥሙ ተአምር አይሆንም? ከበሽታው ባሻገር በዓመታት መግፋት በራሱ ጊዜ ሊጠፉ አይገባውም ነበር?

...ሰው እራሱ ተአምር ነው። ትኩረት የማይሠጠው በሰከንዶች ሽራፊ ከአእምሮው ሲያስወግድ፤ አክብዶ ያየውን ደግሞ እንደ መክሊት ላያተርፍበት አእምሮው ውስጥ ቀብሮት ይኖራል። ከማስታወስ ይልቅ መርሳት እንደ ጉድለት ስለሚታይ፣ የሰው ልጅ የመሳትን ምንጭ ለማግኘት ብዙ ዳክሯል። የሥነ ልቡና ምሁራን፤ ለምን እንረሳለን? ለተሰኘው አውራ ጥያቄ መንታ ምላሾችን ያቀርባሉ። አንዱ ሊታወስ የሚባው መረጃ፣ ከቦታው ሲጠፋ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መረጃው ቢኖርም አንቅቶ ለመጠቀም ሲያዳግት ነው ይላሉ። ነገርየው የቀበሌ መዝገብ ቤት መሰለ እንዴ? "ፋይልህ ጠፍቷል" ለካ ተፈጥሯዊ ነው? ስንቀጥል....

...ስለመርሳት ሳስብ ሌሎች ሁለት ሰዎች ትዝ ይሉኛል። አንዱ እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ በርናንዶ ሾ ነው። በባቡር ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ እየተጓዘ ነው። ፈርማታ ላይ ትኬት ተቆጣጣሪው፤ ሾ ወዳለበት ፉርጎ ገብቶ፡-

"ትኬት አውጡ፣ ትኬት" ሲል ጮኸ።

ሾ ከተመሰጠበት ተናጥቦ ትኬቱን መፈለግ ይጀምራል። የደረት ኪስ፣ የጎን ኪስ፣ የኋላ ኪስ፣ የውስጥ ኪስ፣ የቦርሳ ኪስ፣ የምስጢር ኪስ፣ የፓንት ኪስ.... ትኬት የለም። ተበሳጨ። የፈተሻቸውን ኪሶች መልሶ ፈተሸ፤ አጣው።

ትኬት ተቆጣጣሪው ትኬቱን እንዳጣው ስለገባው፤

"ሚስተር ሾ፣ እርስዎን የማያውቅ ሰው የለም። ቀስ ብለው ይፈልጉት፤ ካጡትም ግዴለም፤ እርስዎ ያጭበረብራሉ ተብሎ ስለማይታሰብ ይጥፉ!" አለ።

ሾ ቱግ ብሎ፤ "ትኬቱን ላንተ የምፈልገው መስሎሃል? ለእኔ ነው፤ የምሄድበትኮ የተፃፈው ትኬቱ ላይ ነው" ለካ መሄጃው ጠፍቶታል። ይሄ መርሳት የጭንቀትላት ጉድለት አይሆን እንዴ? የሾን የመርሳት ልክፍት በሁለተኛው በአይዛክ ኒውተን እናፅናው።

የሒሳብ ሊቅ ሰር አይዛክ ኒውተን፤ በሥራ ከሚጠመድበት ክፍል ፊት ለፊት ጠረጴዛ ላይ የሚመገበው ይቀመጥለት ነበር። እንዳይረበሽ ነው። በሆነ ሰዓት ወጥቶ ይመገብና ተመልሶ ይገባል። አንድ ቀን ግን አንድ ወዳጁ በቀጠሮ መጥቶ

ሲጠብቀው፣ የምግቡን "ጥሬ" መቋቋም ተሳነው። በዚህ ላይ ርቦታል። ቀርቦ መመገብ ጀመረ እስኪጨርስ ድረስ ኒውተን አልወጣም። በኋላ ብቅ ሲል ሰሃኑ ባዶ ነው። እንዲህ አለ፡-

"አይ የኛ ፈላስፎች ነገር! እራት ያልበላሁ መስሎኝ ልበላ መውጣቴ ነበር። ለካ አቀላጥፌው ኖሯል። (How absent we philosophers are, I realy thought that I had not dined)

አለማስታወስ የበሽተኞች ወይም የደደቦች አለበለዚያም የልበ-ቢሶች ብቻ እንዳልሆነ በበርናርድ ሾ እና በኒውተን ያረጋገጥነው ጉዳይ ይመስላል። ታዲያ መርሳት ምንድነው? የማነው? ጉዳት አለው? ጉዳቱ እንዳለ ሆኖ ጥቅምስ? እያልን በጥያቄ መታጠር የሰው ልጅ ሁሉ ባህርይ ነው። የቼኩ ደራሲ ሚላን ኩንዴራ (Milan Kundera) መርሳት ላይ ያተኮረ አንድ ልቦለድ አለው። "The book of Laughter and Forgetting" የሚል። ገፀ-ባህሪዎቹ እንደ ደሴት የተከፋፈሉ ታሪኮችን የሚያስተዳድሩ (እንደ አዳም ረታ) ናቸው። የአንዱ አንባ ታሪክ ገዢ ሚርክ (Mirek) ማስታወስን የሥልጣንና የበላይነት ምንጭ አድርጎ የሚናገርበት ጥቅስ አለው። (The struggle of man against power is the struggle of memory against forgetting) ይላል። ትውስታውን የሚያነቃ የኃይል ባለቤት ከሆነ፣ የማያነቃው የደካማነት ድልድል ውስጥ ይገባል ማለት ነው? እንዲህ ከሆነ በዝንጋኤ ታሪክ የተጥለቀለቀ የህይወት ታሪክ ያላቸው ደራሲዎች፣ ሳይንቲስቶች፣ የሂሳብ ሊቆች ... እንዴት ማስደግደግ ቻሉ?

ጀርመናዊው ፈላስፋ ፍሬዲሪክ ኒች (Friedrich Nietzsche) በመርሳት ላይ የኩንዴራ ተቃራኒ አቋም ያለው ይመስላል። ነገሮችን ለመርሳት አለመቻል፣ ለመኖር አለመቻል ነው በሚል። ታሪክን (ታሪክ ማስታወስ አይደል?) የሚያብጠለጥል አንድ መፅሐፍ አዘጋጅቷል- "Disadvantage of History for life" የሚል እዚህ መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ የሚል አባባል አለ፡-

"መርሳት ባይኖር መኖር ጨርሶ አዳጋች ይሆን በነበር" (without forgetting it is quite impossible to live at all)

ለሰው ልጅ የማስታወስ ጥበብ ብቻ ሳይሆን የመርሳት ክህሎትም ያስፈልገዋል ማለት ነው። ነገሮችን በመርሳት የሚቸገሩ እንዳሉ ሁሉ ለመርሳት ባለመቻልም የሚሰቃዩ ሞልተዋል። በቀላሉ የጦርነት፣ የግርግር የሽብር ሰለባ የሆኑ ግለሰቦችን

ማሰብ ይበቃል። በቀይ ሽብር ዘመን ልጆቻቸውን ያጡ አንዲት እናት ታሪካቸውን ሰምቻለሁ። ልጃቸው ከተገደለ ከአርባ ዓመት በላይ ቢያስቆጥርም እናቲቱ አሁንም የልጁን አልጋ እያነጠፉ፣ ቤቱን እየጠረጉና ውኃ በጠርሙስ እየሞሉ "አትንጫጩ፣ ይተኛበት" ይላሉ አሉ። ይሄ መርሳት አለመቻል፣ ከእውነታ ሲያቆራርጥ አይደለም? ታዲ ኒቼ... ይሄን እንጂ ሌላ ምን አለ?

ስቲፈን ካርፔንተር (Stephen Carpenter) የኒቼን ሀሳብ የሚደግፍና የሚያስደግፍ አቋም ያለው ሰው ነው። ነገር ግን ካርፔንተር መዘንጋት ያለባቸውን በብዛት ይመጥናቸዋል እንጂ እንደ ኒቼ በጅምላ አይፈርጅም። እንዲህ ይላል:-

"መኖርን ለማስቀጠል ካሻህ መረሳት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ።" (There are things that have to be forgotten if you want to go on living) እዚህም ላይ የማስታወስ ብቻ ሳይሆን የመርሳት ጥበብን መማር ሊጠበቅብን ነው ማለት ነው። የሥነ ልቦና ኮርስ 101 (መተዋወቂያ) የማስታወስ ብቃትን እንዴት ማዳበር እንደሚቻልና እራሱ የማስታወስ ባህርይ ምን እንደሚመስል የሚተነትን ምዕራፍ አለው። አእምሮ መረጃዎችን የሚደረድረውና ሲያስፈልግ የሚያቀርበው ነገሮችን ዘርፍ፣ ባህሪና አዝማሚያ እያለ በመደልደል ነው አሉ። መቅደስ እና ቅድስት የተባሉ ስሞችን በባህሪና በድምፅ ዘርፍ ስለሚመሳሰሉ አእምሯችን መመዝገብና ሲያስፈልግ ፋይሉን አውጥቶ ማቅረብ የሚቸገረው ለዚህ ነው። ስለዚህ የነገሮችን አምታቺ ባህሪያት አራግፎ ለአእምሮ ማቅረብ ለማስታወስ አይነተኛ መፍትሄ ነው።

ለምሳሌ ስልክ ቁጥሮችን በጥሬው ለመያዝ ከመሞከር፣ ከሁነቶች ጋር አዛምዶ ማጥናት ከተወለድንበት ቀን ጋር፣ ከአውቶቡስ ቁጥር ጋር ከፔሬዲክ ቴብል ንጥረ ነገሮች ቁጥር ጋር ... የስልክ ቁጥሩን ማዳበል።

ማስታወስ መቻል ለመርሳት ከመቻል በላይ ቀላል ነገር ይመስላል። ከባድ ጉዳት ያላቸውን መጥፎ ገጠመኞች መርሳት እንጂ የሚያስፈልገንን መዘንጋት አይደለም። ውጥንቅጡ የአእምሮ ጉዳይ ውስጥ ገብተን ጨዋታችንን ውጥንቅጥ ውስጥ ከማስገባታችን በፊት ወደ ታላላቆቹ ዝንጋኤ ነገር እናምራ። አንድ እንጥቀስ። አሜሪካዊው ተመራማሪ ቶማስ አልቫ ኤዲሰን፤

ኤዲሰን አረጅም ጊዜውን የሚያሳልፈው የምርምር ክፍል ውስጥ ነው። ግድ ካልሆነበት አይወጣም። ማርጋሬት ካውሲን የፃፈችው የህይወት ታሪክ መፅሐፍ

(The man who Lighted the world) ውስጥ አንድ ጊዜ የረሳውን ነገር ትተርካለች፡-

ለሚሰራቸው ስራዎች የመንግስት ግብር ለመክፈል ወደ ከተማው ማዘጋጃ ቤት ሄዶ ነው አሉ። የግብር መክፈያ ጊዜው ሊጠናቀቅ አንድ ቀን ብቻ ቀርቶታልና ወረፋው ረጅም ነበር። ኤዲሰን ተሰለፈ። ቢሰለፍም የሚያውጠነጥነው ስለ ሳይንስ ምርምሩ ነውና ከቀልቡ አልነበረም። ወረፋው ደርሶት ግብር ተቀባዩ መስኮት ጋ ሲደርስ አንድ ጥያቄ ቀረበለት፡-

"ሥም?" የሚል

"የፈጣሪ ያለህ ዘንግቼዋለሁ። ኧረ ስሜን እረስቼዋለሁ" አለ። አሰበ። አውጠነጠነ። ስሙ ጠፋው።

"ሥምዎ ከጠፋዎ ምንም ማድረግ አልችልም፤ ዘወር ይበሉ" ብሎ ቀጣዩን ግብር ከፋይ ተካ።

ኤዲሰን ግብር ሳይከፍል ዛሬን ካሳለፈ ለነገ ቅጣቱ ብዙ ብር ነውና ጨነቀው። ከግቢው በመውጣት ሰዎች እያስቆመ፤ "ታውቁኛላችሁ? ሥሜ ማነው?" እያለ መጠየቅ ጀመረ። እንደ ዕድል ሆኖ አንድ የሚያውቀው ሰው አግኝቶ ስሙን ነገረው። እ-ፎ-ይ!!

ለመሆኑ እናንተ ሥሙ የጠፋው ሰው መንገድ ላይ ቢያጋጥማችሁ ምን ይሰማችኋል? ቂል? የአእምሮ ህመምተኛ? አጭበርባሪ?... ወይስ ምን? መጠርጠር ደግ ነው፤ እርሱ የአምፖልን መብራት ጨምሮ ከአንድ ሺህ በላይ ሳይንሳዊ በረከት ጀባ ያለን ቶማስ አልቫ ኤዲሰን ሊሆን ይችላልና።

## ሠለስቱ "ፋሲካዎች"

"በአዘቦት ተርፎ ያልተጠራቀመው በፋሲካው ከየት ይገኛል?"

እንኳን ለትንሳኤ በዓል አደረሳችሁ!!

ሦስት ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሉ፤ ፋሲካን ተገን አድርገው ወደኛ ሲመጡ ያገኘኋቸው። ሌሎች ተረቶች ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ። "አንዳንዴ እንዲህ ነው" አለ ዘፋኙ! አለምን እጃችን ላይ ካለው አንፃር ብቻ እንመዝን ዘንድ የተገደድን ፍጡሮች ነና! ደግሞስ እጃችን ላይ በሌለን ምን መብት አለ? ቶሎ እጃችን ላይ ወዳሉ ተረቶች፦

ፋሲካን ያሉ ህማማትን ተቀበሉ (አሀዱ)

ፋሲካን ሊያገኙ ሁዳዴን ይመኙ (ክሌዕቱ)

ፋሲካ የሌለው ጦም ደስታ የሌለው ዓለም (ሠልስቱ)

አበው እና እመው ባህርን በነጥብ የሚወክሉ የሐሳብ ጂኦግራፊሮች ናቸው። እንዳልተረጋጋ ሰው "ጓዘ ቀልጣፋነት" የህይወታቸው መርህ ነው። የተንዛዛውን፣ የተብዛዛውን በኢምንት ቋጠሮ ወክለው የመጓዝ ህይወታቸውን ያቀልላሉ። ዋርካን ያህል ሃሳብ፣ በዘር ፍሬው ወክለው ባሻቸው ጊዜ ሲተክሉት ሊያገኙት...

አሀዱ "ፋሲካን ያሉ ህማማትን ተቀበሉ"

አበው እና እመው የቋጠሩትን እኛ ልናባዝተው ነው።

እዚች ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ “ፋሲካ” ተስፋን ወክሏል። የዛሬን መከራ (ህማም) የምንታገሰው ነገ ላይ ተስፋ (ፋሲካ) ስትንጠለጠል ነው። ተስፋ የሌለበት ምድር “የራስ አጥፊዎች” ሀገር ነው። ይሄንን የሰው ልጅ ባህርይ የጥንቶቹ ግሪኮች (ከእኛ ላይቀድሙ ቢችሉም) ተረድተውታል። (እንደ እኛ ቀልጠፍ አድርገው ባይሸከፉትም) አንዛዝተው ገልፀውታል።

እንዲህ...

...በግሪኮቹ “ዘፍጥረት” በመጀመሪያ “ባዶ” ነበረ፣ አማልክቶቹ ያንን ባዶ ይገዙ ነበረ፤ ከተራራ፣ ከዱርና ከውቅያኖስ በስተቀር የሚንቀሳቀስ ፍጡር መታጣቱ አይናቸውን ይቀለው ጀመረ። ስለዚህ አማልክተ - አማልክቱ ዚወስ፣ ፐሮሚቲየስና ወንድሙ ኢፒሚቲየስን ጠርቶ “ሂዱ ፍጠሩ፣ ምድርንም ሙሏት” አላቸው። የተሰናዳችውን ምድር በፍጡር የሞላት ኢፒሚቲየስ ነው። ኤሊ ይፈጥርና ድንጋይ ያለብሰዋል፤ ፈረስ ይፈጥርና ውብ ጋማ እና ጭራ ይሰጠዋል፣ ወፍን ይፈጥርና ክንፍ ይቸረዋል። ፕሮሚቲየስ ይሄን ሁሉ ያይና በመጨረሻ የአማልክቱን አምሳያ ከአፈር ይፈጥረዋል። እንደ እንስሶቹ በአራት እግሩ አይሄድም፣ ምድርን ብቻ አያይም፣ ወደ ሰማየ ሰማያትና ወደ ኮከቦቹ ይማትራል። ከዚህ ሁሉ በኋላ በአማልክቶች ዘንድ ብቻ የሚታወቀውን የእሳት ምስጢር ሰጠው።

ዚወስ ተበሳጨ፤ ፕሮሚቲየስን ወቀሰ። “የጭቃ አሻንጉሊትህ በኛ ፊት ግርማ እንዲያገኝ አደረክ፣ የእሣትን ምስጢር ሰጠህ፣ ቀና ብሎ ኮከቦችን እንዲማትር ፈቀድክ...ለዚህም ቅጣት ታገኛለህ።” ፕሮሚቲየስን የስቃይ አዙሪት ውስጥ ከተተው፤ አይሞትም ግን ተራራ ላይ ታስሮ በንስሮች ገላውን ይቦጠቦጣል። የዚወስ ንዴቱና ቅጣቱ ወደ ፍጡሩ ሰውም ዞረ። ቅጣቱ ግን ተዘዋዋሪ እንዲሆን በመፈለጉ አማልክቶች ተሰባስበው የመጀመሪያዋን የግሪኮች ሔዋን ፈጠሩ። ቬነስ የተሰኘው አምላክ ውበት ሰጣት፣ ሜርኩሪ ቀልጣፋ ምላስ ቸራት፣ አፖሎ የሙዚቃ ጥበብን አደላት... ፓንዶራ ተባለች።

ነገር ለማይገባው ለኢፒሚቲየስም ተዳረች። ለሠርግ ስጦታቸው አንድ የታሸገ ሳጥን ሰጣቸው።

የስጦታ ሳጥኑን በፍፁም መክፈት እንደሌለባቸው ዚየስ ነገራቸው። (እንደኛ ዕፀ በለስ ፍሬ መሆኑ ነው)

በዚያ የግሪኮች ጊዜ፣ በዚያ የግሪኮች ምድር ምንም ክፋት አልነበረም። መጥፎ ነገሮች ሁሉ አይታወቁም ነበር። ፓንዶራ ከባሏ ተደብቃ ሳጥኑን እስክትከፍት ጊዜ ድረስ ሞት፣ ጦርነት፣ ስስት፣ ክፋት፣ ምቀኝነት፣ በሽታ፣ እርጅና፣ ጥላቻ፣ ጭካኔ...የታሰሩ ነበሩ።

በግሪኳ ሄዋን ከሳጥኑ ውስጥ ተለቀቁ፤ አለምን ናኙ። ፓንዶራ በድንጋጤ ሳጥኑን በፍጥነት ብትዘጋም ከአንድ ነገር በቀር ሁሉም አምልጠው ነበር። በመንቀራፈፉ ሳጥኑ የተዘጋበት "ተስፋ" ነበር። ከፓንዶራ ጋር ይደራደራል።

"ክፈቺልኝ፣ ተስፋ ነኝ፣ ያለ እኔ የሰው ልጅ እነዚያን መጥፎ ነገሮች ሁሉ ሊታገስ አይችልም።"

ፓንዶራ አመዛዘነች። ተስፋ እውነቱን ነበር። ስለዚህ ከፍታ ለቀቀችው። ተስፋ እንደዘጋበት ቢቀር ኖሮ ያንን ሁሉ ህማማት ማን ይታገስ ነበር?

ግሪኮች አንዛዙ፤ ዋርካን ነቅለው ከቦታ ቦታ የማጓጓዝ ሥራን ሰሩ። እኛ ግን ዋርካውን በዘር ፍሬው ወከልን፣ በወፍ ተንጠልጥሎ ከቦታ ቦታ የሚጓጓዝ አደረግን። ተክለን ስናበቅለው ይገዝፋል፤ ስናጓጉዘው ይቀላል። "ፋሲካን ያሉ ህማማትን ተቀበሉ"

ከዕሌቱ "ፋሲካን ሊያገኙ ሁዳዴን ይመኙ"

አበውና እመው ቋጥረው የሰጡንን እኛ ፈትተን ዘርዝረን እንመልከት። እዚችኛዋ ምሳሌ አነጋገር ውስጥ "ፋሲካ" ደምወዝን ወክሏል። የድካም ግኝት፣ የልፋት ውጤት ተደርጓል። የዘመኑን የአቋራጭ ውጤት "የማሣለጫ ጉዞ" ይሄ ተረት አይወክልም። ከስቃይ በኋላ ፈውስ፣ ከድካም በኋላ እረፍት፣ ከመራብ በኋላ ጥጋብ እንዳለ ይሄ ተረት ይፈክራል። ለዛሬ መማሰን ነገ ላይ የተንጠለጠለችው ደምወዝ ምክንያት ናት። አንዳንዴ በደል ካሣ አለው፤ ጥቃት በቀልን ያውጃል። መረገጥም...

...አንድ ተረት ትዝ አለኝ። ቅቤና ማር ከአንድ ቤት ወጥተው ገበያ ደረሱ አሉ። ገበያውም ቀንቷቸው ለአንድ ሰው ተሸጡ። ገዢ ቤት እንደደረሱ ግን ቦታቸው

ተለያየ። ማር ባለበት ደረጃ ሲቀጥል፣ ቅቤ ባለቤቱ እናት ላይ ሆነ። በነገሩ የተገረመው ማር ጥያቄእ ቀረበ፡-

"እያ ቅቤ ምነው እናት ላይ ወጣህ?"

"ስገፋ ስለኖርኩ" አለ አሉ።

"እናት ላይ መውጣትን ሊያገኙ መገፋትን ይመኙ" ልንል ይሆን? መገፋት እረዝሞ እናት ላይ መቆየት ቢያጥርም ግድ የለም። ሁሌም የደምወዝ ቀን የሥራ ቀንን እያከልም። ዋናው "እረፍ" ብሎ፣ ለመጓዝ የሚያስችል ጥላ በየመካከሉ መገኘቱን ማረጋገጡ ላይ ነው። ደራሲ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ህይወቱን በተመለከተ "የካቲት" መጽሔት ሚያዝያ 1978 ዓ.ም የሰጠው ቃለ ምልልስ ለዚህ ጉዳይ ትልቅ ምሳሌ ነው። ቃለምልልሱን ያቀረበው እሸቴ አሰፋ ሲተርከው እንዲህ ነበር ያለው፡-

"የስብሐት ቤተሰብ ኑሮ እጅግም የሚያወላዳ አልነበረም። ከእጅ ወደ አፍ እንኳ የሚሳካላቸው አይደሉም። ኩርማን እንጀራ በብዙ ጐመን አንጀቱም አይደርስለት። ገና ፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ የንግሥ ቀን የአዳጊው ወጣት የስብሐት የደስታ፣ እምብርቱ ፍም እስኪመስል የሚበላባቸው ውስን ቀኖች ናቸው። ደራሲ ስብሐት የልጅነት ረሃብ፣ ጊዜውን አሁንም አይረሳውም"፡-

ለጥቂቶች እነ "ፋሲካ" ከአዘቦት ቀን አኗኗር ጋር መለያየት አቅቷቸው ተመሳስለው ይሆናል። ለብዙዎች ግን እነ ፋሲካ በበረኻ መካከል እንደተገኙ የጉድጓድ ውኃዎች ናቸው። ጥምን አርክቶ፣ ለቀጣይ ጉዞ በጥቂቱ ስንቆ፣ ደግሞ "የበረሃ መንገድ" የሚቀጠልባቸው። በአመት ለአራትና ለአምስት ቀን መጥገብ ከሦስት መቶ ሃምሳ ቀናት በላይ የረበበውን ረሃብ ለመቋቋም ደሞዝ ይሆናል? ይገርማል!! ግን ደግሞ ከዚህም በላይ የሚገርም አይጠፋም።

ሦስቱ "ፋሲካ የሌለው ጠም ደስታ የሌለው ዓለም"

ማባሪያ የሌለው ዝናብ፣ መፍትሔ ያልተገኘለት ስቃይ፣ እረፍት የማይታሰብበት መማሰን፣ ዋጋ የማይቀጠብለት ልፋት አለ? ሌላው ይቅር እንዴት አዳጊው ወጣት ስብሐት በአመት በአላት አራት አምስቴ እንኳን አይታረፍም? ለምን?

እዚህ ውስጥ የተቀረቀረ ኑሮ ምን ህይወት አድርጐ አስቀጠለው?

Frank McCourt የአየርላንድ ተወላጅ አሜሪካዊ መምህር ነበር። ልጅነቱን በአንዴት ያለ መከራ እንዳሳለፈ የተረከበት መጽሐፍ አለው:: "Angela's Ashes" ይሰኛል። "ልጅነቴን መለስ ብዬ ሳስታውሰው፣ ያንን ሁሉ መከራ እንዴት ተቋቁሜ በህይወት እንደተገኘሁ ፍቺ አጣለታለሁ" ይላል። እናቱ አባቱን ጠባቂ የአምስት ልጆች እናት ናት። አባቱ ሥራ-ፈትና ሰካራም። በአዘቦት ቀን ቀርቶ በአውዳመትም ቤተሰቡ ይራባል። ስለዚህ ፍራንክ ማኮርት መንደርተኛው ለበአል ያረደውን የአሳማ ጭንቅላት እየዞረ ይለቅማል። "ፋሲካ የሌለው ጦም..." ማለት ይሄ ይሆን?

እዚህ እኛ ሀገር፣ እዚህ እኛ ከተማ ውስጥ የተሰራ ሌላ የኑሮ ጥናት ታትሞ አንብቤአለሁ:: "Urban Food insecurity and Coping Mechanisms" የሚል ርዕስ ያለው። አጥኚው ያሬድ አማረ ናቸው። ልደታ ክፍለከተማ ላይ መሠረት ያደረገው ይሄ ጥናት፤ ከተማችን ድምጽ በሌለው ሁኔታ እንዴት በችግር እንደምትንተከተክ የሚያሳይ ነው። ጥናት አቅራቢው ስለ አንድ ቤተሰብ ኑሮ እማወራዋን አናግሮ ይሄን ቃሏን አስፍሯል፡- "በየሦስትና በየአራት ቀኑ ጨርሶ የሚበላ ነገር የሚጠፋበት ጊዜ አለ። ይሄንኑ ለልጆቼ ስነግራቸው አፋቸውን ሳይሽሩ ቤቱን ለቅቀው ይወጣሉ። ያለ ቀን ደግሞ እንጀራውን እቆራርስና ጥቂት ዶኬ ወጥ ጣል አድርጌ እሰጣቸዋለሁ። ምናልባት ለአንድ ልጅ ኩርማን እንጀራ ቢደርሰው ነው። አሁን አሁን ተመስጌን ነው፤ ልጆቼ አድገው ያለንበትን ኑሮ ጠንቅቀው ተረድተውታል። የለም ስላቸው አያስጨንቁኝም፣ ሹክክ ብለው ይሄዳሉ።"

በበዓሉ፤ በፋሲካስ? ብላችሁ ጠየቃችሁ? በአዘቦት ተርፎ ያልተጠራቀመ በፋሲካው ከየት ይገኛል? ይቺ ናት ኑሮ፤ "ፋሲካ የሌለው ጦም" የሆነበት። ህይወት ደስታ የሌለው አለም ውስጥ ስትቀረቀር ግን ለምን ይኖራል? እንዴትስ ይኖራል? እነርሱን ባዶ ያስቀረው የኑሮ ማገደል እኛን ስላንበሸበሸን ማፈር አይገባም? እነርሱን ኩርማን እያናጠቀ እኛን ከጥጋብ በላይ የጠቀጠቀ ኑሮ ፍትሁና ርትኡ የት ነው?

ኡ...ፍፍፍፍፍ!!

# በፋሲካ ይበኳል ወይስ ይምኳል?

የዚህ ዘመን መንግሥትና ሕዝብ ባንሆን ኖሮ፣ ይሄን ሠላምታ የምንለዋወጠው እዚያው ቤተ-መንግሥት የአዳራሽ ግብር ላይ ተገናኝተን ነበር። ዕለተ ፋሲካ የአዳራሽ ግብር ከሚካሄድባቸው ሦስት ዐውዳመቶች አንዱ ነበር። የተቀሩት ሁለቱ ልደት (ገና) እና መስቀል ናቸው። በእነዚህ ዕለቶች፣ ማዕረጋችን እንደፈቀደልን ሆነን ግብሩ ላይ እንታደማለን። እንኳን ግብሩ፤ አጠባበቁም በማዕረግ ነው። መኳንንት ከሆንን፣ ግብሩ እስኪጀመር የምንጠብቀው ለእኛ ተብሎ በተዘጋጀው ዛኒጋባ አረፍ እንድንል በእልፍኝ አስከልካዩ ተጋብዘን ነው። ዛኒጋባው ውስጥም የደረጃና የማዕረግ ጥያቄ አይቀርም። ታላላቆቹ መኳንንት ከመጋረጃው ውስጥ በወንበር ሲያርፉ፣ ሌሎቹ መኳንንቶች ከመጋረጃው ውጭ በደረጃ ላይ ይቀመጣሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ ግቢው ውስጥ ፀሐይ ላይ ተሰጥቶ የሚጠብቅ ይኖራል። ማዕረግ የለሹ ህዝብ፤ ከግቢ ውጭ ቆሞ በጅምላ ተንጋፍፎ እስኪገባ፣ ነፋስ እንዳገኘው ሰብል ዘመዎ፣ ቀና... እያለ ይቆያል።

ንጉሠ-ነገሥቱ የማዕረግ ልብሱን እንደለበሰ፤ በበቅሎ ላይ ሆኖ በመኳንንቱ ታጅቦ፣ በክብርና በማዕረግ ከእልፍኙ ብቅ የሚለው ልክ አራት ሰዓት ሲሆን ነው። ማዕረግ ያለው ሁሉ የማዕረግ ልብሱን እንዲጐናፀፍ ሕግ ያስገድዳል። ያዝማሪዎች አለቃ ከንጉሡ ፊት-ፊት እየሄደ በመሰንቆ ዐውደ-አመቱን ያወድሳል። ይሄን ሥርዓት የሚነግሩን ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል "ዝክረ ነገር" በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ነው።

"የእልፍኝ አስከልካዩ ጐራዴውን በረኸርሙ ጣል አድርጐ የማዕረግ ልብሱን ለብሶ ላጀቡ ደንብና ሥርዓት እየሰጠ ከንጉሡ ፊት-ለፊት አርጩሜውን ይዞ ሰውን ‹እልፍ በሉ፣ አትጫኑ› እያለ ይሄዳል፤ መሣፍንቱን መኳንንቱንና የጨዋውን ልጅ በራስጌ በር ካዳራሹ የሚያስገባና ባዳራሹም ውስጥ ከመጋረጃው ግቢ የሚቀመጡትን ሹማምንት ቦታ የሚያሲዝ የእልፍኝ አስከልካዩ ነው። ከደጃፍ ላይ

ቆሞ የተከለከለውን ሁሉ ትንሹንም ትልቁንም ያግዳል፤ ንጉሠ-ነገሥቱም ከከብት ወርዶ ከተከተሉት መካከል ታላላቆቹ መኳንንት እንዲቀድሙ ያደርጋል። ምክንያቱም እንዳይገፉ፣ ክብራቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ነው። መሳፍንቱንና ራሶቹ ከገቡ በኋላ ንጉሠ-ነገሥቱ ይከተላል።"

የፋሲካ ግብር ላይ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ የገበታ አደራደሩና የግብረ-በላው አሰያየም፣ ደረጃና ሥልጣንን ከግምት ያስገባ ነው። የምግቡም ጥራት እንዲሁ አራት አይነት ነው። የመጀመሪያው ነጭ (ማለፊያ) ይሰኛል። እንቁላል ከመሰለ ጤፍ የሚጋገር እንጀራ ነው። ሁለተኛው ምክትል ጤፍ ይባላል። ከዚያ ዝቅ ያለ ደረጃ ካለን የሚቀርብልን መናኛ ጤፍ ነው። ሥም አልባ "ወፈ መዓት" ከሆንን ደግሞ ጋሬ (ድበላ) ተሰናድቶ ይጠብቀናል። ጋሬ ከጥራጥሬ ድብልቅ የሚዘጋጅ እንጀራ ነው። ተቦክቶ ለብዙ ወራት ስለሚቆይ ከፋኛ ይኾመጥጣል አሉ። እንግዲህ እጅ እግር እስኪሰበር፣ አይን እስኪጠፋ የምንራኮተው እዚህ ገበታ ላይ ለመሰየም ነው። የመራኰቱን መጠንና አስከፊነት ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" ውስጥ እንዲህ ገልፀውታል፡-

"...የበላይ አጋፋሪዎች አዳራሹ ውስጥ ያለውን ቦታ አይተው ሰው በርከት ብሎ እንዲገባ ሲያዝዙ ሰው በሰፈረበት ቦታ ያለው አጋፋሪ ከዚህ መለስ ተነሱ ይልና በመንጋ ያዝዛል። ከዚያ ሁሉም አንድ ላይ ተነስቶ እዮተራበሸ አቅም የሌለው በመንጋ ያዝዛል። ከዚያ ሁሉም አንድ ላይ ተነስቶ እዮተራበሸ አቅም የሌለው ሲወድቅ አቅም ያለው በላዩ እዮቆመ አጋፋሪዎች ሲደበድቡት ጨፈቃው በላዩ እየተሰባበረ በሩን ለመግባት ሲሮጥ ከሞት የሚሸሽ እንጂ መብል የሚፈልግ አይመስልም ነበር። እንዲህ እየተራበሸ ሁሉም ሁሉም አይኑን እየጨፈነ የሚቆምበትን ሳያውቅ እጁን የገዛ አካሉ ክፍል እንዳልሆነ ሁሉ በላዩ ለሚወርድበት የጨፈቃ መአት እዮጋረደ አንዳንድ ጊዜ አጋፋሪዎችንም አሸንፎ እንደውሃ ሙላት ጠርጎ ይዞዋቸው ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ከታች አመጣጡን ያዩና አጋፋሪዎች ቶሎ ተረዳድተው በሩን ዘግተው በጨፈቃ ደብድበው ይመልሱታል።"

"ይሄ ሁሉ ለምን?" ብለን ስንጠይቅ የንጉስ ግብር ሁለት አይነት መልክ አለው። አሉታዊ እና አዎንታዊ። ወደአሉታዊነቱ የሚያደሉት ምሁራን፣ ለግብር መራኮትን የረሃብተኝነታችን ማሳያ ያደርጉታል። በአዎንታዊነት የሚመለከቱት ደግሞ የንጉስ ግብር ሀገራዊ ቃል-ኪዳን የሚከናወንበት፣ መተማመን የሚሰፍንበት መታደሚያ ነው ይሉታል። መጀመሪያ አሉታዊውን እንመልከት።

"የእህል ሰቀቀን ያልወጣለት ህዝብ ነን" የሚል አቋም ያላቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የእህል ሰቀቀናችን የፈጠራቸው ብዙ ሥርዓቶችና ልምዶች እንዳሉን ያስረዳሉ። "ከቀኑ በማንኛውም ሰዓት እንግዳ ቢመጣ መጀመሪያ እህል ውሃ ይቀርብለታል። ይህ መስተንግዶ እንግዳው ረሃብተኛ መሆኑን መመስከር ይመስለኛል" ሲሉ "ረሃብና ተስቦ" የተሰኘ ጥናታቸው ላይ ይገልፃሉ። ከቀብር መልስ ከሚቀርበው የእንባ ማድረቂያ ንፍሮ አንስቶ እስከ ሰንበቴ መጠጣት ያለውን ደግሶ የማብላት ባህል፤ ከእህል ሰቀቀን ያለመውጣት ችግር አንፃር ያስተነትኑታል። እንዲህ እንዲህ እያሉ የግብረ-በላነትን ሁኔታም ይጠቋቁማሉ።

"...ንጉሶች፣ በየአውራጃውም ወኪሎቻቸው ለሹማምንትና ለጦር መኳንንት ለህዝብም ተመርጦ ግብር ያገቡ እንደነበር ሰምተናል፤ ያየንም የተካፈልንም እንኖራለን። የተካፈሉ ሰዎች ከግብሩ ገበታ ለመድረስ ስለአለው ‹ተጋድሎ› ሲነግሩን ረሃብ የፀናበት ብቻ የሚታገሠው ይመስላል። ያለው ግፊያ፣ ጉሸምትና ዱላ ተደጋግሞ ባልሰማው ተረት ይመስለኝ ነበር። አንዳንዶቹ እንግዶች ከግብሩ ገበታ ላይ ሥጋ በጉያቸው ይዘው ይሄዱ ነበር።"

የዚህ አቋም አራማጅ ምሁራን ብዙዎች ናቸው። የአማርኛ መዝገበ-ቃላት አዘጋጅ ደስታ ተክለወልድ እዚህ ጐራ የሚካተቱ ይመስል፤ ግብርን በተረት ጭምር የተራበ ሰው መታደሚያ አድርገው ያቀርቡታል፤ "ለተራበ በግብር፣ ለተበደለ በነገር፣" በማለት። የዚህ ተቃራኒውን አቅጣጫ ይዘው የሚነጉዱም አልታጡም። ግብር የሥርዓት፣ የወግ፣ የአንድነት ማስጠበቂያ እንጂ የረሃብተኛ መታደሚያ አለመሆኑን ለማስረዳት ይጥራሉ። ከሐዲስ ዓለማየሁ ልቦለድ እንቆንጥር። ይሄን ቅሬታ የሚያሰሙት አንድ "ጨዋ" ሰው ናቸው።

"የንጉሥ ግብርና ኡ(ቁ)ርባን አንድ በመሆኑ ከረድኤቱ ለመሀ(ካ)ፈልና ጌታችን ከተራ ህዝብ እንድንለይበት የሰጡንን ደረጃ ለመጠበእ(ቅ) ነበር እንጂ እንጀራማ በየቤታችን ከፉኛ ተርፎ ብዙ ሰው እናበላ የለ?"

የሐዲስ ዓለማየሁ ሌላው ገፀ-ባህርይ አጋፋሪ ጉደታ፤ በኩርፊያ ግብር አልበላም ያሉ መኳንንን ላይ አፍጥጦ በቁጣ የሚናገረው ይሄንኑ ነው። የተሰባበረ አማርኛውን አጥርተን ስንሰማው እንዲህ ይላል። "የንጉሥ ግብር ሲፈልጉ የሚበሉትና ሲፈልጉ የሚተዉት የእናት እንጀራ አይደለም። እስቲ ቅስቅስ በልና ውርደት ይከተልሃል! የንጉስ ግብር በግድ እንጂ በውድ የሚበላ ነው?"

የንጉሥ ግብር ብቻ ሳይሆን ሌሎች ድግሶችም ለመጥገብ ከመብላት ጋር የሚያያዙ መስተጋብሮች ናቸው? ወይስ ቅድሚያ የሚሰጠው አብሮ በመታደም የሚተላለፈው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍቺ ነው? ለዚህ ዳኘነት እንዲረዳን ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመሥቀል ለግብር የሰጡትን ትርጓሜ እንቃኝ።

"የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሕዝቡን የሚያስተዳድረው ባገር ግዛት፣ በቀለብ፣ በጉርሻ ብቻ ሳይሆን ሌላ ትልቅ መሳቢያና ማቅረቢያ የጦር ሠራዊት ማደርጃ ግብር የሚባል ማስተዳደሪያ አለው። ግብር የተባለበት ምክንያት ንጉሡ ዘወትር መኳንንቱንና የቤት ልጁን ከእልፍኝ ወይም ከእልፍኝ አዳራሽ በታላላቅም በዓል ቀን ሠራዊቱን ካዳራሽ ያለማቋረጥና ያለማስታጐል በተለመደው ሰዓት የሚያበላ ነውና፤ ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ምንም አስገባሪ ቢሆን ራሱም በበኩሉ ለሕዝቡ የሚያስበውና የሚደክመው ከግብር ይቆጠራልና፤ በዚህ ልማድ ግብር ተብሎ ሲነገር ይኖራል።"

ስለዚህ....

....በፋሲካ ግብር ይበሏል? ወይስ አገር ለመጠበቅ ወግ ለማጥበቅ ይምሏል? ግልፅ ነው። ግብር የሥርዓት፣ የሕግ፣ የወግ፣.... ገበታ ነው። ስለበላህበት ማዕድ ብቻ አይደለም፤ ስለተሰየምክበት "ሆዳም" አትባልም። "ሆዳም!" ከተባልክም አለማወቅ በአቋራጭ ሥልጣን ስላገኘ ነው ያልተገናዘበ ክብረ ነክ የሆነብን።

# "የወረወርኩት አንካሴ መልሶ ለራሴ"

ጀርመናዊው የሥነ ልቡና ሊቅ ኤሪክ ኤሪክሰን "Childhood and society" የተሰኘ መጽሐፉ ላይ እንዲህ ይላል...

"አንድ አገር ሆነ ግለሰብ መመዘን ያለበት በደረሰበት ከፍተኛ ሥልጣኔ ደረጃ ብቻ አይደለም። ደካማ በሆነው የወልማንነት ጭምር እንጂ" /for nation, as well as individuals, are not only defined by their highest point of civilized achievement, but also by the weakest one in their collective identity/

ኤሪክሰን ከላይ በተጠቀሰው በዚሁ መፅሐፉ ላይ የሰው ልጅ የአዋቂነት ዘመን የልጅነት አስተዳደግ ላይ ተመርኩዞ እንደቆመ ለማሳየት ይሞክራል። የአንድ ሰው ድርጊት ማህበረሰቡ በልጅነቱ ካስጨበጠው ውጭ አለመሆኑን ለማስገንዘብ የናዚ ጀርመን መሪ የነበረውን የአዶልፍ ሂትለርን አስተዳደግ በምሳሌነት ያቀርባል። ጀርመንና ህዝቦቿ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት የቀመሱት ልምጭ እራሳቸው ጀርመኖች ሂትለርን በልጅነቱ ያስጨበጡት እንደሆነ ለማስረዳት ይሞክራል። በእኛ ትውፊታዊ አገላለፅ እንዲህ ይባላል፡-

"የወረወርኩት አንካሴ
መልሶ ለራሴ"

እንደ ኤሪክ ኤሪክሰን ሥነ-ልቡናዊ ጥናትና ድምዳሜ ከሆነ እኛም በዚህ ዘመን የምንሸነቆጠው እራሳችን ለመሪዎቻችን ባስጨበጥናቸው የራሳችን ልምጭ ነው ማለት ነው። አሁንም በእኛ ትውፊታዊ አገላለፅ፡-

"ከፉ ከማድረጋቸው
ክፉ ማስለመዳቸው" ይባላል።

መቼም የዚህ ዘመን መሪዎቻችንን ሁናቴ ከልጅነት ዘመናቸው ጋር እያነፀርን ችግሩን አብጠርጥረን ለመረዳት የኤሪክሰንን የጥናት ጉልበት ግድ ይለናልና አዳጋች ነው። ምክንያቱም ኤሪክሰን ሂትለር ላይ እንዳደረገው የመሪዎቻችንን ዘመን፣ ቤተሰቦቻቸውንና የቤተሰቦቻቸውን የኑሮ ሁኔታ በጥልቀት ማጥናት ግድ ስለሚለን ነው። ይሄን ለባለሙያዎቹ ትተን፣ በዚህና በዚያ ዘመን የሚታየውን የወል ማንነት

ከመንግሥታችን ገዢ ባህርይ አንፃር ለመቃኘት ገራገር ጥናት ማካሄድ አያዳግተንም።

አምባገነንነት

ከመሪዎቻችን የሚመነጨው የመንግሥታችን አምባገነንነት ከየት መጣ? እንደዝናብ ከላይ ወረደ? ወይስ እንደ አቧራ ከጐረቤት አገር ነፈሰ?... እንደ ኤሪክሰን ጥናትና ድምዳሜ ከሆነ አምባገነንነቱ ከእኛው ከራሳችን የተገኘ ነው። መለስ ብለን ልጆቻችንን እንዴት እንደምናሳድግ፣ ተማሪዎቻችንን እንዴት እንደምንይዝ፣ በስራችን ያሉትን ሰራተኞች እንዴት እንደምናስተዳድር ... መመልከት ይበቃል።

አሁን አሁን በመጠኑ ተስተካከለ እንጂ ገዢዎቻችን ያደጉበት የወላጅና የልጅ ወግ መቼም አስደንጋጭ ነበር ማለት ይቻላል። ከብት ጠብቆ፣ የወላጅና የእንግዳ እግር አጥቦ፣ ኩራዝ ይዞ አብልቶ፣ በርበሬ ታጥኖ፣ ትርፍራፊ በልቶ... ታዲያ ገዢዎቻችን ዛሬ ጉልበት ሲያወጡ የሌለ ከብት ጠብቁ ቢሉን፣ ኩራዝ ይዛችሁ አብሉን ለማለት መብራት ቢያጠፉብን፣ እግራችንን እጠቡ፣ ኑ በርበሬ ታጠኑ... ቢሉን ይፈረድባቸዋል? ትራፊያችንን ብሉ፣ ስንናገር ወደ ጓዳ ግቡ ቢሉን ጥፋተኛ ያስብላቸዋል?

ወደ ትምህርት ቤት እንሂድ፥ በጥንት ጊዜ ተማሪዎች ለመምህሮቻቸው ከአሽከር በላይ ባሪያዎችም ነበሩ አሉ። ይሄን የታዘቡት አፄ ኃይለሥላሴ የተማሪና አስተማሪ መተዳደሪያ ደንብ አቀረቡ። የመተዳደሪያ ደንቡ ቁጥር አምስትና ስድስት እንዲህ ይላል...

አምስተኛ ክፍል

ተማሪዎቹ ማናቸውንም አይነት ጥፋት ባጠፉ ጊዜ አስተማሪዎቹ ቁም፣ ተቀመጥ፣ ተንበርከክ፣ እጅህን ዘርጋ፣ እጅህን አውጣ፣ ሰብስብ.... እያሉ ይቀጣሉ። ደግሞ እጃቸውን እስከ አሥር አርጩሜ ሊመቷቸው ይችላሉ እንጂ በአለንጋ፣ በበትር፣ በጥፊ፣ በክርን ይህንን በመሰለ ቅጣት እንዳይቀጡ ተከልክሏል። ይህንንም የመሰለ ቅጣት መከልከሉ ልጆች በሽተኞች እንዳይሆኑ ነው።

ስድስተኛ ክፍል

አስተማሪዎች ተማሪዎቹን የየራሳቸውን ሥራ ለማሰራትና ካንዱ ሥፍራ ወዳንዱ ሥፍራ ለመላክ ወይም እንደ አሽከር አስከትሎ ለመሄድ አልተፈቀደላቸውም።"

ከደንቡም ኋላ ቢሆን የተማሪዎች መከራ እንዳልታገሰላቸው የምናውቅ እናውቀዋለን። በክርን፣ በጥፊ፣ በበትር መመታቱም ሆነ እንደ አሽከር መምህርን

መከተሉና መላላኩ ቀጥሎ ነበር። በዚያ የአስተማሪና ተማሪ ግንኙነት ያለፉ ባለስልጣኖቻችን ዛሬ ጉልበት ሲያበጁ በክርን ቢደቁሱን፣ በዱላ ቢነርቱንና እንደ አሽከር ተከተሉን ቢሉ ይፈረድባቸዋል?

ዘረኝነት

ከመደበኛ ትምህርት ጋር ለማይተዋወቅ ማህበረሰብ የዕውቀት ምንጩ ተረቱና ምሳሌያዊ አነጋገሩ መሆኑ ግልፅ ነው። ለዘረኝነት ከሚገፋፉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጥቂቶቹን እንጥቀስ፡-

ከወገኑ የተለየ አንበጣ ይሆናል ፌንጣ።

ወገን ያለው ማንም አይታገለው።

ዘመድ በዘመዱ አይጨክንም ሆዱ።

ዘመድና መድኃኒት የተቸገሩ ዕለት

ዘመድና ሚዛን ከወገብ ይያዛል

ዘመድ ሲፈራ ለማኝ ሲኮራ

ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጅንፎው አይለቀቅም

ይሄ የጥንቱ የዘረኝነት አስተምህሮ ነው። የአሁን፣ የአሁን ደግሞ አለ። በእድር፣ በዕቁብ፣ በጅጊ...ዘርን መፈለግ። ያለፈው መንግስት እንዲህ ያሉ አዝማሚያዎችን በመቀየጥ ለማጥፋት እንደሞከረ የምናስታውሰው ነው። የወሎ፣ የጐንደር፣ የጅሩ፣ የጅማ... እድሮችን አፍርሶ በመደባለቅ የወዛደር እድር ብሎት ነበር። ምንም እንኳን ቡርገዡው፣ ፊውዳሉ፣ ከበርቴው...ቢኖርበትም የወዛደር እድር መባሉ ዘረኝነትን ኩም አድርጐ ነበር።

በዚህ ዘመን ደግሞ ያ ኩም ያለ ዘረኝነት ባንክ እስከመሆን አድጐ ብቅ ብሏል። የግል ባንኮች የትኛው የየትኛው ዘር እንደሆኑ የማያውቅ ማነው? የኦሮሞው ባንክ የትኛው እንደሆነ የሚያጣው አለ? የጉራጌ፣ የትግሬ፣ የአማራ... ሁሉም ይታወቃሉ። አንዳንዶቹ እንደውም ከዘር ወርደው እስከ ጐጥ ደርሰዋል። ከኦሮሞም ጊምቢ፣ ከጊምቢም 08 ቀበሌ ወርደው "G8" በሚል ኮድ ያቀፋሉ - ያሳዝናል። እኛ እስከዚህ ዘቅጠን የህገ-መንግሥት አንቀፅ 39 ላይ ማተኮር ቅድሚያ የሚሰጠው ነው? መጀመሪያ የአይናችንን ውስጥ ግንድ ብናጠራ አይሻልም? ይሄን እያዩ ያደጉ ገገርዎቻችን ይለይላችሁ ብለው ቢከፍሉን፣ ቢከፋፍሉን ይፈረድባቸው ይሆን? የተሸነቆጥነውስ በገዛ ልምጫችን አይደለም?

(ለዕዝራ አብደላ መታሰቢያ)

የእዝራ ከህይወት ድካም ማረፍ የንጉስ ዳዊትን የወቀሳ መዝሙር አስታወሰኝ። ንጉስ ዳዊት እንዲህ ነበር ያለው...

"...ወደ ጥፋት ብወርድ በደሜ ምን ጥቅም አለ?

አፈር ያመሰግንሃልን? እውነትህንም ይናገራልን?"

(መዝ 29(30)፥9)

ይሄ የእዝራም የወቀሳ መዝሙር ነው። ቢሞት ከደሙ ምን ጥቅም አለ? እዚህ ሆኖ ገና ብዙ የሚሰራውና የሚረዳው አልነበረምን? አፈር ያመሰግናልን? እርሱ የሚናገረውን እውነትስ ይናገራልን?...ግን ከምክንያት ውጭ የሆነው የአፈር አሸከርክሪት ላያመሰግን እዝራን ያህል ሰው ከህይወት ዳርቻ ጠልፎ ወሰደ። ግን - ግን አንዱ እዝራ ላይ አነጣጥሮ ሺህ ሰው እንደጣላ ያውቀው ይሆን? ከእዝራ "ጀርባ" ስንቶች አሉ? ተስፋ የተራቡ፣ ሐዘን የጠገቡ፣ ደስታ የራቃቸው፣ ኑሮ የጨከነባቸው... እዝራ ከጠፋበት ያገኛቸው፣ አስጠልሎ ፋታ የሰጣቸው ስንት ናቸው?

...እዚህ ላይ ነው ዓለም የግብር ይውጣ መተረካከሚያ ሆና የምትታየን፣ ቆጥራ ያልደረሰችብን፣ በግል የማታውቀውን፣ እንዳመጣላት ፈራጅ - የጅምላ ተጓዳጅ ... አሁን ተፈጥሮ ናት ለሰው ልጅ ግድ ያላት? ወልዳ ጥላናለች፣ የህይወት አጓለምውታን አድርጋናለች...እንዲያ ባልሆን እዝራ ምንም ባልሆነ ነበር።

የእዝራን ከህይወት ድካም ማረፍ ስሰማ፣ ሰው የመሆን ከንቱነት ጠለፈኝ። እንደ አማሌቅ ንጉስ ከአስፈሪው ሞት ጋር ፊት ለፊት ተጋፈጥኩ። ፈራሁም፣ እዝራ የኋላውን ትቶ የፊቱን ለመያዝ ገና መዘርጋቱም አልነበር? እነዚያ ሁሉ ተስፋዎቹ ስለ ምን በፈጣሪው ዘንድ እንደ ዋጋ ሳይቆጠሩ ቀሩ? እኔስ የኋላዬን ትቼ የፊቴን ለመያዝ እጄን ብዘረጋ ለተፈጥሮ ምኑ ነው?... እንደ አማሌቁ ንጉስ እንደ አጋግ

እንዲህ ማለት ይነሰኝ? "ከመዝኑ ሞት መሪር" (በእውኑ ሞት እንዲህ መራራ ነውን?)

ሞት ለሰው ልጅ ምንጊዜም መራራ ነው። ከሰው ልጅ "ጐጆ" ውስጥ ባይጠፋም መቼም የማይለምድ አውሬ፤ እዝራን አስታኮ የሞት ቀዝቃዛ ትንፋሽ እኔንም ተሰማኝ፣ ከሰራሁት ይልቅ ያልሰራሁት ቆጨኝ፣ ደግሞ - ደግሞ "መስራቱ ለምኔ?" አሰኘኝ፤ ሞት ሲጠጋኝ ሙቀት ያልሰረፀበት ህልውናው ብርድ ለቀቀብኝ። ሞት ሲቀርብ ተስፋ ይሸሻል፤ ነገአችን ስለ ትናንት ይቤዣል። እንደ ንጉስ ዳዊት፤ "ወደ ጥፋት ብወርድ በደሜ ምን ጥቅም አለ?" የማይል የሰው ልጅ በዚህ ምድር አይገኝም። "አፈር ያመሰግንሃልን? እውነትህንም ይናገራልን?" የሚል መደራደሪያ የማያቀርብ የለም።

መርስኤ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ "ትዝታዬ" የተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ የንጉስ ዳዊትን ቃል የተዋሰ ስለ አንድ አሳዛኝ ሟች ይተርካሉ። ዕውር ወልደጊዮርጊስ ይባላል ይላሉ። ከትምህርቱ መስለጥ የተነሣ እጅግ አድርጐ የታበየ ተማሪ ነበር። ገና በህይወት ማለዳ ላይ ፅኑ ህመም ወደቀበት። ሞት የማይቀርለት ሆኖ እራሱን ሳተ፤ በቅዠቱ መካከል ግን ያቺ የሰው ልጅ መማፀኛ የሆነች የንጉስ ዳዊት ከተሸሸገችበት ልቡናው በአፉ በኩል አፈተለከች።

"ምንተ ያሰልጥ ደምየ ለእመ ወረድኩ ውስተ ሙስና፤

መሬትኑ የአምነከ ወይነግር ጽድቀከ"

ዕውር ወልደጊዮርጊስ ስለታበየ ጓደኞቹ፤ "ትዕቢት አበዛ ይቀሰፋል" ሲሉ እንደተነበዩ መርስኤ ሐዘን ይነግሩናል። ነገር ግን አለመታበይ የድንተኛ ሞት መድኃኒት እንዳልሆነ በዕዝራ አይተናል። የቅስፈት ሞት የሰው ልጅ ሁሉ ዕጣ - ፈንታ ነው። ሞት ጉልበቱን የሚመካ ያልሰለጠነ ወገዝ በሬ ነው፤ ያገኘውን ሳይመርጥ ይፈትናል፤ ይፈታተናል።

ህይወት ውስጥ ምን አለን? የትኛው የኛ ሆኖ መነጠቅ ይሰማናል? ምን ተሰጥቶናልና መነፈግ ያትከነክነናል? ፀጉራችን? ቀለማችን? ጥፍራችን? ቅንድባችን? ለመጥፋት የተዘጋጀ፣ እንዳለ ይቆጠራል? መኖርና አለመኖር ልዩነት ያመጣል? መኖር ወደ አለመኖር የመጓዝ እንቅስቃሴ አይደለምን? ህይወት የሞት መጠበቂያ አፍታ ከመሆን ውጭ አማራጭ አላት? ስብሐት ገብረእግዚአብሔር በመጨረሻዎቹ ሰሞናት ያለውን እዚህ መጥቀስ ይበጃል፡ እንደ ንጉስ ዳዊት አልተማጠነም፣ እንደ ንጉስ አጋግ አላማረረም፤ "ተዘጋጀህም አልተዘጋጀህም ጉዳዩ አንድ ቀን ያበቃል። ሁብትህ፣ ዝናህ እና አለማዊ ሃያልነትህ መንምኖ እዚህ ግባ የማይባል ይሆናል። ምን ምን የግልህ እንደነበር ወይም ምን ምን እዳ ሊከፈልህ ይገባ እንደነበረ ልዩነት አያመጣም - ከየት መጣህ ደስተኛ ወይም መከረኛ ኑሮ አሳለፍክ በመጨረሻ

ልዩነት አይኖረውም። መልከ ቀና ነበርክ ወይስ ጥበበኛ? ልዩነት አያመጣም። የታህና የቆዳህ ቀለም ሳይቀር እዚህ ግባ የማይባል ኢምንት ጉዳይ ሆኖ ይቀራል።"

ስለ ሞት ማሰብ ከሞት በላይ ይገዝፋል። ስብሐት ስለ ሞት ሲያስብ፣ ሲያሰላስል የኖረ ደራሲ ነው። ደስታ መሻቶቹ፣ አልባሌነቱ፣ አፈንጋጭነቱ… ከሞት ማሰብ የሚደብቁት አፍታ ጎሬዎቹ ነበሩ። ለሰው ልጅ ሁሉ ሞትን ማሰብ የ "አየሁሽ አላየሁሽ" የልጆች ጨዋታ ነው። በዚህ ሄድን፣ በዚያ መንገዳችን ሁሉ ከሞት ጋር ያለመገጣጠም ማሳለጫያ ነው። ሞትን ማኮሰስ ሆነ ማግነስ ግቡ አንድ ነው። የሚያኮስሱ "ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው አሉ" ይላሉ። የሚያነግሱት እነ ሩሚ ደግሞ ሞትን ከቅንጣት ወደ ግዝፈት፣ ከዚያም ወደ ረቂቅነት መሸጋገሪያ መንገድ ያደርጉታል፡-

ሞት መጣ ከቅንጣትነት ሊታደገኝ
ግዘፍ ነስቶ አትክልት ሊያደርገኝ፣
አትክልታዊነት መች በቅቶ
የእንስሳነት አክሊል ደፋሁ
    እሩህሩህ ሞት መጥቶ
ከእንስሳዊነት ወደ ሰውነት የምሸጋገረው
በሞት ምክንያታዊነት ነው፤
እንደመላዕክት ክንፍ ለማቆጥቆጥ
በላባቸው ለመንቆጥቆጥ
ሞትን መቀበል እጅን ዘርግቶ
(አለበለዚያማ)
ከዚያም በላይ በላይ መርቀቅ የት ተገኝቶ
የሞት መተላለፊያውን ፈርቶ፤
እኔስ ሞቴን ያስመኘኛል
እዚያ ብዙ ብዙ፣ ብዙ ይገኛል።

ይቺ ግጥም ሌላ አይነትዋ የሩሚ ምሽግ ናት። ህይወት የምሽግ ማድፈጥ አይደለች። ሞትን ለማቆንጀት የውበት ሳሎን ማበጀት፤ የእነ ሩሚ ጎሬ ነው፤ ሞትን አከፋፍቶ፣ ከፍርሃት በስተቀር ምን ተገኝቶ? ፍርሃት፣ ፍርሃት፣ የሞት ፍርሃት! የሰው ልጅ ሁሉ የወቀሳ መዝሙር ነው።

እንግሊዛዊው ደራሲ ዶክተር ሳሙኤል ጆንሰንም፤ ይቺን የንጉስ ዳዊት የሞት ፍርሃት መዝሙር ጠንቅቆ ያውቃታል። ቦስዌል በፃፈው "Life of Doctor

Samuel Jonson" የተሰኘ መፅሀፍ ውስጥ ሳሙኤል ጆንሰን በተደጋጋሚ የሞት ፍርሃቱን ያውጃል። አንድ ቀን ቦስዌል፣ ጆንሰንና ሚስስ ኖውለስ ቁጭ ብለው ሲወያዩ የሞት ጉዳይ ይነሳል ሚስስ ኖውለስ አፈፍ ብለው እንዲህ አሉ፡-

"የሰማይ ቤታችን መግቢያ በር የሆነውን ሞት እንዲህ ማስፈራሪያ አድርጎ ማቅረብ ደግ አይደለም።"

ዶ/ር ሳሙኤል ጆንሰን ቀጠለ፡-

"አንድ አመዛዛኝ ሰው ለክፉ ጭንቀት ሳይዳረግ መሞት አይቻለውም።" ሚስስ ኖውለስ ተተኩ።

"የእምነት መፃህፍት የሚነግሩን ፃድቃን በሞታቸው ተስፋ እንደሚያደርጉ ነው።" ዶ/ር ሳሙኤል ጆንሰን መለሰ፡-

"ልክ ነው፣ እመቤቴ፣ አንድ አማኝ ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም። ነገር ግን ያ የመዳን ተስፋው የተመሰረተው አዳኙ በሰጠው ቃል ኪዳን ላይ ብቻ እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል። ለመሆኑ ለመዳኑ የትኛው ፃድቅ እርግጠኛ መሆን ይችላል? ይሄ ነው ጥያቄው። ፃድቅ ነኝ ብሎ ማሰብ በራሱ፣ ዋነኛው የመታበይ ሀጢያት አይደለም? ስለዚህ በመታዘዙና ህግ በማክበሩ ላይ ተመስርቶ መዳንን በማግኘቱ እርግጠኛ የሚሆን ሰው የለም። ሞት ለማንም፣ ሁልጊዜም አስጨናቂና አስፈሪ እንደሆነ ይኖራል።"

ሚስስ ኖውለስ ለዘብ ብለው እንዲህ አሉ፡-

"ያም ሆነ ይሁ፣ ሞት ሲነቁ አስደሳች ነገር የሚገኝበት እንቅልፍ ነው።"

"ደስታም አልነው እንቅልፍ ለእኔ ጨርሶ ካለመኖር፣ ከስቃይ ጋር ቢሆንም በህይወት መገኘት ይበልጥብኛል" አለ ዶ/ር ሳሙኤል ጆንሰን።

ሞት እንኳንስ ለኔ፣ ለእናንተና ለዶ/ር ሳሙኤል ጆንሰን ቀርቶ፣ ፅድቅ ለተበጀለት ለንጉስ ዳዊትም አላስተማመነ፤ እንደ ጥፋት ተቆጠረ እንጂ... ያም ሆኖ ሞት ከሚሰበስበን በላይ ስለሞት ማሰብ ይከፋልና ከቻልን መተው ደግ ነበር .... ።

# ጥቡብ

# "ሥሳቸውን ለመሳም የሚዳዳቸው ደራሲያን"

አንዳንድ ጊዜ ...

... ድንገት የሚጣሩ መፅሐፍት አሉ፣ "ውል" ይሉናል። "በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ" ተይዞ ድንገት አማረኝ እንደሚላቸው እህል ውኃ ፈጥርቀው ይይዛሉ። ከህይወት ወደ ሞት መዳረሻ "ስንቅ" ይመስል። ይሄን ጊዜ በራሴ መሳቅ ይከጃጅለኛል። አንድ መፅሐፍ (ቀደም ሲል የተነበበ) ድንገት ደርሶ የህይወትና ሞት ጥያቄ ሆኖ በአስፈላጊነት እራሱን መሾሙ ከምን እንደሚመነጭ ግራ ያጋባኛል።

አንዳንድ ጊዜ ...

... መፅሐፉ የማይገኝ ይሆናል። ሲታሰስ ቢውል የሚሸጥ ሆነ የሚያውስ ሰው ይጠፋል። ያኔ "የፍቅር እስከ መቃብሩን" አያ ቦጋለ ሙብራቱን መሆን ነው። ባለቤታቸውን "ውዴ፣ ጠላ አማረኝ፣ ወፍራም ጠላ አማረኝ" ያሉት ህመምተኛ። ተጨንቆ ማስጨነቅ ይከተላል። እሙት ውድነሽ በጣሙ ይታወሱዋችሁ ። እንዲህ ያሉት፡-

"ብሪቱ፣ ሻሼ፣ ደብሪቱ፣ በላይነሽ ቶሎ ጠላ አምጡልኝ። የሞት መድሃኒት የሚሆን ጠላ!"

"የሞት መድኃኒት የሚሆን መፅሐፍ"

... አሁን ከወራት በፊት እንዲህ አድርጎኝ ነበር። ካንዴም ሁለት ሶስቴ ያነበብኩት መፅሐፍ "የሞት መድኃኒት" መስሎ "ውል" አለኝ። መፅሐፉ፣ በዓለም ስሙ የነገሮ-ዋቅጅራ ወይም ደግሞ በመንፈሳዊ ስሙ የአለቃ ተክለኢየሱስ "የጎጃም ታሪክ" ነው። ዝግጅትና ሐተታን እንዲሁም አርትኦት ጨምረው ያሳተሙልን ዶ/ር ስርገው ገላው ናቸው። ዶ/ር ስርገው የርዕሱን መጥበብ፣ የይዘቱን መስፋት በማየት

"የጎጃም ታሪክ" ከማለት ይልቅ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚል አሳትመውት ነበር። ሳነበው ልብ ያላልኩት የኖረ የነፍስ ጥማቴ ሲረካ ታውቆኝ ነበር። መልሶ መላልሶ ሊጠማኝ። እና ፈለኩት፤ በፈለኩት መጠን ጠፋ፤ በጠፋ መጠን ፈለኩት። አስታውሳለሁ፤ አንድ አሮጌ መፅሐፍ ሻጭ "ጠብቀኝ" ብሎ ከሰዓታት በኋላ አንድ መፅሀፍ ይዞልኝ መጣ። መፅሀፉ የአለቃ ተክለኢየሱስ ይሁን እንጂ ሌላ ነው። "የጎጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ" በሚል ግርማ ጌታሁን ያሳተሙት። ልጁን አየሁት፤ ላብ በላብ ሆኗል። መፅሀፉን በማግኘቱ ፊቱ ላይ "አልቻልም" የሚል ፉከራ ያነበብኩ መሰለኝ። መፅሐፉን "አይደለም" ማለት በልጁ ላይ የሚፈጥረውን የስሜት መናጋት በማሰብ፣ አመስግኜ ባለኝ ዋጋ ገዛሁት።

አንዳንድ ጊዜ ...
... ይሄ ነው... ያልከው ታጣለህ፣ ያላልከውን ይዘህ ትመለሳለህ። ግርንቢጥ አለም። ቢቸግረኝ እራሳቸው ዶ/ር ስርግው ገላው ጋ ስልክ መታሁ። በትህትና ተቀበሉኝ። መፅሀፉ ግን አልነበራቸውም። ያላቸውን አንድ ቅጂ ለአርትኦት ስራ እየተጠቀሙበት እንደሆነ ነገሩኝ።

"ሊታተም ነው?" ስል ጠየኳቸው

"አዎ፤ እስከዚያው ለተወሰኑ ቀናት ያለኝን አንድ ቅጂ ላውስህ?" ሲሉ የጭንቅ ግብዣ አቀረቡልኝ።

"አመሰግናለሁ፤ ግን እኔ ተውሼዎት አርትኦቱ ከሚደናቀፍ ቢቀርና ቶሎ ቢታተም ይሻለኛል።" በዚሁ ተስማምተን ተለያየን።

አንዳንድ ጊዜ ...
... ለፍላጎት ከመነዳት፤ ፍላጎትን መለስ ብሎ መመርመር ማስታገሻ መድኃኒትነት አያጣም። መፅሐፉን ለምን እንዲህ ፈለኩት? መፅሀፉስ እንዲህ ለምን ፈተረኝ? ውስጤ ምን ጎድሎ ደመነፍሴ ወደዚያ መፅሀፍ መራኝ? ያነበቡትን መፅሀፍ ከማሰስ፣ ያልተነበበት ውስጥ ተስማሚ መፈለግ አይሻልም?

... ይኼም ሆኖ መፅሀፉን መጠየቄን አላቆምኩም ነበር። አንድ ወዳጄን ስጠይቀው በትዝብት አየኝ፡-

"ምነው?" አልኩት

"ይሄን መፅሀፍ ለሶስተኛ ጊዜ ስትጠይቀኝ ነው" አለኝ።

"ጠይቄህ ነበር?"

"አ -- ግን መፅሀፉን እንዳነበብከው ነግረሽኛል። እኔም አንብቤዋለሁ። እንዳንተ መውደድ ቀርቶ እንደውም አናዶኛል"

"እንዴት?"

"ፀሐፊው እራሱን ይቆልላል።"

"ማን? አለቃ ተከለኢየሱስ?"

"አዎ፣ ብዙ ቦታ እራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል። እንዲህ ሲያጋጥመኝ ቋቅ ይለኛል። አንብቤ ስጨርስ መፅሐፉን አንድ ቀን ቤቴ አላሳደርኩም። ለሰው ሰጠሁት። አንዳንድ ሰው ይሄው ነው። ማሸነፍ የሚችልበት ተሰጥኦ እያለው ሽልማቱን በጉልበት ለመውሰድ ይተናነቃል።" (ቃል በቃል እንዲህ ያለኝ ይመስለኛል።)

ከዚህ አንፃር መፅሀፉን የማየት ሌላ ጉጉት ....

... መፅሀፉ እስከሚገኝ የወዳጄ አስተያየት አብሮኝ ቆይቷል። "ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ" የሚለው ነባር ብሂል በውስጡ ትልቅ ማህበራዊ ሂስ አርግዟል። ነቀፌታ ልንለው እንችላለን። ይሄ ብሂል ካፎቱ የተመዘዘበት ሰው መሞካሸት አይሰማውም። እንደውም "ራስ ወዳድ" የምትለውን ስድብ ተፈጥሯዊ አስመስለው እንደማቅረብ ያለ አዝማሚያነት አለው። እንግዲህ በዚህ ብሂል እየተሞረድን አድገን፣ ከእኛ የሚጠየቅን ከመፈፀም እናልፍና ከሰው ሲያጋጥመን ወደ መትፍነኑ ያዘነብልብናል።

እንዳንድ ጊዜ ...

.... ይሄ ብሂላችን የሚገርም ነገር ያስተናግዳል። ፉከራን ያህል ግዳይ የመዘርዘር (ጉራ የመንፋት ልንለው እንችላለን) ባህል እያበረታታን፣ ከዚያ ውጭ ያለውን ሳያሳንሱ ለራስ መቁረስ እናወግዛለን። ግራ ግብት አይልም?

❖ ❖ ❖

መፅሐፉ ሲታተም አንድ ወዳጄ ቤቴ ድረስ ላከልኝ። ጉጉቴ አልበደረም። ከ430 በላይ ገፆች አሉት። ከዚህ ውስጥ አዘጋጁ ዶ/ር ስርግው 95 ገፁን እጅግ አስፈላጊ የሆነ ምርምራቸውን አቅርበውበታል። የመፅሐፉን ምላትና ቀርነት ከመተንተን አልፈው እንደ ማማያ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ያቀርባሉ። የአለቃ ተክሌን ዋና ዋና ሰዎች ተከትለው የማፍታቻ ገለፃ ይሰጣሉ። ዶ/ር ስርግው በመፅሐፉ ላይ ሊነሱ የሚችሉ ብዙ ጥያቄዎችንና እንቅፋቶችን ቀድሞ የመጥረግ ትልቅ ስራ ሰርተዋል። አንዳንድ የታሪክ መፅሐፍ አርታኢም እያለው የአባት ስም እንኳን ሳይሟላ፣ በገረፍ-ገረፍ መውጣቱን ተመልክተን፣ እንዲህ የተደከመበት ስራ ሲቀርብልን፣ የምስጋና ንፍገት ማሳየት ተገቢነት አይኖረውምና ዶክተር ስርግውን አመስግነን እንቀጥል፡-

አለቃ ተክሌ ይሄን መፅሀፍ ከ1901 እስከ 1916 ዓ.ም ባሉት ዓመታት መካከል እንደፃፉት ዶ/ር ስርግው አገናዝበው ደርሰውበታል። አለቃ በአካል የነበሩትን በምስክርነት ከማቅረብ አልፈው የታሪክ መዛግብትን አገላብጠው፣ አዛውንትን አነጋግረው የመፅሀፉን ግዛት ወደ ኋላ እስከ አዳም ድረስ ይገፉታል። አለቃ ተክሌ ከመዛግብት መርምረው ከወሰዱት በላይ በአካል የተገኙበት ዘመን ላይ 1881 እራሳቸውን እያስገቡና ፍርድ እየሰጡ በሰፊው ያትታሉ። እርግጥ እንዲኖሩበት ዘመን አይብዛና አይጠንክር እንጂ በታሪክ መዛግብት ያገኙት ሁነት ላይ አቋማቸውን መግለፃቸው አልቀረም። ለምሳሌ ያህል ማህሌታይ ያሬድንና ተዋነይን የሚተቹበት አግባብ ከተለመደው ኢትዮጵያዊ አቋም ጋር ቀጥታ የሚላተም ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ማህሌታይ ያሬድን ገፅ 114 ላይ እንዲህ ይሉታል፡-

"...በዚያም ዘመን በትግሬ የዛር ዘፈን በዛ፤ በቤተክርስቲያን እስቲዘፈን ድረስ። በዚያውም ወራት አንድ ድምፁ መልካም ደብተራ ተነሳ፤ በግዕዝ ቋንቋ የሚዘፍን ማኅሌታይ፤ ስሙ ያሬድ የተባለ። ... ያሬድ ዜማ ከተጀመረ ወዲህ በኢትዮጵያ ትምህርት ጠፋ። በኢትዮጵያ ሊቃውንት ህፃናቱም ኑሮዋቸውን ብቻ በዜማና በቅኔ አድርገውት ይኖራሉ። ሌላ ትምህርት አላገኙም፤ በዚህ ምክንያት ምስጢረ

ሥጋዊን የሚያውቅ ሰው ታጣ። የቴዎሎጎስ (የቴዎሎጂ፣ ነገረመለኮት) ትምህርትና ክርክር አልተሰበከም። በክርስቶስ ላይ ይሟገታሉ፤ ወዲያው ይጠነቁላሉ፤ ወዲያው ኃይማኖታቸውን ይጥላሉ። ደግሞ የያሬድ ጥበብ ብዙ ሰው አቦዘነ። የቅኔውም ግጥም የተጀመረ በዚያ ወራት ነው። ምልክቱም ያስታውቃል። በልደትና በፀሎት ሐሙስ፣ በቅዳሜ ስዑር፣ በትንሳኤ፣ የእጣነ ሞገር ምልክት በትንሳኤ ዘጉባኤ ቃና ስለመወድስ እስከዛሬ ያመለክተናል። የቅኔ ብልሃት ኢትዮጵያን አደኸየው። አንድ ሰው ቅኔ ሲማር አሥር ዘመን ተቀመጠ። በሰው አሳብ ቁራሽ እየለመነ፤ ላይረባ ዕድሜውን በከንቱ ጨረሰው።"

አለቃ ተክሌ ለታሪክ ድርሳን ባልተገባ አኳኋን ከጠሉና ከወደዱ ጣልቃ ለመግባት አያንገራግሩም። ፀብ የገጠሙትን የታሪክ ሰው፤ ከራቀ በብዕር ቅዝምዝም፣ ከቀረበ በሽመል ይፋለሙታል። እንደ ማህሌታይ ያሬድ ሁሉ የቅኔውን ሊቅ ተዋነይን፤ "የጎንጅ ደብተራ ጠንቋይ የነበረው..." ይሉታል። በተረፈ መፅሐፉ የትርከት አፈሳሰስና የቋንቋ ትባቱ ከስፋ እንዳይለዩ ፈትሮ የሚይዝ ነው። በተለይ በብዙ የታሪክ መፅሐፍቶቻችን ላይ የማይስተዋል ጠባዩ አስገራሚና አስደማሚ የተራ ሰዎች ገጠመኞችን ማካተቱ ነው። ታሪካችን (አሁንም ቢሆን) ከንጉሱ እራስ የማይወርድ ዘውድ አከል ባህርይ መያዙ ለቆጫቸው በከፊልም ቢሆን የአለቃ ተክሌ መፅሐፍ ምላሽ ይዞ መጥቷል ማለት ይቻላል። ብዙ ስም የለሾች ስም ያለው ሥራ ሰርተው እንዳለፉ ሲነገረን ከመገረም በላይ የመዝናኛነት ጠባይም አለው። ለምሳሌ ባሻ ውድነህ እናንሳ። ባሻ ውድነህን አፄ ቴዎድሮስ ጋፋት በግዳጅ ስራ ያሰሯቸው ከነበሩ ፈረንጆች ልምድ ቀስሞ የመጀመሪያውን ኢትዮጵያዊ መድፍ የሰራ ነው። ባሻ ውድነህ ከራስ አዳል ጋር ሆኖ፣ ከራስ ደስታ ጋር ሲዋጋ የሰራውን መድፍ ተጠቅሞ እንደነበር አለቃ ይነግሩናል።

"ያን ቀን ውዴ የኮሶ እሸት፤

በሰራው ጉዳይ እንደ መለኮት፤... ብሎ ቢተኩስ የራስ ደስታ በቅሎ ደንግጣ ተንበረከከች" ይሉናል። ባሻ ውድነህ ለምን አልቀጠለም? ከሱ ወዲያ መድፍና ነፍጥ ፈረንጅ ስንለምን አልኖርንም?.....

.... የአለቃ ተክሌ ሥራ ከአገር ጉዳይ አልፎ በሰው ጠባይም እንድንደመም ግድ የሚሉ ታሪኮች ይዟል። በአፄ ምኒሊክ ዘመን በኩብት ማለቅ በተነሳው ረሃብ ማግሥት የሚቀርብልን የአንዲት ስም የለሽ ታሪክ፤ በእርግጥም የሰው ልጅን ፍላጎት መዝምዞ ለማሳየት ምሳሌ የሚሆን ነው። "ጥጋብ በሆነ ባመቱ" ይላሉ አለቃ ተክሌ "የሰናን ኢየሱስ ደገኛ (የደጋ ሴት) ድንች ያወፈራት እንኳን ባመቱ

በኑኃ ዘመን (ዝንተ አለም) የማይረሳውን ዘመነ ረሃቡን ድሮ ረስታው ጠገበችና እንዲህ አለች:-

ጉንጬም ቅጥ አጣ፣ ቂጤም ቅጥ አጣ
አባከህ ጌታየ የአምናውን ቀን አምጣ።.... ብላ ዘፈነች። ይህ ነገር በንጉሡ በተክለሃይማኖት ጆሮ በደረሰ ጊዜ አስመጥቶ አርባ ገርፎ ወህኒ አስሮ ወፍሩዋ ጎድሎ፤ እንደጨርቋዋ ቅል ገላዋ ሲጨማደድ ፈትቶ ለቀቃት።" (ገፅ 294)

ይቺ ታሪክ ወደ ሰው ልጅ ሁሉ ተፈናጥራ የምትደርስ የእሳት ፍንጣቂ ትመስላለች። ከተራበ ለጠገበ መታዘኑ ለምን ይሆን? የሚያደርጉትን የሚያሳጣው ረሃብ ሳይሆን ጥጋቡ በመሆኑ አይደለም? ድሎት ከችግር በላይ የሚፈትነን አፈጣጠራችን ምን ቢሆን ነው?

"የአለቃ ተከሌ መፅሐፍ አለህ?" ስል የጠየኩት ወዳጄ ይኼንን መልስ እንደሰጠኝ ጠቅሼ ነበር፤

"አዎ፣ አለቃ ተከሌ ብዙ ቦታ አራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል። እንዲህ ሲያጋጥመኝ ቋቅ ይለኛል። አንብቤ ስጨርስ መፅሐፉን አንድ ቀን ቤቴ አላሳደርኩትም። ለሰው ሰጠሁት። አንዳንድ ሰው ይሄው ነው፤ ማሸነፍ የሚችልበት ተሰጥኦ እያለው፣ ሽልማቱን በጉልበት ለመውሰድ ይተናነቃል"

"የኢትዮጵያ ታሪክ"ን ከአንድም ሁለት፣ ሦስቴ ባነበውም፣ ጓደኛዬን ያናደደውን፣ እኔ ልብ አላልኩም ነበር። የንባብ ልዩነት የሚከሰተው ከእንዲህ አይነቱ ልዩ ልዩ ትኩረት አንፃር መሆኑ ግርም አለኝ። አንዳንድ አንባቢ የሚባለውን ልብ ብሎ ሲከታተል፣ ሌላኛው ደግሞ መባያውን አትኩሮ ይከታተላል። አለቃ ተከለኢየሱስ ያሉት እኔ ጋ ሲደርስ፣ ያሉበት መንገድ የት ተቆርጦ ቀረ? የተባለው እንዴት መባያውን ጋርደብኝ?

በነባር መዛግብት ሆነ መፃህፍቶቻችን ዘንድ የሚበዛው የደራሲው ትህትና አራስን አሳንሶ የማቅረብ አባዜ እንጂ ሙብለጥለጥና መታበይ አልነበረም። የመታበይ ጉዳይ በሐይማኖት አስተምህሮ ዘንድ ጠበቅ ያለ ተግሳፅ የሚያስከትል እንደሆነ ስለሚያውቁም ይሆናል፤ መንፈሳቸው ወደ መታበይ አጋድሎ አይስተዋልም። ሉቃስ በወንጌል፤ ኢየሱስ "ፃድቃን" እንደሆኑ ለራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን

ሁሉ በጣም ለሚገቁ" የሚሆን ምሳሌ እንደተናገረ ,ይጠቅሳል። ምሳሌው የቀራጭና የፈሪሳዊ ፀሎት ላይ መሰረቱን የጣለ ነው። ፈሪሳዊው በመታበይ በልቡ እንዲህ ይላል፡-

"እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዓመፀኞች፣ አመንዝሮችም ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሀለሁ። በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፣ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ"

ነባር ሰነዶቻችንና መፃሕፍቶቻችን የሚፃፉት ይሄንን ፈሪሳዊ ላለመሆን በሚጥሩ ሊቆች በመሆኑ የበዛ ትህትና ሲቀርብልን ቆይቷል። ለምሳሌ ያህል ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል የ"ዝክረ ነገር" መፅሐፋቸው መግቢያ ላይ እንዲህ ይላሉ፡- "እኔም ...፤ እዳዬን ለመክፈል ስል ያዋቂነትና የታሪክ ፀሐፊነት ችሎታ አለኝ በማለት አንዳች ትምክህት ሳላስገባ... ይህነን "ዝክረ ነገር" የተባለ ስም የሰጠሁትን መፅሐፍ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ አዘጋጅቻለሁ" ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ። ከዚህ አልፈው ማስታወሻ ማሰናዳት "ክፍሌና ትምህርቴ" አይደለም በሚል "ትህትና" እራሳቸውን ሊታዩ ከሚገባቸው መጠን በታች ያሳንሳሉ።

.... ታዲያ አለቃ ተክለኢየሱስ ይሄን ነባር "ገረገራ" እንደምን ተዳፍረው ዘለሉና (በጓደኛዬ ገለፃ እራሳቸውን ቆለሉ?) ነው ወይስ ነባሩን እራስን የማሳነስ ማስመሰል ጠልተው ለለውጥ አመፁ? እንዴት ደፈሩ?...

... እነዚህን ጥያቄዎች እርስ በእርሳቸው እያጋባሁና እያዋለድሁ መፅሐፉ እስኪወጣ ጠበኩ። አገኘሁት። በአንድ አቅጣጫ የተቀየደው ንባቤ፤ ከብዙ "እኔዎች" ጋር ገና መፅሐፍ የተፃፈበትን አቅድ በሚያስረዱበት መግቢያ ውስጥ እራሳቸውን በነባሩ ብሒል፤ "እኔ" ሳይሆን "እሱ" እያሉ ብዙ ማሞካሻ መሰል እስተያየት ይሰነዝራሉ። እንዲህ....

"..... የአፄ ዮሐንስን ሊቄ መርአዊ፣ የአጼ ምኒልክን የዘጌው አፈወርቅ፣ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መልአከ ፀሐይ ብሩ... ባጭር በጭሩ ጎደሎ ታሪክ፣ ያውም ሐሰትና ውዳሴ ከንቱ የበዛበት ጽፈው ነበር። ነገር ግን ከዚያ ወዲህ ደግሞ አለቃ ተክለኢየሱ መርምሮ፣ የሁሉንም ታሪክ አይቶ በጎ በጎውን ንግግር ቀድቶ፣ ክፉ ክፉውን ንግግር በፀያፍ አውጥቶ ነቅፎ ለማስነቀፍ፣ ነውራቸውን ፅፎባቸዋል።"

ይላሉ። በእርግጥም ደግሞ ሦስቱንም ታሪክ ፀሐፊዎች ነቅፈው የማስነቀፉ ሐይለ ቃል የተቀላቀለበት ትችት ይሰነዝራሉ። በተለይ የዘጌውን አፈወርቅ ገብረኢየሱስ "ለእለቱ እንጀራ ማውጫ ሊሰራበት" እስከማለት ዝቅ ብለው ያዋርዳሉ! ታሪክ ፀሐፊዎቹ ከረመረሙ በኋላ በጉዝጓዙ ላይ እራሳቸውን እንዲህ አቆላምጠው ያስቀምጣሉ፡-

"... ደግሞ በየነገሥታቱ ውስጥ በጎጃም ለተደረገው ታሪክ እንደ አለቃ ተክሌ ምርምረው ሙሉ ታሪክ አገናዝበው አልፃፉም። ... አለቃ ተክሌ ግን ንጉሥ ተክለ ኃይማኖት ወዳጁ ነበርና ወረታውን ለመመለስ ደግንነቱንና ቸርነቱን ለኋላ ልጅ ወሬ ለማቆየት፣ አመስግኖ ለማስመስገን፣ ከአርጌ ልጅ ወገኛ፣ ከጀግና ልጅ አርበኛ፣ ዘምቶ ከአረጀ፣ በልቶ ካፈጀ፣ እየጠየቀ ከቀዳማዊ ራስ ኃይሉ እስከ ዳግማዊ ራስ ኃይሉ ድረስ በእውነት እንበላ ሐሰት ውዳሴ ከንቱ ሳይጨምር ታሪክ ፃፈ። ከዚህ ቀደም እንደአለቃ ተክሌ አድርጎ በጎጃም ታሪክ የፃፈ ሰው አልተነሣም።"

በውጭው አለም ልብ በሉ፤ እራሳችውን ነው እንዲህ የሚያቆለማምጡት። በውጭው አለም ልብ በሉ፤ ጥበብንና ጥበበኞችን ማቆላመጥ ላይ "CRITICAL APPRECIATION" የተሰኘ ጥበብንና ጥበበኞችን ማቆላመጥ ላይ ያተኮረ የሒስ ዘርፍ እንዳለ ሰምቼ ነበር። አለቃ ተክሌ ከዚያም አለፍ ብለው "እራሴን በራሴ፣ አፌን ሌሎች የማቆላመጥ ሒስ እስኪሰሩባቸው አልጠበቁም። "እራሴን በራሴ፣ አፌን በምላሴ" (Self Appreciational (?) ላይ ይጣዳሉ። እራሳቸውን ለመሳም እስኪዳዳቸው ድረስ እርቀው ይጓዛሉ። አለቃ ተክሌ፣ እነ አፈወርቅ ተክለኢየሱስ ነገሥታቱን ለማስደሰት ማሞገሳቸውን ነቅፈው፤ ብዙ ሳይርቁ ለራሳቸው ውዳሴ ከንቱ በማቅረብ ትዝብት ላይ ይወድቃሉ። ከታሪክ አፃፃፍ አንፃር ብቻ ሳይሆን በዋናው ሙያቸውም፤ በስዕልና ቅርፃ ቅርፅ ረገድ ለራሳቸው የሚቆርሱት አንሶ አልተገኘም። እንዲህ...

".... ከቤተክህነት ጥበባቱን ሁሉ ፈፅመው ያወቁ አለቃ ተገኝ እና አለቃ ተክሌ ነበሩ። ንጉሱም ይወዳቸው ነበር .... ስለዚህ ስራተኛው ሁሉ የጌጥ ሥራ ሲያምረው አዲስ አዲስ ጥበብ በየዓይነቱ ከአለቃ ተገኝና ከአለቃ ተክሌ ዘንድ ደጅ ጠንቶ፣ አቆላምጦ ይወስድ ነበር። ንጉሡም ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው ለመስቀልና ለጽዋ፣ ለፅና፣ ለካህናቱ የሚሰጠው ለጸናጽል፣ ለመቋሚያ፣ ለጀግናው የሚሰጠው ላቢተዋና ለሸሆሮ፣ ለኮመድና ለቤነቻ፣ የንቅሉ ጥበብ ከነሱ ልብ ይፈላ (ይመነጭ) ነበር።..... አለቃ ተክሌና አለቃ ተገኝ ከልባቸው ሥፋት፣ ከጥበባቸው ብዛት የተነሣ

ሰው ያልያዘው በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ያልተሰራ፣ አዲስ አይነት በድንጋይ ማኅተም የታተመ፣ መቋሚያና ጽናጽል ሰርተው... አበርክተው ነበረ።"

አለቃ ተከሌ፤ እንደ አለቃ ተገኝ አይነቱ ለፍቅር ሲያቀርቡ፣ ከሙገሳም የሚያካፍሉትን ያህል የተቃረናቸውን ደግሞ በአቃቂር ዝብትልትሉን ለማውጣት ወደ ኋላ አይሉም። ወደ መፅሐፉ መግባደጃ ላይ በራስ ሐይሉ አስተዳደር አለቃ ተከሌ ገሸሽ ተደርገው፣ ሌላ ሰአሊ እንደተተካ ይናገሩና ሊቀጠበብት የተሰኙ ማዕረግ የተቸረው ብርሃኑ የተሰኘው ሰዓሊ፤ "በፎቶግራፍ ያየውን ማንሳት ነው እንጂ ከልቡ አንቅቶ ቤተክርስቲያን መሳል አይሆንለትም ነበረ" ይሉታል። ይሄ አዲስ ተሿሚ ሰዓሊ፤ አለቃ ተከሌን "አንቱ" ከማለት ወደ "አንተ" ስለተሸጋገረ፣ ይሻለኛል ብለው "የሙያ ጅል፣ የጠባይ ታናሽ ያላንተ የለም" የሚል ስድብ እንደላኩበት ይገልፃሉ።

የአለቃ ተከለየሱስ "የራስ ግምት" የበዓሉ ግርማን የኪነት ሰው ድምዳሜ አስታወሰኝ። "በደራሲው" ውስጥ ነው። ዋናው ገፀ ባህርይ ከሰብለ ጋር ስለ ደራሲው እስክንድር ሲያወሩ እንዲህ ይባባላሉ:-

"እራሱን ያመልካል መሰለኝ" አለች በልዩ ልዩ አቀማመጥ የተነሳቸውን ፎቶግራፎች እየተመለከተች።

"የኪነት ሰው አይደል ?"

"ቢሆንስ ?"

"የፈጣሪን ሚና ይጫወታል"

"ታዲያ እግዜር እራሱን ያመልካል ልትለኝ ነው?"

"እሱማ የሚያመልኩትን ፈጥሮአል"

ለበአሉ ግርማ የኪነት ሰው የሚያመልኩትን ፍጡሮች መፍጠር የተሳነው፤ እራሱን አምላኪ ነው። አለቃ ተከለኢየሱስም፤ ከታሪክ ፀሐፊነታቸው በላይ ሰዓሊና

ቀራፂነታቸው፣ በዓሉ ለጠቀሰው ዕጣ-ፈንታ ሳይዳርጋቸው አልቀረም። ቢሆንም ይሄ ለእኛ እንጂ ለተቀረው ዓለም አዲስ ነገር አይደለም። እንደ ፈረንሳዩ ንጉስ Napoleon Bonaparte የተዘጋጀላቸውን "ዘውድ" ከጳጳሱ ነጥቀው፣ እራሳቸውን ለራሳቸው ሥርዓተ ንግሥ የሚያስፈፅሙ የኪነት ሰዎች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ጀርመናዊው ፈላስፋ Friedrich Nietzsche እራሱን የሚያወድስና የሚያንቆለጳጵስ አንድ መፅሐፍ አለው። Why I am so wise (ለምን በጣም ብልህ እንደሆንኩ) በሚል ርዕስ በ1908 ዓ.ም የታተመው ይሄ መፅሐፍ፣ ሦስት ምዕራፎች አሉት። ለምዕራፎቹ የሰጣቸውን ንዑስ ርዕሶች ማየት ብቻ የኒቼን አዝማሚያ ግልፅ ያደርጋል። "Why I am So wise"፣ "Why I am so Cleaver" እና "Why I write such good books" የሚል ነበር። መፅሐፉ በወጣበት ዘመን መነጋገሪያ የሆነ ቢሆንም፣ በመጨረሻ ኒቼ ላይ በወቅቱ የደረሰው የመነጠልና የአእምሮ ህመም ተደራርቦ፣ መፅሐፉን እንዲፅፍ እንደገፋፋው ተደምድሟል። የእኛ አለቃ ተክለኢየሱስ ምክንያታቸው ምን ይሆን?... በእርግጥ ከዚህ ጋር አያያይዙት እንጂ ዶ/ር ሥርግው ገላው የሚነግሩን አንድ የጥናት ውጤት አለ። አለቃ ተክለኢየሱስ በአብነት ትምህርታቸው እጅግ ደካማ ከሚባሉት የሚመደቡ እንደነበሩ፣ ለቅኔ ሆነ ለዜማ ትምህርት ሳይመጥኑ ቀርተው ወደ ስዕልና ቅርፃቅርፅ መዛወራቸው የበታችነት ስሜት አሳድሮባቸው ወደ ተቃራኒው ጥግ ገፍቷቸው ይሆን? አይታወቅም!...

... የሚታወቀው አለቃ ተክለኢየሱስ ለራሳቸው ያላቸውን ግምት፣ እኛም እንድንደግምላቸው ግድ የሚለን ግሩም መፅሐፍ እንዳቀረቡልን ብቻ ነው። እንደ ናፓሊዮን በናፓርቴ፣ ከጳጳሱ እጅ ባይነጥቁም፣ "ዘውዱ" ጭንቅላታቸው ላይ፣ መጥለቁ አይቀርም ነበር። ትንሽ ቸኮሉ ብለን እንለፈው?

# የደሮሲ ቤት ፲ ገነት ቅብ ሲኦል ነው!

ጆርጅ በርናርድ ሾ ቤት የሄደ አንድ ወዳጅ ተዘዋውሮ ቢመለከት አይኑን ቀለለው አሉ፤ ልብ ብሎ ሲያጤን ለካ በዘመኑ እንደ ዋነኛ ቤት ማሳመሪያ ይወሰድ የነበረው የአበባ ዝንጣፊ ሾ ክፍል ውስጥ አልነበረም። ስለዚህ አንድ ጥያቄ ጣል አደረገ፤ "ሚስትር ሾ፤ አበባ የምትወድ ይመስለኝ ነበር"

ሾ መለሰ፤ "ልጆችም እወዳለሁ፤ ነገር ግን ስለወደድኳቸው አንገታቸውን ቆርጬ አላስቀምጥም"

አ! መውደድ በስምሽ ስንት ግፍ ተሰራ ማለት ይሄኔ ነው። የሚወዱትን ነገር ህይወት አሳጥቶ ማጌጥ "በአበባ ይብቃ" አላልንምና በሌሎችም ነገሮች ቀጥሎ ይስተዋላል። ወፍ እንወዳለን፤ የኛ ለማድረግ በፍርግርግ እናስራለን፣ ቢራቢሮ እንወዳለን ሰብስበን እናደርቃለን፣ ሴት እንወዳለን አንቀን እንገድላለን ...

... ከዚህ ጋር ተነፃፃሪው የዘመኑ "መውደድ" ደግሞ በመፃህፍት ላይ ተከናውኖ አጋጥሞኛል። የተወደዱ የአማርኛ መፅሐፍት በሚል መነሻ የተለያዩ ሥራዎችን የኮምፒዩተር ውልድ በማድረግ መቀባበልና በ"ዌብሳይት" መልቀቅ ምን ይሉት "መውደድ" ይሆን? የዚህ ሰለባ ከሆኑ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን አይቻለሁ። የፀጋዬ ገብረመድህን "እሣት ወይ አበባ"፣ የስብሃት ገብረእግዚአብሔር "አምስት ስድስት ሰባት"፣ የደበበ ሰይፉ "የብርሃን ፍቅር"፣ የከበደ ሚካኤል "የትንቢት ቀጠሮ"፣ የብርሃኑ ዘሪሁን "የታንጉት ሚስጢር"፣ የዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስ"፣ የበውቀቱ ስዩም "በራሪ ቅጠሎች" ...

... ካየኋቸው ባሻገር ከሰው የሰማኋቸው ደግሞ እጅግ ብዙ ናቸው። ይሄ ዘመን አመጣሽ ወረርሽኝ ከህግ በላይ በመንሰራፋቱ ከሕሊና ውጭ የሚዳኘው እንደሌለ

ግልፅ ነው። ድርጊቱ ከሕሊና በላይ የሚሆነው እራሱ ሕሊና ሳይኖር ሲቀር ብቻ ይመስለኛል። "ሙጥኝ" የሚባለው የሰው ልጅ አስተውሎት ከሌለ ደራሲውን እንደ አበባ ዘንጥፎ የጥቂት ቀን መድመቂያ ከማድረግ በማይተናነሰው "መውደድ" መቀጠል ይቻላል።

ባለፈው ሳምንት አንድ ወዳጄ ደውሎ የእኔም መፅሐፍ የኮምፒዩተር ውልድ ተደርጎ ዌብሳይት ላይ መለቀቁን ነገረኝ።

"የቱ መፅሐፍ?" ስል ጠየኩት

"አጥቢያ" አለኝ

ግራ ተጋሁ፤ "አጥቢያ" ሦስት ሺህ ኮፒ የታተመው ከስምንት ዓመታት በፊት ነበር። ተሸጦ ያለቀው በሰባት አመታት "ምጥ" በመሆኑ ለዚህ መፅሐፍ መጥፎ ትዝታ አለኝ፤ አሳታሚው ሱቅ ውስጥ ተደርድሮ ስመለከተው እንደ ደም ማነስ ያለ ተስፋ መቁረጥ ኸው አድርጎ ይወስደኝ ነበር። የህትመቱ ወጪ የተሸፈነው በአሳታሚውና በአንድ ጓደኛዬ መዋጮ ሲሆን መፅሐፉ በሰባተኛ ዓመቱ ሲያልቅ ያተረፍኩት ትልቅ እፎይታ ብቻ ነበር። አሁን ከአራት ወር በፊት ደግሞ ለሁለተኛ ዕትም የሚያነሳሱ መረጃዎች በመብዛታቸው ከአንድ አሳታሚ ጋር ተዋውዬ ሦስት ሺህ ቅጂ ታተመ። "ውረድ እንውረድ" ያሉት የ"አጥቢያ" ጠያቂዎች፤ "አፋፍ ቆመው ስላስደበሰቡ" የታተመው እንዳለ ተቀምጧል የሚል መረጃ ሰሞኑን ደርሶኛል። ለሁለተኛው ዕትም ሁለተኛ ዙር ተስፋ መቁረጥ እየዳዳኝ ሳለ ነው በዌብ ሳይት መለቀቁን የሰማሁት። የሚገርመው ደግሞ ኮፒ ያደረጉት ሁለተኛውን እትም ከእነሽፋኑ ነው። ለምን? ዋጋው በዛ? ከገበያ ጠፋ? ያን ያህል ተፈለገ? .... ይሄ ሁሉ ምክንያት አይሆንም መንስኤው። ያው አበባን ወድዶ በመዘንጠፍ የመርካት አባዜ የተጠናወተው ይመስላል።

ጥሩ ደራሲ ሆኖ ግሩም መፅሐፍ ፅፎ የመከበር ባህልም ሎተሪ ቆርጦ ዕድለኛ ከመሆን ጋር ተነፃፃሪ ነው። መከበር ቀርቶ መኖር አይቻልም። ይሄንን በሌሎቹ ደራሲዎች ህይወት ሳይሆን ከእኔ ኑሮ አረጋግጫለሁ። እንዲህ ይከፋል ብዬ ባልጠብቅም ከመጀመሪያው ደራሲነት መሻቴ ጋር ድሎትን አዳብዬ አላሰብኩም። አዘቅቱ ግን እገምተው ከነበረው በታች፣ ጨርሶ የማይታይ እሩቅ ነው። ለተረት የቀረቡ የህይወት ቅንጣቶች የበዙበት ዝንጉርጉር። ይሄም ሆኖ፤ ያንን ሁሉ መከራ ለማካካስ የማይገድደው የሰው መውደድ አለበት። ያለ መዋሸት የደራሲ ቤት ገነት

ቅብ ሲኦል መሆኑ እሙን ነው። በእጥረት የተወጠረ የመከራ ዳስ ሆኖ ሳለ ሌሎች ነፍሶች እንዲጠለሉት ግድ ያለ ግዜ፣ ያኔ መከራው ይከፋል። ሚስትና ልጆች ካሉ ማለቴ ነው። ለዚህ ማሳያ የበአሉ ግርማን "ደራሲው" የተሰኘ ልቦለድ ማንበብ በቂ ነው። ደራሲው ሲራከ በመፃህፍቶቹ የገባውን ኪሳራ ሚስቱና ልጁ ሲገፈግፉ በጉልህ ይታያል። በእጥረት የመወጠሩ ችግር በኑሮ ጉድለት ብቻ የሚተረጎም አይደለም። የፍቅርና የእንክብካቤ ማጣት የተጠናወተውም ነው። ለዚህ ደግሞ የበአሉ ግርማን ልቦለድ ሳይሆን ህይወቱን እንጥቀስ። የ"ከአድማስ ባሻገር"ን መታሰቢያነት ለባለቤቱና ለልጆቹ ሰጥቷል።

የመታሰቢያነቱን ምክንያት ደግሞ ምስጋናው ላይ እንዲህ ሲል ገልፆታል፡-

"ለውጥና ሽርሽር እያማራቸው ቤት ውስጥ ከወር ወር ተዘግተው በመከረም ፍላጎታቸውን መስዋዕት ላደረጉት ለባለቤቴ ለአልማዝ፣ ለልጆቼ ለመስከረምና ለዘለአለም ምስጋና ይገባቸዋል።እነዚህ ነፍሶች መስዋዕት ያደረጉት ፍላጎታቸውን ብቻ ሳይሆን ባለቤት ባሏን፣ ልጆች አባታቸውን ጭምር ነው። ደራሲው ዓመቱን ሙሉ ከድርሰት ጋር ነውና ቤት ውስጥ ቢሆንም ከእነርሱ ጋር እንዳይደለ እሙን ነው። እናስ? ባልንና አባትን ያህል እጥረት እንኳንስ በጎዳደለ ኑሮ፣ ድሎት በበዛበት ህይወት ይካካሳል?

እንግዲህ መፅሐፍትን የኮምፒዩተር ውልድ አድርጎ ያለ ዋጋ ማስቀረት ከህግም በላይ የህሊና ጥያቄ የሚኖርበት እዚህ ላይ ነው። ሰው ስንቴ ይቀጣ? በኑሮ እጥረት፣ በባል ፍቅር እጦት፣ በአባት እንክብካቤ ጉድለት ... ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ በውርስ መፃህፍት መና መቅረት፤ ከዚህ ውስጥ እጅን ማስገባት ንፁሃንን ሰለባ የማድረግ ግፍ አለበት።

አደግመዋለሁ!!

... ይሄ ዘመን አመጣሽ ወረርሽኝ ከህግ በላይ የተንሰራፋ ነውና ከህሊና ውጭ የሚዳኘው እንደሌለ እሙን ነው። ድርጊቱ ከሕሊና በላይ የሚሆነው እራሱ ሕሊና ሳይኖር ሲቀር ብቻ ይመስለኛል። "ሙጥኝ" የሚባለው የሰው ልጅ አስተውሎት ከሌለ፣ ደራሲውንና ቤተሰቡን እንደ አበባ ዘንጥፎ የጥቂት ቀን መድመቂያ ከማድረግ በማይተናነሰው "መውደድ" መቀጠል ይቻላል።

# ደራሲያኑን እንደሰው ያለመመልከት አባዜ

ደራሲ፣ ፊት ለፊት ስራው፣ ከበስተጀርባ ደግሞ ህይወቱ ይገኛል። ሥራው የህይወቱ ማጣቀሻ ነው የሚሉ አሉ። በዚህም ሥራውን እንደ አነፍናፊ ውሻ አስቀድመው ህይወቱን ያንጎዳጉዳሉ። "እንዲህ ሲል የፃፈው በህይወቱ እንዲያ ስለሆነ ነው።" በማለት ሥራና ህይወቱን ያጋባሉ፣ ያፋታሉ። ስለዚህ የደራሲ ቤት በሩ ቢዘጋም ከመግባትና ከመውጣት አይከላከልም። የደራሲ ደጃፍ ውሻ ቢታሰርበትም አያስፈራም። ቢታጠርም ከዘላዮች አያመልጥም።

እኛ ዘንድ እንዲያ ለማድረግና ለመሆን የሚያስችል ሁኔታ የለም። ደራሲ የጓዳ ህይወቱ ቀርቶ አደባባይ ያዋለው ሥራው እንኳን "በሙሉ አይን" አይታይም። ሀዲስ አለማየሁ፣ በዓሉ ግርማ፣ መንግሥቱ ለማ፣ ከበደ ሚካኤል፣ ፀጋዬ ገብረመድህን... የኖሩት ቀርቶ የፃፉትም የሚታየው በእሽኩርምሚት ነው። ከሥራዎቹ ፊት "ተልመጥማጮች" ያጠሩት የሙዚየም "ከር" አለ፤ አይታለፍም። የፅሁፍ ማስጠንቀቂያም አለ፤ "በእጅ መንካት ክልክል ነው" የሚል። እኔ የሚገርመኝ "የተልመጥማጮቹ" በክር ማጠርና መንገር አይደለም። የእኛ አክብሮ ሥነ-ፅሁፍን በሙዚየም ህግ መጎብኘት እንጂ ...።

"የሀዲስ ዓለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር ተረታማ ነው" ከተባለ "ቱግ" የሚሉ "እንቀራባጮች" አሉ። "በዓሉ ግርማ ልቦለድ ያድፋፋል፤ አጨራረሱ መሰላቸት የሚታይበት የተካለበ ነው" ከተባለ የሥራው "ተሸላሚዎች" ፣ "ሐይማኖት የግል ነው፣ ለምን ይነካብናል?" በማለት ህገ መንግሥት መጥቀስ ይዳዳቸዋል። "የመንግሥቱ ለማ ግጥሞች ጥብቀትና ፍላት የሌላቸው በተሃ ናቸው" ከተባለስ? ጉዳዩን የቤተሰብ ፖለቲካ አድርገው "እብዬን?" የሚሉና የዛገ ጦር ከራስጌ የሚመዙ ሞልተዋል። "ከበደ ሚካኤል መከሩ፣ ዘከሩ እንጂ አልተቀኙም" የሚል

ካለ፣ "ባባቶቻችን ደም" ይዘፈንበታል። "ፀጋዬ ገብረመድህን ግጥም እንጂ ዝሩው ያዳግተዋል" ብሎ በህይወት መኖር ያዳግታል ...

የእኛ ሥነ - ፅሁፍ መብላላት ሲገባው የሚደነብሸው ለዚህ ሳይሆን ይቀራል? ገንዘብ ያወጣሁበትን መፅሐፍ (ለመግዛት)፣ ጊዜ ያፈሰስኩበትን ልቦለድ (ለማንበብ)፤ ቦታ የሰጠሁትን ሥራ (ለማስቀመጥ)... እንዴት በሌሎች አይታ እንድገመግመው እገደዳለሁ? እንዳቅሜ ከቻልኩ "ብበላው"፣ ካልቻልኩ "ብደፋው" ከውይይት ያለፈ ከሳሽና ወቃሽ ሊመደብብኝ ይገባል?...

... እንደውም ከሥራዎቹ አልፈን ደራሲዎቹ ህይወትና ኑሮ ላይ ብንሳፈር "ውረድ!" ባይ አልፍኝ አስከልካይ ሊመደብብን ይገባል? ስለ ሀዲስ ዓለማየሁ ብህትውና፣ ስለ በዓሉ ግርማ ውሎና አዳር፣ ስለመንግስቱ ለማ ሽሙጥ፣ ስለ ከበደ ሚካኤል የኩርፊያ ኑሮ፣ ስለ ፀጋዬ ገብረመድህን የተመላኪነት መንፈስ ... ማውራት ግለሰብ ማውሳት ነው?...

ዮሐንስ አድማሱ ስለ ደራሲ ማውሳት ግለሰብ ማማት ተደርጎ እንዳይወሰድ የሚዘከር ተቀዳሚ ገጣሚ ነው። ስለ ዮፍታሔ ንጉሴ ባቀረበው ጥናት ላይ የባለቅኔውን "የቆንጆ ፀርነት" ከማውሳት አልፎ እናቱ "ሒያጅ" እንደነበሩ ይጠቅስና እንዲህ ይላል፤

"ዮፍታሄን እንዲህ ማንሳቴ አለመልኩ እንዳይመለክ፣ አለግብሩ እንዳይወቀስ፣ እንደ <u>ግዑዝ</u> እንዲታይ ነው።"

ዮሐንስ "እንደ <u>ግዑዝ</u>" ሲል ምን ማለቱ ነው? እንደ ዕቃ? እንደ ሀውልት? ወይስ ምን? ብለን እንጠይቅ። ዮሐንስ ማለት የፈለገው ዮፍታሄ እንደ ግለሰባዊ ህልው፣ አድራሻና መዳረሻ እንዳለው ሳይሆን ለመወያያ ወደ ሀሳብነት ደረጃ ከፍ አድርገን፣ የሰው ልጅ ምስጢር ማስተንተኛ ይሁነን ነው። ደራሲን "ከሰውነት" አውጥቶ ወደ "ሀሳብነት" ማሳደግ፣ ለህብረተሰብ አውጠንጣኝነት የሚበጅ ነው። እኛ ግን ለዚህ አልታደልንም።

በተለይ ጥቂቶቹ ደራሲዎቻችን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ በሥማቸው የሥነ ፅሁፍ ደብር ይደበርና ጭፍን አምልኮ ይካሄድባቸዋል። አለመልኩ ይመለካሉ፤ አለግብሩ ይዘከራሉ፤ በመጨረሻም አይመረመሬ ይሆናሉ።

ይሄን አምልኮ ለመሻር በማሰብ ይመስላል ብርሃኑ ዘሪሁን "አዲስ ዘመን" ጋዜጣ ላይ ስለ ደራሲዎች ቁርቁስ ተከታታይ መጣጥፍ አቅርቦ ነበር። በተለይ መንግሥቱ ለማ እና ፀጋዬ ገብረመድህን ያላቸውን የፉክክር "አተካራ" አጠንክሮ ጠቅሶታል። ስለዚህ ጉዳይ የተጠየቀው ጸጋዬ ገብረመድህን፤ "ጦቢያ" መፅሄት ላይ እንዲህ በማለት መልስ ሰጥቶ ነበር፡-

"... ወዳጄ ብርሃኑ ዘሪሁን ነበር በተለመደ ቅንነቱ በሥነ - ፅሁፍ ዓለም የደራሲያን መከራከርና መወዳደር ሙያውን ያዳብራል፣ የአንባቢውንም ህዝብ ጣዕምና ግንዛቤ ያካብታል በሚል ትክክለኛ ሀሳብ ተነስቶ፣ በአዲስ ዘመን አምድ ላይ "የደራሲያን ጦርነት" ብሎ ያስቀመጠው መልዕክት፣ እሱም እኛም ወደ አላሰብነው አቅጣጫ ሄዶ፣ ለከተሜው የቧልት ፍጆታ ሆነ። እስከዛሬ "ጦርነት" እየተባለ "በምሁራን" አካባቢ ይቧለትበታል። እንጂ ከወዳጄ ከመንግስቱ ለማ ጋር እንኳን ጦርነት ቁርቋዞም አልነበረንም"

ፀጋዬ ይሄን ይበል እንጂ መለስ አድርጎ ስለ መንግስቱ ለማ ቀልድ ለበስ ንግግር ሲገልፅ አንዳች ነገር እንደነበር ሊመጠርጠር እንገደዳለን።

"...እኔ ከገጠር ሜጫ ምድር ከገበሬና ከመለስተኛ ነጋዴ ቤተሰብ መጥቼ፣ አዲስ አበባ በምኒልክ ከተማ፣ ብዙ የሥነ ፅሁፍ ታላላቅ ሰዎች በታወቁበት፣ በደረጁበትና ሥር በሰደዱ መሀል ጉብቼ፣ ገና በሀያ ዘጠኝ ዓመቴ ስሸለም፣ የነፍሳቸውን መክሊት እንደወሰድኩባቸው ያህል በተለይ ጉምቱዎቹ የሥነ ፅሁፍ አባቶች ያደረሱብኝን የምቀኝነት ቁስል በቁጭት ሳስታውሰው፣ የወዳጄ የመንግሥቱ ለማ ደማም ቅሬታ፣ የምቀኝነት ቁስል በቁጭት ሳስታውሰው፣ የወዳጄ የመንግሥቱ ለማ ደማም ቅሬታ፣ እንኳንስ ሊያማርረኝ እንደቅድመ ማስጠንቀቂያ ምክር ነበር የጠቀመኝ። በዛሬው ጊዜ ታዲያን እንደመንግስቱ ለማ ደማም ቀልደኛ፣ ኮሰውን ከማር ለውሶ ማሻር የሚያውቅበት ደራሲ ስለጠፋ ነው፣ የጭቃ ጅራፍ ለጣፊና የጭቃ ጅራፍ "ተለጣፊ" ብቻ የተንሰራፋው። ያም ሆኖ የመንግስቱም ቀልድ አንዳንድ ጊዜ መራራ ነበር"

ሥነ ፅሁፋዊው "በደረቁ እጥበት" የደራሲዎቻችንን ህይወት አንፅቶ የአደባባይ ክት - ልብስ አደረገው እንጂ በየስርጉጡ የተነካካ ነበር። የሚገርመው በላውንደሪ ሥራ መጠመዳችንና በማንፃት ሥራ መለከፋችን የነበረው እንደነበረው የማቅረብን ያህል የሚጠቅመን አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ ብቅ የሚሉ መረጃዎቻችንን ስንመረምር፣ ፀጋዬ ቁርቁሱን እጅግ አድርጎ እንዳለዘበው ይገባናል።

የሥዕልና የሥነ-ፅሁፍ ሀያሲው ስዩም ወልዴ "ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ" የተሰኘ መፅሀፉ ውስጥ ስለዚሁ የደራሲያን የመሽራደድና የመጠቃቃት ባህርይ ይነግረናል። ከበደ ሚካኤል የአፄ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት ሲሸልማቸው፣ ደራሲ ዓለማየሁ ሞገስ በዚሁ በሽልማቱ ጉዳይ ስብሰባ ጠሩ። ወወክማ ለታደመው ሰውም በአደባባይ "ከበደ ደራሲም ተርጓሚም አይደለም። ከበደ ሌባና ባንዳ ነው" እንዳሉ ስዩም ወልዴ ነግሮናል።

እንኳን የጓዳው ህይወት እንዲህ ያሉ የአደባባይ መግለጫዎችም ያለተፈጥሯቸው ውስጥ ለውስጥ እንዲስለከለኩ እያስገደድናቸው ነው። ለምን? ለማን?... ደራሲዎቻችንን ከህልፈት በኋላም፣ ሲወጓቸው እንደሚደሙ፣ ሲነግሯቸው እንደሚደመሙ ከማሰብ፣ እንደ ዮሐንስ አድማሱ ወደ ሀሳብ ደረጃ አሳድጎ፣ አጠቃላይ የሰው ልጅን ማጥኛ ማድረግ አይበጅም? እኔ ይበጃል ባይ ነኝ።

## ኦ! የደራሲ እውነት ከወዴት ነሽ?

ያኔ! ገና "ጥበብ አትሸጥም" የሚለው መፈክር ከተሰቀለበት ሳይወርድ አንድ "ዜና" ጆሮአችን ደረሰ። አንድ የኪነ ጥበብ ድርጅት "ፍቅር እስከመቃብር"ን ወደ ፊልም ሊለውጥ እንደሆነ፤ ለደራሲው ለሐዲስ ዓለማየሁ የቅጂ መብት ዋጋ ሰባ ይሁን ስማኒያ ሺህ ብር እንደከፈለ... ኪነት በዋጋ እንዳትተመን "ዘብ የቆምን" ደምፍላታም ወጣቶች ግራ ተጋባን። አይፈረድብንም። ደራሲ ብር መቀበል ክብሩ የሚፈቅድ አይመስለንም ነበርና ...

"ሐዲስ ዓለማየሁ ብሩን በይፋ ቢቀበሉም በድብቅ ለሌሎች ችግረኞች ይሰጣሉ" ስንል ለመፅናናት ከጃጀለን። ግን፤ ያኔ እንዴት እንዲህ አሰብን?

ትዝ ይለኛል በስነ - ፅሁፍ ክበብ ተሰባስበን ልምዱን እንዲያካፍለን የጠራነው ጎምቱ ደራሲ ሁሉ የሚያስጠነቅቀን ጥቅምንና ጥበብን እንዳናነካካ ነበር። ደበበ ሰይፉ ሲያየን በቁጥር ላቅንበት መሰል ዝም ብሎ ሲያስተውለን ቆየና እንዲህ አለ፦

"ገንዘብ ይገኛል ብላችሁ ከሆነ ካሁኑ ምርጫችሁን አስተካክሉ፤ ገንዘብ የሚገኝባቸው ብዙ አማራጮች አሉላችሁ።"

ከደበበ ቀጥሎ ስብሐት መጣና በአካሉም በአንደበቱም እንዲህ የሚል መልዕክት አስተላልፎ ሄደ፤ "ደራሲ ችስታ ነው" ይሄን ንግግሩን ከአካሉና ከአንደበቱ አልፌ ቤቱን በመጎብኘት አረጋገጥኩ። ተረት ሰፈር፤ ጉሮኖ መሰል ቤት በሩ የተዛነፈ ሳንቃ ነው። አንድ ክፍል፤ ወለል አፈር ላይ እንደ ብርድ ልብስ የሳሳች ፍራሽ ተነጥፋ ነበር። እንድቀመጥ ተጋበዝኩ። የብሎኬት ድርድር ላይ ንፁህ ጨርቅ ተነጥፎበት እዚያ ላይ ተቀመጥኩ። የስብሐት ባለቤት የትምወርቅ ክብሪት ሆነ ሳሙና ስትፈልግ ከእግሬ ስር ከብሎኬት አፍ ውስጥ ትመዝዛለች።

ይቺ ናት ደራሲ! ግን አልፈራሁም። በወጣትነት ደምፍላት መንፈስ እንጂ ሥጋ/አካል መኖሩን ገና አላረጋገጥኩማ!

... አንድ ሌላ ቀን ፀጋዬ ገ/መድህንን ጋበዝን፤ "እናንተ ኑ" ብሎ ላከብን። አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ከበብ ውስጥ ተንጋግተን ገባን። የተመካከሩ ይመስል የሁሉም ደራሲዎች መግቢያ ንግግር አንድ አይነት ነው። "በጥበብ ለመሽቀጥ ያደፈጥክ ካለህ ጥበብ የሚመለከበት ቤተ መቅደስ እንጂ የገበያ ዕቃ እንዳልሆነ እነግርሃለሁ" አለ በሚንቀጠቀጥ ግን በሚያስገመግም ድምፅ፤ "አውቀህ ግባበት!!"

ከእኛ በዕድሜ ብዙም የማይልቀው የሺጥላ ኮከብ እንኳን ከግዴለሽ አለባበስና ሁኔታ ጋር በግዴለሽ አንደበት እንዲህ አለን፤ "በድርሰት ያለህን ታጣለህ እንጂ የሌለህን አታገኝም፤ የጥበብ ትርፏ በጥበብ መርካቱ ላይ ብቻ ነው።"

እንደ ሩቅ ምስራቅ ምዕመን እኛም በስምምነት የአካልን መኖር ካድን፤ ሥጋ የነፍስ ቅዠት ነው አልን። የማይኖርበት ህይወትን ከአለማዊነት ቁስ ሳይሆን ከማይጨበጥ መንፈስ ቀለስን። በችግር ተጠበስን፣ ተደጋግፈንም መቆም ተሳነን ... የኛ ዕውነት ከብስቁልና ጋር ተፈጣጥሞ፣ ከችግር ጋር ቆረበ። ጥሪታችን በማንበብና በመፃፍ ላይ ተወስኖ ረሃብ የሚከላ ጉርስ፣ እርቃን የሚሸፍን ልብስ ማግኘት መከራ ሆነ። ያኔ! ከመካከላችን አንዳንዶች በጋዜጠኝነት እስኪቀጠሩ ድረስ አካል በተካደበት ጥበባዊ ዓለም ውስጥ በመንፈስ ቆየን። ሳህታቱም፣ ቅዳሴውም፣ ውዳሴውም ቤተ መፃህፍት ውስጥ ሆነ።

ያኔ! ስህተት ላይ ወድቀን ነበር ለማለት አይደለም። ግን ግማሽ እውነት አንጠራውዞናል (ግማሽ እውነት ካለ) በጥበብ አምልኮት ውስጥ ነፍስ ወረብ የምትረግጠው አካልን ምርኩዝ አድርጋ እንደነበር ካድን። ይሄ የእኛ ብቻ አቋም እንዳልነበር ያረጋገጥኩት ሔለን ዱንሞር የተሰኘች ደራሲ ያለችውን ሳነብ ነበር፦

"People are always surprised when writers receive money, as if they don't have mortgages to pay" (እንደማንኛውም ሰው ደራሲዎች የሚከፍሉት የቤት ዕዳ እንደሌለባቸው ሁሉ ገንዘብ ሲቀበሉ ከታዩ ተደናቂው ሰው ይበዛል።)

እኛም በህዲስ ዓለማየሁ ተደነቅን። በዓሉ ግርማ "ደራሲው" ልቦለዱ ውስጥ ሲራከ የተሰኘው ገፀ ባህርይ የሚናገረውን ደጋግመን እንል ነበር "ሆድ ሲሞላ ጭንቅላት

ባዶ ይሆናል" ተቃራኒውን የጠየቅነው ግን ዘግይተን ነው። ሆዱ ባዶ ሲሆን ጭንቅላቱ ይሞላል? የሚያስበውስ ከረሃቡ ፈቅ ይላል?...

...ቆይተን ቆይተን የአለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራን መጽሐፍ አገኘን። "የጐጃም ታሪክ" ውስጥ አለቃ ተክለኢየሱስ እኛን ተቃርነው የሚሉት አለ። ለእቴጌ ጣይቱ የሳሉት የቅድስት ማሪያም ምሥል ሥር "እመቤቴ አታስርቢኝ፤ አታስጠሚኝ። ረሃብና ጥማት የጥበብ ጠሮች ናቸውና" ሲሉ ፃፉ። መልዕክቱ ለማሪያምም ለጣይቱም፤ እንዲሁም ለእኛም ነበር። ተከራከርን። "የደራሲነት እውነት ከወዴት ነሽ?" አልን።

ተክለኢየሱስ እውነት አላቸው። ባልዛክን ያህል የፈረንሳይ ደራሲ ችግር ሲያራውጠው፣ ረሃብ ሲያድፈጠፍጠው ባሏ የሞተባትን ማዳም ሐንስካንን በሚስትነት አልተጠለለም? እንግሊዛዊው ዶ/ር ሳሙኤል ጆንሰንም ችግር አከለፍልፎ የጋለሞታ "ጭን አሽከር" አላደረገውም?

የደራሲነት እውነት ከሆድና ከጭንቅላት፣ ከብስቁልናና ከድሎት ፈንቅ አይል ይሆን? ሌሎች አማራጮች ፈለግን። አሁንም ዞሮ ፀጋዬ ገብረመድህን አገኘን። ፀጋዬ "ሕሊና" መፅሔት ላይ የደራሲን እውነት ከባቢያዊ አድርገው አገኘን። እንዲህ ይላል።

"ሕዝብ መካከል ሆነህ ነው ስለ ሕዝቡ የምትፅፈው፣ የሕዝቡ ሙቀት ካልሞቀህ፣ በሕዝቡ ሕዝባዊነት ውስጥ ካልታቀፍክ የሱን ሕይወት አትተረጉምም። ስለዚህ ብዙ የብዕር ሰዎች፣ እንደምሳሌ የአሁኑን ትልቁን የሩሲያ ደራሲ ሶልዘንሂትሲንን እንመልከት፣ የታል የሚፅፈው? መሞት መጀመር ማለት እኮ ነው ከሀገር ሕዝቦች አካል ውጭ ከተለየ በኋላ፣ የሕዝብን ሳቁንና ብሶቱን ለመካፈል ከማትችልበት ርቀት ትዝታህ ሁሉ ይተንብህል፣ እሰው በር ላይ ተቀምጠህ ምን ትፈጥራለህ? አጥንቴ የህዝቦቼን ሙቀት ተመግቦ ያደገ ስለሆነ አፍሪካዊ ሙቀቴን እንዳጣ አልፈልግም፣ በረዶም አልወድ፣ አለም ካደነቀው ጠንካራው የኢትዮጵያ ባህል መለየትም ለእኔ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው። እርሱን ደካማ አድርጎ የማቅረብ ቅጥረኝነት ነው። ያኔም ብዕሬን ካገር ለማራቅ የተወጠነብኝ። ደስቶየቭስኪ ካገሩ ሲወጣ ነው የብዕሩ ሞት የተቃረበው።"

ለፀጋዬ ህዝብ ባህር ነው። ደራሲ ደግሞ የባህር ውስጥ ነዋሪ ፍጡር፤ ያለ ባህር የባህር ነዋሪ ምን መጠጊያ አለው? ይሄን ይዞን ወደ ፀጋዬ ገብረመድህን ህይወትና ሥራ ጉራ ካልን በግብርም ተተርጉሞ እናገኘዋለን። የፈራው እና የጠላው የበረዶ አገር፣ ኑሮውን አበድኖበት ይማረር ነበር። አሜሪካ ብሮንክስ ኒውዮርክ ተቀምጦ ልቡና መንፈሱ ግን ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ላይ ይንሳፈፍ ነበር። ሥራው ግን እዚህ እንደነበረበት ዘመን አልሰላለትም። ንግግሩ በተሃ፣ ግጥሙ ዘገባ ሆኖ ነበር።

ዛሬ የዶላሩ ብድር ባፋቸው ገብቶ ልጓሙ
ይኸው በአዲስ ግዳጅ ፍቅር፣ ወንድማማቾች ተሳሳሙ
የሚል ዜና አስታራቂዎች፣ በአለም ነጋሪት ቢያሰሙ
እኔም ቴሌግራፍ ደብዳቤ፣ ለወንድሞች ለማቀበል...

አሁን ይሄ ምኑ የፀጋዬን ግጥም ይመስላል? በእርግጥም እንዳለው ከሀገር መውጣቱ ሥራውን ነጥቆታል። ይሁንና ጉዳዩ የሁሉም ደራሲዎች እውነት አይደለም። ለምሳሌ አዳም ረታ፣ የፀጋዬ ተቃራኒ ደራሲነቱን እንደሚያሰላው ይናገራል። ለአዳም ሀገር እንደ ተራራ ነች። ካልራቋት እራሷ ላይ ሆነው ምኗም የማይታይ "ተራራኮ ቁልጭ ብሎ የሚታይህ ስትርቅ ነው" ይላላ።

ይሄን ጊዜ ነው አ! የደራሲ እውነት ከወዴት ነሽ? ማለት።

## ደራሲያን እንደ አባት ሲፈተሹ...

እንደ ውስጥ ደዌ ጤና የሚነሳ "ታሪክ" አለ፤ እንደ ግርፋት ገላ የሚሸነትር፣ በመጠቃት ልብ የሚመትር። የበዓሉ ግርማን ቅንጫቢ ታሪክ ከአንድ አዛውንት ጓደኛው የሰማሁ ቀን እንደ ያዕቆብ እግዚአብሔርን "ካልባረከኝ" ሳይሆን "ካልነገርከኝ አለቅህም!" ብዬዋለሁ። ለምን? ለምን? ለምን እንዲህ አደረከን? ስል ተሟግቼዋለሁ። መቼም ከእርሱ በላይ ማንም የለ!

... ያንን ሸንታሪ የበዓሉን ቅንጫቢ ታሪክ እንዳለጌታ ከበደ አጭር ልቦለድ አድርጎ "ፅላሎት" የተሰኘ መፅሐፉ ውስጥ አካትቶ አንብቤዋለሁ። ያኔ እንዳለጌታ በታሪኩ እውነትነት ላይ እምነት ስላጣ ወደ ልቦለድነት የቀየረው መስሎኝ ነበር። ነገር ግን አሁን በቅርቡ ያሳተመው "በዓሉ ግርማ - ህይወትና ሥራዎቹ" ውስጥ አካትቶት ድጋሚ አነበብኩት። ድጋሚ ታመምኩ፤ ድጋሚ ፈጣሪን "ለምን ተውከን?" ብዬ መጠየቅ አሰኘኝ፤ ለምን ለመሰቀልና ለመወገር ብቻ ትፈጥራለህ? ...

ታሪኩ እንዲህ ነው ....

.... በዓሉ ግርማ "ደርግ" ከተባለ "ዛር" ጋር ተጣልቶ፣ ተጠልቶ በመንፈስ ደዌ ተይዟል። የሚሄድበት ሁሉ የሚከተሉት መልአከ ሞት መሰል ጠባቂዎች ተመድቦበታል። በዓሉ "ያዳቆነው" ደርግ "ሳያቀስ" እንደማይለቀው ቢገባውም ከመሸሽና ከመደበቅ ይልቅ፣ የበለጠ ለእይታ ይጋለጥ ጀመር። ቀን በብርሃን ብቻ ሳይሆን ሌት በጨለማም እጅግ ዘግይቶ ቤት ይገባል።

አደጋ ላይ መሆኑን የሚያውቁ ወዳጆቹ ስጋት ተጠናወታቸው። "ምን ይሻላል?" ተባባሉ። በተለይ መዲና ግሮሰሪ ለረጅም ጊዜ በዓሉንና ጓደኞቹን በማስተናገዱ ወዳጅነት የፈጠረው መሐመድ በሁኔታው ግራ ተጋብቷል። ብቻውን መብሰክሰኩ አላዋጣ ቢለው አንድ የበዓሉ የቅርብ ወዳጅ ጋ ቀርቦ አቤቱታ አቀረበ።

"ምንድነው?" አሉ አቤቱታው የቀረበላቸው አስፋው ዳምጤ።

"የበዓሉ ነገር ነው" አለ መሐመድ።

"ምን ሆነ?"

"ምን ይሆናል፤ ብቻ እዚህ እስከ እኩለ ሌሊት ያመሻል፤ ምናለ በጊዜ ወደ ቤቱ ቢሄድ? ያለበትን ሁኔታ እያወቀው ..."

ጋሽ አስፋው በዓሉን በመሐመድ አንደበት ወቀሱት።

በዓሉ ወቀሳውን ሰምቶ ዝም አለ፤ ተከዘ።

"ተናገራ! ለምን ታመሻለህ?"

"ነገሩ ወዲህ ነው" አለ በዓሉ። ከዚህ በኋላ የተናገረውን ከእንዳለጌታ መፅሐፍ ላይ ልተርከው፡- "አሳዳጆቼ ቤተሰቦቼ ፊት፤ ልጆቼ ፊት፣ ደሜን እንዲያፈሱት አልፈልግም። .... ልጆቼ ፊት እርምጃ የተወሰደብኝ እለት ነው መልሰው መሳልሰው እንደገደሉኝ የሚሰማኝ ... የትም ልሙት ... የሞቴን ፅዋ ግን ልጆቼ ፊት አልጨልጣትም። የትም ልሙት፣ እነሱ (ልጆቼ) ፊት እንዳይገድሉኝ ብዬ ነው እዚህ ዝግጁ ሆኜ የምጠብቃቸው ..." (ገፅ 425)

እንደ ውስጥ ደዌ ጤና የሚነሳ "ታሪክ" ነው። በዓሉ "ይቺ ፅዋ ከእኔ ትለፍ" ማለት እንዳልቻለ ገብቶታል። "መስቀሉ" ከፊቱ እንደተዘጋጀችም ተረድቶታል። በተስፋ መቁረጥ የጠየቀው ትንሽ ነገር ሞቱ በልጆቹ ፊት እንዳይሆን ነው። ግን ያ ምኞቱ ባይሳካ፣ ወይም እንዲሳካ በማምሸትና ማምሻውን ቦታ ባይቀያይር ኖሮ፣ ልጆቹ አሁን ባሉበት ሁኔታና ጤና ባልተገኙ ነበር። በዓሉ መጥፋት እየቻለ ያልሞከረው ለልጆቹና ለቤተሰቡ ሥጋት ስለገባው ሳይሆን አይቀርም። ልጓማችን ምንድነው? ማበቻችን ያለው የት ነው? እንደምን ሰው ሞቱ ቀርባ ሳለ አይሸሻትም? ስቃዩን አያመልጣትም? .... ይሄኔ ነው ፈጣሪን "ካልነገርከኝ አለቅህም" ማለት።

እንደ በዓሉ ግርማ በልጆቹ የታበተች አንድ የገጠር እናት ጭቆናና ስቃይ ቢበዛበት እንዲህ ስትል ገጠመች አሉ፡-

> "ኧረ ልጅ ማሰሪያው፣ ኧረ ልጅ ገመዱ፣
> ጎጆማ ምን ይላል ዘግተውት ቢሄዱ፤"

ልጅ ማሰሪያ ነው፤ ልጅ ገመድ ነው፤ ሌላው ሌላው ትርፍ ነው። "ጎጆ" (ትዳር) እንኳን ጣጥለውት ለመሄድ የሚያዳግት ተፈጥሯዊ ማሰሪያነት የለውም። ልጅን፣ ትውልድን በተመለከተ ተፈጥሮ አምባገነን ናት። ህጓ የማይታለፍ፣ ቅጣቷ የማይዛነፍ ነው፤ ግን ስውር ህግ፣ ድብቅ ቅጣት ...

... ፈረንሳዊው Victor Hugo በ1837 ዓ.ም አንድ የፃፈው ግጥም አለው። "my thoughts" ይለዋል። የልጅ መታሰሪያውን፣ የልጅ ገመዱን... እንቆንጥር፡-

My thoughts?
Far from the roof
Sheltering you, my thoughts
Are of you my children, and the hopes
That lie in you, my summer days
....
ሀሳቤ?
ከኩዳን ቆርቆሮው ከሰቀላው በላይ
እንዲያ ወደ ሰማይ
ከችግር፣ ችጋር ጠል
እናንተን ሲጠልል
እናንተን ፣ ልጆቼን፣ እና ተስፋዎቼን
ፀደይ ብራ ቀኔን ፀናሽ ወላጆቼን።

ሁጎ እና በዓሉ የታበቱበት "ዘለበት" አንድ ነው። እወዲያ ሥጋት አለ፤ ሐሳብ ተዳብሎታል። እወዲህ በልጆች ተስፋ ማድረግና ሐሴት ማግኘት ጣምራ ሆነው ቆመዋል። የሁጎ ባለ ስድስት አንጓ ግጥም መላልሶ የሚደቀድቀው እነዚህን ጥንድ መንቶ ያልተረጋገጡ ማበቻ ግዶች ነው። ሁጎ ልጆቹ ሲስቁ ይስጋል፤ ሲያለቅሱ ይመናተላል፤ መጨነቅ መጠበብ የአባትነት ዕጣው ይሆናል። እነዚህ ተጠራቅመው የበዓሉን ግድ ይሆናሉ። ሰውነትን ወደ ልጆች ከለላነት መቀየር።

የልጅ ፍቅር አቅል ነስቷቸው "ከለላነታቸው" ቅጥ የሚያጣ አባቶችም አሉ። ሁሉን ለልጆቻቸው የሚደነግጉ፣ ከልምዳቸው ተነስተው የልጁን ህይወት በድምዳሜ የሚያሳርጉ አባቶችም አሉ። አሜሪካዊው ደራሲ ኤርነስት ሔሚንግዌይ ለዚህ ምሳሌነት ቢጠቀስ ግብሩ የተሟላ ይሆናል። ሔሚንግዌይ በ1931 ዓ.ም ጀርመን በርሊን ውስጥ ሆኖ ያየውን ስለጠላ፣ ለአንድ ልጁ እንዲህ ሲል ፃፈ፡-

Never trust a white man
Never kill Jew
Never sign a contract,

Never rent a pew.
Don't enlist in armies;
Nor marry many wives;
Never write for magazines;
Never scratch your hives.

ሔሚንግዌይን ልጅ እንደ ዛር ተጠናውቶ አስጓራው እንጂ እሱስ እንዲህ በብዕር የሚባትል አልነበረም። የልጁ ነጮችን አለማመን፣ ፅዮናውያንን አለመግደል፣ መቀመጫውን አለማከራየት፣ ብዙ ሴት አለማግባት፣ ለመጽሔት አለመፃፍ የመሳሰሉት አሳሰቦት በብዕር ጕራዴ የሚያስፎክረው ኖሯል። ለዚህ የእኛ አባቶች ምሳሌ አያጡለትም። "ልጅ ያለ ልጅ አከለ" የሚል። አንዳንድ አባት ደግሞ አለ፤ ልጅ እና የዓላማ አጋር የተምታታበት። Groucho marx ለዚህ ልከኛ አብራሔ ነው። ለልጁ ለአርተር የፃፉቸው ደብዳቤዎች ሁሉ ኮሚኒስታዊ ኹምጣጣነት የተሞሉ ነበሩ። እንደውም ወደ መጨረሻ ሰሞን ልጁን "ጓድ አርተር" እያለ መጥራት ጀምሮ ነበር አሉ። የተፈጥሮ ማበቻው እንዲህ ላያስርቅ የሚያስጉዝ መሆኑ አይደንቅም።

የአባት ማሰሪያው፣ የአባት ገመዱ ልጁን "የእኔ" ብሎ ማሰቡ ነው። አንዳንድ ምሁራን ይሄ ልጁን "የእኔ" ብሎ ማሰብ የተፈጥሮ ግዳጅ ሳይሆን የማህበራዊ ኑሮ ማሳለጫ ዘዴ የጫነበት ግዱ ነው ይላሉ። ለምሳሌ ዶክተር ማርጋሬት ሚድ እንዲህ ያለ አቋም አላት፡-

"አባትነት ከተፈጥሮ የተቸረ ሳይሆን አብሮ ለመኖር ስለሚበጅ በሴቶች የተፈጠረ ዘዴ ነው" ትላለች። ጥንታዊው ወንድ ዘላን ነበር አሉ። በጊዜ ሂደት ግን በእናቶች ሥልጠና ይሰጠው ጀመር። አንድ ወንድ ልጅ ለማኅበራዊ ግልጋሎት ዕድሜው ሲደርስ ሴቶችንና ልጆቻቸውን የመመገብ ግዴታ እንዲገባ የሚያደርግ ይሄ ግዴታ በብዙ ወንዶች ኩብለላ የተነሳ ሊሳካ ባለመቻሉ ሌላ ዘዴ አስፈለገ። በመሆኑም ወንዶች "የእኔ" የሚሉት ሴት እና ልጆችን መመደብ። "ትዳር" ልንለው እንችላለን። በዚህ ዘዴ ወንድ "አባት" መባል ጀመረ፤ ከእናቶች ጋርም "እሹሩሩን" ዘፈነ።

አባትነት የተፈጥሮ ሆነ የልምድ (by nature of nurture) ውጤት የልጅን ግፊት ሲቋቋሙ የሚታዩ ወንዶች በታሪክ ተከስተዋል። ለዚህ ምሳሌ የምናደርጋቸው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ በላይ ዘለቀ ናቸው። ጣሊያንን ላይ ታች እያሉ ቢያንገበግቡት ልጃቸውን ሻሼን ያዘ። "ልጅህን ልሰቅላት ነው፣ እጅህን ስጥ" አላቸው። የበላይ ምላሽ ከበዓሉ ይለያል። "ከሀገር ማን ይበልጣል? ልጄን ከሀገሬ አላስበልጥም" ጣሊያን እንደፎከረው አላደረገም። ቢያደርግስ እውነትም ከሀገር ማን ይበልጣል?

(ልብ በሉ!) "ሀገር" እንጂ "ሥልጣን" አላልኩም። ስለዚህ የበላይ ዘለቀን ከኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ታሪክ ጋር ማዛነቅ ተገቢነት የለውም ማለት ነው። ኰሎኔሉ ገና በአፍላ የሥልጣን ዘመናቸው አደረጉት የተባለው ከበዓሉ ግርማ ውሳኔ ጋር ፍፁም በተፃራሪ የሚቆም ነበር። ኮሎኔል መንግሥቱን ከፊታቸው ገለል እንዲሉላቸው ብቻ አዲስ አበባ የላኳቸው አለቆቻቸው ነገሮች እንዳሰቡት ሳይሆኑ መቅረታቸው ሃሳብ ላይ ጣላቸው አሉ። ስለዚህ ኮሎኔሉ ወደ እናት ክፍላቸው እንዲመለሱ ጠየቁ፤ አልሆነም። ደብዳቤ ፃፉ፣ መልስ አላገኙም፤ በመሆኑም እዚያው ሐረር የቀሩ የኮሎኔሉን ቤተሰቦች አግተው፣ ኮሎኔሉ ወደ ሐረር ካልተመለሱ እንደሚፈጁቸው ዛቱ። ኮሎኔሉ መወላወል አልታየባቸውም። ሌላው ቀርቶ የጨቅላዎቹን ልጆቻቸውን መጥፎ ዕጣ - ፈንታ መልሰው መላልሰው ለማሰብ ጊዜ አልሰጡም። ወዲያውኑ ምላሻቸውን አሳወቁ።

"ቀቅላችሁ ብሏቸው!"

አጥፊና ጠፊነት እዚች ጋ ድንበሯን ታኖራለች። "አጥፊው" የቆረጠውን ያህል "ጠፊው" ልቡ ቢደነድን ኖሮ ዛሬ በዓሉ ግርማ በህይወት ይኖር ነበር። ቤተሰቡቹ ግን እንጃ! እናስ? የተፈጥሮን ሆነ የማህበራዊ ኑሮ ድንጋጌን የተቀበለ፤ ልቡን ወለል አድርጎ የከፈተ፣ ርህራሄን ትልሙ ያደረገ የልበድንጋይ ጭዳ መሆኑ አይቆጭም? ከፈጣሪ ጋር አያሟግትም? ሳትነግረኝ አለቅህም አያሰኝም?

# ደራሲ ማደሪያ የለው ህዝብ ይዞ ይዞራል

አንድ የጥበብ ሰው ተቸግረዋል መባልን ሰማሁ። ከችግሩ ሁሉ የጠናባቸው ደግሞ ሰው ማጣት ነው አሉ። ማንን አገልግለው? አፍላ ጉልበታቸውን ለማን ሲጨልፉ ኖሩና በስተመጨረሻ ሰው ቸገራቸው? አስራ ስድስት ልቦለዶችን ፅፈው የለም? ታዲያ ያ ሁሉ መማስን ሰው ካላተረፈላቸው ምን? ሰው ያልጐበኘውን የደራሲ ልብ ምን ይሞላዋል? የአመሻሽ እድሜ መፅናኛውስ ምንድነው? በጉብዝናው ወራት ስለሰው ከተፈጥሮው፣ ስለሰው ከኑሮው፣ ስለሰው ከፈጣሪው አልተኳረፈምን? ምን እያየ ደስ ብሎት ይሙት? ምን ተስፋ አድርጐ?...

...በነግ በኔ "ዋዬ!" አልኩ። የቀኝ-ጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ የብቸኝነት እንጉርጉሮ ልቤን ጐበኘው።

"ዐይኔን ሰው አማረው፣ ዐይኔን ሰው አማረው፤

ወየው! የሰው ያለህ የሰው።"

የቀኝ-ጌታ ዮፍታሔ ‹የሰው ያለህ የሰው" የሚለው በግሪኩ ፈላስፋ በዲዮጋን መንፈስ በተንጣለለ የሰው ባህር ተከብቦ ነው። የቅብጠት አይደለም። ሀቀኛና የአቋም ሰው ፍለጋ ይቺን ግጥሙን ፋኖስ አድርጐ በጠራራ ፀሐይ ወደ ገበያ ወጣ። ዘመኑ እንደአሁኑ ዘመን መጥፎ ነበርና ዮፍታሔ ሰው አጣ። "እናቴ" የሚላት አገሩ በጠላት እጅ ከመውደቋ በላይ በወለደቻቸው "አውሬዎች" ስትነቸፍ ተመለከተ። እና በሰው መሐል ሰው አጥቶ ግጥሙን "ዋዬ!" እያለ እንዲህ አስኬደው።

> "በቀበሮ አዋጅ አገሩን ወራሪ — ዋዬ!
>
> በለሰለስ እርሻ አሜኬላ ዘሪ — ዋዬ!

እጅግ ተጠንቅቆ አባቱን አፍቃሪ — ዋዬ!

አባቱን አፍቅሮ እናት አቃጣሪ — ዋዬ!

እናቱን አቃጥሮ ̣አባት አሳሳሪ — ዋዬ!

አባቱን አሳስሮ በእናቱ መካሪ — ዋዬ!

በእናቱ ላይ መክሮ አዋጅ አስነጋሪ — ዋዬ!"

75ኛ አመቱን ያከበረውን ይሄን አዛውንት ግጥም ለዚህ አፍላ ዘመን እስኪ እናልብሰው፤ ልኩ ሳይሆን ይቀራል? ዘመን ሰው ካጣ ገመና መሸፈኛው ምን ሊሆን ነው? "አገሩን ወራሪ" ና "አሜኬላ ዘሪ" መች ህፍረት መከለያ እራፊ ይሆንና?...

....ከገንዘብ እጥረትና ከጤና መጓደል በላይ ሰው መቸገራቸውን የሰማሁት ደራሲ ይልማ ኃብተየስ ናቸው። በሥራዎቻቸው ለአስርት አመታት አውቃቸዋለሁ። በአካል ለአፍታ ያየኋቸው ግን ባለፈው ዓመት ነበር። የደራሲ ጥቅሙ ይሄ ነው። መዳረሻውን ራሱ ደራሲውም አያውቀውም። በጊዜና በቦታ ያልተቀነበበ ውሎው የትኛውን ታዛ ተጠልሎ ከየትኛው እንግዳ ተቀባይ ጋር እንዳወጋ ግንዛቤው የለውም። እና ከእኔም ጋር በመፅሐፍቶቻቸው ተጨዋውተን ነበር። በአካል ሳገኛቸው እንደማገኛውም ደራሲ እሳቸውም ላይ መጽሐፍቶቻቸው አጥልተውባቸው ነበር። ከባድ የአይን መነፅራቸው ድሎት የማይነበብበት ፊታቸውን ውጦታል። ምርኩዝ ይዘዋል። ጋሽ አፈወርቅ በቀለ ወስዶ ሲያስተዋውቀኝ....

"በሥራዎቹ አውቀዋለሁ።" አሉ።

አንዳንድ ሰው ከአፉ በሚወጣ የመጀመሪያ ቃል ማንነቱ በግልፅ ይታወቃል። ጭምት፣ ግልፅና የማይብለጠለጡ እንደሆኑ ገባኝ። በእሳቸው እድሜና ሥራ ለእኔ ሙከራ እውቅና ለመስጠት አልተቸገሩም። ይሄ ለዚያ ዘመን ትውልዶች የማይወጡት አቀበት ሆኖ መቆየቱን የምናውቅ እናውቃለንና የጋሽ ይልማ ሁለት ቃል ብዙ ትርጓሜና ፍንጭ አላት። የተመኘሁትን ያህል ሳንጨዋወት በዚሁ ተለያየን። እነሆ ከአመት በኋላ እሳቸውን የሚመለከተው አሳዛኝ ወሬ እኔ ዘንድ ደረሰ። ስለሀገር እንዳልማሰኑ፣ ስለማህበረሰብ እንዳልባተሉ፣ ስለሰው ልጅ እንዳልባከኑ.... የትም ተጣሉ? አስራ ስድስት መጽሐፍ ስንት ነው? ስንት ሌሊት?

ስንት መአልት? ስንት በስንት ተተምኖ የሚመገቡት ማዕድ ነሳናቸው? የሚጠለሉበት ጎጆ ነፈግናቸው?... ከዘመናችን ጋር የሚያኳርፈን እንዲህ ያለው የዘመነኞቻችን ብያኔ ነው። "አገሩን ወራሪ" እና "አሜኬላ ዘሪ" በእንዴት ያለ ምድራዊ ገነት እንዲኖር እንደሚፈቀድ እያየን ነው።

ለማውቃቸው ደራሲዎች ሁሉ ደወልኩ። ያልደነገጠ የለም። ቢያንስ ሰው ያማረው አይናቸው "የሰው ያለህ ሰው" ብሎ እንዳይቀር እናደርጋለን ብለን ተቀጣጠርን። ወደ ቀጠሮ ስፍራ ሳመራ መጽሐፍቶቻቸውን በአይነ ህሊናዬ እየመላለስኩ በመመልከት ነበር። "ያልተከፈለ ዕዳ"፣ "የአበቅ የለሽ ኑዛዜ"፣ "ሦስተኛው ሰው"፣ "ሌላው እጅ"፣ "ከቀብር መልስ"...

ቀጠሯችን "ጣይቱ ሆቴል" ነበርና ወደፒያሳ አመራሁ። ታክሲው "አይኔን ሰው አማረኝ" በሚሉ ፍርስራሽ መንደሮች መካከል ይሽሎከሎካል። መንደርተኞቻቸው እነዚህን መንደሮች እንደሞተ-አህያ የተሸከሙትን አራግፈው ብቻ ጥለዋቸው ሄደዋል። እኔ እንኳ ተወልጄ ያደኩባትን መንደር መለስ ብዬ አላየሁዋትም። አድባሬ፣ ቆሌዬ፣ አዋዬ... እዚህ ሰፍረው አልነበረምን? ታዲያ? የተቋጠረ እትብቴን ምን በጠሰው? እራሴን ጠየቅሁ። "አይኗን ሰው ያማረው መንደሬን ስለምን ሰው ነፈግኋት? በቀን ሁለቴ እንቶሎቶስ አልነበር?... ግልፅ ነው፣ መንደር ሰው ነው። ሰው የሌለበት መንደር ከተቀረው ባደማ ጋር ይቀላቀላል። ይሄን ይሆን በድሉ ዋቅጅራ "ሀገር ማለት የኔ ልጅ" ያለው?

"....

ዥረቱም ግድ የለውም፣ ቦይ ለማሰለት ይፈሳል

ተራራውም ደንቆሮ ነው፣ ለቦረቦረው ይበሳል።

መሬቱም አይደለም የኔ ልጅ አድርተኛው ነው ሀገርሽ፣

ስትቸገሪ ታድጌ፣ ስትታመሚ አስታሞ፣ ስትሞቺ አፈር የሚያለብስሽ

በእጅሽ ያለ ብሩህ ፅጌ፣ ሰው ነው ልጄ ሀገርሽ።

ወገን ነው ልጄ ሀገርሽ።

...."

ስቸገር የታደጉኝ የዚህ መንደር ሰዎች ወዴት አሉ? ስታመም ያስታመሙኝ፣ ስሞት የሚቀብሩኝ ከወዴት አሉ? በሙጃ፣ በሰንሰልና በዘልዛላ ቅጠል ማን ተካቸው?... ይሄኔ የዚች መንደር ሰው ሁሉ በባህር እንደተከበበ ደረቅ መሬት ሆኗል። ከሰው መገናኛ "ታንኳ" አጥቶ ደረቅ ህይወት በባይተዋርነት ያጠራሙታል ለራሴ "ዋዬ!" ማለት አሰኘኝ። በግድ ከራሴ ውስጥ ወጣሁ።

ጣይቱ ሆቴል ስደርስ የጠበቅኋቸውን ሁሉ አገኘሁ። ደስ አለኝ። አይን የተጠማ አይን ጥማቱን ይከላል። ኢትዮጵያ ከጥንት እስካሁን ከሰውና ከወገን ውጭ ምን ሀብት አላት? ወታደሩ የሚሞተው፣ ገበሬው የሚያርሰው፣ ናዝራዊው የሚመንነው.... ከሰው ውጭ የሌላት አገሩን በማሰብ አይደል? በተረታችን ይሄው አለ። "ለሰው ከበሬታው ሰው፤ ለወጥ ማጣፈጫው ጨው" እንላለን። ከሰው የተነጠለ ሰው ህይወቱ ጨው እንዳልገባበት ወጥ ልፋትን ያላገናዘበ ውጤት ያለው ነው። ለሰው ለፍቶ ከሰው የተነጠለስ?

ያመራነው ወደ አስኮ ነበር። ደራሲ ይልማ ኃብተየስ ኑሮ እየከበደ፣ መኖሪያ ቤት እየተወደደ ሲያስቸግራቸው መሀል ከተማውን እየለቀቁ አፈግፍገው ነው አስኮ መኖር የጀመሩት። ሠፈሩ በተለምዶ "ብርጭቆ ማሪያም" ይሰኛል። ሚኪሊላንድ ኮንዶሚኒየም ሳይት መዳረሻ ላይ ወደቀኝ ይታጠፋል። ቤተ-ክርስቲያኒቱ ከተለምዶ ስሟ በተጨማሪ ትክክለኛ መጠሪያዋ ግንብ አጥሯ ላይ ቀስተ ደመና ቅርፅ ባለው ብረት ላይ ተፅፏል። "በፍኖተ ሰላም የቅድስት ድንግል ማሪያም ቤተክርስቲያን" የደራሲ ይልማ ቤት ከቤተ-ክርስቲያኒቱ መቶ እርምጃም ሳይርቅ ይገኛል። ግቢው የገዳም ግርማ ያለው ነው። መደዳውን ከተቸመቸሙት "ሰርቪስ" ቤቶች አንዱን ከግለሰብ ተከራይተው ይኖራሉ።

ባለቤታቸው እንግዳ ለመቀበል በመሽቆጥቆጥ ላይ ናቸው። ተከታትለን ገባን። ፊት ለፊት ድንክ የመጽሐፍ መደርደሪያ ትታያለች። ግዙፍ መጽሐፍ መደርደሪያ ለካ በህይወት የመረጋጋት ምልክት ኖሯል! ግለሰብ ቤት እየተኖረ በአጭር መታጠቅና በተጠንቀቅ መጠበቅ ግድ ነው። ‹ውጡ!› ሲሉ ውልቅ! ለማለት።

ጋሽ ይልማ ፀአዳ ጋቢ ደርበው አልጋ ላይ ጋደም ብለዋል። እንደደካከማቸው ያስታውቃል። ከጭንቅላታቸው ብቻ ቀና ለማለት እየሞከሩ እንግዶቻቸውን ተቀበሉ። የአእምሯቸው ንቃት ግን አስደማሚ ነው። ከአመት በፊት የተከናወነ አፍታ ትውውቃችንን ተመስርተው በስሜ ጠሩኝ። ከእኔ ቀጥላ የጨበጠቻቸው

እቱ ገረመው ነበረች። ከአራት አመት በፊት ቃለ-ምልልስ አድርጋቸዋለች። እሷንም ያለማንገራገር በስሟ ጠሯት። በየአገኘንበት ተቀምጠን ስለጤናቸው ጠያየቅን።

እንደበታቸውን ቀድሞ አይናቸው ምላሽ ሰጠን። አለቀሱ።

ውስጤ ተናወጠ። "ያልተከፈለ ዕዳ" ያለብን እኛ እንጅ እርሳቸው ስለምን ያለቅሳሉ? ወደ ጆሮ ግንዳቸው የሚወርድ እንባቸውን እየጠራረጉ እንዲህ አሉን:-

"ዛሬ ዘውድ ደፋሁ። ንጉስ ሆንኩ። ከእንግዲህ ብሞትም አይቆጨኝ።"

ሰው ለሰው ይሄን ያህል ነው። ያውም ለጥበብ ሰው ሌላ ምን አላማ? ሌላ ምን ህይወት? ሌላ ምን ዕድቅ አለው? ይሄን በማየት ሳይሆን ይቀራል የደቹ ሰዓሊ ቪንሰንት ቫን ጎህ "የሰውን ልጅ ከማፍቀር በላይ ጥበብ የለም።" ያለው። ህዝብ ለማፍቀር ጥበብ ደራሲ ማደሪያ ባይኖረውም ሰው ይዞ ይዞራል።

## ዘመኝና ገብረክርስቶሳዊ ዕጣ-ፈንታ

ካለንበት ቀናት ወደኋላ... ቀናት ወደፊት። ሁለት ዕለታት አሉ። ሁለት አንጋፋ ባለቅኔዎች የሚታወሱበት። ቀናት ወደኋላ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን አለ። ቀናት ወደፊት ባለቅኔና ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ አለ። ፀጋዬ የካቲት 18 ቀን በስደት እጅ ተይዞ አሜሪካ ውስጥ ሞተ፤ ገብረክርስቶስ የስደት ቁራኛ አማቅቆት መጋቢት 21 ቀን እዚያው አሜሪካ አረፈ። ፀጋዬ ስምንት አመት ሞላው፤ ገብረክርስቶስ 32 ጥቢ አሳለፈ። ፀጋዬ ለአገሩ አፈር በቃ፣ ገብረክርስቶስ ግን...

...እግዚኦ! የሰላሳ ሁለት ዓመታት ዝምታና ቸልታችን እንደ ፉርጎ ተቀጣጥለው በፊታችን ነጎዱ። መጋቢት 21 ቀን 1973 ዓ.ም. ገብረክርስቶስ ህይወቱ ያለፈችበት ዕለት ነበረች። በአብዮቱ ግፊት ሳይወድ የተሰደደበት ባዕድ ሀገር፣ ፍቅሩን በግጥም ሲያስታምም ለሶስት ዓመታት ያህል ቆይቶ ነው የፀጉረ-ልውጥ ሞት የሞተው። ይቆጫል!!

“ሀገሬ ውበት ነው
ለምለምና ነፋስ የሚጫወትበት
ፀሐይ የሞላበት፣ ቀለም የሞላበት
ሀገሬ ቆላ ነው፣ ደጋ ወይናደጋ
እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ ሲነጋ
....
እዚያ ዘመድ አለ
ሁሉም የእናት ልጅ ነው
ሁሉም ያባት ልጅ ነው
ጠላትም አንዳንዴ ይመጣል መቃብር
ባላጋራም ቸር ነው “ያገር ልጅ” ሲቸገር
...
ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ
እዚያው ነው አፈሩ የእማማ-ያባባ”

ገብረክርስቶስ "ሀገሬ" ሲል በስየማት ግጥሙ ውስጥ ምኞቱን እንዲህ አስፍሮ ነበር። የሚያሳዝነው ግን ይህ ሁሉ ምኞት፣ ይህ ሁሉ የወገንና የሀገር ፍቅር ነፋስ የገፋው ጠል ሆኖ ነው የቀረው። የሰላሳ አመታት ዝምታና ቸልታችን ተስፋውን አገንትሮበት እንደቀነጨረ ጥሬ ቢዘራ የማይበቅል እስከመሆን የደረሰ ይመስላል። እንደምኞቱ ለአገሩ መሬት ሳይበቃ አሜሪካ አክላሆማ ውስጥ "በመሸ እንግዳ" ተቀብሯል። አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች እንዲህ ይጨክናሉ፤ ብዙ አትጠይቅም-እሱኑ አታገኝም።

ገጣሚ ሰሎሞን ዴሬሳ ስለገብረክርስቶስ እንዲህ ብሎ ነበር፤

"(በአብዮቱ ዘመን) ለኢትዮጵያውያን ፀሐፊዎችና ሰዓሊዎች ችግር ይደርስባቸዋል ብዬ አገምት ነበር። ገብረክርስቶስ ደረሰበት፤ መጨረሻው ላይ ስለአወጣጡ የሰማሁት ነገር አለ። እሱን አላጣራሁምና አልደግመውም። ችግር ደርሶበት ወጥቶ ታም በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አንድም ኢትዮጵያዊ በሌለበት ማንም በማያውቀው ሀገር አክላሆማ በተባለ ቦታ ሞተ። አሜሪካ መሆኑንም አላውቅም ነበር። እኔ ያለሁበት ሚኒሶታ እሱ ያለው አክላሆማ ነበር። ብሰማና ባውቅ ኖሮ ቢያንስ ቢያንስ ሲሞት የሚያውቀውን ፊት እያየ ይሞት ነበር። አሁን ሳስታውሰው በጣም ሆዴን ይበላኛል።"

ከአሟሟቱ በላይ ሆድ የሚበላው ወጥቶ የመቅረቱ ጉዳይ ነው። የገብረክርስቶስ መንፈስ ከትውልድ አገሩ መሬት የማይነጠል"የብርቅዬ ተክል" ባህሪይ አለው። በለመለመበት ብቻ ለመድረቅ፣ ባፈራበት ብቻ ለመርገፍ የተፈጠረ...

"መቅደስ ነው አገሬ

አድባር ነው አገሬ

አገሬ አርማ ነው የነፃነት ዋንጫ

በቀይ የተጌጠ ባረንጓዴ ቢጫ

አገሬ ታቦት ነው መቅደስ የሃይማኖት

ዘመን የፈተነው በጠበል በፀሎት

ለምለም ነው ሀገሬ

ውብት ነው ሀገሬ።"

ገብረክርስቶስ ሀገሩ ፍቅሩ ነበረች። የህይወቱ ትርጓሜ። በግጥሞቹ ውስጥ ስለፍቅር፣ ስለናፍቆት፣ ስለቸርነት፣ ስለጠላትነት… ሲያጫውተን ሀገሩ የነገሮቹ ማንፀሪያ ሆና ነው የምትቀርበው። ለገብረክርስቶስ ኢትዮጵያ ቁዘሜው ነበረች። አዝሎ እሹሩሩ የሚላት… ታዲያ ምን ይሆናል? ለህይወቱ ቀርቶ ለአስከሬኑ ማረፊያነት ተነፍጋው መንፈሱ ውጭ-ውጪውን ሲል ሰላሳ ሁለት አመታት ደፈነ። ጥቂት ነገር ጠየቀ-እሱኑ ነፈግነው። አንዳንድ ጊዜ እኛና ሁኔታ እንዲህ እንጨክናለን።

ፀጋዬ ገብረመድህንም ያው ነው። የሀገሩ ነገር አይሆንለትም ነበር። ሊሞት አስራ አምስት ቀን ሲቀረው እንኳን ሀገሩን አደራ አላለም። አዝኗት ነው የሞተው። የካቲት 18 ቀን ሊሞት፣ የካቲት 1 ቀን የወጣ "ጦቢያ" መጽሔት ላይ "እኔንም እንደ አባቶቹ ያልቋጨሁት ነገር ይቆጨኛል" ብሎ ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ አንደበት-እሱው ባስታጠቃቸው:-

"ያለፈው ጥረታችንን ሳስታውሰው

ትዝ ሲለኝ፣

ከሰራነው ነገር ይልቅ-

ያልሰራነው ነው የሚቆጨኝ!"

ፀጋዬ እንደገብረክርስቶስ ልስልስ አይደለም። ሀገር ነክ ግጥሙ ለበቅ ነው። ውዴታው ህማም ነው። ሀገሩን እንደ እሾህ አክሊል የሚያጌጥባት እየደማባት ነው። እየተናቸፈባት። ያም ሆኖ አልታከተም፤ በቃኝ! አላለም። "ማነህ ባለሳምንት"ን አልለፈፈም። በህመም የተሰደደበት ሆኖ "በበቃኝ የተሰደዱት" ላይ ይጮህ ነበር። "ይድረስ ለኛ" በሚል ግጥሙ:-

"ይድረስ ወገን ከኛው ለኛ፣

አበቅቴ ውሉን አልሳተም

ዕዋህን ተቀበለኛ

ይድረስ ለክቡር ወገኔ ምነው ጥላችን ቀለለ?

እማማ ኢትዮጵያችን ለምን እያደር እየዋለ

ማህፀኗ ከጐዶሎ በቀር-

ሙሉ ሰው አልወልድም አለ?

ስደተኝነት ግቡ፣ ለሆድ ባርነት ሩቅ ማደር

እንደ ወዶ ገባ ውሻ በባዕድ እብሪት መደፈር

የቁም ሞት ኑሮ ነው ስሙ፣

አለሁ ለማለት መገደር።"

ፀጋዬ ይህን ባለ አመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ በጤና ዕክል ምክንያት ለስደት ተዳረገ። "የፈራው ደረሰው፣ የጠላው ወረሰው"፤ ህመሙ እንኳን ከአህጉር አህጉር ቀርቶ ከመንደር መንደር የሚያላውስ አልነበረም። ኒውዮርክ ከተማ ብሮንክስ ውስጥ ቅዱስ ባርናባስ ሆስፒታል ዳያሌሲስ (የኩላሊት ህክምና) ማዕከል በሳምንት ሶስት ቀን እየተመላለሰ ይታከም ነበር። ይሁንና ከመንፈስ ጉድለቱ በላይ የጤና እክሉ የሚያሳስበው አይመስልም። "ጦቢያ" መጽሔት ላይ ሲጠየቅ እንዲህ ነበር የመለሰው፡-

"የኢትዮጵያ አምላክ ይመስገን፣ ከአገር ናፍቆት በስተቀር ጤንነቴን ደህና ነኝ።"

ስለፀጋዬ የሚቆጨን ከሁኔታዎች መጥመም ጋር ተያይዞ ነው። በህማም እግር ብረት ታስሮ ለሚያነውረው ስደት ከሚዳረግ ምናለ ኢትዮጵያ ዕቅፍ ውስጥ እንደተገኘ እቅፏ ውስጥ በጠፋ የሚል። ቁጭትና ወቀሳ ያለብን ከወደ ገብረክርስቶስ ገደማ ነው። "ብሞት እሄዳለሁ..." ሲል ሙት እግር እንደሌለው አጥቶት ይሆን? አይደለም! እኛ ላይ የጣለውን ተስፋ ነው የመተማመኛ ፍካሬ ያደረገው።

"እዚያ አለ ነፃነት

በሀገር መመካት

በተወዳጅነት

በባለቤትነት

እዚያ አለ ነፃነት።"

ሲል መግጠሙ ለአፀደ-ሥጋው ብቻ አልነበረም፤ ለመንፈሱም እንጂ...።

እንደ ብርቅዬ ተክል በለመለመበት መሬት ላይ ብቻ ለመድረቅ፣ ባፈራበት አገር ላይ ብቻ ለመርገፍ የተፈጠረው ገብረክርስቶስ ብቻ አይደለም። ሁሉም አንጡራ ኢትዮጵያዊ እንዲያ ነው። በቅርቡ ከወደ ዳር አገር የመጣ የረጅም ዘመን ስደተኛ እንዲህ ብሎ አጫውቶኛል። "ወድቄ መቅረቴ ነው ብሎ ማሰብ የህይወት ጥንጣን ነው፣ ባዶ ያስቀርሃል። የላይ ላይ ኑሮ እንጂ ሥር የሰደደ ደስታ አይኖርህም።"

የኢትዮጵያዊ ስደተኛ ሁሉ መትከንከን ይሄ ነው።

ብዙ ገብረክርስቶሶች ባዕድ አገር ወድቆ በመቅረት ፍርሃት ተቀፍድደው በአፀደ ስጋ አሉ። በሀገር ናፍቆትና በወገን እጦት ሳይሞቱ መንፈሳቸው ድንበር ድንበሩን የሚጠራሞት።

"ብሞት እሔዳለሁ ከመሬት ብገባ

እዚያው ነው አፈሩ የእማማ-ያባባ"

የእማማና የአባባቸውን አፈር በዚህ መንግስት የተነፈጉ። ይሄ መንግስት እንደሆን እንደትምክህተኛ ባል አስወጥቶ በር መዝጋትን ብቸኛ መፍትሄው አድርጎታል። እዚያ "ብሞት እሄዳለሁ..." ቢባልም፤ እዚህ "ብትሞቱም አትመጡም..." የሚል ገርጋሪ መንፈስ የተጠናወተው መንግስት አለ።

ማን ይሁን ማን፣ "ፀረ-ህዝብ" ይሁን "አሸባሪ" ለውጥ አያመጣም። ኢትዮጵያዊ-ኢትዮጵያዊ ነው። ከኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ጀምሮ። ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ፣ አብርሃም ያየህ፣ ነገደ ጎበዜ፣ አልማዝ መኮ፣ አሰፋ ጩቦና ሙሉጌታ ሉሌ... የብዙ ገብረክርስቶሶች ተስፋ ይሄው ነው። "ወድቆ የመቅረት" ፍርሃቱ እድሜያቸው የገፋው ብቻ አይደለም። የወጣቶቹም ጭምር እንጂ፤ አብይ ተክለማሪያም፣ ደረጀ ሀብተወልድ፣ ማስረሻ ማሞ፣ ግርማ ተሰፋው፣ መስፍን ነጋሽ፣ ታምራት ነገራ፣ በፍቃዱ ሞረዳ፣ አበበ ቶላ፣.... ገብረክርስቶሳዊ ተስፋ የጣለብን ገብረክርስቶሳዊ ዕዳ... ወይስ ሌላ አማራጭ አለ? ለማንኛውም እንደ ጋኔን ከሥጋ አልፎ በመንፈስ የሚቀጣውን እጅ ያላላልን! አሜን!!

# በሥነ-ፅሑፍ መንገድ ላይ (ከዳኛቸው ወርቁ እና ከአዳም ረታ ጋር)

ወቅቱ 1982 ዓ.ም ነው። ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር አንድ የሥነ-ፅሑፍና የቴአትር ስልጠና ለወጣቶች አዘጋጅቶ ነበር። እዚያ ስልጠና ላይ ገጣሚ ደበበ ሠይፉ ስለግጥም እንዲያብራራ ተጋብዞ መጥቷል። እንደሚመስለኝ ደበበ ያንን ሁሉ የሥነ-ፅሁፍ ሰልጣኝ አልጠበቀም። ገና እንደገባ ፊቱን አኮፋትሮ ተመለከተን።

"ይሄ ሁሉ ምንድነው?"

"የሥነ-ፅሁፍ ሰልጣኝ" የሚል መልስ አገኘ።

"ይሄ ሁሉ?" ባለማመን።

"አዎ"

ወደተዘጋጀለት መድረክ ወጥቶ ድጋሚ ተመለከተን። ሁለት መቶ እንሆናለን። እንዲህ አለን፡-

"እኔ ከእናንተ የምጠብቀውን ልንገራችሁ? አሥር ጥሩ አንባቢ፣ አምስት ሃያሲ እና አንድ ደራሲ"

በወቅቱ እኔ የተቀመጥኩት መካከል ላይ ነበር። ወደፊትና ወደኋላ አየሁ። ብዙ አሳት የላሱ ወጣት ፀሐፊያን እንዳሉ አውቃለሁ። እኔን የደበበ ትንቢት ተቋዳሽ የሚያደርገኝ አንድም መነሻ አልነበረኝምና ያኔውኑ አዳራሹን ጥዬ መውጣት ተመኘሁ። ግን ድፍረት አጣሁ። የሚገርመው ከሃያ አምስት አመታት በኋላ የእነዚያን ሰልጣኞች ሁኔታ ሳጤን፣ ሁሉም ውሻ እንደገባበት የዝንጀሮ መንጋ በየአቅጣጫው ተበትኖ ቀርቷል። አንዳንዱን ጋዜጠኝነት፣ ሌሎቹን ኑሮ፣ የተቀሩትን ደግሞ የፍላጎት ለውጥ ከሥነ-ፅሁፍ አሰናከላቸው። ከሞላ ጎደል የደበበ ሠይፉ ትንቢት ሞላ። የሀያሲዎቹንና የጥሩ አንባቢዎቹን ባላውቅም የደራሲዎቹ መረጃ

ግን አለኝ። ያኔ ከነበሩት ስልጣኞች ደራሲነትን የገፋበት ድርቡ አደራ ብቻ ነው። (እኔን እናንተ ቁጠሩኝ)

ሌላኛው ሥነ-ፅሁፋዊ "ትንቢት" በዚያው ዘመን፣ በዚያው ሰው (በደበበ ሰይፉ) የተሰጠ ነው። "ብሌን" የደራሲያን ማህበር መፅሔት ላይ ሀያሲ አብደላ ዕዝራ አምስት የሥነ-ፅሁፍ ምሁራንን በአማርኛ ልቦለድ ዕድገት ላይ አወያይቶ ነበር። መነሻው ልቦለድ "ጦቢያ" ሲሆን መድረሻው ደግሞ "አደፍርስ" ነው። ደበበ ሠይፉ ትንቢት የተናገረው የዳኛቸው ወርቁ ሥራ በሆነው "አደፍርስ" ላይ ነበር። እንዲህ፡

-

"... እንደተባለውም ልቦለዱ (አደፍርስ) ከታተመ ሃያ ዓመት ሆኖታል። ዛሬ ቢታተም ብለን ብንጠይቅ በዕውነት ተቀባይነቱ ይጨምራል ባይ ነኝ። የዛሬ ሰላሣ አርባ አመት ደግሞ በጣም በጣም ይጨምራል" ("ብሌን" 1982፤ ገፅ 37)

ደበበ ይሄን ካለ ሃያ አምስት ዓመት ሞልቶታል። "ትንቢቱ" ሊፈፀም አምስት ቀሪ አመታት አሉ። ይሁንና "አደፍርስ" በዚህ ዘመን ከሙታን የመነሳት ያህል የአንባቢያንና የሀያሲያን ጥያቄ እየሆነ መምጣቱን ስንመለከት ደበበ ትንቢቱ ያዘለት ለማለት እንገደዳለን? "አደፍርስ" ከአርባ አምስት ዓመታት በኋላ በዚህ ዘመን ዳግም ለመታተም መብቃቱስ "ትንቢቱ" ቀድሞ ለመፈፀሙ እንደጠቋሚ ይታያል? ለመሆኑ እኛ የትውልዱ ተሳታፊዎች እንኳን ቀና ግምት የሌለን እዚህ ዘመን ላይ እንዴት ደበበ አሻጋግሮ ተስፋ ሊጥልበት ቻለ? ደበበ እዚህ ትውልድ ላይ ትንቢት የወለደው ተስፋ እንዲጥል ያደረገው ምክንያት አለው?

ደበበ እና ዘመኑ ተምኔታዊያን አልነበሩምና ጥሬ እምነት የወለደው "ትንቢት" አያሳድጉም። ደበበ እዚህ ትውልድ ላይ ተስፋ ለመጣሉ ያቀረበው ምክንያት የዲያሌክቲካዊ ሥነ-አመክንዮን (Dialectical logic) ጠገግ የያዘ ነበር። ደበበ እንዲህ ይላል፡-

"... (አደፍርስ) ተቀባይነት ቢያጣ በጊዜው በተደራሲ የኪነ ውበት ንቃተ ህሊና ማነስ ነው እኔ የሚመስለኝ። ተደራሲያን እንደሌላው አይነት ንቃተ ህሊና ሁሉ ኪነ ውበታዊ ንቃተ ህሊናቸው እያደገ ይሄድና ይህንንም መፅሀፍ የሚያጣጥሙበት ጊዜ ይመጣል። .... ምክንያቱም የህዝብ ንቃተ ህሊና ወደፊት ነውና የሚሄደው። በዚህም በኪነ ጥበብም ረገድ ንቃቱ ያድጋል። ለዚህ ነው ይህ ልቦለድ ትናንት ተነባቢነት ባይኖረው እንዲገርመን ያማያስፈልገው"

ደበበ "አደፍርስ"ን ያለዘመኑ ተፈጥሮ ትውልድ በዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ እስኪበስል በባይተዋርነት የሚጠብቅ ዘመናዊ ልቦለድ ነው እያለን ነው። እዚህ ላይ ሁለት ድምዳሜዎችን ለይተን መፈተሽ ግዳችን ይሆናል። እነሱም የአደፍርስ

ዘመናዊነት እና አሁን ያረፈበት ትውልድ ናቸው። አደፍርስ ዘመናዊ ልቦለድ ነው? በምን? ይሄስ ትውልድ "አደፍርስ" ሲጠብቀው የነበረው ልከኛ አንባቢ ነው? እንዴት?

... የ"አደፍርስ"ን ዘመናዊነት በተመለከተ ዋቢ የምናደርገው ቴዎድሮስ ገብሬን ነው። "አደፍርስ ዘመናዊው ልቦለድ" የሚል ጥናት አላቸው። እዚህ ጥናታቸው ላይ ዘመናዊ ልቦለድነትን ከቨርጂኒያ ውልፍ እና ከግሬት ዊንተርሰን መደምደሚያ አንፃር በመነሳት "አደፍርስ"ን ይዳኛሉ። ከጅማሬው የ"አደፍርስ"ን ዘመናዊነት በማወጅ ማሳያዎቹን ያስተነትናሉ።

"አደፍርስ ዘመናዊ ልብወለድ ነው ስንል፤ ያነሳቸውን ጉዳዮች፤ የተመሰረተባቸውን ጽንሰ ሐሳቦች፤ የተረከባቸውን ቴክኒኮች እና የተከየነበትን ዘይቤ አዲስነት ተመልክተን ነው። የአማርኛን የረጅም ልቦለድ አተራረክ ልማድ በእጅጉ የፈተነው አደፍርስ፤ ከነባሮቹ የሥነ ልሳናትና የሥነ ፅሑፍ ደንቦች ያፈነግጣል። በትልም አነዳደፉ ከተለመደው የአከያየን ሥርዓት አይገጥምም። በስርክ አይን ሲታዩ የተበጣጠሱ የሚመስሉ ሁነቶችና ገጠመኞች እየተፈራረቁና እየተጎራበቱ ይቀርብበታል። ይህ ልብወለድ ይሁነኝ ተብሎ በሚፈፀም አሻሚነት (deliberate Ambiguity) እና የአጨራረስ እንጥልጥልነት የተሞላ ነው።"

ቴዎድሮስ ገብሬ የ"አደፍርስ"ን ዘመናዊነት ለማስረገጥ ብዙ ማሳያዎችን ጠቅሰዋል። "አደፍርስ" በተወለደበት ዘመን መግባባት የተሳነውና ሌሎች ትውልዶችን ጥበቃ የተቀመጠው በወቅቱ አማርኛ ልቦለድ የማያውቀውን ዘመናዊነት ይዞ በመምጣቱ እንደሆነ ግልፅ ነው።

አሁን ወደ ሁለተኛው ጥያቄያችን እናምራ። ይሄ ትውልድ የ"አደርፍርስ" አቻ አንባቢ ነው? ኪነ - ውበታዊ ንቃተ ህሊናው የ "አደፍርስ" ተገዳዳሪ ያደርገዋል? "አደፍርስ"ን የሚሸከም "ጉልበት" አበጅቷል? ወይስ ሆሆታ ብቻ ነው? "አደፍርስ" ዳግም ለመታተሙ ጥያቄው የትውልዱ ነው? ወይስ የሚዲያዎች ጉልበታም ግፊት ጎርፍ ሆኖ ወሰደው? .... ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ብዙ ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙበት ጥናት መከናወን አለበት። እስከዚያው ደግሞ እጅ አጣምሮ መቀመጥ ተገቢነት የለውምና አንዳንድ ፍተሻዎችን እናከናውን።

"አደፍርስ" የዚህ ዘመን ልከኛ ልቦለድ መሆኑን አስረግጦ ለማሳየት የትውልዱን መንፈስ መቃኘት በቂ ይመስላል። ትውልዱ ጊዜና ቴክኖሎጂ በሰጠው ጠባይ በሉት ንቃተ ኅሊና ተመስርቶ የራሱን ተደናቂዎች ሰይሟል። ሌላውን ትተን በሥነ-ፅሁፍ ረገድ ከሄድን አዳም ረታ የዚህ ዘመን ተመራጭ ደራሲ ሆኗል ማለት ይቻላል። አዳም በዚህ ዘመን አንባቢ የተመረጠበትና ዳኛቸው በዚያ ዘመን አንባቢ ተገፍታሪ የሆነበት ምክንያቶች ከሞላ ጎደል አንድ ናቸው ማለት ይቻላል። ዳኛቸው

አዲስ አይነት የአፃፃፍ ስልት ይዞ መጥቶ ነባሩን፣ ተረታማውን ልቦለድ ተጋፋ። አዳምም ያደረገው ይሄንኑ ነው። እንደውም ዳኛቸው ለአዳም የበረሃ ላይ ሰባኪ (መጥምቁ ዮሐንስ) ነበር ማለት ይቻላል። ቴዎድሮስ ገብሬ ከዘመናዊ ልቦለድ አንፃር አደፍርስን የመጠነበት ገለፃ ለአዳም ሥራዎች በልክ የተሰፉ ናቸው። ዳኛቸው እና አዳም ሒስ ለመዋዋስ የሚያስችል አንድ አይነት የደራሲነት ቁመና አላቸው። ለምሳሌ ያህል በጀማሪነት ዳኛቸውን፣ በቀጣይነት አዳምን እያነሳን የጋራ የሆኑ አንዳንድ የአፃፃፍ ቴክኒኮችን እንመዝን።

ዳኛቸው "አደፍርስ" ውስጥ ትርክትና ጊዜን ለማጣጣም ተጨናቂ ሆኖ የቀረበበት ቦታ አለ። በልቦለድ አተራረክ ረገድ ድርጊት የተፈጸመበት ጊዜ ተፋትቶ ኢ-ተአማኒ በሆነ መንገድ መቅረቡ የተለመደ ጉዳይ ነው። ይሄን ችግር ቅድሚያ የተረዳው ዳኛቸው፤ የሦስት ማዕዘን ድርጊቶችን የጊዜ አንድነት ለማጣጣም አንድ የአተራረክ ዘዴ ተግባር ላይ አውሏል። "አደፍርስ" ውስጥ አባ ዮሐንስ ትምህርት ቤት ለማሰራት የመዋጮ ጥሪ ያደርጋሉ፤ በዚያው ላይ፣ ተደራቢ ሆኖ ፍሬዋ በላይ ፍቅረኛዋ የላከላትን ደብዳቤ ታነባለች። ከሌላ ማዕዘን ደግሞ አንድ አህያ ነጂ ይዘፍናል። እነዚህ ሦስት ድርጊቶች አንድ ጊዜ ላይ የተከሰቱ ንብርብሮች ናቸው። በተለምዶ ፍርቅርቅ ትረካ አንዱን ጨርሶ ወደ ሌላው መዛወር፣ የጊዜን ግንዛቤ ማፍለስ ይሆናል። ስለዚህ ዳኛቸው ድርጊቶቹን ድቅቅ አድርጎ በመከተፍ በጊዜ ጣባ ውስጥ አዋህዶ አቀረባቸው።

ቀጣዩ የጊዜና የአተራረክ ተጨናቂ አዳም ደግሞ "ግራጫ ቃጭሎች" ውስጥ ባለአራት ጎን ድርጊያዎች አላግባብ የጊዜ ትዳራቸውን እንዳይፈቱ አንድ ዘዴ ተጠቅሟል። ገፅ 46 ላይ የወሰን እናት፣ ጠጅ ሻጯ፣ ተራኪው እና የእንጀራ እናቱ በጊዜ ሽራፊ ላይ ሆነው ሳይገፋፉ ያደረጉትንና ያሉትን ከነቅፅበታዊ ስሜቱ ለማስተላለፍ ሰንጠረዥ ተጠቅሟል። በደቂቃ ረድፍ ውስጥ የተከናወኑ ንብርብር ድርጊቶችና የተደበላለቁ ንግግሮች መቱን እንዲቀመጡ አድርጓል። ሰፊው የሰከንድ አፍ ስንት ድርጊትና ድምፅ ሊያነባብር፣ ሊያዳብል ይችላል?

ይሄ የጊዜና የድርጊያ ፍቺ ችግር ዳኛቸው እና አዳም በአንድ አይነት አእምሯዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው የሚፅፉ ደራሲዎች እንደሆኑ የሚጠቁም ነው። ሌላም አለ። ቅርፅን የሀሳብ ደጋፊ አድርጎ ማቅረብ። ዳኛቸው "አደፍርስ" ውስጥ ከገፅ 312 እስከ 319 ድረስ ቅርፅን የሀሳብና የአእምሮ ሁኔታ መግለጫ አድርጎ አቅርቧል። ፂወኔ አደፍርስ ላይ የጣለችው ተስፋ ሲንኮታኮትባት ስሜቷ ይምታታል፣ አእምሮዋ ይናውዛል። ዳኛቸው ይሄን የተምታታ ስሜትና የናወዘ አእምሮ፣ ከቃላት ይልቅ በሦስት ጎን ቅርፅ ይገልጸዋል። ሦስት ጎኑ የእንቀፅ መከፈቻና መዝጊያ ሆኖ በተደጋጋሚ ይቀርባል። ቅርፅን በማየት ብቻ የፂወኔ ሀሳብ ከብዙ ወደ ትንሽ፣ ከትንሽ ወደ ብዙ እንደሚንጠራወዝ እንረዳለን።

አዳም ረታ ይሄንኑ ችግር መፍቻ ዘዴ፣ "ግራጫ ቃጭሎች" ላይ እና ሌሎቹም ሥራዎቹ ውስጥ ተጠቅሞበታል። ተራኪው መዝገቡ፤ በቃላት የማይገለፅ የከተማ ጉዞ ሲያደርግ አዳም ይሄን መናወዝ በቅርፅ ያቀርብልናል። አሁንም አዳም ረታና ዳኛቸው ወርቁ በአንድ አይነት አእምሯዊ ሁኔታ ውስጥ የሚፅፉ መሆኑን የሚጠቁም ስልት ነው።

ሌላ የመጨረሻ ማሳያ እናንሳ። ዳኛቸው ወርቁ "ከአደፍርስ" ሌላ በእንግሊዝኛ የፃፋት ልቦለድ አለችው። "The Thirteenth Sun" የተሰኘች። እዚች ልቦለድ ውስጥ አንድ አዲስ የአተራረክ ስልት ተጠቅሟል። ገፀባህሪዎቹ ፊታውራሪ ወልዱ (አደፍርስ ውስጥ አሉ) ጎይቶም እና ወይኒቱ ናቸው። ወደ ዝቋላ አቦ የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች ናቸው። የዚህ ልቦለድ ትረካ በፍርቅርቅ ነው። ዋናዎቹ ተራኪዎች ጎይቶምና ወይኒቱ ሲሆኑ አልፎ አልፎ አንዳንድ ስም የለሾች በወል ስም ተወከለው ለምሳሌ Peasant ተብለው ትረካ ይረከባሉ።

አዳም ረታ ይሄንን የፍርቅርቅ ትረካ ስልት ከመጀመሪያ ሥራው ከ"ማህሌት" አንስቶ እስከ መጨረሻው "መረቅ" ድረስ በተደጋጋሚ ተጠቅሞበታል። "ማህሌት" ውስጥ "ኤልዛቤል" የተሰኘው አጭር ልቦለድ በጳውሎስ፣ በመስፍንና በሠላማዊት ቅብብሎሽ ትረካ ይከናወናል። ዳኛቸው እና አዳም የሒስ አልባስ ለመዋዋስ የሚያስችል አንድ አይነት የደራሲነት ቁመና ቢኖራቸውም በየትውልዳቸው ተመሳሳይ አቀባበል አላገኙም። ዳኛቸው ተወግዟል። ባለቅኔው ከቡር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል፣ "አትሁን እፊት/ ያደርግሃል ወንፊት" ያሉት ይሄን ይሆን? ዳኛቸው በዚያ ዘመን የአዳም የበረሃ ላይ ሰባኪ እንደሆነው ሁሉ አዳምም በዚህ ዘመን የዳኛቸው መንገድ ጠራጊ ነብይ ነው። አዳምን የተቀበለና ከፍ ከፍ ያደረገ ትውልድ፣ ለዳኛቸው ልቡን መክፈትና ማስተናገድ ይሳነዋል?

# "ሌቱም አይነጋልኝ" እና "ዞርባ ዘ ግሪክ" ጎን ለጎን

.... ለህይወት የሞት እንቅርት ያንጠለጠለ፣ ለወጣትነት የአርጅና ባላጋራ የፈጠረ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ብቻ ይመስለኝ ነበር። የማሚት እሹሩሩ የአርጅና ፍርሃት፣ የአጋፋሪ እንደሻው የሞት ሽሽት፣ የከንፈ የጊዜ መባከን ቁጭት፣ የእትዬ አልታዬ ከወርቅ ጥርሳቸው አንስው ድብዝዝ ማለት ... ያ ... ሁሉ ትርከት ለአርጅና እና ሞት መሰዋት ... የስብሃት ብቻ የደራሲነት አምልኮት ይመስለኝ ነበር።

ወጣቶች በሩን ቆለፉ

ተዋደዱ ተቃቀፉ ተጣደፉ

አንቀላፉ

ኩኩሉ!

ሌሊቱን ለብሶ እርጅና ደረሰ ቀኝ እጁን ሰደደ

ውብ ጡት ዳሰሰ

ወጣቶች ጠወለጉ

ጠወለጉ ጠወለጉ

ሲነጋ ተያዩ

አለቀሱ አለቀሱ እሜት መሬት ያለ ቅሬት

ሳታላምጥ ዋጥ - ስልቅጥ!

ዋይ ዋይ

ዋይ ዋይ (ሌሊቱም አይነጋልኝ፤ ገፅ 23)

ለወጣቱ ስብሐት ህይወት አንድ ሴት መተኛት ናት። ዳግም መንቃት የሌለባት፤ የሚገፋፋው ሳይታወቅ የሚጣደፉባት። እንዴት? ህይወት ለአንድ ወጣት እንዲህ ናት? በልጅነት የወተት ጥርስ ወጣትነትን ታኝካለች? በአፍላነት የቀዘቀዘ ዕድሜን ጠርታ ጉያዋ ትከትታለች? ....

... ለእኔ በህይወት ጅማሬ ላይ ልጅነት ልቅ ነች - ያልተገራች። መተከዣ ጊዜ ያላበጀች። እንዲሁም በአፍላነት ላይ ወጣትነት እርጅናን አያዋየውም። መቼ ነው ዘላለማዊነት ታፀናለች። ለልጆች ልጅነት ልብ የማይባል ዘላለማዊነት አልቦ - ለወጣቶች የወጣትነት ፀሐይ መቼም የማትጠልቅ ግትር ናት። ዕድሜ የሰጠንን ስናልፈው ወደኋላ እንጂ ወደፊት እንዳናየው ተጋርዶብናል ... የወጣቱ ስብሐት ገፀባህሪ ማሚት እሹሩሩ ግን በአፍላ ብርሃማነት ላይ የእርጅና ከል ደርባ ትንቀሳቀሳለች።

......."እርጅና ሳስበው ያስጠላኛል። አየህ አሁን ወጣት ነኝ፣ ቆንጆ ነኝ፣ ወንዶች ውቃ ይሆኑልኛል፣. የጠየኩትን ይከፍሉኛል። ግን ቁንጅና እንደ ፍሬ ነው። እየበሰለ ሲሄድ በጣም ያስጎመጃል። አንድ ሀሙስ ቆይቶ ይበሰብሳል። ይረግፋል። መልኬ ሲጨማደድ፣ ቁንጅናዬ ሲረግፍ ምን እሆናለሁ? ..." (ሌቱም አይነጋልኝ፣ ገፅ 186)

ህይወት የኋልዮሽ እያዩ ወደፊት የሚሾፍሯት መዘውር ናት። እንደቴፐ አጠንጥነው የሚያደምጡት። ወጣቱ ስብሀት ግን እንደትንቢት መድረሱ የሚያጠራጥረውን እርጅና አምና የምትብሰከሰክ ወጣት ገፀ ባህሪ መፍጠር ችሏል። እርሱ እራሱ፣ ግድ ይላል። እንዴት? አለበለዚያስ ለገፀባህሪው ይሄን ሸክም ከየት አመጣው? ...

ስብሐት ትኩሳትን ሲፅፍ ገና ሃያ አምስት አመቱ እንደነበር መግቢያው ላይ ይገልፃል። ይሁንና ከወጣትነት አሻግረው እርጅናን ከሚማትሩ አፍላዎች በተጨማሪ ከአዛውንትነት ድንዛዜ ጋር እየተጎተቱ ከተጎራባች፡ ወጣቶች "እሳት" የሚጫጫሩ ገፀባህሪዎችንም ፈጥሯል። የሌቱም አይነጋልኝ "አልተገናኘንም" የእነዚህ አይነቶቹ ተወካይ ናቸው። የቅፅል ስማቸው ትዕምርትም በዕድሜ መተላለፍን ወካይ ነው። በእርጅና ተጨምድደው ወደ ሞት እየተጓዙ፣ ወደ ህይወት ከሚንቀለቀሉት መፅናኛ ትኩሳት ከየመሸታ ቤቱ ይሸምታሉ።

ሌላዋ የዚህ ስልፍ ተሳታፊ ገፀባህርይ እትዬ አልታዬ ናቸው። ስብሀት "ፊታቸው የሚስቅ መዳፍ ይመስላል" ይላቸዋል። ብርሃኑ ከተሰኘ መሸተኛ ደንበኛቸው ጋር ይቀላለዳሉ። "ሙቀት፣ ሙቀት፣ ሙቀት" ሲሉት:-

"ያረቄና ያንቱ ፍቅር ሙቀት" አላቸው። ሁለቱ ሁሌ እንደተቃለዱ ነው።

"አይ አንተ! ምነው የዛሬ ስላሳ ዓመት ተገኝተህ በሆነ?"

"ያኔማ አይመችም ነበር። የለሁም ነበር" አላቸው

"እሱ ላይ ነው ጉዱ ይኸውልህ! እኔ ደግሞ አሁን የለሁም"

እትዬ አልታዬ በህይወት መተላለፍን መሰረት አድርገው "አልተገናኘንም" ሲሉ ነው። ግን ህይወት እንዲህ ናት? በአመሻሽ ድንግዝግዝ፣ አጥበርባሪ ተንራባች ለማየት ይዳዳታል? መተላለፍና አለመገናኘት ሆዷን ይበላታል? ...

... እዚህ ላይ ነው ስብሐትን ግሪካዊው ደራሲ ኒኮዝ ካዛንትዛኪዝ (Nikos Kazantzakis) የሚዳበለው። ቀደም ሲል የስብሐት ብቻ የሚመስለኝ የህይወትና ሞት፣ የወጣትነትና እርጅና ጉዳይ የካዛንትዛኪዝ ግድ መሆኑን ካወቅሁ ጥቂት ዓመታት አልፈዋል። የደራሲውን "ZORBA THE GREEK" የተሰኘ ልቦለድ ካነበብኩ በኋላ መሆኑ ነው። እዚህ ልቦለድ ውስጥ አንድ "አልተገናኘንም" ዕጣ ፈንታቸው የሆነ ገፀባህርይ አሉ። ስማቸው አሌክሲስ ነው። ሞቶ ዓመት ቢሞላቸውም ሴቶችን መቋመጥ አላቆሙም። አይናቸው ማጠራጠር ይዟል። ደጃፋቸው ላይ ወንበር አውጥተው ይቀመጣሉ። በአጠገባቸው ልጃገረዶች ሲያልፉ ይጣራሉ።

"ማነሽ አንቺ?"

"የፂኒዮ (ወይም) የማስትራንጶኒ ልጅ ነኝ"

"እስቲ ቅረቢና ልንካሽ፣ አይዞሽ አትፍሪ" ልጃገረዶቹ ከሀፍረት ጋር ፊታቸውን ያቀርባሉ። አሌክሲስ እጃቸውን ሰድደው ለስላስ ባለ ሁኔታ፣ በእጃቸው እያጣጣሙ ይዳስሱና እንባቸው ኩልል ብሎ ይወርዳል። ተራኪው ዞርባ አንድ ቀን ጠየኳቸው ይላል።

"አያቴ ስለምን ያለቅሳሉ?"

"የማለቅስበትን ጉዳይ መረዳት ተስኖህ ነውን የእኔ ልጅ? እኔ ወደሞት ሳዘግም ከበስተኋላዬ ስንት ልጃገረዶች ቀሩ መሰለህ"

በዓለም ግርማ ከስብሐት ገብረእግዚአብሄር ወስዶ (ባይገልፅም) ያደራጃቸው ገፀባህርይ እትዬ አልታዬ፣ "ደራሲው" ውስጥ የአሌክሲስን ብሒልና መብሰክሰክ ሲደግሙት እናያለን።

"... የደረስ ጎረምሳ ሲያዩ ምን ይላሉ መሰለህ? ‹ይኸ ሎጋ ወደ ህይወት፣ እኔ አልታዩ ወደ መቃብር። በመንገድ ተላለፍን እቴ!› ብለው እንትፍ እንትፍ ይሉበታል" (ደራሲው ገፅ፡ 156)

የአመሻሽ ህይወት የራሷ የሆነ የማታ የጀንበር ሙቀት የላትም? የወጣቶችን "ከፍ ዝቅ" የመናቂያ ልበና አልተሰጣትም? ዕድሜ በማይፈቅደው፣ አካል በማይሸከመው መውብራት ትሞቃለች? ወይስ የመረጋጋት መከዳ ታበጃለች? ጉኗን ታሳርፋለች? ....

ስብሐት ባልበረደ የማታ ጀንበር የሚመስሉ ሌላ ገፀባህርይም አለው። "ትኩሣት" ውስጥ ጃምቪድ የተሰኘ ገፀባህርይ ታሪካቸውን የሚያወሳው አያቱ፤ በሙቶ ስምንት ዓመታቸው የሰው ሚስት ወሽመው ባሏ ሲመጣባቸው በመስኮት ሲዘሉ እግራቸው የተሰበረ። ለጉድ የተፈጠሩት እኚህ አዛውንት፤ ከወጣት በላይ ፈጥነው እግራቸው ይድንና ወደ ወትሮው የአፍላ መዛለላቸው ይመለሳሉ።

የካዛንትዛኪዝም ዞርባ ከወንድ አያቱ ተስፈንጥሮ ሴት አያቱንም በዕድሜ አለማወቅ ሽሙጥ ይጎበኛል። የልጅ ልጆቻቸውና እኩዮቻቸው እንዲት ሴት በዘፈን የሚያሸበሊብሉበትን ቅዳሜ እየጠበቁ አያቱ ይኳኳላሉ ይላቸዋል። በሰማኒያ ዓመት ዕድሜያቸው በምስጢር የፍቅር አጋር መቃበዛቸው ትክክል አለመሆኑን ወጣቱ ዞርባ ከስድብ ጋር ስለነገራቸው፣ በዚህ ተስፋ መቁረጥ መኖራቸው ይሚጠጣል። ወደ መቃብር የሚያመሩት የልጅ ልጆቻቸው ከልባቸው ተራግመው ነው። ዞርባ ይሄንን ተርኮ ሲጨርስ እንዲህ ይላል፡- "ሴት ልጅ በሰማኒያ አመቷ እንኳን ጨርሶ የማይጠግግ አንድ የቁስል ከፍተት አላት። ብዙ ቁስሎቿ ተፈውሰው ቢጠፉም፣ ያ ልዩ ቁስሏ ግን እንደተከፈተ አብሯት ወደ መቃብሯ ይወርዳል።" ስብሐት ይሄንን "የሴቶች ቁስል" ከካዛንትዛኪዝ ጋር በመጋራት ይሆን ማሚት እሹሩሩ ከእርጅና አድማስ አሻግራ ስለመፈቀር እንድታሰላስልና እንድትጨነቅ ያደረጋት? "... ያኔ እንግዲህ ወንዶች አይፈልጉኝ" ትላለች። ከንፈን የመሰለ ወጣት ስትመለከት ለማነጋገር ትሞክርና እንደሚያዳግታት ታስባለች። በዚህ ጭንቀት ያርዳታል። ለሁለት ጫፍ ዕድሜ (ለወጣትነትና እርጅና) አንድ አይነት ምላሽ የሚሰጥ አካል እንዴት ሊኖር ይችላል? ለወጣቷ ማማሚት እና ለአሮጊቷ ማሚት ከንፈ አንድ ነው? እንደምን? ...

ይሄንን ጉዳይ ካዛንትዛኪዝም በ "ዞርባ ዘግሪክ" ውስጥ ሲደግመው አስተውያለሁ። ዳሜ ሆርቴን (Dame Hortense) የተሰኘች የጥንት ኮማሪት ገፀባህርይ አለችው። በወጣትነት ዘመኑዋ፣ የክሬት አብዮት በፈነዳበት ወቅት ታፈቅረው የነበረውን ጣሊያናዊ የባህር ኃይል ወታደር፣ በስተርጅና ዘመኗ ከአፏ ባለማጥፋቷ በቀቀናም ስሙን መጥራት ልማዷ አድርጋ፣ "ካናቫሮ" ትላለች። ሆርቴን የደረሰችው የማሚት እሹሩሩ የገና ለገና ፍርሃት ውስጥ ነው። ማሚት እሹሩሩም ብትሆን ከንፈን የምሽት ስንቅ ማድረጓ ስለማይቀር፣ በቀቀን የሚኖራት ከሆነ ሥሙ በልምድ

ድግግሞሽ ውስጥ ተስተጋቢ ነው ማለት ይቻላል። ማሚት እሹሩሩንና ዳሜ ሆርቴን ካወሳን አይቀር የሚመሳሰሉበትን አንዳንድ ነጥብ አንስተን ወደ ድምዳሜ እናምራ። ሁለቱም እርጅናን ይፈራሉ፤ ሁለቱም ከእርጅና ፍርሃት ጋር እንዳይጋፈጡ የሚከላከሉባቸው አፍቃሪዎች አሏቸው። ለማሚት ክንፈ፣ ለሆርቴን ዞርባ። ክንፈ ማሚት ከእርጅና ጋር እንዳትጋፈጥ ማታለያ የፍቅር ቅጭልጭልታዎችን ያበጃል። ዞርባም እንደዚያው። ሆርቴን በእርጅናና ሞት ፍርሃት ስትርድበት ጊዜ መግዣ ሀሳቦችን ያቀርባል። "መልካሙ ሐኪም፣ ቮሮኖፍ አንድ አስደናቂ ምርምር አድርጎ እርጅናን የሚያጠፋ፣ ወጣትነትን የሚያመጣ መዳኒት አግኝቷል። እሱን በበርሜል ሞልቼ አመጣልሻለሁ" ይላታል። ሆርቴን በተስፋ ተሞልታ እርጅናን በመተው፣ ስለ ሰርግና ስለ ቬሎ ማውራት ትጀምራለች።

ማሚት እሹሩሩና ዳሜ ሆርቴን የሚገናኙበት ሌላ የህይወት መስቀልኛ መንገድም አለ። ሁለቱም ካደፈ፣ ከጎደፈ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት ውስጥ እንደ ዕንቁ የሚያበራ የወገናዊነት ስራ ሲሰሩ ይስተዋላሉ። ማሚት ሴተኛ አዳሪነቷን፣ ውበቷን ተጠቅማ ተጣመው ሊያድጉ የተዘጋጁ ወጣት ችግኞችን ታቀናለች። ክንፈ እና እንዲሁ አንድ ሌላ ወጣት በፍቅር ሳቢያ ችላ ያሉትን ትምህርት እንዲያጠብቁ ብሎም ጠንካራ ተማሪ እንዲሆኑ ስትነግራቸው ይስተዋላል። ሆርቴን ደግሞ ልጅነቷን፣ ወጣትነቷን አይተው በፍቅር የነሆለሉ አራት የባህር ኃይል አድሚራሎች በክሬት ህዝብ፣ ላይ መድፋቸውን እንዳይተኩሱ ትከላከላለች። "No Boom-boom!" ትላቸዋለች። በዚህም ህዝቡን ከእልቂት ታድጋለችና ዞርባ ቦምቦሊና (Bouboulina) ይላታል። ቦምቦሊና የግሪክ ጀግና ሴት ስም ነው፡ ሆርቴን ብቻ ሳትሆን ማሚትም "ቦምቦሊና" አይደለችም? ጀግንነት ከአንድ ግንባር ብቻ ይገኛል ያለው ማነው? ይሄንን ስብሐትም ሆነ ካዛንትዛኪዝ ቀድመው የተረዱት ይመስላል።

ቀደም ሲል ....

.... ለሕይወት የሞት ነቁጥ፤ ለወጣትነት የእርጅና ማዲያት አዳብለው የሰው ልጅን አጣፈንታ የሚያዝጎረጉር ደራሲ ስብሀት ገብረእግዚአብሔር ብቻ ይመስለኝ ነበር። ቆይቶ ኒኮዝ ካዛንትዛኪዝ በ "ዞርባ ዘ ግሪክ" ብዘገይም በንባብ መጣልኝ። ሞት የህይወት፣ እርጅና የወጣትነት ንቅሳቶች ተደርገው የቀረቡበት የጥበብ ሥራ።

# "ልብ ብዬ ሳየው የሚያስቀኝ መፅሐፍ አለኝ"

"ልብ ብዬ ሳየው የሚያስቀኝ መፅሐፍ አለኝ"

"ልብ ብዬ ሳያት የምታስቀኝ ሚስት አገባሁ" ያለ አንድ የአገሬ ሰው አለ። ይሄ ግለሰባዊ መትከንከን ምሳሌያዊ አነጋገር የሆነው ለብዙ ሰዎች በቀጥታ አለያም በተዘዋዋሪ ተተርጓሚነት ስላለው ነው። ይሄኔ ምሳሌያዊ አነጋገሩ በተወለደበት ዘመን "...አለ፣ አያ እከሌ" እየተባለ ይነገር የነበረ ይሆናል። ከጊዜ ብዛት፣ ከበባታ መስፋት "አያ እከሌ" ተዘንግቶ፣ ምሳሌው እርቃኑን ቀርቶ ይሆናል። (እንዲያም አለ እንዲህ) ምሳሌው እኔ ጋ ደርሶ ዛሬ መግቢያ አድርጌዋለሁ። መግቢያ ብቻ ሳይሆን አንግዳ ስሜቴን ቅልብጭ አድርጐ የሚያሳይ ዘዴ ሆኖ አገልግሎኛል። እንዲህ:-

"ልብ ብዬ ሳያቸው የሚያስቁኝ መፅሐፍት ገዛሁ" እንዴ? ያሰኛል። መልሱ እንዲህ ነው:-

አንዳንድ መፅሐፍት አሉ፤ የአንባቢን ድክመት መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ። እነዚህ መፃህፍት በተለይ ከሰው በስጦታ መልክ ከቀረቡ እንደ ስድብም የሚቆጠሩ አይነት ናቸው። ለምሳሌ እኔ'ጋ ካሉትና ልብ ብዬ ሳያቸው ከሚያስቁኝ መፅሐፍት አንዱን ልጥቀስ - "The Complete IDIOT's Guide" (የተሟላ የደደቦች መመሪያ) የሚል ርእስ አለው። ይሄን መፅሐፍ አንድ የቅርብ ሰው በስጦታ መልክ ካቀረበልዎ አንድም እርስዎ፣ አለበለዚያም እርሱ (ከሁለት አንዳችሁ) ደደቦች ናችሁ። 'እንዴት?' ያሰኛል። 'እንዲህ' ነው።

ሰውየው ይሄን መፅሐፍ የሰጠዎ ሆን ብሎ ከሆነ ድድብናዎን ወይም ጅልነትዎን አለያም ፋዞነትዎን አይቶ ያዘነልዎ፣ ወይም ቀርቦ የተማረረብዎ፣ ካልሆነም ተመራምሮ የደረሰብዎ ሰው ነው ማለት ነው። ፍቺ በሌለው መንገድ፣

ያለምክንያት፣ በእንዝህላልነት ይሄን መፅሐፍ ገዝቶ ከስጦዎ ደግሞ ሰውየው እራሱ ደደብ፣ ወይም ጅል አለበለዚያም ፉዞ ነው።

ይሄ መፅሐፍ የተበረከተበት አግባብ እንዴት ነው? ብሎ ማጤን ደግሞ ደግ ነው። መፅሐፉ እቤትዎ ድረስ ወይም ብቻዎን ሳሉ ተሸፋፍኖ ከተሰጥዎ "ምክር" ነው። በአደባባይ ተገላልጦ ከተበረከተልዎ ደግሞ "ስድብ" ነው። እንዴት? ቢሉ ይሄንን ነባር ምሳሌ ያጤናሉ። "ለብቻዬ የሰደበኝ - መከረኝ፤ በሰው መካከል የመከረኝ - ሰደበኝ"

"The Complete IDIOT's Guide" ሦስተኛው እትም (2003 ዓ.ም) እኔ'ጋ አለ። ይሄ መፅሐፍ ከያዛቸው ርእሰ ጉዳዮች መካከል እኔ "ደደብ" የሆንኩበትን የቤት አያያዝ መርጬ በማስቀደም አነበብኩ። አካፋይ ቦታ ላይ ቆሞ በመምከር ይጀምራል። ቤትዎ ጭንቅላትዎ ውስጥ እንዳለው ህልምዎ አድርገው ማደራጀትና መሰደር ከቻሉ፣ ከዚህ ምስቅልቅል አለም የሚሸሹበትን ብቸኛ ቦታ በድል አድራጊነት መመሥረት ችለዋል ይላል። ጐጆ'ኮ "ከራስ በላይ ጣሪያ" ተብሎ የሚጠቃለል ጉዳይ አይደለም። (Your home doesn't have to mean just a roof over your head) ይልና ስለቤት አያያዝ ወሳኝነት ይመከራል። ምክሩን አንብቤ እንዲህ አደመድማለሁ።

ያልተደራጀና የተመሰቃቀለ ቤት እንቅፋት እንደበዛበት የባህር ቀዘፋ አንግልት የሞላበት መንፈስ ፈጥሮ ያደክማል። ሰው በጠዋቱ ከቤቱ ሲወጣ ከደከመው ፋክክር በበዛበት ዓለም ውስጥ ምኑን ተወዳደረው? በአግባቡ የተያዘ መኖሪያ ግን ለልዩ ተልእኮ ማዕከል እንደሚያደርጉት ወታደራዊ ቤዝ ነው...

....ወደ እኔ እውነታ ስመጣ ግን እንደዚያ አይደለም። ቤቴ በሰዎች "ሥርዓት" ሲይዝ ይዞርብኛል። ከምስቅልቅሎሹ ጋር ተግባቦት አለኝ። ስላልተሰደረ ደክሞኝ ከቤቴ አልወጣም፣ ቤቴን አልጠላም፣ የፈለኩትን ከቤቴ አላጣም፣ መንፈሴ በቤቴ ላይ አይጐሽም... ለመሆኑ "ከ'Idiot' እነቴ" ጋር ተስማምቼ ኖርኩ? ወይስ Idiot አይደለሁም? ደግሞስ ምስቅልቅሎሹ ካልተስማኝና ካልረበሸኝ መፅሐፉ ለምን አስፈለገኝ? እንዴትስ አብሮኝ ለአመታት ቆየ?... እያልኩ ልብ ብዬ ሳየው ከሚያስቀኝ መፅሐፍ ጋር አለሁ።

እኔ ጋ ካሉትና ልብ ብዬ ሳያቸው ከሚያስቁኝ መፅሐፍት ሌላኛው "Bathroom Reader" (ለመታጠቢያ ቤት አንባቢ) የሚል ጠቅላይ ርእስ ያለው ነው።

በ"Bathroom Reader" ኢንስቲትዩት እየተዘጋጀ የሚቀርብ ተከታታይነት ያለው መፅሐፍ ነው። ለትህትና መታጠቢያ ቤት ይባል እንጂ አላማው መፀዳጃ ቤት ነው። ሽፋኑ ላይ የመፀዳጃ ቤት ወረቀት፣ የመፀዳጃ ቤት ውሃ መልቀቂያ ይታያል። ከመፀዳጃ ቤት ወረቀቱ ጋር መፅሐፉ ቦታ ተጋርቷል። የመፅሐፉ አላማ በመፀዳጃ ቤት ቆይታ ወቅት የተመጠነ እውቀት ማስተላለፍ እንደሆነ ከርዕሱ እና ከሽፋን ምስሉ እንረዳለን። የፅሁፎቹ መጠን እንደ መፀዳጃ ቤት ቆይታችን እንድንመርጣቸው ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። አጭር (Short)፣ መካከለኛ (Medium)፣ ረጅም (Long) እና ሰፋ ያለ (Extended) በሚል ተከፋፍለዋል። ይሄን መፅሐፍ ልብ ብዬ ባየሁ ቁጥር አንድ ቀልድ ትዝ ይለኛል።

መፀዳጃ ቤቱ የጋራ የሆነበት መንደር ውስጥ ነው። ልጁ ገብቶ ብዙ የቆየባቸው ተጠቃሚዎች እየተንጫነጩ ነው። ከመካከላቸው አንዱ አዛውንት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ልጁን ያናግሩታል፤

"ሰማህ አንተ ልጅ"

"አቤት"

"ሽንት ቤቱን ብቻህን ያዝከውኮ። እኛም መጠቀም እንፈልጋለን፣ ለምን አትወጣም?"

ልጁ ውስጥ እንዳለ ይመልሳል፡-

"ቢወጣስ የት ይኬዳል?"

እኛ ከምናውቀው የጋራ መፀዳጃ ሽታ በላይ የከረፋ የሥራ እጥነት አለም ልጁን ይጠብቀዋልና ተደበቀበት። ቀልድ ይመስላል እንጂ መራር እውነት ነው።

...እና (በእኛ ዓይን) የቀበጡት ፈረንጆች መፀዳጃ ቤት ተቀምጦ የሚባክን ጊዜን ሥራ ላይ ለማዋል "Bathroom Reader" አቀዱና ተገበሩ። መፅሐፉ ግን "መፅሐፍ" ነው። ታሪክ፣ አስቂኝ ገጠመኝ፣ ፖለቲካ፣ ሥነ-ፅሁፍ፣ ጥያቄና መልስ፣ ሥነ-ልቦና... ያልያዘው ነገር የለም። ያለ መፅሐፉ አላማ መኖሪያ ቤት ውስጥ እያነበብኩት ነው። እንኳን መፀዳጃችን ከተማችን እንደ ጋራ ሽንት ቤት በከረፋችበት አግባብ ሌላ ምን አማራጭ አለ?

ሦስተኛው ሳየው የሚያስቀኝ መፅሐፍ "100 MISTAKES THAT CHANGED HISTORY" (ታሪክ የቀየሩ መቶ ስህተቶች) የሚል ርእስ አለው። መግቢያው እንኳን "History Making Mistake" (ታሪክ ሰሪው ስህተት) የሚል ንዑስ ርዕስ ተሰጥቶታል። ታዲያ እኛ ምን ሆነን ነው "ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው" እያልን የከረምነው? ከዚህ መፅሐፍ አንፃር "ቆራጡ" (ምናምን) የሚባል መሪ የለም። ወይም ይቺ አለም እዚህ የደረሰችው በታቀደላት ቀጥተኛ መንገድ ተጉዛ ሳይሆን መሪዎችና ሌሎች ተሳስተው በፈጠሩት ክስተት ነው። ስለዚህ "Your Kingdom, or your life is a mistake" ይላል መፅሐፉ። ይሄንንም ለማስረገጥ መቶ ስህተቶች እንዴት የዓለምን ታሪክና ገፅታ እንደቀየሩት ያስነብባል።

2500 ዓመታት ወደኋላ ተጉዞ የአይኦኒያን ከተማ ከሆነችው ከሚሊተስ (Miletus) መሪ አሪስታጎራስ (Aristagoras) ስህተት ይጀምራል። የአሪስታጎራስ ስህተት ምዕራብ አውሮፓ አሁን ባለችበት ሁኔታ እንድትገኝ አስተዋፅኦ አድርጓል። አሪስታጎራስ የፐርሺያውን ንጉስ ቀዳማዊ ዳሪየስ አስደስቶ ለመሾም ለመሸለም ሲል ያመፀችውን የናክሶስ ከተማ ለመውረር ተነሳ። ድል ሳይቀናው ቀርቶ ተሸነፈ። ለመሸነፉ ከባቢሎን ንጉስ የሚደርስበትን ቅጣት ያውቃልና የአካባቢውን ከተሞች በባህል ስም ለአመፅ አስተባበረ። "ቋንቋችንና ባህላችን ለግሪክ እንጂ ለፔርሺያ ባእድ ነው። ስለዚህ ባቢሎናውያንን አንቀበልም" አለ። የአቴንስንና የመላው ግሪኮችን ድጋፍ አግኝቶ ቢዋጋም ከፔርሺያዎች ሽንፈት አላመለጠም። በዚህ ስህተት አውሮፓ ከግሪክ ግለሰብን ማዕከል ካደረገ ባህል ባሻገር ጠንካራ ማዕከላዊነት ያለውን የፔርሺያ ባህል ለማካተት ተገደደች። በዚህም አሁን ያለችውን ሆነች።

ይሄ የመፅሐፉ ጅማሬ እስከ 2008 ዓ.ም የአውሮፓ የኢኮኖሚ ድቀት ድረስ ይጓዛል። እና ብዙ የፖለቲካ፣ የሳይንስ፣ የማህበራዊ ህይወት ስህተቶች የቀየሩትን ታሪክ ያሳየናል። እንዲህ ያለው ምርምር ከታሪክ ጋር በባላንጣነት ከመኖርና እሱን ከማመንዠግ አይገላግልም ትላላችሁ።

አራተኛውን ልብ ብዬ ሳየው የሚያስቀኝን ያገኘሁት ከወደ ሩሲያ ነው። ሊያኪሚንኮ (LYAKIMENKO) የተሰኘ የሥነ ዕሁፍ ተመራማሪ፣ ሾሎሆቭ (Sholokhov) የተሰኘ ደራሲ ሥራዎች ላይ ጥናት ያካሄደበት መፅሐፍ ነው። ርእሱ "Sholokhov: A Critical Appreciation" (ሾሎሆቭ፡ የማድነቅ ሂስ) ይሰኛል። ማድነቅ ብቻ ከሆነ ምኑን ሂስ ሆነ? ስህተት ፈልጎ ማጣት አንድ ነገር ነው፤

ስህተትን ወዲያ ብሎ ማድነቅን ብቻ በማነፍነፍ እንዴት ሂስ ይሰራል? እያልኩ መፅሐፉን ሳየው ያስቀኛል።

ሌላኛው መፅሐፍ የማርክ ክሪክ ነው። "The Household Tips of the Great Writers" ይሰኛል። መፅሐፉ በቤት አያያዝና በአትክልት ቦታ እንክብካቤ ውስጥ አጣማጅ አድርጎ ያላነሳቸው ደራሲዎች የሉም። ፍራንዝ ካፍካ፣ ጄን ሀውስቲን፣ ማርሲል ፕሩስት፣ ኤርነስት ሔሚንግዌይ፣ ቬርጂንያ ዎልፍ፣ ቶማስማን፣ ሆሜር፣ ዤን ፖውል ሳርት፣ ኤድጋር አለን ፖ... የሚገርመው ግን አንዱም የሉም። ደራሲው በፀሐፊዎቹ ስታይልና የሥነ ፅሁፍ አይነት የቤት አያያዙን፣ የመታጠቢያ ቤት እንክብካቤውንና የአትክልት ስፍራ አያያዙን ፅፎ አቅርቧል። አሁን ይሄ ማታለል ነው ወይስ...? ቢሆንም፣ ቢያንስ ሳየው ከሚያስቁኝ መፅሐፎች ተርታ ገብቷል። የመፅሐፉ አሰናኝ ይሄን እንደ ድል ከቆጠረው ማለቴ ነው።

# የሁለቱ ደራሲዎች የሁለት ሴት አባዜ

ከሩሲያ ፊዮዶር ደስተየቭስኪ፣ ከኢትዮጵያ በዓሉ ግርማ አንድ አይነት የሥነ-ፅሁፍ አከዋወን ጠባይ አላቸው። በየልቦለዶቻቸው ውስጥ የሚቀርፅዋቸው ዋና ገፀባህርያት ከግራ እና ከቀኝ የጎን አጥንቶቻቸው መንታ ሴቶች የተመዘዙ ግራ አጋቢ "አዳሞችን" ነው። እነዚህ ገፀባህሪዎች ሴቶች ተራዳና ቋሚ ሆነው በመሰረቱት መስቀል ላይ ተቸንክረው "ለምን ተውኸኝ?" የሚል እሮሮ ያሰማሉ። አቀበትና ቁልቁለቶቻቸውም እነዚያው ሴቶች ናቸው። እነርሱው ላይ ይወድቃሉ፣ በእነርሱ ይነሳሉ እነርሱኑ ይጠማሉ፣ በእነርሱው ይደቃሉ...

...ደስተየቭስኪ ጥንድ ሴቴ ፀሐዮች የገነኑበት ወንዴ ዓለም የፈጠረው ደጋግሞ ነው። "The Brothers Karamazov" ውስጥ ኢቫኖቭና እና ግሩሼንካ በእኩል ጉልበት ገናን ብርሃን ይለቃሉ። "The Idiot" የተሰኘው ልቦለድ ውስጥ ደግሞ እንዲሁ አግላያ እና ናፃስያ፤ ልዑል ሚሽኪን በተሰኘው ገፀ ባህርይ ልብ ውስጥ የሚፋለሙ ፍቅር ታጣቂዎች ናቸው። "Insulted and Humiliated" የተገነባው በሁለት ግራ አጋቢ ሴት ገፀባህሪዎች መካከል የሚዋዥቅ ልብ ባለው ሰው ላይ ተመስርቶ ነው። የአስራ ሦስት አመቷ ኔሊ የማይገባትን የፍቅር ትኩረት በመሻት ከኮረዳዋ ሉቦቭ ጋር በባላንጣነት ትቆማለች። "The Crime and Punishment" ውስጥ ይሄው ጉዳይ አለ። ቫርያ እና ሶኒያ የዋናው ገፀባህርይ የራስኮሊንኮቭ "ውኃቅዳ-ውኃመልሶች" ናቸው።

ወደ በዓሉ ግርማ እንመለስ። በአሉ ግርማ እንዲሁ በአብዛኞቹ ሥራዎች ውስጥ የፈጠራቸው ወንዴ ዓለሞች ባለሁለት ሴቴ ፀሐዮች ናቸው። የ"ደራሲው" ዋና ገፀባህሪ ሲራክ እንደ ሸማኔ መቂናጥ ሁለት ሴቶችን ለመዳረሻነት አበጅቶ ከወዲያ ወዲህ የሚራወጥ ነው። እወዲያ ሰብለወርቅ ታፈሰ ብሩ አለች፤ እወዲህ ደግሞ ፅጌ። የራሱ እና የሰው ሚስት ላይ ተንጠልጥሎ እንደ እባብ እሁለት ተቆርጦ፣

ሁለት ቦታ የሚንቀሳቀስ ልዩ ፍጡር ሆኖ ቀርቧል። "ዩቀይ ኮከብ ጥሪ" ውስጥም የደርቤ እጣ ፈንታ ከሲራክ የተለየ አይመስልም። ከፊቱና ከኋላው ሁለት ሴቶች ተተክለዋል። እሱ ሒሩትን ያያል፤ በፍኖት ይታያል። ፍኖት በአማዕላፍ ግፊት ደርቤን ትማትራለች። እንዲሁ ደርቤም በፍኖት ተራዳኢነት ሒሩትን ይማፀናል። እምአእላፍ ከፍኖት ፊት በሞት ይገለላል፣ ሒሩትም እንደዚያው ከቁራኛዋ ደርቤ ባለየለት ሞት ትነጠቃለች። ዥዋዥዌው ደርቤ ፊቱን ወደ ፍኖት እስኪመልስ የሚጠብቅ ይመስላል።

በዓሉ ዋና ገፀባህሪዎቹን ወታደራዊ ቅጣት የበየነባቸው ያክል የሚሰማን ጊዜ ብዙ ነው። "ሀዲስ" ውስጥ ሀዲስ የተሰኘው ገፀባህርይ በሁለት "ችካል" ሴቶች መካከል ነፍሱ ማረፊያ አጥታ የሚንጠለጠል ፍጡር ነው። እንዲሁ የ"አሮማይ" ዋና ገፀባህርይ አዲስ አበባና አስመራ ላይ በተከለው መንታ የፍቅር ተራዳ ቀጬን የሰቀቀን ገመድ ወጥሮ የሚጓዝ ጀብደኛ ሆኖ ተስሏል።

ደስተየቭስኪም ሆነ በዓሉ ባለ ሁለት አፍ የፍቅር ጐጆን ለገፀ ባህሪዎቻቸው መቀለሳቸው "ለምን?" የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ግድ ይለናል። መደጋገሙስ ምንን ያመለክታል? ደስተየቭስኪ ለአንድ ተባዕት ጥንድ እንስት የሚያቀርበው በአንዲት ሴት ላይ ማሳየት የሚከብደውን የተለያየ ገፅታ ለመከሰት ከመሻት እንደሆነ አንዳንድ የሥነ ፅሁፍ ሀያሲያን ያስረዳሉ። ራኬል ቶማስ የተሰኙ አጥኚ፤ "Ideas imbued and Exploration of Experience: The works of Fyodor Dostoevsky" በተሰኘ ምርመራቸው እንዳረጋገጡት፤ ደስተየቭስኪ የሴቶችን ጥንካሬ ከሁለት አቅጣጫ የመቃኘት ዝንባሌ ያሳያል። አንድም በሩሲያ ማህበረሰብ ጫና ውስጥ ሴቶች እንዴት ችግሩን ተቋቁመው እንደሚወጡ ሲሆን ሌላው በምዕራባውያን አስተሳሰብ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን የነፃነት ገፅታ ነው።

ለምሳሌ "The Brothers Karamazov" ካተሪና ኢቫኖቭና በአጮኛዋ የሚደርስባትን ማህበረሰብ ወካይ ንቀት ለመበቀል በወንጀል ምስክርነት ስትቆም እንመለከታለን። "The Idiot" ውስጥ ደግሞ አግላያ ለጥ ሰጥ ያለ ወግ አጥባቂ ቤተሰቧን ጣጥላ፣ በወቅቱ ለሴቶች አደገኛ የሆነውን ነፃነት ለራሷ የምታጎናፅፍ ተደርጋ ተስላለች።

የደስተየቭስኪ ሴቶች የመከሰቻ አላማቸው በፍቅር አቃኘት የተገደበ አይደለም። ለምሳሌ የ ከዚያ አልፎ ለወንዶችም ትብታብ መበጣጠሻ ምክንያትነት አለው። "Crime and Punishment" ዋና ገዐባህርይ ከተተበተበበት የአእምሮ ወቀሳ ነፍሱ

ነፃ የምትወጣው በሶኒያ ነው። በተመሳሳይ "The Brothers Karamazov" ውስጥ ግሩሼንካ እንዲሁ ለኢቫን የነፃነት መለከት ሆና ቀርባለች። "Insulted and Humiliated" ውስጥ እንዲሁ ኒሊ በይቅርታ ንፍገት የዘመን ፍዳ ነዋሪዎች የሆኑትን አባቷን፣ እናቷንና አያቷን በእርሷ ሞት ስትፈውስና ወደ ዘመን-ምህረት ስታሸጋግር የምትታይ ታዳጊ ገፀባህርይ ናት።

የደስተየቭስኪ ሴት ገፀ ባህርይዎች በሙሉ ከወንዶቹ የላቀ ቦታና አላማ ተሰጥቷቸዋል ማለት ይቻላል። በሚታይና በማይታይ ኃይል የተሞሉ ናቸው። ናሙናው ደግሞ ናታሊያ ፎንቪዚና የተባለች ሴት እንደሆነች ተደጋግሞ ይነገራል። ይቺ ሴት ደስተየቭስኪ መንግሥት ላይ ደባ በመስራት ሲወነጀል፣ አብሮት ሞት የተፈረደበትና በኋላም በምህረት ወደ ሳይቤሪያ የተጋዘ ጓዱ ሚስት ነበረች። ባላቸውን ተከትለው ወደ ሳይቤሪያ በፈቃድ ከተጋዙት ጠንካራ ሴቶች አንዷም ናት። ከደስተየቭስኪ ጋር የተዋወቁት በሳይቤሪያ ጉዞ ላይ ሳሉ ሲሆን በወቅቱ የአዲስ ኪዳን መፅሐፍ አስር ሩብል ጨምራ ሰጥታው ነበር።

በሳይቤሪያ ቆይታው በተዳባይ አፍቃሪነት ይቺን ሴት ልቡ ውስጥ ሲያጉላላት መቆየቱ በሥራዎቹ ውስጥ "የስርቆሽ በር" ያላቸው የፍቅር ጉጀዎችን ለመመስረቱ እንደ ዋነኛ ምክንያት ይጠቀሳል። በዓሉስ?...

...በግልፅ እንደሚታወቀው የእኛ ሥነ-ፅሁፍ ሆነ የደራሲዎች ህይወት በጥልቅ የሚመረመርበት አግባብ የለም። በዓሉ ግርማ በአብዛኛዎቹ ሥራዎቹ ውስጥ ባለመንታ አፎት ፍቅር እንዲሽሚጠጥ የማድረጉ ምንጭ በውል አልተመረመረም። ከህይወቱም ጋር አልተገናዘበም። ይሁንና አንዳንድ ጥቁምታዎችን ከመዘዝን ወደ አንድ መዳረሻ ማግምራታችን ግድ ነው። ለምሳሌ የቀድሞው ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ኃይለማሪያም ከጋዜጠኛ ገነት አንበሴ ጋር ተወያይተው ወደ መፅሐፍ በተለወጠው ሥራ ውስጥ በዓሉ ግርማ የድምፃዊቷ ብዙነሽ በቀለ ወዳጅ እንደነበር ይናገራሉ። በ"ደራሲው" ዋና ገፀ ባህርይ በሲራክ፣ በ"ህዲሱ" ሀዲስ፣ በ"ቀይ ኮከቡ" ደርቤ፣ በ"ኦሮማይ" ፀጋዬ ኃይለማሪያም ላይ የታየው የሁለት ቤት ስቅለት በደራሲው የተጠና ወይም የተኖረ ነበር ለማለት የምንችልበት ቀዳዳ እዚህ ላይ ይፈጠራል። ታዲያስ? ደስተየቭስኪ "He retreated to the confines of his novels for exploration of his experiences." እንደተባለው መሆኑም አይደል?



ትግራይ ብቻ፣ አማራ ብቻ፣ ኦሮሞ ብቻ፣ ጉራጌ ብቻ፣ ሐረሪ ብቻ፣ ጋምቤላ ብቻ፣ ቤኒሻንጉል ብቻ፣ አፋር ብቻ፣ ሱማሌ ብቻ፣ ወላይታ ብቻ፣ ሲዳማ ብቻ፣ . . . መሆን ለኔ የተሰጠ አይደለም። ትግራይነትን ብቻ፣ አማራነትን ብቻ፣ ኦሮሞነትን ብቻ፣ አፋርነትን ብቻ፣ ወላይታነትን ብቻ. . . በሚያስቡ መገዛት ለእኔ ማነስ ነው። ማነስ ብቻ ሳይሆን ውርደት ነው። እንዴት ሁሉን ጥቂት ይበልጠዋል? እንዴት ባሕርን ወንዝ ይውጠዋል? በቀዬ ውስጥ አገር እንዴት ያድራል? ብዙ በጥቂት ይታሰራል? . . .

ከመጽሐፉ



የ[illegible]
ዓለማየሁ ገ[illegible]
ቀደምት ሥራዎች

- ቅበላ
- የፍልስፍና አፅናፍ
- አጥቢያ
- ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት
- ኢህአዴግን እከሳለሁ
- ኩርቢት
- የብርሃን ፈለጎች
- መልከአ ስብሐት
- ወሪሳ
- በፍቅር ሥም

ዋጋ፦ 71.50 ብር

አታሚ [illegible] ማተሚያ ቤት 011 840 45 49